ትልቅ ሕልም አለኝ!

# ሳምንት ፩

# ትልቅ ሕልም

ዳዊት ዳሬምስ

# ሳምንት ፩

*******

# ትልቅ ሕልም


ቀን ፩ እኔ ድንቅ ነኝ! 3

ቀን ፪ ይቻላል! 9

ቀን ፫ ራስን መገምገም 17

ቀን ፬ ራስን መቀየር 27

ቀን ፭ ትልቅ ሕልም 37

ቀን ፮ ፓራዳይም 59

ቀን ፯ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች 77

፳፩ ቀን “የ፳፩ ቀን ስር ነቀል ለውጥ ልምምድ” 93

# ቀን ፩

*******

# እኔ ድንቅ ነኝ!

*"እኔ ድንቅ ነኝ! እኛ ድንቅ ነን! ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው! ኢትዮጵያ ድንቅ ናት!"*

አውሮፕላን በወፍ ምሳሌ እንደተሠራው ሁሉ፣ ኮምፒዩተርም በሰው ምሳሌ የተሠራ ነው። በመሆኑም የኮምፒዩተርን አሠራር መመልከት፣ እኛ ሰዎች እንዴት እንደምንሠራ ለመረዳት ስለሚያግዘን፣ ውይይታችንን በዚሁ እንጀምር።

ኮምፒዩተር ከተፈበረከበት ዕለት አንስቶ፣ ዓለምን ወደ ተሻለች የመኖሪያ መንደርነት እየቀየራት ይገኛል። በእያንዳንዱ ቀን፣ ሰዓትና ደቂቃ፣ በኮምፒዩተር በመታገዝ፣ ዓለማችን ላይ ብዙ ድንቅ ነገሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ። የሥራ፣ የትምህርት፣ የግንኙነት እና የተለያዩ የሕይወት ዘርፎች በተሻለና በፈጠነ ሁኔታ የሚከናወኑትም በኮምፒዩተር እገዛ አማካኝነት ነው። በየዕለቱ ከምንጠቀምበት ተንቀሳቃሽ ስልካችን አንስቶ፣ የዓለማችንን እንቅስቃሴዎች ፍንትው አድርገው እስከሚያሳዩት ሳተላይቶች ድረስ፣ ኮምፒዩተር በሕይወታችን እና በዓለማችን ላይ እንደ መልህቅ ሆኖ የሚያገለግል ድንቅ ግኝት መሆኑን እየተመለከትን ነው። ታዲያ ኮምፒዩተር ይህን ሁሉ ተዓምር የሚሠራው እንዴት ነው? ከምናየው ገሀዳዊ የኮምፒዩተር ገጽ ጀርባ ያለው ምስጢርስ ምንድን ነው?

ማንኛውንም ኮምፒዩተር ከፍተን ብንመለከት፣ በውስጡ "ፕሮሰሰር" የተባለ አንድ ድንቅ *መሣሪያ* እናገኛለን። ይህ *መሣሪያ* የኮምፒዩተሩ አንጎል ሲሆን፣ በኮምፒዩተሩ የሚከናወኑ ማናቸውንም ዐይነት *ሥራዎች* የሚቆጣጠር አካል ነው። ፕሮሰሰር፣ የኮምፒዩተሩን የተለያዩ አካላት *(በሙያው ቃል አጠራር ሀርድ ዌር፣ ሶፍት ዌር፣ ኢን ፑት፣ አውት ፑት፣ ፕሮሰሰር፣ ሜሞሪ እና ስቶሬጅ)* በመጠቀምና በመቆጣጠር፣ የተለያዩ *ሥራዎችን* ማከናወን የሚችል *መሣሪያ* ነው። ፕሮሰሰር ሁሉንም የኮምፒዩተር *ሥራዎች* ማከናውን የሚችል *መሣሪያ* ቢሆንም፣ ከኮምፒዩተሩ አጠቃላይ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር ግን መጠኑ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። በንፅፅር ለማየት ብንሞክር እንኳ፣ አንድ ፕሮሰሰር ከአንድ የፓስፖርት ፎቶግራፍ የሚበልጥ መጠን የለውም።

ማንኛውም ፕሮሰሰር፣ አንድ ኮምፒዩተር *ሥራዎቹን* እንዲያከናውን የሚያደርጉትን፣ በጣም ብዙ ትራንዚስተሮች በውስጡ ይዞ ይገኛል። እነዚህ ትራንዚስተሮች አንድን ኮምፒዩተር ለመ*ሥራት* ወይም ለመፈብረክ የምንጠቀምባቸው አስፈላጊ *መሣሪያዎች* ናቸው፤ መጠናቸውም የትዬለሌ ነው። በአንድ የድሮ የኮምፒዩተር ፕሮሰሰር ውስጥ፣ እስከ አምስት ሚልየን የሚጠጉ ትራንዚስተሮች ሲገኙ፣ በዘመናዊ ኮምፒዩተር ውስጥ ደግሞ በሚልየን ሳይሆን በቢልየን የሚቆጠሩ ትራንዚስተሮች ይገኛሉ።

ያለንበት ይህ ድንቅ ዘመን፣ "ታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር" የሚባል ከፍተኛ አቅም ያለው ኮምፒዩተር የተሠራበት ዘመን ነው። ታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር፣ ከሌሎች ኮምፒዩተሮች በፍጥነት፣ መረጃ በመያዝ አቅም፣ በሚሰጣቸው ውጤቶች፣ በሥራው ጥልቀትና ምጥቀት እንዲሁም በተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ኮምፒዩተር ነው። በታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር ውስጥ በሚገኘው አንድ ፕሮሰሰር ላይ ብቻ፣ ወደ ስምንት ቢልየን የሚደርሱ ትራንዚስተሮች ይገኛሉ። በጣም የሚገርመው ግን በአንድ ሱፐር ኮምፒዩተር ውስጥ፣ አንድ ብቻ ሳይሆን በሺዎች የሚቆጠሩ ፕሮሰሰሮች መኖራቸው ነው። አንድ ታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር በአሁኑ ወቅት ወደ አዲስ አበባ ቢመጣ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ኮምፒዩተሮች በድምር ከሚሰሩት ሥራ አስር በመቶ የሚሆነውን መሥራት ይችላል።

እነዚህ ሱፐር ኮምፒዩተሮች፣ ከማንኛውም የኮምፒዩተር መሸጫ ሱቅ የምንገዛቸው ሳይሆኑ፣ በልዩ ትዕዛዝ ተመርተው ለገበያ የሚቀርቡ ናቸው። የአንድ ታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር ዋጋ ወደ መቶ ሚልየን ዶላር ($100,000,000.00) ይደርሳል። ይህም ከሦስት ቢልየን ብር (3,000,000,000.00) በላይ እንደ ማለት ነው። ምናልባት በአገራችን በጣም ውድ የተባለ ኮምፒዩተር በመቶ ሺህ ብር (100,000.00) ሊሸጥ ይችላል። ይህ ታይታን የተባለ ሱፐር ኮምፒዩተር ግን በሺዎች ሳይሆን በሚልየኖች፣ በብር ሳይሆን በዶላር ነው የሚሸጠው። ዓለማችን እየሄደችበት ያለው የእድገት ፍጥነት  በጣም አስደናቂ ነው።

አንድ ምስጢር ልንገርህ? ከታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር ስለሚበልጥና ብዙ ቢልየን ብሮች ስለሚያወጣ አንድ ትልቅ ምስጢር! ከታይታን ሱፐር ኮምፒዩተር የበለጠ ዋጋ ያለው፣ አንድ ልዩ ሱፐር ኮምፒዩተር፣ የት እንደሚሸጥና እንዴት አድርገህ ልትገዛው እንደምትችል አሁን ልነግርህ ነው። ሱፐር ኮምፒዩተሩ ወደሚገኝበት ድንቅ ቦታ በቶሎ ስትሄድ፣ ከሦስት ቢልየን ብር በላይ ዋጋ ያለው ሱፐር ኮምፒዩተር በነጻ እየተሰጠ ታገኛለህ። የኮምፒዩተሩ ባለቤት ኮምፒዩተሩን በነጻ ከመስጠቱ በፊት ግን፣ አንድ ጥያቄ ይጠይቅሃል። "ይህን ከሦስት ቢልየን ብር በላይ የሚያወጣ ኮምፒዩተር በነጻ ስሰጥህ፣ ለምን ዓላማ ነው የምትጠቀምበት?" የሚል ጥያቄ። ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛና አሳማኝ መልስ መስጠት ከቻልክ፣ የሱፐር ኮምፒዩተሩ ተሸላሚ ትሆናለህ። አሁን እኔ ይህንን ሱፐር ኮምፒዩተር በነጻ የምታገኝበት ቦታ፣ የት እንደሆነ እንድነግርህ ትፈልጋለህ?

ይህ ሱፐር ኮምፒዩተር የሚገኘው በአሜሪካ፣ በቻይና ወይም በዱባይ አይደለም። ይህ ድንቅ ኮምፒዩተር የሚገኘው በአፍሪካ ውስጥ ነው። በአፍሪካ ውስጥ ስልህም በናይጀሪያ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በአልጀሪያ ወይም በሞሮኮ ሳይሆን ኢትዮጵያ በምትባል አገር፣ አንተ በምትኖርባት ከተማ፣ አሁን ባለህበት ሰፈር፣ ይህንን መጽሐፍ በምታነብበት ቦታ ነው። አሁን ኮምፒዩተሩ የት ሊገኝ እንደሚችል የገመትክ ይመስለኛል።

ይህ ሱፐር ኮምፒዩተር በአጠገብህ የሚገኝ አይደለም፤ ይልቁንስ በውስጥህ የሚገኝ ውድ በረከት እንጂ። ከተወለድክበት ዕለት አንስቶ፣ ይህ ሱፐር ኮምፒዩተር ከአንተ ጋር አብሮ የኖረ፣ ስትጠቀምበት ደግሞ ከራስህ አልፎ ቤተሰብህን እና መስሪያ ቤትህን ብቻ ሳይሆን አገርህን፣ ከዚያም አልፎ ዓለምን ሊቀይር የሚችል፣ ከፍለህ ልታገኘው፣ ዋጋ ተከራክረህ የራስህ ልታደርገው ስትል እንዳይከብድህ በነጻ የተሰጠህ፣ ሕይወትህን መለወጥ የሚችል ድንቅ ስጦታ ነው። ለነገሩ በሕይወታችን ውስጥ እጅግ በጣም ውድ የሆኑ ነገሮች፣ በነጻ ነው የተሰጡን!

ይህ ውድና ድንቅ ሱፐር ኮምፒዩተር፣ የሰው አንጎል ነው። የሰው አንጎል በዓለማችን ላይ ካሉ ፍጥረታት ሁሉ ተወዳዳሪ የሌለው፣ እጅግ በጣም ግሩም እና ድንቅ ፍጥረት ነው። እኛ የሰው አንጎል ስላለን ብቻ፣ በዚች ዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌለን እፁብ ድንቅ ፍጥረታት ነን። ታዲያ የሰው ልጆች መሆናችን በራሱ ደስ አይልም? ይህን የምነግርህ ደስ እንዲልህ ወይም እንዲሞቅህ አይደለም፤ ሕይወትህን ሊቀይር የሚችል ትልቅ ምስጢር በውስጡ ስላለ እንጂ።

የኒውሮ ባዮሎጂ ተመራማሪዎች በሰው አንጎል ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር አድርገው ያገኙት ውጤት በጣም የሚገርም ነው። አንጎላችን በአጉሊ መነጽር ሲታይ፣ በጣም ደቃቅ ከሆኑ በዐይን ከማይታዩ የአንጎል ሕዋሳት (Brain Cells) ወይም ከኒውሮኖች (Nuerons) የተሠራ ነው። አንድ የአንጎል ሕዋስ ወይም ኒውሮን በዐይን የማይታይ ቢሆን እንኳ፣ በአጉሊ መነጽር ስትመለከተው ግን፣ በውስጡ ፋብሪካ እንዳለ ማየት ትችላለህ። በአንድ የአንጎል ሕዋስ ውስጥ ሙሉ ፋብሪካ አለ። አሁን ኢንተርኔት ከፍተህ ስለ አንጎል ሕዋሳት ጥናት ብታደርግ፣ በውስጥህ ምን ዐይነት የሚገርም ድንቅ ፋብሪካ እንዳለ ማየት ትችላለህ።

ስለዚህ አንድ የአንጎል ሕዋስ አለህ ማለት አንድ ፋብሪካ አለህ ማለት ነው። ለመሆኑ ፋብሪካ ያለው ሰው ምን ያስፈልገዋል? አንድ የምታውቀው ሰው፣ የራሱ የሆነ ፋብሪካ ቢኖረው፣ ነገር ግን ፋብሪካውን ባይጠቀምበት፣ አልያም ባይሠራበት፣ ፋብሪካው በርግጥ ይከስራል። ይህ ባለ ፋብሪካ፣ ከተማ ላይ ወጥቶ "...እኔ እኮ ማንንም የለኝም፤ ምንም የለኝም" እያለ ሲያማርር ብትሰማው፣ ምን ብለህ ትመክረዋለህ? "አንተ ሰውዬ የራስህ ፋብሪካ አለህ አይደል እንዴ? ታዲያ ፋብሪካ ካለህ ምን ያስፈልግሃል? ቆይ ግን ለምን ፋብሪካውን በሥነ-ሥርዓት እና በጥሩ ሁኔታ አትሠራበትም?! ፋብሪካህን በአግባቡ ከተጠቀምክበት፣ አይደለም የራስህን ሕይወት፣ የቤተሰብህን እና የአገርህንም ጭምር መቀየር ትችላለህ!" ብለህ አትመክረውም ነበር?

አሁን ሰውዬውን ከመምከር መለስ እንበልና ራሳችንን እንፈትሽ። "በውስጣችን አንድ የአንጎል ሕዋስ አለ ማለት፣ አንድ ፋብሪካ አለን ማለት ነው" ብለናል። ታዲያ በዚህ ግሩም ፋብሪካችን ምን እየፈጠርንበት ነው? ምን እየሠራንበት፣ ምን እያመረትንበት፣ ምን እየቀየርንበት፣ ምንስ እያሻሻልንበት ነው? አብዛኛው ሰው ድንቅ ፋብሪካውን ትናንሽ ሥራዎችን ለመሥራት፣ ለመስነፍ፣ ለማሳበብና ለመዝናናት ብቻ ነው የሚጠቀምበት። በጣም የሚገርመው፣ በውስጣችን አንድ የአንጎል ሕዋስ (ፋብሪካ) ብቻ ሳይሆን፣ ከምናስበው በላይ እጅግ በጣም ብዙ የአንጎል ሕዋሳት ወይም ፋብሪካዎች አሉን። አንድ ሰው ምን ያክል የአንጎል ሕዋሳት እንዳሉት መገምት ትችላለህ? በእያንዳንዳችን ውስጥ በሺዎችና በሚልየኖች ሳይሆን በቢልየኖች የሚቆጠሩ የአንጎል ሕዋሳት ይገኛሉ። አዎ! በእያንዳንዳችን አንጎል ውስጥ እስከ መቶ ቢልየን የሚደርሱ የአንጎል ሕዋሳት አሉ።

ራሳችንን በማስተዋል ስንመለከት፣ ውስጣችንን የሞላው ተዓምር ብቻ ነው። የአንጎል ሕዋሶቻችን እርስ በርሳቸው ሲገናኙ፣ ሰይናፕሶችን (Synapses) ይፈጥራሉ። በማንኛውም ሰው ውስጥ መቶ ትሪልየን የሚደርሱ ሰይናፕሶች ይገኛሉ። አንድ ሰይናፕስ አንድ ባይት ዴታ (Data Byte) ብቻ የማስቀመጥ አቅም ቢኖረው እንኳ፣ በአንጎላችን ውስጥ የመቶ ቴራ ባይት ሀርድ ዲስክ ይኖር ነበር። ነገር ግን በአንድ ሰይናፕስ ውስጥ ያለው አቅም ከዚያ በላይ ስለሆነ፣ የእያንዳንዳችን አንጎል ከሁለት ነጥብ አምስት ፔንታ ባይት (2,500,000,000,000,000,000) ዴታ በላይ የማስቀመጥ ዕምቅ አቅም አለው።

መቶ ቢልየን ኒውሮኖች፣ መቶ ትሪልየን ሰይናፕሶችና ሁለት ነጥብ አምስት ፔንታ ባይት አቅም ያለው የዴታ ማከማቻ ቋት በመያዛችን፣ በርግጥም እኛ ድንቆች ነን። ሕይወታችንን ለመቀየር እና ትልቁን ሕልማችንን እውን ለማድረግ ደግሞ፣ የመጀመሪያው ርምጃ፣ እኛ ድንቅ መሆናችንን ማወቅ፣ መረዳት እና ማመን ነው። ስለዚህ ከአሁን በኋላ፣ "እኔ ድንቅ ነኝ! አቅሜ ድንቅ ነው! ድንቅ ሥራ እየሠራሁ ነው!" ብለን መነሳት አለብን። እንደዚህ ስናደርግ፣ ከውስጥ ወደ ውጪ መኖር እንጀምራለን።

አብዛኛው ሰው ግን ከውስጥ ወደ ውጪ ሳይሆን፣ ከውጪ ወደ ውስጥ ነው የሚኖረው። የሰው ልጅ በአካባቢው ላይ ያለውን ውጫዊ ዓለም በመመልከት፣ የሚፈልገውን ሰው፣ ገንዘብ ወይም ሌላ አዎንታዊ ነገር ካላገኘ ተስፋ ይቆርጣል፤ አሁን ያለው የማይፈልገው ነገርም ውስጡን እንዲቆጣጠር ይፈቅድለታል። በአካባቢው ያሉ ሰዎች "አትችልም! ከአቅምህ በላይ ነው!" የሚሉና ሌሎች አሉታዊ ሀሳቦችን ከነገሩት፣ የነገሩትን አሉታዊ ሀሳቦች ወደ ውስጡ ያስገባቸዋል። በአካባቢው ያለው የውጪው ዓለም ችግርም፣

የውስጡን ሰላም እንዲረብሽ ይፈቅድለታል። አንተም ከውጪ ወደ ውስጥ የምትኖር ከሆነ፣ በርግጥ የውጪው ዓለም መጫወቻ ነው የምትሆነው። መኖር ያለብህ ከውስጥ ወደ ውጪ ነው፤ ምክንያቱም በውስጥህ ተዓምር በመኖሩ፣ ተዓምሩን በደንብ መጠቀም ስትጀምር፣ ከውስጥ ወደ ውጪ በመኖር፣ የውጪውን ዓለም መቀየር ስለምትችል።

ብዙ ሰዎች ስለሚገርም አቅማቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰሙ ደስ ይላቸዋል። ትንሽ ቆይተው ግን ከውጪው ዓለም አንድ ከበድ ያለ ፈተና ሲያጋጥማቸው፣ ተስፋ ይቆርጣሉ፤ እጃቸውንም ይሰጣሉ። ከዚያም "ይህ ነገር ከአቅሜ በላይ ነው" ብለው ስለሞከሯት ትንሽ ነገር አለመሳካት ማማረር ይጀምራሉ። እነዚህ ሰዎች በርግጠኛነት አቅማቸውን አያውቁም። እኛ ሰዎች እኮ የመቶ ቢልየን (100,000,000,000) ፋብሪካዎች ባለቤቶች ነን! ይህ ደግሞ በአንጎላችን ውስጥ ብቻ ያለ አቅም ነው።

ምርምሩን ወደ ሌሎቹ የሰውነት ክፍሎቻችን ብናሰፋው፣ በአንድ የሰው ልጅ አካል ውስጥ፣ ወደ መቶ ትሪልየን (100,000,000,000,000) የሚጠጉ ሕዋሳት አሉ። አንድ ሕዋስም ልክ እንደ ኒውሮን በዐይን የማይታይ ቢሆንም፣ በአጉሊ መነጽር ሲታይ ግን በውስጡ ፋብሪካ አለው። በውስጥህ ያሉ መቶ ትሪልየን ሕዋሳትን ለመቁጠር ምን ያክል ጊዜ እንደሚያስፈልግህ መገመት ትችላለህ? ሙሉ ቀን ያለ ምንም ዐይነት ዕረፍት መቶ ትሪልየን ሕዋሳትን ለመቁጠር ብትሞክር እንኳ፣ በአንድ ቀን ውስጥ ባሉት 86,400 ሰከንዶች 86,400 ሕዋሳትን መቁጠር ትችላለህ። ያለ ምንም ዕረፍት መቁጠርህን ብትቀጥል፣ ሁሉንም በሰውነትህ ውስጥ ያሉ ሕዋሳት ለመቁጠር ብቻ፣ ሦስት ሚልየን (3,000,000) ዓመታት ያስፈልግሃል። ይህ ነው እንግዲህ የእኛ አቅም! እኛ ድንቅ ነን...! የእውነት ማን መሆናችንንና ምን ማድረግ እንደምንችል ስንረዳ፣ ተዓምር መሥራት እንችላለን።

ሕይወትህን ለመቀየርና ድንቅ ሕይወት ለመኖር፣ በመጀመሪያ አንተ ድንቅ መሆንህን መረዳት ያስፈልግሃል። ከዛሬ ጀምሮ በጥዋት እንደተነሳህ፣ ቀንህን "እኔ ድንቅ ነኝ! አንተ ድንቅ ነህ! አንቺ ድንቅ ነሽ! እኛ ድንቅ ነን! ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው! ኢትዮጵያ ድንቅ ናት!" በማለት ጀምር። በርግጥ አንዳንድ ቀናት ጥዋት ስትነሳ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ወይም ነገሮች ድንቅ ላይሆኑ ይችላሉ። በአካባቢህ ያሉ ሰዎችና ነገሮች ድንቅ ሆኑም አልሆኑም፣ ቀንህን "እኔ ድንቅ ነኝ፣ ዛሬ ድንቅ ነው!..." ብለህ ስትጀምር፣ ሙሉ ቀን ራስህን ድንቅ የምታደርግበትን መንገድ ብቻ በማሰብ፣ በመፈለግና በማድረግ፣ ራስህንና ቀንህን "ድንቅ" ታደርጋለህ።

ሁሌም ቢሆን ጥዋት ስነሳ "እኔ ድንቅ ነኝ! እኛ ድንቅ ነን! ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው!" በማለት ነው ቀኔን የምጀምረው። በየቀኑ ጥዋት ስነሳ ቀኔን "መልካም አዲስ ዓመት!" በማለት ነው የምጀምረው። ቀኔን "መልካም አዲስ ዓመት!" ብዬ ለመጀመር፣ እንደ አብዛኛው ሰው አዲስ ዓመት ወይም መስከረም አንድ እስኪመጣ አልጠብቅም። ዛሬ ጥዋት እስትንፋሴ ከኔ ጋር ስላለች ፈጣሪዬን በማመስገን፣ ቀኔን "መልካም አዲስ ዓመት!" ብዬ ነው የምጀምረው። በርግጥ እንደ ሁሉም ሰው በሕይወቴ የተለያዩ ፈተናዎችና ችግሮች ያጋጥሙኛል። ነገር ግን ከዕንቅልፌ እንደነቃሁ፣ "እኔ ድንቅ ነኝ! አንተ ድንቅ ነህ! አንቺ ድንቅ ነሽ! እኛ ድንቅ ነን! ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው! አገሬ ድንቅ ናት! መልካም አዲስ ዓመት!" በማለት ቀኔን እጀምራለሁ። በዚህም በሕይወቴ ያሉ ፈተናዎችንና ችግሮችን አሸንፋለሁ። በዚህ መንገድም ራሴንና ቀኔን ድንቅ የማደርግበትን መንገድ በመፈለግና በማድረግ ድንቅ ሆኜ እውላለሁ።

አንተም ከዛሬ ጀምሮ "እኔ ድንቅ ነኝ! አንተ ድንቅ ነህ! አንቺ ድንቅ ነሽ! እኛ ድንቅ ነን! ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው! አገሬ ድንቅ ናት! መልካም አዲስ ዓመት!" በማለት ቀንህን በመጀመርና መክፈል ያለብህን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ራስህን፣ ቀንህን፣ ቤተሰብህን፣ አገርህን፣ አህጉርህንና ዓለምን ድንቅ ማድረግ ትችላለህ። አንተ ድንቅ የፈጣሪ ልጅ ስለሆንክ፣ ለአንተ ሁሉም ነገር ይቻላል፤ የማይቻል ነገርም

የለም። የሚቀጥለው "ይቻላል" የሚለው ምዕራፍ፣ ሁሉም ነገር እንደሚቻልና የማይቻል ነገርም እንደሌለ ልዩና ድንቅ በሆነ መንገድ ትልቁን ሕልምህን እንዴት ማሳካት እንደምትችል በግልጽ ያስረዳሀል።

ቀጥለው የቀረቡት መፈክሮች ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር የሚረዱህ ድንቅ የሕይወት እና ስኬት መፈክሮች ናቸው። ከዛሬ ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ቀናት እነዚህን መፈክሮች በየቀኑ ደጋግመህ በመጻፍና ጮክ ብለህ በማንበብ፣ በልብህ ስትወቅራቸው፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል ራስህን፣ ቤተሰብህንና መስሪያ ቤትህን ብቻ ሳይሆን፣ አገርህን፣ አህጉርህንና ዓለምን እንድትቀይር ይረዱሀል።

እኔ ድንቅ ነኝ!

አንቺ ድንቅ ነሽ! አንተ ድንቅ ነህ! እርስዎ ድንቅ ነዎት!

እኛ ድንቅ ነን!

ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው!

አገሬ ድንቅ ናት! አህጉሬ ድንቅ ናት! ዓለም ድንቅ ናት!

ትልቅ ሕልም አለኝ! ሕልሜ ይቻላል!

አቅሜን ከመረዳቴ በፊት፣ ሕልሜ የማይቻል እና ከአቅሜ በላይ ይመስለኝ ነበር።

አሁን ግን ገብቶኛል!

ፈጣሪ በሕይወት ዘመኔ ሙሉ፣ ከምጠቀምበት በላይ፣ አቅም እና ችሎታ ሰጥቶኛል!

ፈጣሪዬን ለማመስገን፣ ድንቅ አቅሜን በመጠቀም፣ ትልቁን ሕልሜን እያሳካሁ ነው!

ሕልሜን ለማሳካትም መሆን ያለብኝን እየሆንኩ፣ መሥራት ያለብኝን እየሠራሁና

መክፈል ያለብኝን መሥዋዕትነት ያለ ምንም ድርድር እየከፈልኩ ነው!

ሲደክመኝ አላርፍም!

እኔ የማርፈው ሕልሜን በማሳካት ራሴን፣ ቤተሰቤን እና መስሪያ ቤቴን ስቀይር ነው!

አዎ! ሲደክመኝ አላርፍም!

እኔ የማርፈው ሕልሜን በማሳካት አገሬን፣ አህጉሬን እና ዓለምን ስቀይር ነው!

ተመስገን! ዛሬ ___|___|______ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!

ትልቁ ሕልሜ ስለተሳካ...

ራሴን፣ ቤተሰቤን እና መስሪያ ቤቴን ብቻ ሳይሆን አገሬን፣ አህጉሬን እና ዓለምን ቀይሬአለሁ!

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። እባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረክሁ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋናና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሃል!

# ቀን ፩

*******

# ይቻላል!

*"ሁሉም ነገር ይቻላል! የማይቻል ነገርም የለም!"*

"ሁሉም ነገር ይቻላል!" ሲባል ሰምተህ፣ አልያም ብለህ ሊሆን ይችላል። እውነት ግን፣ ሁሉም ነገር ይቻላል? "የማይቻል ነገር የለም" ሲባልም እንሰማለን። በርግጥ ግን የማይቻል ነገር የለም?

በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ የስኬት ሴሚናሮችንና ስልጠናዎችን ስሰጥ፣ አስቀድሜ ተሳታፊዎችን ከላይ ያነሳሁልህን ሁለት ጥያቄዎች እጠይቃቸዋለሁ። እነሱም መልሰው "አዎ ሁሉም ነገር ይቻላል! የማይቻል ነገር የለም!" ብለው ይመልሱልኛል። ከዚያ ግን አንድ ወረቀት አንስቼ፣ "ይህ ወረቀት መብረር ይችላል?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ "አይችልም!" ብለው ይመልሱልኛል። ተንቀሳቃሽ ስልኬንም ከኪሴ አውጥቼ፣ "ተንቀሳቃሽ ስልኬስ መብረር ይችላል?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ "አይችልም!" ብለው ደግመው ይመልሱልኛል። "እኔስ መብረር እችላለሁ? እኛስ አብረን መብረር እንችላለን?" ብዬ ስጠይቃቸውም፣ "አንችልም!" ብለው ይመልሱልኛል። ምናልባት አንተም እንደ ሌሎቹ ተሳታፊዎች ሁሉ "አይቻልም" ብለህ ልትመልስልኝ ትችላለህ። ታዲያ ሁሉም ነገር ይቻላል ሲባል፣ የእውነት አይደለም ማለት ነው? ወይስ ከማይቻሉ አንዳንድ ነገሮች በስተቀር ማለት ነው? ይህንን ጥያቄ ከመመለሴ በፊት፣ አስቀድሜ የማይቻል ነገር እንደሌለ ስላረጋገጡ ሁለት ድንቅ ወንድማማቾች ልንገርህ።

ሁለቱ የራይት ወንድማማቾች "መብረር እንችላለን" ብለው ሲነሱ፣ "መብረር ይቻላል!" ብሎ የሚያምን ሰው አልነበረም። ኦርቪል እና ዊልበር ግን "መብረር እንችላለን" ብለው በማመን፣ ሙከራቸውን ጀመሩ። በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች፣ "እናንተ እብዶች ናችሁ እንዴ?! እንዴት ነው የምትበሩት? ሰው'ኮ በመሬት ላይ እንዲሄድ ነው የተፈጠረው! ይህ የምታስቡት ሀሳብ የሰይጣን ሀሳብ ነው! እንደዚህ በማሰባችሁ ደግሞ በሲኦል ትቃጠሏታላችሁ" ይሏቸው ነበር። ሁለቱ ወንድማማቾች ግን፣ "ይቻላል!" ብለው በማመን የመጀመሪያውን አውሮፕላን ለመሥራት የጀመሩትን ሙከራ አጠናክረው ቀጥለዋል።

እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር፣ ታሕሳስ 17፣ 1903 ዓ.ም. የራይት ወንድማማቾች የመጀመሪያውን አውሮፕላን በመሥራት፣ ለአስራ ሁለት ሰከንዶች በአየር ላይ መንሳፈፍ ችለዋል። በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ግን፣ "አዎ መብረሩንስ በራችኋል፤ ነገር ግን የበረራችሁት ለአስራ ሁለት ሰከንዶች ብቻ ነው!" ነበር ያሏቸው። የራይት ወንድማማቾች፣ "እኛ መጀመሪያ 'ይቻላል' ብለን እንደተነሳን መብረር ችለናል፤ እንዲያውም ለአስራ ሁለት ሰከንዶች አየር ላይ ለመንሳፈፍ ችለናል" ብለው ነበር የመለሱላቸው። የሰው የዕይታ ልዩነት በጣም ነው የሚገርመው! የራይት ወንድማማቾች በ19ኛው ክፍለ ዘመን "አይቻልም" ይባል የነበረን የመብረር ሕልም፣ እንዴት እንደሚቻል፣ ለዓለም በተግባር በማስተማር ታሪክ ቀይረዋል።

ከዚህ ምዕራፍ አንድ ቁም ነገር መውሰድ ካለብህ፣ ሁሉም ነገር እንደሚቻልና የማይቻል ነገርም እንደሌለ ነው። ለአንተ ድንቅ የፈጣሪ ልጅ፣ ሁሉም ነገር ይቻላል፤ የማይቻል ነገርም የለም። ስለዚህ ለአንተ ሁሉም ነገር የሚቻል ስለሆነ፣ ሕልምህ ምንድን ነው? ትልቁን ሕልምህን በአዕምሮህ ስታስበውና በልብህ ስታምነው፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመከፈል ሕልምህን የእውነት መኖር ትችላለህ። በልብህ ይህን እውነታ ማመን ይከብደዋል። "ሕልሜን መኖር እችላለሁ" ብሎ ቢያስብም፣ ሕልሙን መኖር እንደሚችል በልቡ እምነት የለውም። እንዲህ ዐይነቱ ሰው፣ "ሕልሜን መኖር እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን አሁን አልችልም፤ ምክንያቱም አቅሙ የለኝም፤ እውቀቱ የለኝም፤ ገንዘቡ የለኝም፤ የሚረዳኝ ሰው የለም፤ ሕልሜን ለማሳካት የሚያግዝ ምንም ነገር የለኝም፤..." በማለት ተስፋ ይቆርጣል። "እኔ እኮ እንደ ራይት ወንድማማቾች ሁሉም ነገር የተመቻቸለት ሰው አይደለሁም!" ብሎ በሕልሙ ተስፋ ሊቆርጥ ይችላል።

የራይት ወንድማማቾች፣ ሁሉ ነገር ስለተመቻቸላቸው ነበር እንዴ መብረር የቻሉት? አይደለም! የራይት ወንድማማቾች "እንበራለን" ብለው ሲወስኑ፣ በጣም ብዙ ያልተመቻቹና የሚጎድሏቸው ነገሮች ነበሩ። በዚያን ጊዜ፣ እንደ አሁኑ ዘመን፣ ኢንተርኔት ከፊት አድርገው የሚያስፈልጓቸውን መረጃዎች በቀላሉ ሊያገኙ የሚችሉበት ምንም ዐይነት ድረ ገጽ ወይም መንገድ አልነበረም። እንዴት መብረር እንደሚችሉ የሚያሳያቸው ሰውም አልነበረም። እነሱ ግን ያንን ተዓምራዊ የሆነ ሕልማቸውን፣ "እውን ማድረግ እንችላለን" ብለው ስላመኑ፣ የዓለምን ታሪክ በሚገርም መንገድ ቀየሩ።

ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ "በራይት ወንድማማቾች ውስጥ ያሉ መቶ ቢልየን ኒውሮኖች የመጀመሪያውን አውሮፕላን ከሰሩ፣ በእኔና በአንተ ውስጥ ያሉ መቶ ቢልየን ኒውሮኖች ምን እየሰሩ ነው?" የሚል መሆን አለበት። "እኔ ድንቅ ስለሆንኩ፣ ሁሉ ነገር የሚቻል ስለሆነና የማይቻል ነገርም ስለሌለ፣ የእኔ ትልቅ ሕልም ምንድን ነው? ምን መሆን እፈልጋለሁ? ምንስ ማድረግ እፈልጋለሁ?" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን።

በዛሬው ጥናታችን መጀመሪያ ላይ በተለያዩ ሴሚናሮች፣ ተሳታፊዎችን "ሁሉም ነገር ይቻላል?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ "አዎን ሁሉም ነገር ይቻላል! የማይቻል ነገርም የለም" ብለው እንደመለሱልኝ፣ ነገር ግን በእጄ የነበረው ወረቀት እና ተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም እኔ እና እነሱ መብረር እንደምንችል ስጠይቃቸው "አይቻልም" ብለው እንደመለሱልኝ ጠቅሰን ነበር። ለምንድን ነው ሰው "ሁሉም ነገር ይቻላል፤ የማይቻል ነገርም የለም!" እያለ፣ "አንተስ እንደዚህ ማድረግ ትችላለህ?" ተብሎ ሲጠየቅ "አልችልም" ብሎ የሚመልሰው? ምክንያቱም "አይቻልም" የሚል ቃል እና አስተሳሰብ ከልጅነታችን ጀምሮ በውስጣችን ስለተቀረጸ ነው። ሁሉም ነገር ይቻላል፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር እንዲቻል፣ "ሁሉም ነገር ይቻላል" የሚል ሀሳብ እና እምነት በልብህ መወቀር አለበት።

በሴሚናሮቹ ላይ ብዙዎቹ "አይቻልም" ብለው የመለሷቸውን አስቀድመን ያነሳናቸውን ጥያቄዎች አሁን ደግመን እንመልከታቸው። ለምሳሌ ወረቀት መብረር ይችላል። ልጆች እያለን ወረቀት አጣጥፈን፣ የአውሮፕላን ወይም ጀት ቅርፅ አስይዘን እንዲበር እናደርገው ነበር። ወረቀት መብረር ይችላል፤ መብረር እንደሚችልም፣ ከልጅነታችን ጀምሮ የምናውቀው ነገር ነው። ወረቀቱ እንዲበር ግን የወረቀቱ ቅርፅ መቀየር አለበት። አንተም ሕልምህን እውን ማድረግ ትችላለህ። ነገር ግን በመጀመሪያ ራስህን መቀየር አለብህ። ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ስትቀይር፣ ሕልምህን ማሳካት ትችላለህ፤ ማሳካት የማትችለው ሕልምም አይኖርም።

ወረቀቱ እንደበረረው ሁሉ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክም መብረር ይችላል። የተንቀሳቃሽ ስልካችንን መሸፈኛ በአንድ ዘመናዊ የሆነ የድሮን መሸፈኛ ብንቀይረው፣ ተንቀሳቃሽ ስልካችን ከሰማይ ሆኖ ፎቶ ሲያነሳና ቪዲዮ ሲቀርጽ እንደሚችል በተለያዩ አጋጣሚዎች አይተህ ይሆናል። ተንቀሳቃሽ ስልክህ መብረር ይችላል፤ መሸፈኛው መቀየር አለበት። አንተም ሕልምህን ማሳካት ትችላለህ። የምትነሳበትንና የምትተኛበትን ሰዓት፣ የምትውልበትን ቦታ፣ እንዲሁም የምታስብበትንና የምትንቀሳቀስበትን መንገድ መቀየር አለብህ።

በሴሚናሩ ከጠየቅኳቸው ጥያቄዎች ሌላኛው "እኔስ መብረር እችላለሁ?" የሚል ነበር። ልክ በእጄ እንደነበረው ወረቀት እና ተንቀሳቃሽ ስልክ ሁሉ፣ እኔም መብረር እችላለሁ፤ ነገር ግን ጫማዬ ወይም ልብሴ መቀየር አለበት። በዚህ ድንቅ ዘመን አንድ ሰው ለሰዓታት እንዲበር የሚረዱ ድንቅ ጫማዎች እና ልብሶች እየተሰሩ ነው። ስለዚህ እኔም መብረር እችላለሁ፤ ነገር ግን እንድበር ጫማዬ ወይም ልብሴ መቀየር አለበት። ዋናው ቁም ነገር አሁን በሕይወትህ ያሉ ሕልምህን እንዳታሳካ ዕንቅፋት እየሆኑብህ ያሉ ሀሳቦችን፣ ሰዎችን እና ነገሮችን በሌሎች ሕልምህን ለማሳካት በሚረዱህ ሀሳቦች፣ ሰዎች እና ነገሮች ስትቀይራቸው፣ ሕልምህን ማሳካት ትችላለህ፤ ማሳካት የማትችለው ነገርም የለም።

በሴሚናሩ ከጠየቅኳቸው ጥያቄዎች መካከል የመጨረሻው "እኛስ አብረን መብረር እንችላለን?" የሚል ነበር። የዚህ ጥያቄ መልሰም "አዎ! አብረን መብረር እንችላለን" የሚል ነው። ነገር ግን ሁላችንም አብረን እንድንበር፣ አሁን የተቀመጥንበትን ወንበር እና ያለንበትን ከፍል በአንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን መቀየር አለብን። እኛ የሰው ልጆች በአውሮፕላን ውስጥ ከቤተሰቦቻችንና ከጓደኞቻችን ጋር እየበላን፣ እየጠጣን፣ እየተዝናናን፣ ኢንተርኔት እየተጠቀምን፣ ደመናውን ሰንጥቀን፣ ከአገር ወደ አገር እየተጓዝን ነው። "ሁሉም ነገር ይቻላል፤ የማይቻል ነገርም የለም" ሲባል፣ እውነት ስለሆነ አሁን መፈለግ ያለብን፣ የምንፈልገው ነገር የሚቻልበትን መንገድ ብቻ መሆን አለበት።

የአብዛኛው ሰው ችግር "ሕልሜ ይቻላል!" ብሎ ቢያስብም፣ በልቡ ሕልሙ እንደሚቻል እምነት አለማሳደሩ ነው። አብዛኛው ሰው ሕይወቱን መቀየር የሚችል ትልቅ ሕልም ያልማል። ነገር ግን "ይቻላል!" ብሎ ከልቡ ስለማያምን፣ ሕልሙን ወደ ኋላ አስቀምጦ፣ የማይፈልገውን ሕይወት መኖሩን ይቀጥላል። ከመቶ ዓመት በፊት በሰማይ ላይ መብረር ከተቻለ፣ አንድ ጊዜ አስበኸው የነበረ፣ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች፣ "አይቻልም" ብለህ ተስፋ የቆረጥከበት ሕልም፣ ለምን አይቻልም?! በርግጥ ይቻላል! ከዚህ በኋላ፣ የአንተ እምነት፣ "ሁሉም ነገር ይቻላል! እኔም ሕልሜን መኖር እችላለሁ!" የሚል እምነት ብቻ መሆን አለበት። ይህ የስኬት ዋናው ቁልፍ ነው።

ይህንን የስኬት ቁልፍ ይዘህ ሕይወትህን ለመቀየርና ሕልምህን ለማሳካት ስትነሳ፣ ከአንድ በውስጥህ ካለ የስንፍና ድምጽ ጋር መከራከር ትጀምራለህ። ይህ የስንፍና ድምጽ፣ በሁላችንም ውስጥ የሚገኝ ድምጽ ሲሆን፣ "ሰበበኛው" ይባላል። ለምሳሌ እኔ ዳዊት ድሪምስ ነኝ። በውስጤ ግን አንድ ሌላ "ዳዊት ሰበበኛ" የሚባል ሰውዬ አለ። እኔ ዳዊት ድሪምስ በመሆን በጥዋቱ፣ "እኔ ድንቅ ነኝ! ትልቅ ሕልም አለኝ! ሕልሜ ይቻላል! ሕልሜን ለማሳካት መከፈል ያለብኝን መሥዋዕትነት እየከፈልኩ ነው!" ብዬ ስነሳ፣ ሰበበኛው ዳዊት ደስ አይለውም። ሰበበኛው ዳዊት በጥዋት ተነስቼ፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ሕልሜን እንዳላሳካና ሕይወቴን እንዳልቀይር፣ ገና ከዕንቅልፌ ሳልነሳ ጀምሮ የማሳበብ እና የማሳነፍ ሥራውን ይጀምራል።

ሰበበኛው ዳዊት በጥዋት የምነሳበት ሰዓት ደርሶ የማንቂያ ደውል ሲጮህ፣ እንደዚህ ብሎ የማማከር እና የማሳበብ ሥራውን ይጀምራል። "ዳዊትዬ አንተ እኮ ትልቅ ሕልም ያለህ ድንቅ ዳዊት ድሪምስ ነህ። አዎ! የጥዋት ዕንቅልፍህን መሥዋዕት በማድረግ፣ ሕልምህን ማሳካት እና ሕይወትህን መቀየር የምትችል ሰው ነህ። ነገር ግን ዛሬ ጥዋት ዝናባማ ነው፤ አሁን መነሳት ይደብራል፤ ትንሽም አመም አድርጎሀል። እናም እንደዚህ ሆነህ ከተነሳህ፣ ቀኑን ሙሉ ያምሀል። ስለዚህ ትንሽ እንተኛ" ብሎ እንድሰንፍ እና ሰበቡን ተቀብዬ እንድተኛ ያማክረኛል። በፊት በፊት፣ የራሴ ሰበበኛ እንደዚህ እያለ ሁሌ ያሸንፈኝና ይጫወትብኝ ነበር። አሁን ግን የራሴን ሰበበኛ ስለነቃሁበት አላዳምጠውም። የተለመደውን ሰበብ ማሳበብ ሲጀምር፣ "ዞር በል!" ብዬ በማባረር፣ መሆን ያለብኝን እሆናለሁ፤ መሥራት ያለብኝንም እሠራለሁ።

የአንተ ሰበበኛስ ጥዋት ምን ብሎ ነው የሚያሳብበው? ከዚች ደቂቃ ጀምሮ፣ ያንተን ሰበበኛ በመዝጋትና በማባረር፣ ትልቁን ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ሁሉ አሁኑኑ መከፈልህን ጀምር።

ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እስከምታሸንፈው ድረስ፣ ሰበበኛው ምንም ዕረፍት አይሰጥህም። ሰበበኛውን በጥዋት አሸንፈኸው ከቤት ስትወጣ ደስ ስለማይለው፣ መሥሪያ ቤትህ ስትገባም ሌሎች ሰበበኞችን ይጠብቅሃል። የኔ ሰበበኛ፣ ሕልሜን ለማሳካት እና ሕይወቴን ለመቀየር ወደ ቢሮ ስገባ፣ "ዳዊትዬ አንተ ለዚ ሕልምህን ለማሳካት ከጥዋት ጀምሮ የምትከፍለው መሥዋዕትነት በጣም የሚገርም ነው። ነገር ግን ይህ ትልቅ ሕልም ይቅርብህ። ይህ 'ኢትዮጵያንና አፍሪካን እቀይራለሁ' የሚለው ትልቁ ሕልምህ፣ በጣም ከባድ ሕልም ነው። ከአቅምህ በላይም ነው። አንተ ደግሞ አማርኛ ይከብድሃል። የምታውቀው ሰውም የለም። ምን አደከመህ? ምንስ አለፋህ? ይህ ትልቅ ሕልም የማይቻል ነገር ስለሆነ ይቅርብህ" ብሎ ነበር የሚያማክረኝ። የራሴን ሰበበኛ እስከማሸንፈውና እስከማባርረው ድረስ፣ ሕይወቴን መቀየር ከብዶኝ ነበር። አሁን ግን የራሴን ሰበበኛ ከሕይወቴ ስላባረርኩት፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ሕልሜን እያሳካሁ እና ሕይወቴን እየቀየርኩ ነው።

ያንተ ሰበበኛስ ምን ብሎ እያማከረህ ነው? ሰበበኛውን ካላሸነፍከውና ካላባረርከው፣ ሁሌም ያዳክምሃል። የራስህ ሰበበኛ ሕልምህን ለማሳካት፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት እንዳትከፍል፣ ሁሌም ሰበብ ይደረድርልሃል። መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ሁሉ ብትከፍል እንኳ፣ ሕልምህን ማሳካት እንደማትችል ሊያሳምንህ ይሞክራል። ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልግህ ገንዘብ፣ ሰው፣ ትምህርት፣ ልምድ፣ ጊዜ፣ ቦታ ወይም ሌላ ነገር እንደሌለህ ደጋግሞ ይነግርሃል። "ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልጉህ ነገሮች ስለሌሉህ፣ አሁን ሕልምህን ማሳካት አትችልም" ብሎም ያሳምንሃል። አሁን የአንድ ሕፃን ልጅ ታሪክ እነግርሃለሁ። ይቺ ሕፃን ልጅ የራሷን ሰበበኛ በማሸነፍና ሕልሟን በማሳካት፣ ሕይወቷን ብቻ ሳይሆን፣ ዓለምንም ቀይራለች።

ይቺ ሕፃን ልጅ በጣም ድሀ ከሆነ ቤተሰብ እና የትዳር አጋር ከሌላት ብቸኛ እናት ስለተወለደች፣ በዚች ዓለም ያላሳለፈችው ምንም ዐይነት ችግር እና መከራ አልነበረም ማለት ይቻላል። ይቺ ምስኪን ሕፃን፣ ከዘጠኝ ዓመቷ ጀምሮ እስከ አስራ አራት ዓመቷ ድረስ፣ በተደጋጋሚ በተለያዩ የቅርብ ቤተሰቦቿ ተደፍራለች። በአስራ አራት ዓመቷ ልጅ ወለደች። ነገር ግን የወለደችው ልጅ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሞተባት!

በነዚህ ሁሉ መከራዎች እያለፈች ቢሆንም፣ ተስፋ ሳትቆርጥ፣ ትምህርቷን በመማር፣ በአስራ ዘጠኝ ዓመቷ ጋዜጠኛ ለመሆን በቃች። ከዚያም በሃያ አንድ ዓመቷ ፊልም መሥራት ጀመረች። ይቺ ድንቅ ሴት ማን ትመስልሃለች? ይቺ ሴት ኦፕራ ዊንፍሬ ናት። ብዙ ሰው ኦፕራ ዊንፍሬን በቴሌቪዥን ሲመለከታት፣ "ይቺ ደግሞ ምን ችግር ታውቃለች? ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ የሆነላት ሴት ናት" ብሎ ነው የሚያስበው። የኦፕራ ሕይወት ግን አልጋ በአልጋ አልነበረም። እሷ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ሕይወቷን አልጋ በአልጋ ማድረግ ቻለች እንጂ። ታዲያ ያንተን ሕይወትስ ማን አልጋ በአልጋ እስከሚያደርግልህ ድረስ እየጠበቅክ ነው?

ኦፕራ ጋዜጠኛ መሆን ፈልጋ ወደ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ስትሄድ ሁሉም አልተቀበሏትም፣ ፊልም መሥራት ፈልጋ ወደ ፊልም አሠሪዎች ስትሄድም ይቀልዱባት ነበር። "መልክሽ ለቴሌቪዥን አይሆንም፣ ስምሽ ደግሞ ምንድን ነው?! በጣም ያስጠላል፤ ባይሆን ሬዲዮ ጣቢያ ላይ ብትሞክሪ ይሻልሻል። በዚያ ላይ ልምድ እንኳ የለሽም" እያሉ ያጣጥሏት ነበር። አያቷም "ልጄ፣ እኔ የምልሽን ስሚ፤ ቆንጆ ሕይወት መኖር የምትፈልጊ ከሆነ፣ ለነጮቹ ቤታቸውን አጽጂላቸው፤ ምግብ አብስዪላቸው፤ ልብሳቸውን አጥበሽ ተኩሺላቸው፤ ይህን ታዛዥነትሽን አይተው ደግሞ እነሱ የተሻለ ሕይወት እንድትኖሪ ይረዱሻል" ብላ ትመክራት ነበር።

ኦፕራ ድንቅ አስተሳሰብ ስለነበራት፣ "ሕልሜን መኖር እችላለሁ!" የሚል ትልቅ እምነት ነበራት። ይህን ሕልም እውን ለማድረግ መከፈል ያለባትን መሥዋዕትነት ሁሉ በመክፈል፣ ማድረግ ያለባትንም ነገር ሁሉ በማድረግ፣ የራሷን ሕይወት ብቻ ሳይሆን ዓለምንም በሚገርም ሁኔታ እየቀየረች ትገኛለች። ኦፕራ በዚያ ሁሉ ፈተና አልፋ፣ ማንም ሳይረዳት ሕልሟን እውን አድርጋ ዓለምን ከቀየረች፣ "እኔስ ምን ማድረግ

እችላለሁ?" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። አሁን የአጥራን ታሪክ ስታነብ፣ የራስህ ሰበበኛ ለጊዜው ጸጥ ይላል። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን የተሻለ ሰበብ ያቀርብልሀል። ሰበበኛው "አዎ! አንተም ልክ እንደ አጥራ፣ አንድ ቀን ሕይወትህን እና ዓለምን መቀየር ትችላለህ። አሁን ግን ሕልምህን ለማሳካት የሚሆን በቂ ገንዘብ የለህም፤ ጊዜም የለህም፤ የሚረዳህ ሰውም የለም፤ ትምህርት እና የሥራ ልምድም የለህም" ይልሀል። "ሕልምህን ለማሳካት ብዙ ነገር ስለሌለህ፣ አሁን ሕልምህን ማሳካት አትችልም" ብሎም ተስፋ ያስቆርጥሀል።

ሰበበኛው እንደዚህ ብሎ ወደ ኋላ እንዳይመልስህ፣ እጅና እግር ስለሌለው ኒክ ቩይሲክ ስለሚባል አንድ ሰው ልንገርህ። የኒክ ቩይሲክ ሰበበኛ፣ "እጅና እግር የለህም! ስለዚህ ሕልምህን ማሳካትም ሆነ ሕይወትህን መቀየር አትችልም!" እያለ ተስፋ ሊያስቆርጠው ሞክሯል። ኒክ ቩይሲክ ግን "እጅና እግር ባይኖረኝ እንኳ፣ ሕልሜን ማሳካት እችላለሁ!" ብሎ በመነሳት ሰበበኛውን አሸንፎታል። ኒክ ቩይሲክ "LIFE WITHOUT LIMITS" የሚል መጽሐፍ ጽፏል። ኒክ የጻፈው መጽሐፍ "እጅ እና እግር አልባ ሕይወት" (LIFE WITHOUT LIMBS) የሚል ሳይሆን "ገደብ አልባ ሕይወት" (LIFE WITHOUT LIMITS) የሚል ነው።

ኒክ "እጅ እና እግር አልባ ሕይወት" የሚል መጽሐፍ መጻፍ ይችል ነበር። ነገር ግን ስለ ችግር ማውራትም ሆነ ማማረር ስለማይወድ፣ መጽሐፉን "ገደብ አልባ ሕይወት" ብሎ ነው የጻፈው። አገራችን ላይ የታዘብኩት አንዱ ነገር፣ አብዛኛው ሰው ስለ ችግር ማሰብ እና ማውራት ልማድ እንደሆነበት ነው። ለምንድን ነው ሰው በጥዋት ተነስቶ፣ ቁርስ ከመብላቱ በፊት ስለ ችግር በማሰብ እና በማማረር ፊቱንና ቀኑን የሚያበላሸው? ለምንድን ነው ሰዎች ስለ ትልቅ ሕልማቸው ማውራት ትተው፣ ስለ ችግራቸው በማማረር፣ ጊዜያቸውን የሚያቃጥሉት? ምክንያቱም አብዛኛው ሰው ስለ ችግር የማውራት እና የማማረር ሱስ ስላለበት ነው።

እኔን የሚገርመኝ፣ አንዳንድ ሰዎች ችግር ካልሰሙ የሚደብራቸው መሆኑ ነው። ብዙ ሰዎች በጥዋት ተነስተው ስልካቸውን ከፍተው ዜና ሲጎረጉሩ፣ መጥፎ ዜና ካልሰሙ፣ ብዙም ደስ አይላቸውም። በርግጥ እነዚህ ሰዎች በአገራችንም ሆነ በዓለም ዙሪያ ምንም ዐይነት ችግር እንዲፈጠር አይፈልጉም። ነገር ግን የችግር ዜና ሱስ ስላለባቸው፣ የችግር ዜና ካላዩ ወይም ካልሰሙ ደስ አይላቸውም። እነዚህ ሰዎች ስልካቸውን ከፍተው፣ አንድ መጥፎ ዜና ካዩ ወይም ከሰሙ፣ የወሬ ሱሳቸውን የሚያረካ ለሙሉ ቀን የወሬ ፍጆታቸው የሚውል ርዕስ ስለሚያገኙ፣ ምንም ሳያስቡት ደስ ይላቸዋል። ሙሉ ቀን ለሚያገኙት ሰው ሁሉ፣ "የዛሬውን ዜና ሰምተሀል? ከነዚህ ሰዎች ጋር እኮ መኖር አልቻልንም!" በማለት ወሬ ሲያቀባብሉ ይውላሉ። ስለ ችግር በማውራት እና በማማረር፣ የራሳቸውንና የሌሎች ሰዎችን ቀን በማበላሸት፣ ተስፋ ቆርጠውና አሉታዊ ስሜት ተሸክመው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። መረዳት ያለብን ነገር፣ "ችግር ስለ ችግር በማውራት አይፈታም"

አዎ! ችግር የሚፈታው፣ በመፍትሄ ብቻ ነው። ውድ ጊዜያችንን ስለ ችግር በማውራትና በማማረር ከምናባክነው፣ መፍትሄ ለመፈለግና ለመፍጠር ብንጠቀምበት፣ አገራችንን መቀየር እንችላለን። ኒክ ይህንን ስለተረዳ ነው "እጅ እና እግር አልባ ሕይወት" ብሎ ሳይሆን "ገደብ አልባ ሕይወት" ብሎ መጽሐፉን የሰየመው።

ኒክ ቩይሲክ በብቃት ከሚከውናቸው ነገሮች መካከል አንዱ "ዋና" ነው። እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ። አንተ መዋኘት ትችላለህ? መልስህ "አዎን" የሚል ከሆነ፣ ዋና ለመዋኘት የትኛውን የሰውነት አካልህን ትጠቀማለህ? እጅና እግርህን ነው አይደል? አሁንም ሌላ ጥያቄ ልጠይቅህ። እጅና እግር የሌለው ሰው መዋኘት ይችላል? አንተስ እጅና እግር ባይኖርህ ኖሮ መዋኘት ትችል ነበር? አብዛኛው ሰው ከልጅነቱ ጀምሮ "አይቻልም" የሚለው እምነት በውስጡ ተገንብቶ ስለሚያድግ፣ "እጅና እግር የሌለው ሰው'ማ መዋኘት አይችልም" ብሎ ነው የሚመልሰው። ኒክ ቩይሲክ ግን "እጅና እግር ባይኖረኝም፣ መዋኘት እችላለሁ" ብሎ በመነሳት ታሪክን ቀየረ።

---

፪. ይቻላል

ብዙ ሰው "ገንዘቡ ስለሌለኝ፣ የራሴን ሥራ መጀመር አልችልም፤ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ስለሌለኝ፣ የምፈልገውን ሥራ ማግኘት አልችልም፤ ሰው ስለሌለኝ፣ የምፈልገውን እድገት ማግኘት አልችልም..." ብሎ ተስፋ ይቆርጣል። ነገር ግን ከኒክ የምንማረው፣ "ገንዘቡ ባይኖረኝም፣ ሥራ መጀመር እችላለሁ፤ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ባይኖረኝም፣ የምፈልገውን ሥራ መሥራት እችላለሁ፤ ሰው ባይኖረኝም፣ የምፈልገውን እድገት ማግኘት እችላለሁ..." የሚል የአሸናፊነት አስተሳሰብ ነው። ኒክ ስለሌለው ነገር በማማረር ሳይሆን፣ ባለው ነገር በማመስገን እና ለሕልሙ በመታገል ነው የሚታወቀው። በዚህ ሰዓት ከሚወዳት ሚስቱ አራት ልጆችን ወልዶ፣ ዓለምን እየዞረ፣ ሰዎች ሕልማቸውን እንዲኖሩ በተግባር እያስተማረና እየረዳ ይገኛል።

በአገራችን ኢትዮጵያም ሕልማቸውን ለማሳካት የሚገርም ታሪክ የሰሩ ብዙ ሰዎች አሉ። ስለ አንድ የአሰላ ብላቴና አስቀድሜ ልንገርህ። ይህንን ብላቴና ከተወሰኑ ዓመታት በፊት "ሕይወት እንዴት ነው?" ብለን ብንጠይቀው፣ ስለነበሩበት ችግሮች እያነሳ ሊያማርርብን ይችላል። "በአገራችን ትራንስፖርት የለም፤ ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ሁሌ በእግራችን እየሮጥን ነው የምንመላለሰው። ይሄ ሩጫ የሚባል ነገር ስልችት ብሎኛል" ብሎ ማማረሩን ሊቀጥል ይችላል። ለዚህ ብላቴና፣ "ይህንን ሩጫ እንዳትጠላው። ምክንያቱም ይህን ሩጫ በዓላማ ከተጠቀምክበት፣ አንድ ቀን ሕይወትህን ሊቀይር ይችላል" ብለን ብንመክረው፣ ላይረዳን ይችላል።

ምክራችንን በመቀጠልም "ይህንን ሩጫ በደንብ ከሮጥከና ትልቅ ሯጭ መሆን እንደምትችል ካመንክ፣ በኢትዮጵያ በሚደረገው የሩጫ ውድድር አሰላን ወክለህ ታሸንፋለህ! ከዚያም ኢትዮጵያን ወክለህ በአፍሪካና በዓለም የሚደረጉ የሩጫ ውድድሮች ላይ አሸናፊ በመሆን ብዙ ሜዳሊያዎችን ትሸለማለህ። 'የዓለም የሩጫ ንጉሥ' ትሆናለህ። በየክፍለ አገራቱ ሪዞርቶችን ትገነባለህ፤ ሕንጻዎችን ትሠራለህ፤ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚደንት ትሆናለህ፤ በራስህ ፍላጎትም ትለቃለህ፤ የሀይንዳይ ሞተርስ ፋብሪካን ትከፍትና በሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች የሥራ ዕድል ትፈጥራለህ..." ብንለው፣ ራሱን ሊስት ይችላል። አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ ግን ይህንን ትልቅ ሕልም እውን አደረገ።

ብዙ ሰዎች ስለ ኃይሌ የተለያዩ ወሬዎችን ሲያወሩ ስሰማ በጣም ይገርመኛል። "ኃይሌ እኮ አይረባም፣ ቋጣሪ ነው፤ የማይሆኑ ማስታወቂያዎችን ነው የሚሠራው" ወዘተ... እያሉ በኃይሌ ላይ ሲቀልዱ በጣም ነው የሚገርመኝ። ኃይሌ ምን ማድረግ እንዳለበት ከማውራቴ በፊት፣ እኔ ምን እያደረግኩ እንደሆነ ራሴን መፈተሽ አለብኝ። ኃይሌ እኮ ከዜሮ በመነሳት ሕይወቱን እና ቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን አገሩንና ዓለምን እየቀየረ ያለ ሰው ነው። ኃይሌ ሕይወቱን እና ዓለምን የቀየረው፣ ቢሮ ውስጥ ቁጭ ብሎ ቀላላል ሥራዎችን በመሥራት ሳይሆን፣ ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮችን በመሮጥ ነው።

ብዙ ሰው ረዘም ያለ ርቀት ስለማይሮጥ፣ አስር ሺህ ሜትር መሮጥ ምን ያክል መሥዋዕትነት እንደሚያስከፍል ላይረዳ ይችላል፤ ኃይሌ ግን መሮጥ ያለበትን ሩጫ በመሮጥና መክፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ በዓለማችን ላይ ታሪክ ሰርቷል። በርግጥ ኃይሌ ሰው ስለሆነ ሊሳሳትና ልክ ያልሆኑ ነገሮችን ሊያደርግ ይችላል። ታዲያ የኃይሌን ትናንሽ እንከኖች በመልቀም "ከመፎተት"፣ የኃይሌን ድንቅ ነገሮች በማድነቅ ብናመሰግን አይሻልም? የኃይሌን ብቻ ሳይሆን በአገራችን ላይ ትላልቅ ሥራዎችን የሠሩ ሰዎችን እንከን በመልቀም ምንም ጥቅም አናገኝም። እነዚህ ድንቅ ሰዎች የሠሯቸውን ድንቅ ሥራዎች በማመስገን ስናደንቃቸው ግን ብዙ ትምህርት መማር እንችላለን።

ወደ ኃይሌ ስንመለስ፣ ከኃይሌ የምንማረው ዋና ቁም ነገር፣ "አሁን ሕልምህን ለመኖር ሩጫ ከጀመርክ፣ የት መድረስ እንደምትችል ማንም ሰው እንደማይገምተውና ሁሉም ነገር እንደሚቻል" ነው። ይህንን "የይቻላል መንፈስ" ስትለማመድ ግን በውስጥህ ያለው ሰበበኛ ዝም አይልም። "ኃይሌ'ማ ይችላል! ምክንያቱም ለሩጫ የሚሆን እግርና ሰውነት ነው የተሰጠው። አንተ ግን ለየት ያለ ሰውነትም ሆነ ችሎታ የለህም። ስለዚህ ሕልምህን ማሳካት አትችልም" ብሎ ያሳንፍሀል። ነገር ግን ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልግህ የኃይሌ

እግር ሳይሆን፣ የራስህን አቅም እና ችሎታ በመጠቀም ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ እንደምትችል የሚያስረዳ እምነት ነው። ለዚህ ማሳያ የምትሆንን ሌላ ድንቅ ኢትዮጵያዊት ሴት አለች።

ቤተልሔም ጥላሁን ትባላለች። አነስተኛ ደመዎዝ እየተከፈላት ተቀጥራ ትሠራበት ከነበረው መሥሪያ ቤት፣ "ለሥራው ብቁ አይደለሽም" በመባል ትሰናበታለች። ሆኖም ቤተልሔም ትልቅ ሕልም ስለነበራት፣ ለአለቃዋ "ልጆችህንና የልጅ ልጆችህን የሚቀጥር ድርጅት እከፍታለው" በማለት ከድርጅቱ ትወጣለች። ከዚያም የተጣሉ የመኪና ጎማዎችን በመሰብሰብ፣ በተለምዶ "ጋዶ" ወይም "በረባሶ" በመባል የሚታወቀውን ጫማ በልዩ ሁኔታ መሥራት ጀመረች። ከዚያ የበረባሶ ጫማ ሥራ በመነሳት አሁን ላለችበት የስኬት ደረጃ በቅታለች።

በአሁኑ ሰዓት ቤተልሔም "ሶል ሬብልስ" (Sole Rebels) የሚባል ትልቅ የጫማ ፋብሪካ በመክፈት፣ ወደ 30 የሚሆኑ አገራት ላይ ምርቶቿን በማከፋፈል፣ ጫማዎቿን ለዓለም አስተዋውቃለች። ከዚህም አልፎ በአፍሪካ ካሉ አምስት፣ እንዲሁም በዓለም ላይ ካሉ ሃያ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴቶች መካከል አንዷ ለመሆን በቅታለች። በተጨማሪም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2017 ዓ.ም. "የአፍሪካ የሴቶች መሪ" በሚል ዘርፍ ልዩ ሽልማት አግኝታለች። በአንድ ወቅት ግን፣ ቤተልሔም ልክ እንደ አብዛኛው ሰው ሁሉ በትንሽ ደመዎዝ እና ሥራ በመርካት፣ የተለመደ ኑሮዋን ትገፋ ነበር።

አንተስ አሁን በምታገኘው ትንሽ ገቢ ወይም ውጤት ተረጋግተህና ረክተህ እየኖርክ ነው? ወይስ መሆን ያለብህን ሁሉ እየሆንክ? ያለህን አቅምና ችሎታ በደንብ መጠቀም ስትጀምር፣ የዛሬ አንድ ዓመት የት መድረስ እንደምትችል ማሰብ ትችላለህ? የነዚህን ከላይ ያነሳናቸውን ድንቅ ሰዎች ታሪክ ስንሰማ፣ ማንኛውም ሰው ከየትኛውም ችግር፣ ሁኔታ፣ መከራ፣ አስተዳደግ እና ድህነት ወጥቶ የሚፈልገው ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚችል ስለሚያሳስበን፣ "ያለኝን አቅምና ችሎታ በመጠቀም፣ የት መድረስ እችላለሁ?" ብለን ራሳችንን በጥልቀት መፈተሽ ያስፈልገናል።

እኔ ሕይወቴን ለመቀየር ያደረግኩት የመጀመሪያው ነገር፣ "ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እችላለሁ!" ብዬ ራሴን ማሳመን ነበር። "ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እችላለሁ!" ብዬ ራሴን ሳሳምን ግን ሕልሜን ለማሳካት ምንም የተመቻቸ ነገር አልነበረም። ትልቁን ሕልሜን ሳስቀምጥ፣ በሕይወቴ በጣም ብዙ ፈተናዎችና ችግሮች ነበሩ። በሕይወቴ ብቻ ሳይሆን በአገሬም የተለያዩ ፈተናዎችና ችግሮች ነበሩ። የራሴ ሰበበኛ ብቻ ሳይሆን፣ የብዙ ሰዎች በተለይም የወዳጆቼና የቤተሰቦቼ ሰበበኛ "ትልቁን ሕልምህን ማሳካት አትችልም..." ይሉኝ ነበር። በወቅቱ፣ ማንም ሰው ወይም ምንም ነገር እስኪቀየር ሳልጠብቅ፣ ራሴን ለመቀየር ወሰንኩ። ራሴን ለመቀየርም ትልቅ ሕልም አስቀመጥኩ። "ሁሉም ነገር ስለሚቻልና የማይቻል ነገርም ስለሌለ፣ ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እችላለሁ" ብዬ ራሴን አሳመንኩ።

አንተም በመጀመሪያ ትልቁን ሕልምህን ማሳካትና ሕይወትህን መቀየር እንደምትፈልግ ርግጠኛ ሁን፤ ከዚያም የይቻላል እምነት በውስጥህ አሳድር። ምናልባት አሁን ላይ የሚታይህ ነገር ትልቁን ሕልምህን የምታሳካበት ሳይሆን የማታሳካበት መንገድ ብቻ ሊሆን ይችላል። በአካባቢህ ያሉ ሰዎች፣ ቤተሰቦችህ፣ ጓደኞችህና ወዳጆችህ በተለይ ደግሞ በውስጥህ ያለው ሰበበኛ፣ ትልቁን ሕልምህን ማሳካት እንደማትችል እየነገሩህ ሊሆን ይችላል።

ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት የማንንም ርዳታ እንደማያስፈልግህ መቼም አትርሳ። በአካባቢህ እንዲቀየር የምትፈልገው ሰው ወይም ነገር ባይቀየርም እንኳ፣ ሕይወትህን ለመቀየርና ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት አሁኑኑ ወስን። "ሁሉም ነገር የሚቻል ስለሆነ፣ የማይቻል ነገርም ስለሌለ፣ ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እችላለሁ" ብለህ ራስህን አሳምን። ማስተዋል ያለብህ ዋናው ቁም ነገር ትልቁን ሕልምህን ማሳካት እንደምትችል በማመን፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ስትከፍል፣ ለአንተ ድንቅ ለሆንከው የፈጣሪ ልጅ፣ ሁሉም ነገር ይቻላል! የማይቻል ነገርም የለም!

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። እባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረከኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*
*
*
*
*
*
*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*
*
*
*
*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋናና ደስታ ሞልቷል!

*
*
*

አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሃል!

ቀን ፫

*******

# ራስን መገምገም

*"ወደ ትልቁ ሕልሜ ለመሄድ፣ አሁን ራሴን የት እንዳለሁ እየፈተሽኩ ነው"*

በሕይወት ዘመናችን ሙሉ ከምንጠቀምበት በላይ፣ ፈጣሪ ድንቅ አቅም እና ችሎታ ሰጥቶናል። ይህ የፈጣሪ ስጦታ ደግሞ፣ በዚች ምድር ለምንኖር ለኛ ለሰው ልጆች ብቻ የተሰጠ ልዩ ስጦታ ነው። ለዚህ ከፈጣሪ ዘንድ ለተሰጠን ስጦታ፣ መልሰን የምንሰጠው ስጦታ፣ ውለታ መክፈያ የሚሆን ዳረጎት ባይኖረንም እንኳ፣ አንድ ነገር ግን ልናደርግ እንችላለን፤ ፈጣሪያችንን ማመስገን! ፈጣሪያችንን ከምናመሰግንባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ደግሞ፣ የተሰጠንን አቅም እና ችሎታ፣ እስከምንችለው ጥግ ድረስ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በመጠቀም፣ በመጀመሪያ ሕይወታችንን እና ቤተሰባችንን፣ በመቀጠል ደግሞ አገራችንን እና ዓለምን መቀየር ነው።

አስቀድመን የተሰጠንን ድንቅ አቅምና ችሎታ እንዴት እየተጠቀምንበት እንዳለን ራሳችንን መፈተሽ ያስፈልገናል። ልክ እንደኛው የሆኑ ሰዎች፣ ውስጣቸው ያለውን ድንቅ አቅም በመጠቀም፣ ብዙ ተዓምሮችን ሠርተዋል። ፈጣሪ የሰጠንን እፁብ ድንቅ የሆነ አቅማችንን በመጠቀም፣ ምን እየፈጠርን፣ ምን እየሠራንና ምን ዐይነት ሕይወት እየኖርን እንደሆነ አሁን ራሳችንን እንፈትሽ።

በዚህ ምዕራፍ የምንፈትሸው ምን ያክል ድንቅ አቅም እንዳለንና እንደሌለን አይደለም። ምክንያቱም ሁላችንም የሰው ልጆች በአፈጣጠራችንና በተሰጠን ተፈጥሯዊ አቅም ድንቆች ነን። በሕይወታችን ውስጥ ያሉ ፈተናዎችና ችግሮች ምን ያክል እየፈተኑን እና እያስቸገሩን እንደሆነም መፈተሽ አያስፈልገንም። ምክንያቱም ድንቅ ሰዎች፣ በምንም ዐይነት ፈተና እና መከራ ውስጥ ቢገቡ እንኳ፣ የሚያሸንፉበትን ድንቅ መንገድ በመፈለግ፣ ሁሌም የሚፈልጉትን ነገር የሚያሳኩ በመሆናቸው ነው። አንተም ድንቅ የፈጣሪ ልጅ ስለሆንክ፣ አሁን በሕይወትህ ላይ እያጋጠሙህ ያሉ ችግሮችን በማሸነፍ፣ የምትፈልገውን ሕይወት መኖር ትጀምራለህ።

በዚህ "ራስን መገምገም" የሚል ምዕራፍ ስለ ሌሎች ሰዎች ሕይወት አንፈትሽም። አንድ ጊዜ አንዲት ወጣት ሴት፣ በዚህ ምዕራፍ ካሉ ጥያቄዎች ተነስታ፣ ራሷን እንድትፈትሽና እንድትገመግም ስጠይቃት፣ የራሷን ሳይሆን፣ በመሥሪያ ቤቷ ያሉ ሰዎችን ሕይወት በመፈተሽ፣ የሥራ ባልደረቦቿ ድንቅ አቅማቸውን በምን መልኩ እየተጠቀሙ እንዳሉ ስታጫውተኝ ነበር። ነገር ግን ራሷን በመገምገም፣ እሷ ድንቅ አቅሟን በየትኛው ደረጃ እየተጠቀመችበት እንደነበር አልነገረችኝም። በዚህ ምዕራፍ የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች የቀረቡት፣ ራስን መመልከቻ መነጽር እንዲሆኑህ እንጂ፣ ሰዎችን መገምገሚያ እንዲሆኑህ አይደለም። በመሆኑም፣ ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎቹንም ሆነ ሀሳቦቹን ራስህን ብቻ ለመፈተሽ ተጠቀምባቸው።

አሁን መፈተሽ የምንፈልገው፣ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች በየትኛው ደረጃ ላይ እንዳሉ ሳይሆን፣ እኛ ራሳችን በየትኛው ደረጃ ላይ እንዳለን ነው። ድንቅ የሆነ አቅማችንን በመጠቀም፣ ምን እየሠራን፣ ምን እየፈጠርን ምን እያሻሻልን እንገኛለን? አሁን እየኖርን ያለነውን ሕይወት፣ የምናገኘውን ገቢ፣ የምናደርገውን እንቅስቃሴ፣ የምናመጣውን መፍትሄ፣ እንዲሁም በሕይወታችን የምናፈራውን ውጤት ስንፈትሽ፣ ድንቅ አቅማችንን እየተጠቀምንበት ያለው መንገድ፣ ድንቅ ነው ወይስ ተራ? ራስህን በትክክል ስትፈትሽ፣ ድንቅ አቅምህን እየተጠቀምክ ያለህበት መንገድ ድንቅ ካልሆነ፣ ያለህበትን ደረጃ በማሻሻል፣ ድንቅ ወደሆነው ደረጃ እንዴት መድረስ እንደምትችል እንመረምራለን።

ፈጣሪ የሰጠህን አውሮፕላን እና ኮምፒዩተር መሥራት የሚችል ድንቅ አቅም እና ስጦታ፣ በየትኛው ደረጃ እየተጠቀምክበት ነው? ካለህበት ደረጃ የተሻለ ሰው መሆን የምትችለውስ እንዴት ነው? ከማለዳ እስከ ጊዜህን እንዴት ነው የምትጠቀመው? ሕይወትህን ለመቀየር እየከፈልክ ያለኸው መሥዋዕትነትስ ምን ያክል ነው? አሁን ድንቅ አቅምህን በመጠቀም፣ በሕይወትህ፣ በቤተሰብህ፣ በሥራህ፣ በአገርህ፣ በአህጉርህ እና በዓለም ዙሪያ እየሠራህ ያለኸው ታሪክና እየፈጠርክ ያለኸው ተጽዕኖ በየትኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው? ድንቅ ነው? ወይስ ተራ? እፁብ ድንቅ (ክስተት) ነው? ወይስ እጅግ በጣም መጥፎ?

ከዚህ በመቀጠል ሰዎች አቅማቸውን የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ደረጃዎች ተዘርዝረዋል። እባክህ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ደረጃዎች መካከል፣ አሁን አቅምህን እየተጠቀምክ ያለህበት ደረጃ የትኛው እንደሆነ ራስህን ፈትሽ።




የስኬት የመጀመሪያው ቁልፍ፣ አሁን ያለህበትን የእድገት ደረጃ በትክክል መገንዘብ ነው። አቅምህን እየተጠቀምክ ያለህበት መንገድና እያገኘህ ያለኸው ውጤት በየትኛው ደረጃ ላይ ነው የሚገኙት? በድንቅ ወይስ ተራ? በተለያዩ አጋጣሚዎች ያስተዋልኩት፣ በጣም ብዙ ሰው አሁን የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ በእንቅስቃሴው እያገኘ ያለው ውጤት እና ተዓምር መሥራት የሚችል አቅሙን እየተጠቀመ ያለበት ደረጃ "ተራ" መሆኑን ነው። አብዛኛው ሰው ድንቅ አቅሙን ተራ በሆነ መንገድ በመጠቀም "ተራ ሰው" ይሆናል።

"ተራ ሰው ድንቅ የሆነ አቅሙን ተራ በሆነ መንገድ በመጠቀም፣ ተራ ውጤት ያገኛል!" ተራ ሰው፣ ተራ የሆነ ሀሳብ ያስባል፤ ተራ ሥራ ይሠራል፤ በተራ ችግር ያማርራል፤ ተራ ገቢ ያገኛል፤ ተራ እድገት ያድጋል፤ በአጠቃላይ ተራ ሕይወት በመኖር ተራ ሞት ይሞታል። ከዚያም ተራ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ይፈጸምለታል። ድንቅ የሆነ ሰው ግን ልክ እንደ ተራ ሰው በተለያዩ ችግሮች ቢፈተንም፣ ድንቅ ሀሳብ በማሰብ፣ ድንቅ ሥራ በመሥራት፣ ድንቅ መፍትሄ በመፈለግ፣ ድንቅ ገቢና እድገት በማግኘት፣ ድንቅ ሕይወት በመኖር፣ ድንቅ ሞት ይሞታል፤ ድንቅ የቀብር ሥነ-ሥርዓትም ይፈጸምለታል። አሁን ዋናው ቁም ነገር ተራ ወይም ድንቅ የቀብር ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምለት ሰው መሆን አይደለም። ዋናው ቁም ነገር፣ ተራ የሆነ የሕይወት ሥርዓት እየመራህ አለመሆኑንና በድንቅ የሕይወት መስመር ላይ እየተጓዝክ መሆኑን ማረጋገጡ ነው።

ድንቅ ሰው የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የሚያምርለት፣ ውድ የሆነ የሬሳ ሳጥን ውስጥ ስለተቀበረና የሚያምር የመታሰቢያ ሐውልት ስለተሠራለት ሳይሆን፣ ፈጣሪ የሰጠውን አቅሙን በሙሉ አሟጦ፣ መሥራት የነበረበትን ሁሉ፣ በሙሉ ብቃት ሠርቶ ሲያልፍ ነው። በዚች ዓለም በሕይወት እያለህ የምትሠራው ሥራ ድንቅ ከሆነ፣ ብትሞትም አትሞትም። አንተነትህ ሰዎች ውስጥ የሚቀመጠው በአካል ገዝፎ ሳይሆን፣ በህሊና ረቅቆ ነው። አብረውን ያሉ ያክል የሚሰሙን፣ የዳሰስናቸውና ሁልጊዜም የምናውቃቸው፣ እነሱም የሚያውቁን የሚመስሉን፣ ብዙ በሥጋ የተለዩን ሰዎች አሉ። በዓለማችን ላይ ድንቅ ሥራ የሠሩ ድንቅ ሰዎች፣ አሁን በሥጋ አብረውን ባይሆኑም፣ የአዕምሯቸው ውጤት የሆነው ታሪካቸው ግን ሁሌም ሕያው ሆኖ ይኖራል። ተራ ሰው ግን፣ አይደለም ሞቶ፣ ኖሮም መታወሻው እንደ መስቀል ወፍ በዓመት አንዴ ነው፤ እሱንም ከታወሰ። ተራ ሰው፣ ከተራ ምሽጉ እስካልወጣና የድንቅ ኑሮ ውስጥ እስካልገባ ድረስ፣ አይደለም በዓለማቀፍና አገር አቀፍ ደረጃ ቀርቶ፣ በቤተሰቡና መሥሪያ ቤቱ እንኳ፣ መታወሻው በአካል መገኘቱ ብቻ ነው የሚሆነው።

እኛ ሰዎች ድንቅ ሆነን የተፈጠርነው፣ ድንቅ ሆነን በመገኘት፣ ድንቅ ሕይወት ለመኖር ነው። ታዲያ ለምንድን ነው ብዙ ሰው ድንቅ ማንነቱን ትቶ፣ ተራ ሆኖ በመገኘት ተራ ሕይወት የሚኖረው? ምክንያቱም ተራ መሆን በጣም ቀላል ስለሆነ ነው። ድንቅ መሆን ቀላል ነገር አይደለም፤ በነጻም አይገኝም፤ ዋጋ ያስከፍላል፤ መሥዋዕትነትም ይጠይቃል። ተራ ሰው ልክ እንደ ድንቅ ሰው ሁሉ ድንቅ ሕይወት መኖር ይፈልጋል። ነገር ግን ለድንቅነት የሚከፈለውን ዋጋ መክፈል አይፈልግም። ተራ ሰው፣ ድንቅ መሆን ይጀምራል፤ ከዚያም ትንሽ ከበድ ሲለው፣ ተስፋ ይቆርጣል፤ እጁን ይሰጣል፤ ወደ ተራ ሕይወቱም ይመለሳል።

# የተራ ሰው ሕይወት

ተራ ሰው "ዛሬ" የሚባል ቀን የለውም። ተራ ሰው "ከነገ ጀምሮ ድንቅ እሆናለሁ!" ብሎ በመፎከር፣ ጥዋት እንዲቀሰቅሰው የማንቂያ ደውሉን ሞልቶ ይተኛል። ምሽቱ መሽቶ ሌሊቱም ነጉዶ፣ ጥዋት መንቂያው ሰዓት ደርሶ፣ የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ ግን የማስተኛ ሰበብ በመፈለግ ተመልሶ ይተኛል። "ዛሬ ጥዋት ያለው ብርድ ኀይለኛ ነው! እኔ ደግሞ ብርድ አይስማማኝም፤ ያመኛል፤ ቀኑም ጨለማ ነው፤ ኧረ አሁን መነሳት በጣም ይደብራል፤ አምስት ደቂቃ ብቻ ልተኛና ከዚያ እነሳለሁ..." ብሎ ከራሱ ሰበበኛ ጋር በመመካከር ተመልሶ ይተኛል። እስከሚረፍድ ድረስም ዕንቅልፉን ይለጥጣል። ከዚያም የሆነ ነገር ሲቀሰቅሰው፣ ብንን ብሎ ይነሳና በሩጫ የተለመደ ሕይወቱን መግፋቱን ይያያዘዋል።

ተራ ሰው ተቻኩሎ፣ ምናልባትም መያዝ ያለበትን ዕቃ እንኳ በቅጡ ሳይዝ ከቤቱ ይወጣል። ከዚያም ከቤቱ ሲወጣ፣ መንገዱ ጭንቅንቅ፣ ትራንስፖርትም የውሃ ሽታ ይሆንበታል። ከቤቱ ከወጣበት ሰዓት አንስቶ፣ አገልግሎት ለማግኘት በሚሄድበት ቦታ ሁሉ፣ ወረፋ፣ ግርግርና መጋፋት አያጣውም። ተራ ሰው፣ ተራ ሰዎች በሚነሱበት ሰዓት በመነሳትና ተራ ሰዎች ከቤት በሚወጡበት ሰዓት በመውጣት ጥዋቱን በወረፋ፣ በጭቅጭቅ፣ በግርግርና በመጋፋት ነው የሚጀምረው። ለምንድን ነው ግን ተራ ሰው ከቤቱ ሲወጣ ሁሌ በወረፋ፣ በግርግር፣ በመጋፋትና በተጨናነቀ መንገድ የሚቸገረው? ምክንያቱም ሌሎች ተራ ሰዎች ከቤታቸው በሚወጡበት ሰዓት ስለሚወጣ ነው። ድንቅ ሰው ግን አስቀድሞ ከመኝታው ተነስቶ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አድርጎ፣ ገላውን ታጥቦ፣ ቁርሱን በልቶ፣ የቀን ውሎውን አቅዶ፣ ተራ ሰዎች ከዕንቅልፋቸው ከመነሳታቸው በፊት፣ የሥራ ቦታው ደርሷል።

ተራ ሰው፣ እንደተለመደው የግፊያ ሩጫውን ጨርሶ፣ አርፍዶ የሥራ ቦታው ሲደርስ፣ "ዛሬስ ለምንድን ነው ያረፈድከው?" ተብሎ ሲጠየቅ፣ የተለያዩ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ የሚያገለግሉ "ምርጥ ሰበቦችን" በመምዘዝ ማሳበቢያው ያደርጋቸዋል። "ዛሬ እኮ መንገዱ ዝግ ነበረ! ትራንስፖርት አልነበረም! በዓል ስለሆነ ቶሎ ማለፍ አልቻልኩም ነበር! መኪናዬ መንገድ ላይ ተበላሽታብኝ ነበር! ልክ ልወጣ ስል፣ እንግዳ መጣብኝ! ሰው ታሞብኝ ነበር..." የሚሉና ሌሎች ሰበቦችን በመደርደር፣ ቀኑን በሰበብና በማማረር ይጀምረዋል።

ከቤቱ ቁርስ በልቶ ስለማይወጣ፣ ከትንሽ ጊዜ በኋላ፣ ሹልከ ብሎ ቁርስ ፍለጋ ይሄዳል። የሚፈልገውን አገልግሎት ካላገኘ ደግሞ "እዚህ አገር እኮ ተሰቃየን! ቁርስ እንኳ በሥርዓቱ የሚሠራ ጠፋ!" ብሎ ማማረሩን ይቀጥላል። ድንቅ ሰው ግን ቁርሱን በጥዋት ግጥም አድርጎ በልቶ፣ ሥራውን በብቃት እየሠራ ነው።

ተራ ሰው ከቁርስ ፍለጋ መልስ፣ ወደ ቢሮ ተመልሶ ተራ ሥራውን ይያያዘዋል። በየመሀሉ ታዲያ ፈስ ቡክ ይጠቀማል፤ ማኪያቶ ሊጠጣ ይወጣል፤ ኢንተርኔት ላይ የረባ ያልረባውን ይጎረጉራል፤ ብቻ ምንንም ሳይሠራው፣ ምሳ ሰዓት ይደርሳል። ከምሳ ሰዓት በኋላም እንደ ጥዋቱ ተመሳሳይ ተራ ሥራ መሥራቱን ይቀጥላል። ቢድጋሚ ቡና ይጠጣል፤ ኢንተርኔቱን ይጎረጉራል፤ የሚመለከተውንም ሆነ የማይመለከተውን ወሬ ያወራል፤ ከዚያም ሙሉ ቀን እንደሠራና እንደደከመ ሰው፣ ለዕረፍትና ለመዝናናት ከጓደኞቹ ጋር ይገናኛል። በተለመደው መዝናኛ ቦታ ጊዜውን አሳልፎ ቤቱ ሲገባ ደግሞ የእርሱን መምጣት በጉጉት የምትጠብቀው ቴሌቪዥን በመቁነጥነጥ ዐይኑን እስኪሰጣት ድረስ ትጠባበቃለች። ከዚያም ድከም እስኪለው ድረስ ያያትና ዕንቅልፉ ሲመጣ ደግሞ ወደ አልጋው ያመራል። ወደ አልጋው ሲሄድ ግን የዋለው ውሎ፣ ያሳለፈው ቀንና አጠቃላይ ሕይወቱ ያስጠሉታል። ከዚያም በቁጭት "ከነገ ጀምሮ ራሴን አቀይራለሁ!" ብሎ የማንቂያ ደውሉን በድጋሚ ይሞላል። ሌሊቱ ያልፍና ሌላ ጥዋት ሲመጣ ግን፣ ልክ እንደ ትናንቱ፣ "ከአምስት ደቂቃ በኋላ እነሳለሁ" ብሎ የማንቂያ ደውሉን አጥፍቶ ተመልሶ ይተኛል። ከዚያም "ዛሬ" ብሎ በሚጠራው ቀን ሁሉ፣ የትናንት ውሎውን ከ"ሀ" እስከ "ፐ" ይደግመዋል።

ተራ ሰው በዚህ ዓለም ለሰባ ዓመታት ቢኖር፣ የእውነት ሰባ ዓመታት አይኖርም፤ አንዱን ዓመት ሰባ ጊዜ እየደጋገመ የሕይወት ዘመኑን ይፈጃል እንጂ። በተራ ሰው ሕይወት፣ ዛሬ ከትናንት አይለይም። ነገም ከዛሬ ልዩነት አይኖረውም። በተራ ሰው ሕይወት፣ አምናም ሆነ ካቻምና ከዘንድሮው ዓመት ልዩነት አይኖራቸውም። የሚቀጥለው ዓመትም ከዚህኛው ዓመት ልዩነት አይኖረውም። ድንቅ ሰው ግን በየዓመቱ ብቻ ሳይሆን፣ በየቀኑ እና በየሰዓቱ ድንቅ የሆኑ ሥራዎችን በመሥራት፣ የራሱንም ሆነ የሌሎች ሰዎችን ሕይወት በመቀየር ድንቅ ልዩነት ይፈጥራል። አንተስ በዚች ዓለም መኖር የምትፈልገው አንዱን ዓመት ሰባ ጊዜ እየደጋገምክ ነው ወይስ የእውነት ሰባ እና ሰማኒያ ድንቅ ዓመታትን?

"ተራ ሰው በሰላሳ ዓመቱ ይሞታል፤ በሰማኒያ ዓመቱ ይቀበራል!" ተራ ሰው ይወለዳል፤ ያድጋል፤ ትምህርት ቤት ይገባል፤ ይመረቃል፤ ሥራ ይጀምራል፤ ያገባል፤ ይወልዳል፤ ደግሞ ይወልዳል፤ ከዚያም ተረጋግቶ ይኖራል። የሚገርመው ነገር ይህ ተራ ሰው የሚሞተው በሰላሳ ዓመቱ፣ የሚቀበረው ደግሞ በሰማኒያ ዓመቱ ነው። ተራ ሰው ሕይወትን ለማሸነፍ ሲል ለተወሰነ ጊዜ ይታገላል፤ ከዚያ ግን በመረጋጋት አልያም ተስፋ በመቁረጥ፣ ይሞታል። ተራ ሰው ሥጋዊ አካሉ እስከሚቀበርበት ዕለት ድረስ ሕይወትን ለነገ እየገፋ ይቆያል። በመንፈሳዊና አዕምሯዊ አካሎቹ ግን ከሞተ ቆይቷል። ብዙ ሰው፣ ተራ በመሆን፣ በመንፈሳዊና አዕምሯዊ አካሉ ማደግ በማቆምና በመሞት፣ ሥጋዊ አካሉ የሚቀበርበትን ዕለት እየጠበቀ ነው። ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ፣ "እኔስ እያንዳንዷን፣ በሕይወት ዘመኔ የምትመጣ ቀንና ደቂቃ የእውነት እየኖርኳት ነው ወይስ ቀድሞውኑ ሞቻለሁ? እየጠበቅኩ ያለሁትስ የምሠራቸውን ድንቅ ሥራዎች ነው ወይስ የቀብር ሥነ-ሥርዓቴን?" የሚል መሆን አለበት።

## የተራ ሰው ዋና ችግር

የተራ ሰው ችግር ከላይ የጠቀስናቸውን ዐይነት ቢሆንም፣ ሀቁን መቀበል ግን አይፈልግም። ተራ ሰው "ሕይወቴ እንደምፈልገው ድንቅ ያልሆነው፣ እኔ ተራ ስለሆንኩ እና የማደርገው ነገር ሁሉ ተራ ስለሆነ ነው" ብሎ እውነታውን ከመቀበል ይልቅ፣ "ሁኔታዎች ስላልተመቻቹልኝ ነው" ብሎ ማሳበብና ማማረር ይቀለዋል። ተራ ሰው፣ "ሕይወቴ ድንቅ እንዲሆን ከፈለግኩ፣ እኔ ድንቅ መሆን አለብኝ" ብሎ ራሱን ለመቀየር ከመሞከር ይልቅ፣ በአካባቢው ያሉ ሰዎችና ነገሮች ድንቅ ባለመሆናቸው መውቀስና ማማረር ነው የሚመርጠው።

ተራ ሰው የሕይወት ዘመኑን ሙሉ "እኔ'ኮ ምንም የለኝም፤ አባቴ ድሀ ነው፤ ሚስቴ አታዳምጠኝም፤ ጎረቤቴ አስቸጋሪ ሰው ነው፤ አለቃዬ እድገት አይሰጠኝም፤ መንግሥት አይረዳኝም፤..." እያለ ዓለምን ሙሉ ሲወቅስ ይኖራል። ተራ ሰው ሕይወቱን ለመቀየር፣ እናቱ፣ አባቱ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹ፣ ጎረቤቶቹ፣ መንግሥትና ሌሎች እስኪቀየሩ ስለሚጠብቅ፣ በዋናነት መቀየር ያለበትን ራሱን ለመቀየር ጊዜ ያጣል። ራሱ ላይ ምንም ዐይነት ለውጥ ሳያደርግ፣ ሁሉም ነገር እስኪሻሻልለት ይጠብቃል። ነገር ግን አልበርት አይንስታይን እንዳለው "ተመሳሳይ ነገር ደጋግሞ በማድረግ የተሻለ ውጤት መጠበቅ፣ ሞኝነት ነው።"

## ተራ እንዳትሆን ራስህን ፈትሽ

አንድ ጊዜ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድናችን፣ በአፍሪካ ዋንጫ ሲጫወት እያየን ነበር። አንድ የምሰጠው አጭር ስልጠና ላይ የተሳተፈ ልጅ ወደ እኔ መጥቶ፣ "ዳዊት" ብሎ ጠራኝ። "አቤት" ብዬ ስዞር፣ "ከነዚህ ሁሉ የዋልያ ተጫዋቾች እኮ 'አንትና' ብቻ ነው ድንቅ እንጂ ሌሎቹ ተራ ናቸው" አለኝ። ቀጠል አድርጎም "አይደለም እንዴ ዱቬ?! ተራ ናቸው አይደል?" ብሎ "ተራ ናቸው" እንድለው በመጠበቅ ጠየቀኝ። እኔም "እነሱ ተራ አይደሉም፤ ባይሆን አንተ ራስህ ተራ እንዳትሆን ተጠንቀቅ" አልኩት። በርግጥ ዋልያዎቹ፣ ጨዋታቸውን ለማሻሻል ብዙ ሥራና ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን ባላቸው አቅም አገራችንን ኢትዮጵያን በአፍሪካና በዓለም አደባባዮች ለማስተዋወቅ እየሞከሩ ነው። የሚገርመው ግን፣ ልጁ ስለ ዋልያዎቹና ስለ ሌሎች ታዋቂ ሰዎች ከማውራት ባለፈ፣ ምንም ቁም ነገር ያለው ሥራ ሲሠራ አይቼው አላውቅም።

ተራ ሰው የራሱን ሕይወት ትቶ፣ ስለ ሌሎች ታዋቂ ሰዎች ማውራት ነው የሚቀለው። የራሱን ሕይወት ለመቀየር ቅንጣት ታክል ሳይሞክር፣ ዋልያዎቹ፣ ዘፋኞቹ፣ ተዋንያኑ፣ ባለ ሥልጣኖቹና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች እንዴት አድርገው ድንቅ መሆን እንደሚችሉ ማውራት እና ማማረር ነው የሚቀለው። ተራ ሰው ሕልሙን የሚያሳካበት መንገድ ምንም አይታየውም። ነገር ግን ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ምን ማድረግ እንደነበረበት ገለጻ ሲሰጥ ትሰማዋለህ። ቤተሰቡንና ድርጅቱን በተገቢው ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል ተግባራዊ ዕቅድ እንኳ ሳይኖረው፣ ፕሬዚደንት ዶናልድ ትራምፕ አሜሪካን ለመምራት መጠቀም የነበረበትን ዕቅድ፣ ለከተማው ሁሉ ሲያስተምር ይውላል። "የራሷ ሲያርባት..." የሚሉት ዐይነት ማለት ነው።

እኔ በጣም የሚያስቀኝ፣ አንድ ምንም ቁም ነገር የማይሠራ እና ተኝቶ የሚያረፍድ ሰው የሚመክረው ምክር ነው። ይህ ተራ ሰው አርፍዶ ይነሳል። ከዚያም ፌስ ቡኩ ላይ ጣድ ይልና "ዐቢይ አህመድ ማድረግ ያለበት አስር አስቸኳይ ነገሮች" ብሎ ይለጥፋል። እንዴ! እስኪ በመጀመሪያ እነዚህን አስር ነገሮች ሥራ ለመፈለግና ለማግኘት ተጠቀምባቸው። ከዚያም በነዚህ አስር ነጥቦች ሕይወትህን ቀይር። ባይሆን፣ ያኔ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ምን ማድረግ እንዳለበት ትመክረዋለህ። ለሰዎች እየመከርክ ያለኸውን ምክር ለራስህ የማትጠቀምበት ከሆነ፣ ምክርህ ምንም ትርጉም የለውም። እኔ በዚህ መጽሐፍ የጻፍኳቸውን ሀሳቦች፣ ሕይወቴን ለመቀየር የማልጠቀምባቸው ከሆነ፣ መጽሐፉን ባልጽፈው ይሻለኝ ነበር።

ሌላው በጣም የሚገርመኝ ነገር፣ በትዳራቸው እና በቤተሰባቸው ብዙ ችግር ያለባቸው ተራ ባልና ሚስት፣ ቴሌቪዥን መስኮት ላይ አፍጥጠው፣ "ዛራና ቻንድራ" ትዳራቸውን ለማስተካከል ምን ማድረግ እንደሚገባቸው፣ ሲከራከሩ ማምሸታቸው ነው። የራሳቸውን ትዳር ለማስተካከል የሚሆን ጊዜ የሌላቸው ሰዎች፣ ለዛራና ቻንድራ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ሊያውም በነጻ።

ትላልቅ መሪዎች እና የድርጅት ሥራ አስኪያጆችም፣ የራሳቸውን ሠራተኞች እና ድርጅት በአግባቡ ሳይመሩ፣ በአገራቸውና በዓለም ዙሪያ ያሉ መሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመከራከር፣ በየቦታው የሚያቃጥሉት ጊዜ ጥቂት የሚባል አይደለም። ሌሎች ሰዎችንና ባለ ሥልጣኖችን መምከር የምትፈልገውን ምክር፣ መጀመሪያ ራስህን በመምከር፣ ራስህንና ድርጅትህን ቀይር። ከዚያም የምከርከውንና የተጠቀምክበትን፣ በተግባርም የፈተሸከውን ድንቅ ምክርህን፣ ሌሎች ሰዎችን ለመምከር ተጠቀምበት።

በአጠቃላይ፣ ተራ ሰው የራሱ ሕይወት በጣም ተራና አሰልቺ ስለሚሆንበት፣ ከአሰልቺ ኑሮው የሚወጣበትና ዕረፍት የሚያገኝበት አንዱ መንገድ፣ ስለ ሌሎች ድንቅ ሰዎች ሕይወት ማውራትና መከራከር ስለሚመስለው፣ በማይጠቅም "ጉንጭ አልፋ" ንግግር ጊዜውን ያቃጥላል። ቀኑ በመሸነፍ የተሞላበት ተራ ሰው፣ ከተራ ሕይወቱ ዕረፍት የሚያገኘው፣ በቴሌቪዥን ታዋቂና ድንቅ የሆኑ ሰዎች ሲያሸንፉ እና ተዓምር ሲሠሩ በመመልከት እና በማጨብጨብ ነው። ትልቅ ደረጃ ላይ ያሉ ኳስ ተጫዋቾች፣ ዘፋኞች፣ ተዋንያን፣ ባለ ሥልጣናት እና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች ድንቅ ሥራ ሲሠሩና ሕልማቸውን ሲያሳኩ በቴሌቪዥን ሲመለከት፣ ደስ ይለዋል። እሱ ራሱ ተዓምር የሠራ እስኪመስለው ድረስ፣ በሶፋው ላይ ቁጭ ብሎ፣ ተዓምር የሚሠሩትን ሰዎች እየተመለከተና እያጨበጨበ ጊዜውን ይፈጃል።

አንተም የራስህን ታሪክ መሥራትህን ትተህ፣ የሌሎች ሰዎችን ታሪክ በቴሌቪዥን ስትከታተል ብቻ የምታመሽ ከሆነ፣ ቤተሰቡን ለማዝናናት ወደ "ኤድና ሞል" ሄዶ፣ በመዝናኛ ቦታዎቹ ሳይሆን፣ በመኪና ማቆሚያ ስፍራ ውስጥ እንደተቀመጠ ሰው ነው የምትሆነው። ለመዝናናት ወደ ኤድና ሞል የሄደ ሰው፣ የኤድና ሞልን ድንቅ ሲኒማዎችና መዝናኛ ቦታዎች ትቶ፣ ከመሬት ስር ባለው የመኪና ማቆሚያ ስፍራ፣ ከነቤተሰቡ መኪና ውስጥ ታፍኖ፣ "በኤድና ሞል ውስጥ እየተዝናናን ነው" ማለት ይችላል እንዴ? በጭራሽ! ሕይወትም እንዲህ ናት። ፈጣሪ ድንቅ አቅምና ችሎታ የሰጠን የራሳችንን ድንቅ ታሪክ እንድንሠራና ሕልማችንን እንድናሳካ እንጂ፣ የሌሎች ሰዎችን ስኬት እና ታሪክ በቴሌቪዥን ቁጭ ብለን እንድንከመኩም ብቻ አይደለም። ድንቅ ከሆኑ ሰዎች ታሪክ መማር ያለብህን ትምህርት በመማር፣ አሁኑኑ የራስህን ድንቅ የሆነ ታሪክ መሥራት ጀምር።

ተራ መሆን የሚፈልግ ማንም ሰው የለም። ሁሉም ሰው ድንቅ መሆን ነው የሚፈልገው። የተራን ሰው ሕይወት ከላይ እንዳሳየሁህ አድርጌ የገለጽኩት፣ ሳታስበው ተራ ሕይወት መኖር ጀምረህ ከሆነ፣ ውስጥህን በደንብ እንድትፈትሽ ብዬ ነው። ታዲያ አንተ የቱ ጋር ነው ያለኸው? ራስህን የት አገኘኸው? ድንቅ ነህ ወይስ ተራ? እየኖርከ ያለኸው ሕይወት የድንቅ ሰው ሕይወት ነው ወይስ የተራ? አንዳንዴ በሕይወትህ ሙሉ በሙሉ ተራ ባትሆን እንኳ፣ በአንዳንድ የሕይወት ዘርፎች ላይ ግን ተራ ሆነህ ልትገኝ ትችላለህ። ስለዚህ አሁን ትንሽ ጊዜ ወስደህ፣ በሕይወትህ ውስጥ ያሉ ዘርፎችን ሁሉ በጥንቃቄ ፈትሻቸው። በተወሰነ መልኩ፣ ራስህን ወይም በሕይወትህ እያገኘህ ያለኸውን ውጤት ተራ ሆኖ ካገኘኸው፣ አሁኑኑ ርምጃ ውሰድ፣ ድንቅ ለመሆን ለራስህ ቃል ግባ፤ የገባኸውንም ቃል በትጋት ጠብቅ።

ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ሆቴሎች ስልጠናዎችን እንሰጣለን። ስልጠናውም፣ ሆቴሎቹ ጥንት የነበራቸውን ድንቅ ስም፣ ከመረሳት ወደ መታወስ እንዲመጣ፣ መሥራት ያሉባቸው ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ነው። ድሮ ላይ ድንቅ የነበሩ፣ ድንቅ ስምም የነበራቸው፣ ነገር ግን አገልግሎታቸውን ለረጅም ጊዜ ተራ ስላደረጉ፣ ብዙ የተረሱ ሆቴሎች አሉ። አንድ እንግዳ "የት አካባቢ ነው ቆንጆ ሆቴል ማግኘት የምችለው?" ብሎ ቢጠይቀን፣ እነዚህ ሆቴሎች ትዝ አይሉንም። እነዚህ ሆቴሎች፣ ምናልባትም ትዝ የሚሉን፣ ለቦታ መጠቆሚያና መቀጣጠሪያ ስንፈልጋቸው ብቻ ነው። ስማቸው የሚጠራውም "እንትን ሆቴል ፊት ለፊት ወይም ጀርባ እንገናኝ" ሲባል ብቻ ነው። እነዚህ ሆቴሎች ያላቸው ስፋት፣ የያዙት ቦታ፣ የሚገኙበት አካባቢና የተሠሩበት መንገድ ድንቅ ነው። ነገር ግን የሚሰጡት አገልግሎት፣ የሚያስተናግዱበት መንገድ እንዲሁም ለደንበኞቻቸው የሚሰጡት እንክብካቤ ተራ ስለሆነ፣ ተረስተው ቀርተዋል።

አሁን ስለ ሆቴሎቹ ማውራት ፈልጌ ሳይሆን፣ እኛም ተረስተን እንዳንቀር መጠንቀቅ እንዳለብን ላሳስብህ ነው። ምክንያቱም ብዙ በአካባቢያችን ያሉ ተራ ሰዎች ተረስተዋል። አንዳንድ በትላልቅ መሥሪያ ቤቶች የሚሠሩ ሰዎች ተራ ስለሆኑ፣ እያሉ ይረሳሉ። እነዚህ ሰዎች ከሥራ ቢለቁ፣ ከሥራ መልቀቃቸው የሚታወቀው፣ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው። "እዚህ ጋር የነበረው ልጅ የት ሄደ?" ተብሎ ሲጠየቅ ነው "ውይይ... እሱ'ማ ሥራ ከለቀቀ አንድ ወር አለፈው እኮ!..." የሚባልለት። ድንቅ የሆነ ሰው ግን፣ አይደለም ድርጅቱን ለቆ፣ ከመልቀቁ በፊት እንኳ፣ "እለቃለሁ" ብሎ ቢያወራ፣ ድርጅቱ ይታመሳል።

ተራ ሰቅም፣ እንደ ተራው ሰው ነው። ተራ ሱቅ እንደተዘጋ ሰፈሩ የሚያውቀው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ነው። ድንቅ ሱቅ ግን "ሊዘጋ ነው" ቢባል እንኳ፣ ሁሉም ሰው ይደነግጣል። ተራ ሰው በሥራው ምንም ልዩነት ስለማያመጣ፣ ቢኖርም ባይኖርም፣ አካባቢው ምንም አይመስለውም። ድንቅ ሰው ግን ሁሌም ለየት ያለ ሥራ በመሥራት፣ ሕይወቱንና ቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን፣ አገሩንና ዓለምን በመጥቀም፣ በሁሉም ሰው ዘንድ ተፈላጊ ይሆናል፤ መቼም አይረሳም።

አሁን በየትኛው ደረጃ ላይ እንዳለህ ራስህን ለመፈተሽ መጠየቅ ከምትችላቸው ጥያቄዎች አንዱ፣ "ከዛሬ ጀምሮ አንድ ወር ለሚሆን ጊዜ፣ ቤት ወይም ሥራ ቦታ ባልገባ፣ በቤተሰቤ ወይም በሥራዬ ላይ ምን ዐይነት ልዩነት ይፈጠራል?" የሚለውን ነው። አንተ ኖርከም አልኖርከም፣ መኖርህ ልዩነት የማይፈጥር ከሆነ፣ ወይም ማንኛውም ሰው መጥቶ በቀላሉ የሚተካህ ከሆነ፣ ምናልባት ተራ ሆነህ ሊሆን ይችላል። ድንቅ ስትሆን ግን፣ ሁሌም የምታመጣው ሀሳብ፣ የምትሰጠው መፍትሄ እና የምትሠራው ሥራ ድንቅ ስለሚሆን፣ ማንኛውም ሰው፣ ለአንድ ቀንም ቢሆን ሊያጣህ አይፈልግም። ማንም መጥቶም አንተ የምትሠራውን ሥራ በቀላሉ አይተካውም። ስለዚህ ለራስህ፣ ለቤተሰብህ፣ ለአገርህ እና ለምትኖርባት ምድር ልዩነት የምትፈጥር ድንቅ ሰው ለመሆን፣ መክፈል ያለብህን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ አሁኑኑ ድንቅነትህን አጣጥመው።

እኔ ዳዊት ድሪምስ፣ ሕልሜን ማሳካትና ሕይወቴን መቀየር የጀመርኩት፣ ራሴን በትክክል ስፈትሽ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ራሴን በትክክል ስፈትሽ፣ ተራ እንደነበርኩ ነው የተረዳሁት። ሕይወቴን ለመቀየር "ዳዊት ድሪምስ፣ አንተ ድንቅ ነህ፤ ትልቅ ሕልምም አለህ፤ ነገር ግን ድንቅ አቅምህንና ውድ ጊዜህን እየተጠቀምክ ያለህበት መንገድ ተራ ነው" ብዬ ራሴን መገሰጽ ነበረብኝ። በመሆኑም ትልቁን ሕልሜን ለማሳካትና ሕይወቴን ለመቀየር፣ ራሴን ከተራ ሰውነት ወደ ድንቅ ሰውነት ለመቀየር መወሰንና የሚያስከፍለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁና ቁርጠኛ መሆን ነበረብኝ። በወቅቱ ራሴን ከተራነት ወደ ድንቅነት ለመቀየር የወሰንኩት ውሳኔና የከፈልኩት መሥዋዕትነት፣ ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ቀይሮታል።

ራስን መፈተሽ አንዴ ተሰርቶ የሚጠናቀቅ ቅጽበታዊ ጉዳይ ስላልሆነ፣ አሁንም ቢሆን ወደ ተራነት እንዳልመለስ ራሴን እፈትሻለሁ። ሙሉ በሙሉ ወደ ተራነት መመለስ፣ ለኔ አማራጭ አይደለም። ነገር ግን አንዳንዴ በተወሰኑ የሕይወት ዘርፎቼ ላይ ወደ ተራነት እንዳልመለስ ራሴን በጥንቃቄ እፈትሻለሁ። በማንኛውም የሕይወት ዘርፍ ላይ ራሴን ተራ ሆኜ ካገኘሁት፣ ወዲያውኑ ራሴን በመገሰጽና በመገምገም ራሴን ወደ ድንቅነት እቀይራለሁ። በሕይወት ዘርፎቼ ላይ በማንኛውም መንገድ ተራ ስሆን፣ ራሴንም ሆነ ሌሎችን እንደማልጠቅም ስለማውቅ፣ ድንቅ ከመሆን ለአንድ አፍታ እንኳ ዝቅ ማለት አልፈልግም። ራሴንና ቤተሰቤን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንና አፍሪካን ድንቅ ለማድረግ መሆን ያለብኝን በመሆንና መሥራት ያለብኝን በመሥራት፣ በዓለም ላይ ታሪክ ለመሥራት ወስኛለሁ። ከሞትኩ በኋላ የሚረሳ ታሪክ ሳይሆን፣ ልጆቼ መጽሐፍ የሚጽፉለት፣ የልጆቼ ልጆች ደግሞ ፊልም የሚሠሩለት ድንቅ ታሪክ ለማስቀመጥ፣ አሁኑኑ መክፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ያለ ምንም ድርድር እየከፈልኩ ነው።

ነገ "ራስን መቀየር" በሚለው ምዕራፍ፣ እንዴት አድርገህ ራስህን መቀየር እንደምትችል እንመለከታለን። ዛሬ፣ በዚህ ምዕራፍ በአንዱ ወይም በሁሉም የሕይወት ዘርፎችህ ዙሪያ ወደ ተራነት ገብተህ እንዳይሆን ራስህን በጥንቃቄ ፈትሽ። ወደ ተራ የሕይወት ልምምድ ውስጥ ከገባህባቸው የሕይወት ዘርፎች በመውጣት ድንቅ ኑሮ ለመኖር፣ ድንቅ ሕይወት የሚሰጡህን ድንቅ ውሳኔዎች አሁኑኑ ወስን። ተራ መሆን ለጊዜው ቀላል ቢሆንም፣ በመጨረሻ ግን ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። ድንቅ መሆን ደግሞ ለጊዜው ከባድ ቢሆንም፣ በመጨረሻ ግን ብዙ በረከቶችን ያስገኛል። ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር፣ ተራ መሆን አማራጭ አይደለም። እኛ ድንቅ የሰው ልጆች ያለን አማራጭ ድንቅ መሆን ብቻ ነው። አዎ! ያለን አንድ አማራጭ መክፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ራሳችንን እና ቤተሰባችንን ብቻ ሳይሆን አገራችንን እና አህጉራችንን በመቀየር፣ በዓለማችን ላይ ታሪክ መሥራት ነው። ለመጪው ትውልድ የሚረሳ ታሪክ ሳይሆን፣ መጽሐፍ የሚጻፍበት እንዲሁም ፊልም የሚሠራበት ድንቅ ታሪክ እናውርስ።

# እኔ ድንቅ ነኝ!

ዛሬ እንዴት ነህ? ምን ብለህ ነው ጥዋት "እንደምን አደርክ?" ወይም ምሽት ላይ "እንደምን አመሸህ?" ብለው ሰዎች ሲጠይቁህ የምትመልስላቸው? ብዙ ሰው አንድ ከባድ እና በፈተና የተሞላ ቀን ካሳለፈ በኋላ፣ "እንዴት ነህ?" ተብሎ ሲጠየቅ የሚመልሰው መልስ ያለውን ተጽዕኖ በትክክል አይረዳም። የሰው ልጅ ከአንደበቱ የሚያወጣቸው ቃላት ያላቸውን ኀይል ስለማይረዳም፣ ጥዋት ተነስቶ ቀኑ ደስ የሚል ካልመሰለው ወይም ከቤቱ ሲወጣ "የሚደብር" ነገር ካጋጠመው፣ "ዛሬ ደብሮኛል" ብሎ ቀኑን በአሉታዊ ቃላት አሀዱ ብሎ ይጀምራል። ቢሮ ሲገባ ደግሞ፣ ሌላ እንደሱ የደበረው ሰው ካገኘ፣ "በርግጥም ዛሬ ቀኑ ይደብራል" ብሎ ይደመድማል። ቀንህን "የዛሬው ቀን ይደብራል" ወይም "በጣም ደብሮኛል" ብለህ ከጀመርክ፣ እውነትም ቀንህ የሚደብር ቀን እንዲሆን በር ትከፍታለህ።

"ዛሬ ደብሮኛል" ብለህ ቃል ስታወጣ፣ እነዚህን የሚደብሩ ቃላት አስቀድመህ የምታዳምጣቸው አንተው ራስህ ነህ። የምታወራቸውና የምታዳምጣቸው ቃላት የሚደብሩ ከሆኑ፣ ሀሳቦችህም የሚደብሩ ነው የሚሆኑት። የሚደብር ሀሳብ፣ በልብህ የሚደብር ስሜት ይፈጥራል። በልብህ ያለው የሚደብር ስሜት ደግሞ፣ የሙሉ ቀን እንቅስቃሴዎችህንና የምታገኛቸውን ውጤቶች ስለሚቆጣጠር፣ ሙሉ ቀን የሚደብሩ እንቅስቃሴዎችንና ድርጊቶችን በመውሰድ፣ የባሱ የሚደብሩ ውጤቶችን ያሳጭድህል።

ጥዋት ተነስተህ፣ "ፈጣሪዬ ሆይ! ስለ ሁሉም ነገር ተመስገን! ድንቅ አድርገህ ስለፈጠርከኝም ተመስገን! እኔ ድንቅ ነኝ! ቀኔ ድንቅ ነው!" ብለህ ቀንህን በድንቅ መንፈስ ስትጀምር፣ ሁሉም ነገር ድንቅ ይሆናል፤ ድንቅ ያልሆነ ነገር ቢያጋጥምህ እንኳ ድንቅ ማድረግ ትችላለህ። በርግጥ ሁሌም ጥዋት ከዕንቅልፍህ ስትነሳ፣ ድንቅ ስሜት ላይሰማህ ይችላል። ምናልባትም የማትፈልጋቸው ነገሮች ገና ከአልጋህ ላይ ሳትወርድ፣ ሊያጋጥሙህ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች እያሉ፣ የምታስበውን ሀሳብና ስሜት መቆጣጠርና መቀየር ትችላለህ። ችግር በአካባቢህ እያለ፣ "እኔ ድንቅ ነኝ!" ብለህ በተደጋጋሚ ስትናገር፣ እነዚህን ድንቅ ቃላት በመጀመሪያ የምታዳምጣቸው አንተ ነህ። የምታወራቸውና የምታዳምጣቸው ቃላት ድንቅ ከሆኑ፣ ሀሳብህ ሁሉ ድንቅ ይሆናል። በተደጋጋሚ የምታስባቸው ድንቅ ሀሳቦች ደግሞ በልብህ ድንቅ ስሜት ይፈጥራሉ። ድንቅ ስሜቶችህ ደግሞ የሙሉ ቀን እንቅስቃሴህን ድንቅ በማድረግ፣ ድንቅ ውጤቶች ይሰጡሀል።

ሰዎች "ዳዊት ድሪምስ እንዴት ነህ?" ብለው ሲጠይቁኝ፣ ሁሌም ቢሆን "እኔ ድንቅ ነኝ!" ብዬ ነው የምመልሰው። አንዳንዶቹ በመልሴ ግራ ሲጋቡ አያለሁ። ነገር ግን እኔ ምን እያደረግኩ እንደሆነ ጠንቅቄ አውቃለሁ። "እኔ ድንቅ ነኝ!" ብዬ ስመልስ፣ በሕይወቴ አንዳንድ ከባባድ ፈተናዎች የሉም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን እነዚህ ፈተናዎች፣ ሀሳቤንም ሆነ ስሜቴን እንዲቆጣጠሩ አልፈቅድላቸውም፤ ቀኔን "እኔ ድንቅ ነኝ! ዛሬ ድንቅ ነው!..." ብዬ በመጀመር፣ ድንቅ ሕይወት የምኖርበትን መንገድ ሁሌም እፈልጋለሁ። አሁን እኔ ብቻ ሳልሆን፣ በአካባቢዬ ያሉ ብዙ ሰዎችና በተለያዩ ስልጠናዎች ላይ ያገኘኋቸው ሰዎች፣ ይህንን ድንቅ ምስጢር በመጠቀም፣ ቀናቸውን ከሚደብር ቀንነት ወደ ድንቅነት እየቀየሩ ነው።

አንተም ይህንን ምስጢር በመጠቀም፣ ቀንህን እና ሕይወትህን ድንቅ ማድረግ ትችላለህ። አሁን በአካባቢህ ያለው የውጪው ዓለም በሚደብር ሁኔታ ላይ ቢሆንም፣ የውስጥህን ድንቅነት እንዲረብሽ አትፍቀድለት። ሰዎች "እንዴት ነህ?" ብለው ሲጠይቁህ፣ የምትመልሰው መልስ ምን ያክል በሕይወትህ ላይ ተጽዕኖ እንዳለው አትዘንጋ። ከዛሬ ጀምሮ፣ ሰዎች "እንዴት ነህ?" ብለው ሲጠይቁህ፣ በመጀመሪያ በእምነትህ መሠረት፣ "እግዚአብሔር ይመስገን!" ወይም "አልሃምዱሊላህ!" በማለት ፈጣሪህን አመስግን። ከዚያ ቀጥሎ ግን "ዛሬ ይደብራል፤ ቀኑም ይቀፋል..." የሚሉ ቃላትን በምንም ተዓምር ከአንደበትህ አታውጣ። ፈጣሪህን ካመሰገንክ በኋላ፣ ልትላቸው የሚገቡህ ቃላት "እኔ፣ ሕይወቴ፣ ቤተሰቤ፣ ቀኔ፣ ሥራዬ፣ አገሬና ሁሉም ነገር ድንቅ ነው!" የሚል ብቻ መሆን አለበት። አሁን ድንቅ የሆኑ ቃላትን ከዘራህ፣ ኋላ ድንቅ የሆኑ ውጤቶችን ታጭዳለህ፤ ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው።

"እንዴት ነህ?" ተብለህ ስትጠየቅ፣ ከተለመዱና ተራ ከሆኑ አንዳንድ መልሶች መቆጠብም አለብህ። አስቀድመን፣ እጅግ በጣም መጥፎ ከሚባል ደረጃ አንስቶ፣ እፁብ ድንቅ የሚለው ደረጃ ድረስ በጣም ብዙ ደረጃዎች እንዳሉ ተመልክተን ነበር። ለምሳሌ "እንዴት ነህ?" ተብለህ ስትጠየቅ፣ "ዛሬ ደብሮኛል" ብለህ ከመለስክ፣ በየትኛው ደረጃ እንዳለህ መገመቱ አይከብድም። "ድንቅ ነኝ" የሚል ወይም ተመሳሳይ ድንቅ የሆኑ መልሶችን ስትመልስም ድንቅ በሆነ ደረጃ ላይ እንዳለህ ግልጽ ነው።

አንዳንድ በተራ ደረጃ ያሉ፣ ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው አጓጉል መልሶችም አሉ። አብዛኛው ሰው "እንዴት ነህ?" ተብሎ ሲጠየቅ፣ "አለሁልህ" ወይም "አለሁልሽ" አልያም "ምንም አልልም" ወይም "አለን፣ አለን" ብሎ ይመልሳል። እነዚህ መልሶች በተናጋሪው ሰው ውስጥ ሁሌም ተራ የሆነ መንፈስ ነው የሚያንጸባርቁት። አብዛኛው ሰው "አለሁልህ" ወይም "ምንም አልልም" ብሎ ሲመልስ፣ ከመልሱ ጀርባ "መኖሩን'ማ አለሁ፤ ነገር ግን ምንም ለውጥ ማምጣት አልቻልኩም" ወይም "በተራ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለሁት" የሚል ተራ መንፈስ ይደመጣል። "ዛሬ ተራ ነኝ" ብለህ የምትመልስ ከሆነ ደግሞ፣ ሀሳብህና ስሜትህ ሁሉ ተራ ስለሚሆን፣ እንቅስቃሴህና የምታገኘው ውጤትም ተራ ይሆናል።

ይህ ተራ የሆነ ንግግር፣ በግል ብቻ ሳይሆን፣ በአገር ደረጃም ሲነሳን ይታያል። ለምሳሌ ተደጋግመው ከምንሰማቸው፣ ምናልባትም ለራሳችንም ደግመን ደጋግመን ከምንላቸው መፈክሮች አንዱ "ትልቅ ነበርን፤ ትልቅም እንሆናለን!" የሚል ነው። እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ ከፈተሽካቸው በውስጣቸው ተራ የሆነ መንፈስ ያዘሉ ናቸው። ይህ መፈክር "አዎ! ድሮ ትልቅ ነበርን፤ ወደ ፊትም ትልቅ እንሆናለን፤ አሁን ግን ተራ ነን!" የሚል ውስጠ ወይራ አለው። በሕይወት በጣም ወሳኝ የሆነው ጊዜ ትናንት ወይም ነገ ሳይሆን፣ ዛሬና አሁን ብቻ ነው። ትናንት ምንም ታላቅ ወይም ተራ ብንሆን፣ ነገም ምንም ያክል ታላቅ ወይም ድንቅ መሆን ብንፈልግ፣ ዛሬ ላይ ድንቅ ካልሆንን ምንም ትርጉም የለውም። ዛሬንና አሁንን ድንቅ ከሆንን ግን፣ የትናንትናውን ታሪክ በማሻሻል፣ የተሻለ ነገ መፍጠር እንችላለን። የአገራችን መፈክር "ትልቅ ነበርን፤ ድንቅ ነን፤ እፁብ ድንቅ እንሆናለን!" የሚል መሆን አለበት።

እኔ "ድንቅ" የሚለውን ቃል ስለምጠቀም፣ አንተም የግድ ድንቅ የሚለውን ቃል መጠቀም የለብህም። ከድንቅ ጋር አቻ የሆኑ ቃላትን ግን መጠቀም ትችላለህ። መጨበጥ ያለብህ ዋናው ነገር፣ በአዕምሮህ የምታስባቸውና በአንደበትህ የምታወጣቸው ቃላት፣ በሕይወትህ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እንዳላቸው ነው። ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ፣ ሕይወትህ በየትኛውም ደረጃ ላይ ቢሆን፣ ቀንህ ምንም ያክል ከባድ ወይም ቀላል ቢመስልም፣ ቀንህን በነዚህ ድንቅ ቃላት በመጀመር፣ ራስህን፣ ቤተሰብህን እና መሥሪያ ቤትህን ብቻ ሳይሆን አገርህን፣ አህጉርህን እና ዓለምህን ወደ ድንቅነት ቀይር።

**እኔ ድንቅ ነኝ!**

**አንቺ ድንቅ ነሽ! አንተ ድንቅ ነህ! እርስዎ ድንቅ ነዎት!**

**እኛ ድንቅ ነን!**

**ዛሬ ድንቅ ነው! ሕይወቴ ድንቅ ነው!**

**አገሬ ድንቅ ናት! አህጉሬ ድንቅ ናት! ዓለም ድንቅ ናት!**

**ትልቁንና ድንቁን ሕልሜን ለማሳካት፣ መከፈል ያለበትን ድንቅ መሥዋዕትነት እየከፈልኩ ነው!**

በዚህ መጽሐፍ በ፩ኛ ቀን፣ በገጽ 7 ላይ ያሉትን የሕይወትና ስኬት መፈክሮች ደጋግመህ በመጻፍና ጮክ ብለህ በማንበብ፣ በልብህ ውቀራቸው። እነዚህ መፈክሮች መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል ራስህን፣ ቤተሰብህን፣ መሥሪያ ቤትህን፣ አገርህን፣ አህጉርህን እና ዓለምን እንድትቀይር ይረዱሀል።

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። እባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረከኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋናና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሀል!

ቀን ፬

፯፤

*******

# ራስን መቀየር

*"ተራ እያለሁ ዓለም እስኪቀየር እጠብቅ ነበር፤ ድንቅ ስሆን ግን ራሴን እየቀየርኩ ነው"*

ተራ ሰው፣ ሕይወቱን ለመቀየር እናቱ፣ አባቱ፣ ሚስቱ፣ ቤተሰቡ፣ ጎረቤቶቹ፣ መሥሪያ ቤቱ፣ መንግሥት እና ሌሎች አካላት እስኪቀየሩ ይጠብቃል። እነዚህ አካላት ከተቀየሩ ይቀየራል፤ ካልተቀየሩ ደግሞ ተስፋ ይቆርጣል። ድንቅ ሰው ግን፣ ራሱን በመቀየር ሕይወቱን ይቀይራል፤ ማንም ሰው ወይም ምንም ነገር እስኪቀየር ሳይጠብቅ፣ ሕልሙን ለማሳካት መክፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ከማለዳ አንስቶ መክፈል ይጀምራል። ሙሉ ቀን፣ መሆን የሚገባውን በመሆን፣ ማድረግ ያለበትን በማድረግ፣ መቀየር ያለበትን በመቀየር፣ መሥራት ያለበትንም በመሥራት፣ የማንንም ሰው ርዳታ ሳይጠብቅ፣ ራሱን በመቀየር ሕይወቱን ይቀይራል።

"ሕይወትህ እንዲቀየር ከፈለግክ፣ መቀየር ያለበት ከአንተ ውጪ ያለ ሌላ አካል ሳይሆን፣ አንተ ራስህ ነህ" ሲባል ሰምተህ ሊሆን ይችላል። የሰማኸውን ነገር በደንብ ካልተረዳኸውና ወደ ተግባር ካልቀየርከው ግን "ሰሚ" እንጂ ውጤታማ አትሆንም። ብዙ ሰው "አሁን ምስጢሩ ገብቶኛል፤ ሕይወቴን ለመቀየር እኔ ራሴ መቀየር አለብኝ" ብሎ ያወራል። ነገር ግን፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ነገሮች እንዳሰበው ሳይሄዱ ሲቀሩ፣ ውሳኔውን ይሽረዋል። የወሰነውን ውሳኔ፣ ሆን ብሎ ባይሆን እንኳ፣ ሳያስበው ያፈርሰዋል። ከዚያም ሌሎች ሰዎች ወይም ነገሮች እስኪቀየሩ ወደ መጠበቅ ልማዱ ይመለሳል።

ብዙ ሰው በወኔ ተነሳስቶ፣ ዳግም፣ "አዎ! ሕልሜን ለማሳካት ራሴን መቀየር አለብኝ!" ብሎ ያስባል። ነገር ግን፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ "አበድርሃለሁ" ያለው ሰው ሳያበድረው ሲቀር፣ ቤተሰቡ ሳይረዳው ሲቀር፣ መንግሥት ፍቃድ አልሰጥ ሲለው፣ አለቃው ሳይፈቅድለት፣ ሠራተኞቹ ሳያግዙት ወይም ያሰበው ነገር ሳይሳካለት ሲቀር ተስፋ ይቆርጣል። በቃ ተስፋ ይቆርጣል! ሌሎች ሰዎች እስኪቀየሩ ወደ መጠበቅ ልማዱም በድጋሚ ይመለሳል።

ድንቅ ሕይወት ለመኖር እና ሕልምህን ለማሳካት፣ ማንም አንዳች ነገር እስኪያደርግልህ መጠበቅ የለብህም። ሕልሙ ያንተ ነው፤ የታየህም ለአንተ ነው። ስለዚህ መክፈል ያለበትን ዋጋ መክፈል ያለብህ አንተ ራስህ ነህ። አንተ ለሕልምህ ምንም ዐይነት ዋጋ ሳትከፍል፣ ሌሎች ሰዎች ለአንተ ሕልም ዋጋ እንዲከፍሉ መጠበቅ የለብህም። አንተ ለሕልምህ የመጨረሻውን ዋጋ እና አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ሁሉ ስትከፍል፣ ሌሎች ሰዎች ሊረዱህ ይችላሉ። ራስህን ስትቀይር፣ ሌሎች ሰዎችም ሊቀየሩ ይችላሉ። ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ሰውነት ስትቀይር፣ በአካባቢህ ያሉ ሰዎችም ሕልምህን እንድታሳካ ሊረዱህ ይችላሉ። ራስህን ስትቀይር፣ ሁሉም ነገር መቀየር ይጀምራል። ሕይወትህ፣ ቤተሰብህ፣ ሥራህ፣ ገቢህ፣ ጤንነትህ እንዲሁም የምትፈልገው ነገር ሁሉ እንዲቀየር፣ በመጀመሪያ አንተ መቀየር አለብህ። ይህ ጥልቅ ምስጢር ነው።

ዴት አድርገህ ነው ሙሉ በሙሉ ራስህን ልትቀይር የምትችለው? “ራሴን መቀየር አለብኝ” ብለ ስታስብ፣ “ምንህ እንዲቀየር ነው የምትጠብቀው? ምንህስ ነው መቀየር ያለበት? የሰው ልጅ ማን ነው? ምንድንስ ነው? በምንና እንዴት ነው የሚሠራው? ራስን ለመቀየር መቀየር የሚያስፈልገው ነገር ምንድ ነው?” እነዚህን ጥያቄዎች በትክክል መመለስ ስትችል፣ ራስህን እንዴት አድርገህ መቀየር እንደምትች በቀላሉ መረዳት ትችላለህ። አሁን ራሳችንን እንዴት አድርገን መቀየር እንደምንችል ከመመርመራች በፊት፣ “የሰው ልጅ ማን ነው? እንዴትስ ነው የሚሠራው?” የሚለውን አስቀድመን እንፈትሽ።

# የሰው ልጅ

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ መልኩ፣ በፈጣሪ መልክና አምሳል የተፈጠረ ፍጥረት ነው። ሁላችንም የሰው ልጆች ወደዚች ዓለም ስንመጣ፣ ፈጣሪ የሚያስፈልገንን ሁሉ ነገር ሰጥቶናል። በውስጣችን ያለውን ተዓምር ስንፈትሽ፣ ድንቅ መሆናችንንና የፈለግነውን ነገር ማሳካት እንደምንችል እናስተውላለን። ይህንን ምስጢር በደንብ ካልተረዳነው ግን ሕይወት እንቆቅልሽ ልትሆንብን ትችላለች። ማንነታቸውን በትክክል ያልተረዱ ሰዎች፣ ትልቅ ሕልም አስቀምጠው ድንቅ ሕይወት ለመኖር ሲያልሙ፣ ወዲያውኑ፣ “ይህ ሕልም'ማ አይቻልም፤ በጣም ከባድ ነው! ደግሞም ከአቅሜ በላይ ነው!” ብለው ተስፋ ይቆርጣሉ። እንዲህ ዐይነት አስተሳሰብ፣ “ማን መሆንንና አቅምን አለማወቅ” ይባላል። “በፈጣሪ አምሳል ተፈጥረናል” ሲባል'ኮ ለቀልድ አይደለም። እኛ እጹብ ድንቅ የሆንን የሰው ልጆች፣ ትልቁን ሕልማችንን በአዕምሯችን ስናልመው፣ እንደምናሳካው በልባችን ስናምነው፣ እንዲሁም መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ስንከፍል፣ የትኛውም “ትልቅ” የሚባል ሕልም ከአቅማችን በታች እንጂ ከአቅማችን በላይ አይሆንም።

ትናንት ባጠናነው “ራስን መገምገም” በሚለው ምዕራፍ እንዳየነው፣ ሕልማችንን ለማሳካት ዕንቅፋት የሚሆንብን፣ የአፈጣጠራችንና የድንቅ አቅማችን ችግር ሳይሆን፣ ድንቅ አቅማችንን የምንጠቀምበት ዘዴ ትክክል አለመሆን ነው። ድንቅ የሆነ አቅማችንን የምንጠቀምበትን ደረጃ ከተራነት ወደ ድንቅነት ስንቀይረው፣ ሕይወታችንም አብሮ ይቀየራል። ስለዚህ ሕይወታችንን እንዴት አድርገን ከተራነት ወደ ድንቅነት ልንቀይረው እንደምንችል ማወቅ ያሻል።

ብዙ ጊዜ፣ ሰዎች ከተራነት ወደ ድንቅነት ለመቀየር ይሞክራሉ፤ ነገር ግን ሳይሳካላቸው ሲቀር እናያለን። ራሳቸውን ከተራ ወደ ድንቅ ሰውነት ለመቀየር ብዙ መጻሕፍት ያነባሉ፤ የተለያዩ ስልጠናዎችን ይወስዳሉ፤ ከሌሎች ሰዎችም ምክር ይቀበላሉ። ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ ድንቅ መሆን ይጀምራሉ። ቀናት ከተቆጠሩ በኋላ ግን በድጋሚ ወደ ተራ ማንነታቸው ይመለሳሉ። አዲስ ዓመት ሊመጣ ሲል፣ “ከአዲስ ዓመት በኋላ አዲስ ሰው እሆናለሁ” ብለው ያቅዳሉ። ከዚያም ለሳምንት ያክል እንዳቀዱት ራሳቸውን ይቀይራሉ። ከሳምንት በኋላ ግን ወደነበሩበት ተራ የሕይወት ምልልስ ይገባሉ። አንተም በሕይወትህ እንዲህ ዐይነት ነገር አጋጥሞህ ከሆነ፣ “ራስን ወደ ድንቅነት መቀየር” የሚለው ሀሳብ ተስፋ ሲያስቆርጥህ፣ ሊፈትንህና ሊገዳደርህም ይችላል።

ይህንን “ትልቅ ሕልም አለኝ” የሚል መጽሐፍ ስታነብ፣ “በርግጠኛነት እቀየራለሁ” ብለህ ብታስብም፣ በውስጥህ ልትጠራጠር ወይም ሙሉ እምነት ላይኖርህ ይችላል። በርግጠኛነት የምነግርህ አንድ ነገር ቢኖር፣ ይህ መጽሐፍ ብዙ ሰው ወደ መቃብሩ ይዞት የሚሄደውን ችግር እንደሚፈታልህ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምስጢሮች የእኔን ሕይወት ሙሉ በሙሉ ቀይረውታል። እነዚህን ምስጢሮች ከመረዳቴና ከመጠቀሜ በፊት፣ በሕይወቴ በጣም ብዙ ችግሮች አጋጥመውኝ ነበር። ያጋጠሙኝን ችግሮች ለመፍታትና ሕይወቴን ለመቀየርም የተለያዩ መንገዶችን ለረጅም ጊዜያት በተደጋጋሚ ተጉዤ ነበር። የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ፣ ቪዲዮዎችን በመመልከት፣ ፕሮግራሞችን በመከታተልና ምክሮችን በመጠቀም፣ በሕይወቴ ላይ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት ጥሬያለሁ። ነገር ግን ሳገኛቸው የነበሩት ለውጦች ዘለቄታነት አልነበራቸውም።

እነዚህን፣ ለአንተ እያካፈልኩህ ያሉትን ምስጢሮች በትክክል በማጥናትና በመረዳት መጠቀም ስጀምር ግን፣ ከጠበቅኩት በላይ በሕይወቴ ላይ ትልቅ ለውጥ እያመጣሁ ነው። ለውጡም ዘለቄታዊ ነው። ብዙ ሰው ከልቡ መቀየር ፈልጎ የማይቀየረው፣ እነዚህን የሕይወት ምስጢሮች በመጠቀም፣ እንዴት አድርጎ ራሱን መቀየር እንደሚችል ስለማያውቅ ነው። እነዚህን ለሕይወት ቁልፍ የሆኑ ምስጢሮች፣ ትምህርት ቤት "ሀ፣ ሁ..." ስንቆጥር፣ መምህሮቻችን አላስተማሩንም። ወላጆቻችንም በዚህ ዕውቀት አልኮተኮቱንም። እነዚህን ምስጢሮች በመጠቀም፣ እንዴት እንደምንሠራና እንዴት እንደምንቀየር ካላወቅን ደግሞ፣ ለመቀየር የምናደርገው ልፋት ከንቱ ነው የሚሆነው። ስለሆነም ከሁሉ አስቀድመን የምንሻው ጉዳይ፣ እኛ የሰው ልጆች ማን ነን? እንዴት ነው የምንሠራው? እንዴትስ ነው ራሳችንን መቀየር የምንችለው? የሚሉትን ጥያቄዎች በትክክለኛው መንገድ መረዳት ነው።

# ሰው አንድም ሦስትም!

የሰው ልጅ ከሦስት አካላት የተሠራ ነው። ሕይወታችንን ለመቀየር እነዚህን ሦስቱን አካላት መቀየር ያስፈልገናል። የሰው ልጅ ከመንፈሳዊ (Spirit)፣ አዕምሯዊ (Mind) እና ሥጋዊ (Body) አካሎች የተሠራ ነው። በዚህ ምዕራፍ ስለ አዕምሯዊ እና ሥጋዊ አካላችን እንጂ ስለ መንፈሳዊ አካላችን አናነሳም። የማይታየውና የማይጨበጠው መንፈሳዊ አካላችን ምን እንደሆነና እንዴትም መጠቀም እንደምንችል፣ በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ላይ እንመለከታለን። አሁን አዕምሯዊ እና ሥጋዊ አካሎቻችን ምን እንደሆኑና እንዴት አድርገን መጠቀም እና መቀየር እንደምንችል እንመረምራለን። አዕምሯዊ እና ሥጋዊ አካሎቻችን ምን እንደሆኑና እንዴት አድርገን መጠቀም እና መቀየር እንደምንችል በመረዳት ስንጠቀምባቸውና ስንቀይራቸው ደግሞ፣ ሕይወታችንን መቀየር እንችላለን።

## አዕምሯዊ እና ሥጋዊ አካላችን

ሥጋዊ አካላችን፣ በአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻችን አማካኝነት ማየት፣ መዳሰስ፣ መስማት፣ ማሽተት እና መቅመስ የምንችለው ክፍላችን ሲሆን፣ አዕምሯዊ አካላችን የምንለው ደግሞ፣ በአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻችን ሳይሆን፣ በስድስቱ የአዕምሮ መሣሪያዎቻችን ልንመለከተውም ሆነ ልንጠቀምበት የምንችለው አካላችን ነው። (ስድስቱ የአዕምሮ መሣሪያዎቻችን ምን እንደሆኑና እንዴት እንደምንጠቀምባቸው፣ በሚቀጥለው ሳምንት በምናጠናው ሁለተኛው የዚህ መጽሐፍ ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን)

አውሮፕላን በወፍ ምስል እንደተሠራው ሁሉ ኮምፒዩተርም በሰው ሞዴል የተሠራ ስለሆነ፣ የኮምፒዩተርን ዋና ዋና አካሎች መመልከት፣ እኛ ሰዎች እንዴት እንደምንሠራ ለመረዳት ቀለል እንደሚያደርግልን፣ በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ተመልክተናል። ኮምፒዩተር ልክ እንደ ሰው ከሁለት ክፍሎች ማለትም ከሀርድ ዌር እና ሶፍት ዌር የተሠራ ነው። የኮምፒዩተር ሀርድ ዌር፣ በአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻችን መጠቀምና መጨበጥ የምንችለው የኮምፒዩተር ክፍል ነው። የኮምፒዩተር ሶፍት ዌር ግን፣ ልክ እንደ አዕምሯዊ አካላችን በአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻችን የማንጨብጠው ክፍል ነው። ማስተዋል የሚገባን ነገር ቢኖር፣ ሁልጊዜ፣ ሀርድ ዌር በማይጨበጠው ሶፍት ዌር ቁጥጥር ስር መገኘቱን ነው።

ብዙ ሰው በሚያየውና በሚጨብጠው ነገር ብቻ ስለሚንቀሳቀስ፣ ለሥጋዊ አካሉ እንጂ ለማይታየው እና ለማይጨበጠው አዕምሮው ብዙ ትኩረት አይሰጥም። አዕምሯዊ አካል የማይታይና የማይጨበጥ ቢሆንም፣ ሙሉ ሥጋዊ አካላችንን የመቆጣጠር ትልቅ አቅም ያለው የእኛነታችን ዋና መሥሪያና መምሪያ አካል ነው። ሁሌም ቢሆን ሥጋዊ አካላችን፣ በአዕምሯዊ አካላችን ቁጥጥር ስር የሚገኝ በመሆኑ፣ አዕምሯዊ አካላችንን ሳንቀይር፣ ሥጋዊ አካላችንን ለመቀየር ብንሞክር፣ በጣም አድካሚ ይሆንብናል። አዕምሯችንን በትክክል ስንቀይር ግን፣ ሰውነታችንም አብሮ ይቀየራል። የተስተካከለና ሥርዓት የያዘ አዕምሮ ሲኖረን፣ ሰውነታችንም የተስተካከለና ሥርዓት የያዘ ይሆናል፤ ውጤታማ የሆነ ሥራም ያከናውናል።

ስለ ኮምፒዩተር ወዳነሳነው ምሳሌ ብንመለስ፣ "አንደኛ" የሚባል የኮምፒዩተር ሀርድ ዌር ቢኖረን፣ ሶፍት ዌሩ የድሮና ያልታደሰ ወይም በቫይረስ የተጎዳ ቢሆን፣ ኮምፒዩተሩ ፈጣን እና ውጤታማ አይሆንም። ሀርድ ዌሩ ብዙ ሥራዎችን ማከናወን እየቻለ፣ ሶፍት ዌሩ ዕንቅፋት ይሆንበታል። እንበል አንድ ዘመናዊ "ኮር አይ 7" (Core i 7) ኮምፒዩተር ገዝተን፣ የድሮ "ዊንዶውስ 95" (Windows 95) ሶፍትዌር ብንጭንበት፣ በኮምፒዩተሩ መሥራት በጣም አድካሚ ይሆናል። ሀርድ ዌሩ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ባለበት ፍጥነት አይሠራም፤ ሶፍት ዌሩ ሀርድ ዌሩን ማንበብ፣ ማሠራት እና መምራት ስለሚከብደው፣ ኮምፒዩተሩ ትላልቅና ዘመናዊ ነገሮችን መሥራት ይከብደዋል። ሶፍት ዌሩን ወደ "ዊንዶውስ 10" (Windows 10) ወይም ወደተሻለ ሶፍት ዌር ብናሳድገው ግን፣ አዲሱ ሶፍት ዌር፣ ሀርድ ዌሩን ተግምር እንዲሠራ በማዘዝ፣ የሚገርም ውጤት ያስገኝዋል!

የሰው ልጆችም ልክ እንደ ኮምፒዩተር፣ ድንቅ የሆነውን ሥጋዊ አካላችንን፣ ተስፋ በቆረጠና በደንብ ባልተገነባ አዕምሯዊ አካል ልንጠቀምበት ብንሞክር፣ በጭራሽ ውጤታማ አንሆንም። ነገር ግን ድንቅና ታላቅ የሆነውን አዕምሯዊ አካላችንን፣ በድንቅ አስተሳሰብ፣ በጠንካራ እምነትና በታደሰ አመለካከት ስንገነባ፣ ሥጋዊ አካላችንን በትክክል በማዘዝ፣ ድንቅ የሆኑ ነገሮችን እንድንሠራ ይረዳናል። አዕምሯዊ አካላችን ሲቀየር፣ ሥጋዊ አካላችንና ሕይወታችን ሁሉ ይቀየራል። የሥጋዊ አካላችንና የሕይወታችን መለወጥ ምስጢር፣ በአዕምሯችን ውስጥ የተሰነደ ነው።

ጤናማ አዕምሯዊ አካል ያለው ሰው፣ ጤናማ ሥጋዊ አካል ይኖረዋል። በሽተኛ አዕምሯዊ አካል ያለው ሰው ደግሞ፣ በሽተኛ ሥጋዊ አካል ይኖረዋል። ውጤታማ አዕምሯዊ አካል ካለን ውጤታማ ሥጋዊ አካል፣ ሰበበኛ አዕምሯዊ አካል ካለን ደግሞ ሰበበኛ ሥጋዊ አካል ይኖረናል። ሀብታም አዕምሯዊ አካል ያለው ሰው ሀብታም ይሆናል፤ ድሀ አዕምሯዊ አካል ያለው ሰው ደግሞ ድሀ ይሆናል። ደካማ አዕምሯዊ አካል ደካማን ሥጋዊ አካል፣ ጠንካራ አዕምሯዊ አካል ደግሞ ጠንካራን ሥጋዊ አካል ይፈጥራሉ። ፈሪ አዕምሯዊ አካል ካለህ፣ ፈሪ ሥጋዊ አካል፣ ጀግና አዕምሯዊ አካል ካለህ ደግሞ፣ ጀግና ሥጋዊ አካል ይኖርሀል። የሰነፍ አዕምሯዊ አካል ውጤት ሰነፍ ሥጋዊ አካል ሲሆን፣ የነጻ አዕምሯዊ አካል ውጤት ደግሞ ጤናማና ነጻ ሥጋዊ አካል ነው። ልብ ብለህ ከተመለከትክ ሥጋዊ አካላችን፣ ሕይወታችንና የምናገኘው ውጤት ሁሉ፣ የአዕምሯችን ውጤት መሆናቸውን ታስተውላለህ።

ለምሳሌ ያክል የሁለት ሰዎችን አዕምሯዊና ሥጋዊ አካል እንውሰድ፣ የአትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴን እና የአንድ በጣም ወፍራምና ቦርጫምን ሰው። ኃይሌ አዕምሯዊ አካሉ የአትሌት ስለሆነ፣ ሥጋዊ አካሉም የአትሌት ነው። ሁለተኛው ሰው ደግሞ፣ አዕምሯዊ አካሉ ወፍራምና ቦርጫም በመሆኑ፣ ሥጋዊ አካሉም ወፍራምና ቦርጫም ነው። የነዚህን ሁለት ሰዎች አዕምሯዊ አካል ብንቀያይርና ሁለቱም ተኝተው ባሉበት፣ የኃይሌን አዕምሯዊ አካል ለቦርጫሙ ሰውዬ፣ በተቃራኒው ደግሞ የቦርጫሙን ሰውዬ አዕምሯዊ አካል ለኃይሌ ብንቀያይርላቸው፣ ምን የሚፈጠር ይመስልሀል?

ጥዋት፣ ኃይሌ ከዕንቅልፉ ሲነሳ፣ ሥጋዊ አካሉን፣ በጣም የወፈረ እና ቅርጽ አልባ ሆኖ ስለሚያገኘው፣ በጣም ነው የሚደነግጠው። የሚያውቀውን ያንን ጠንካራ የአትሌት ሥጋዊ አካሉን ለማምጣት ማሰብ ይጀምራል። ወዲያው ተነስቶም የሩጫ ልምምዱን ይጀምራል። የተለያዩ ስፖርቶችን በመሥራት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ወደ ቀድሞው አቋሙ እንደሚመለስ በአዕምሮው ያስባል። አዕምሮው ባመነበት ጠንካራና አትሌታዊ ቅርጽም ራሱን ያስተካክላል። አዕምሯዊ አካሉ የአትሌት በመሆኑ፣ ሥጋዊ አካሉም በልምምድ የአትሌት ይሆናል።

ወፍራሙም ሰውዬ ጥዋት ከዕንቅልፉ ሲነቃ በኃይሌ ሥጋዊ አካል ሲነሳ፣ በጣም ነው የሚደነግጠው! ሥጋዊ አካሉ ጠንካራና ቅርጹን የጠበቀ ስለሆነ በጣም ይደሰታል። ደስ ስላለው ደግሞ፣ የደስ ደስ እንዲሆን ቁርጥ፣ ጮማና ቦርገሩን እየበላ በመተኛት፣ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ወደ ወፍራምና ቦርጫም ሥጋዊ አካሉ በፍጥነት ይመለሳል። ወፍራም አዕምሯዊ አካል ስላለው፣ ወፍራም ሥጋዊ አካል ሊኖረው ግድ ይላል።

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት በቴሌቪዥን ስላየሁት አንድ ፕሮግራም ልንገርህ። የቴሌቪዥን ፕሮግራሙ አዘጋጆች፣ አንድ ጎዳና ተዳዳሪ የሆነ ሰው ፈልገው፣ በተኛበት ስፍራ ላይ አንድ ሚልየን የአሜሪካን ዶላር ያስቀምጡለታል። ሰውዬው ሲነሳ፣ ገንዘቡን ይመለከታል፤ በጣምም ይደነግጣል! የደስታም የጥርጣሬም ሳቅ ከፊቱ ይነበባል። ከደስታው ብዛት የተነሳ የሚያደርገው ጠፍቶታል። ጓደኞቹን በሙሉ ይጠራና ለራሱ ቤት፣ ለነርሱም መኪና እና የፈለጉትን ስጦታ ሁሉ ይገዛላቸዋል። ይህ በተኛበት ስፍራ ያላሰበው ሲሳይ ያጋጠመው ሰውዬ በየቀኑ መብላት፣ መጠጣት እንዲሁም ማበድ ሥራው ሆነ።

አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ግን ገንዘቡ አለቀ። ቤቱንና መኪናዎቹን መሸጥ ጀመረ። ጓደኞቹም አንድ በአንድ ጠፉ። "ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ" በመጨረሻም ሥጋዊ አካሉን አንስቶ፣ አዕምሯዊ አካሉን ወዳላነሳበት የጎዳና ሕይወቱ ተመለሰ። የድህ አዕምሮ ስለነበረው ሥጋዊ አካሉም ድሀ ሆነ። የሰውነት ውጤት የአዕምሮ ዘር ብቅለት ነው። አዕምሮህ ላይ የተዘራው ሲበቅል፣ ሰውነትህ ይሆናል።

በተመሳሳይ ጊዜ እነዚህ የፕሮግራሙ አዘጋጆች፣ አንድ በጥናታቸው ቅር እንደማይሰኝ የገመቱትን ሚልየነር፣ በሥራዎቹ ላይ የተለያዩ ዕንቅፋቶችን በመፍጠር፣ አከሰረው ባዶውን ያስቀሩታል። ነገር ግን አንድ ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሚልየነር አዕምሯዊ አካሉ ተመልሶ ሚልየነር እንዲሆን አደረገው። "ባዶ" ከሚባል የኪሳራ ሕይወቱ በመነሳት፣ ወደ ሚልየነርነት ሕይወቱ ሊመለስ ችሏል። ሚልየነር አዕምሯዊ አካል፣ ሚልየነር ሥጋዊ አካል!

እነዚህን እና ሌሎች ብዙ ታሪኮችን ስንመረምር፣ እኛ ሰዎች የአዕምሯዊ አካላችን ውጤቶች መሆናችንን እንረዳለን። አሁን እያገኘን ያለነው ውጤት፣ አዕምሯችን "ይቻላል" ብሎ የሚያምነው ውጤት ነው። የአዕምሯችንን እምነት ስንቀይረው፣ ውጤታችንም አብሮ ይቀየራል።

አንድ ሰው በወር መቶ ሺህ ብር ማግኘት እየፈለገ፣ አስር ሺህ ብር ብቻ የሚያገኘው፣ አቅሙ አስር ሺህ ብር ስለሆነ ሳይሆን፣ በአዕምሮው ማግኘት የሚችለው አስር ሺህ ብር ብቻ እንደሆነ ስለሚያስብና ስለሚያምን ነው። የአዕምሮውን ሀሳብ እና የልቡን እምነት፣ ወደ መቶ ሺህ ብር መቀየር ቢችል፣ በእምነቱ መሠረት በወር መቶ ሺህ ብር ማግኘት እንደሚችል አያውቅም። በአካባቢህ ያሉ ብዙ ሰዎችን ብትመለከታቸው፣ የሚፈልጉትን ሥራ እየሰሩ የሚፈልጉትን ያክል ገቢ የሚያገኙ ሳይሆኑ፣ ለራሳቸው "ይቻላል" ብለው ያመኑትን ብቻ የሚያገኙ ናቸው። ሰዎች ድንቅ አቅማቸውን ቢያውቁትና ድንቅ በሆነ መንገድ ቢጠቀሙበት፣ የሚፈልጉትን ሁሉ ማግኘት ይችሉ ነበር። ብዙዎች ግን ያላቸውን ድንቅ አቅም በትክክል ስለማይረዱት ተራ ሕይወት ለመኖር ይገደዳሉ። "ድንቅ አቅም የለኝም!" የሚል አስተሳሰብ ይዞ፣ ድንቅ ሕይወት መኖር የማይታሰብ ነገር ነው።

ሰው በአዕምሮው ያሰበውንና በልቡ የሚያምነውን ነው የሚያገኘው። ለምሳሌ አንድ በወር መቶ ሺህ ብር የሚያገኝ ሰው፣ በተለያየ ምክንያት፣ ገቢው ወደ አስር ሺህ ብር ቢወርድ፣ ገቢው መቶ ሺህ ብር እስኪደርስ ድረስ፣ በጭራሽ አይተኛም። በአዕምሮው "መቶ ሺህ ብር ማግኘት እችላለሁ" የሚል እምነት ስላለው፣ ወደ መቶ ሺህ ብር የወር ገቢው እስኪመለስ ድረስ ጠንክሮ ይሠራል። ረጅም ጊዜ ቢፈጅበትም እንኳ፣ በወር መቶ ሺህ ብር ወደ ማግኘት መመለሱ አይቀርም። በወር አንድ ሚልየን ብር ለማግኘት ግን ላያስብ ይችላል። ምክንያቱም በአዕምሮው "በወር መቶ ሺህ ብር ብቻ ነው ማግኘት የምችለው" ብሎ ስለሚያስብ እና ስለሚያምን ነው።

በአንተስ አዕምሮ ውስጥ ምንድን ነው የተቀረጸው? አሁን እያገኘህ ያለኸው ውጤት እንዲሁም እየኖርክ ያለኸው ሕይወት፣ አዕምሮህ የተቀረጸበት መንገድ ውጤት ነው። አሁን እያገኘህ ያለኸውን ውጤት በጣም ካልወደድከው፣ የምትፈልገውን ዐይነት ውጤት እንዲሰጥህ፣ አዕምሮህን መቀየር አለብህ። አዕምሮህ ሲቀየር፣ ሕይወትህ አብሮ ይቀየራል። ከዚህ ቀጥሎ አዕምሮ እንዴት እንደሚሠራ እና እንዴት እንደሚቀየር እንመለከታለን።

# የሰው አዕምሮ

አብዛኛው ሰው በሚያየው እና በሚጨብጠው ነገር ብቻ ስለሚንቀሳቀስ፣ ለሥጋዊ አካሉ እንጂ ለማይታየው እና ለማይጨበጠው አዕምሮው ብዙ ትኩረት አይሰጥም። ስለ ማንነቱ የማያውቅ ሰው ራሱን ሲመለከት፣ ራሱ ሥጋዊ አካል እንደሆነና የሚያስበውም በአንጎሉ እንደሆነ ብቻ ነው የሚረዳው። ነገር ግን የሰው ልጆች የምናስበው በአዕምሯችን እንጂ በአንጎላችን አይደለም። አዕምሮ አንጎል አይደለም። አዕምሮ፣ እጅና እግር እንዳልሆነው ሁሉ፣ አንጎልም አይደለም።

አንጎል በጭንቅላታችን የሚገኝ የሥጋዊ አካላችን ክፍል ነው። አዕምሮ ግን የማይታይና የማይጨበጥ አካላችን ሆኖ፣ አንጎላችንንም ሆነ ሙሉ ሰውነታችንን የሚቆጣጠር የማይታየው አካላችን ነው። ሁሌም ቢሆን ሰውነታችን በአዕምሯችን ቁጥጥር ስር ነው ያለው።

አስቀድመን ወዳነሳነው የኮምፒዩተሩ ምሳሌ ብንመለስ፣ ሶፍት ዌር ማለት *ፕሮሰሰር፣ ሀርድ ዲስክ*፣ ራም ወይም ሌላ *ሀርድ ዌር* አይደለም። እነዚህ ሁሉ ጠቃሚ እና የሚጨበጡ የኮምፒዩተሩ ሀርድ ዌር አካላት ናቸው። ሀርድ ዌርን ደግሞ አንዴ ከገዛኸው፣ ልታስተካክለው፣ ልታድሰው ወይም ልታሻሽለው ብትፈልግ፣ እንዳሻህ ለማድረግ ትንሽ ይከብዳል፤ ብዙ ጊዜም ይፈጃል። ሶፍት ዌርን ለማስተካከል፣ ለማደስ ወይም ለማሻሻል ግን ብዙ ጊዜና ትግል አያስፈልገውም።

ሥጋዊ አካላችንን ቶሎ መቀየር ይከብዳል፤ በጊዜ ሂደት ግን መቀየሩ አይቀርም። ዋና ዋና የሰውነታችን ክፍሎች ከታመሙ ወይም ከአገልግሎት ውጪ ከሆኑ፣ ለመዳን፣ ሐኪም ቤት ገብተን ከባድ ምርመራ ማድረግና የጽኑ ሕክምና ክትትል ማድረግ ሊያስፈልገን ይችላል። ቀለል ያለ ጉዳት የደረሰባቸው የሰውነታችን ክፍሎችም ቢሆኑ፣ ለመስተካከል ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ጸጉራችንን እንኳ ለማስተካከል ከሰላሳ ደቂቃ በላይ ሊያስፈልገን ይችላል።

አዕምሯችንን ለመቀየር ግን ቅጽበታዊ ውሳኔ ብቻ ነው የሚያስፈልገን። ብዙ ሰው ውሳኔ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚወሰን ስለማያውቅ፣ ዛሬ ይወስንና ነገ ይረሳዋል። (ውሳኔ ምን እንደሆነና እንዴት መወሰን እንዳለብህ በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ እንመለከታለን) በእምነት የተመረኮዘ ትክክለኛ ውሳኔ ስትወስን፣ አዕምሮህን በቅጽበት ትቀይረዋለህ። አዕምሮህ ሲቀየር ደግሞ ሰውነትህና ሕይወትህ ይቀይራሉ።

# የአዕምሮ ክፍሎች

ሕይወታችንን ለመቀየር ራሳችንን መቀየር አለብን። ራሳችንን ለመቀየር አዕምሯችን መቀየር አለበት። አዕምሮ ሁለት ክፍሎች አሉት። ሕይወትህ እንዲቀየር ደግሞ ሁለቱም የአዕምሮ ክፍሎችህ መቀየር አለባቸው። የመጀመሪያው የአዕምሮ ክፍል፣ “ንቁ አዕምሮ” ይባላል። ሁለተኛው ደግሞ “ድብቁ አዕምሮ” ይባላል። አዕምሮህን በመቀየር፣ ራስህንና ሕይወትህን ለመቀየር፣ ንቁውንና ድብቁን የአዕምሮ ክፍሎችህን መቀየር አለብህ።

**ንቁ አዕምሮ፣** ነቅተን እያለ የምናደርገውን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠረው የአዕምሯችን ክፍል ነው። አሁን ይህንን መጽሐፍ ስታነብ፣ ስታደንቅ፣ የሚመስጥህ ክፍል ላይ ስታሰምር፣ በምስጢሮቹ ስትደመም፣ ከዚያም ልትጠቀምባቸው ስትወስን፣ ወዘተ... ንቁውን አዕምሮህን ነው የምትጠቀመው። ይህንን መጽሐፍ እያነበብክ ሰው ቢጠራህ፣ ወይም ስልክህ ቢጮህ፣ በንቁ አዕምሮህ ነው ተገቢውን ምላሽ የምትሰጠው። አምስቱ የስሜት ሕዋሶቻችንም በቀጥታ ከንቁ አዕምሯችን ጋር ነው የሚገናኙት። ንቁ አዕምሮ አምስቱን የስሜት ሕዋሶቻችንን በመጠቀም፣ ከአካባቢያችን ጋር ለመገናኘት እና ለመግባባት ያስችለናል።

ድብቁ አዕምሮ፣ ያለ ምንም ሀሳብ፣ መንቃት ሳይጠበቅብን፣ የምናደርጋቸውን ሁሉንም እንቅስቃሴዎቻችንን የሚቆጣጠርና የሚያሠራ የአዕምሯችን ክፍል ነው።

ንቁ አዕምሯችን በአካባቢው ያሉ ነገሮችን እና እንቅስቃሴዎችን እያስተናገደ እያለ፣ ድብቁ አዕምሯችን የሚያስፈልጉንን ሁሉንም እንቅስቃሴዎቻችንን በመቆጣጠር፣ መደረግ ያለበትን ሁሉ ነገር እንድናደርግ የሚያስችለን ክፍል ነው። ለምሳሌ አሁን ይህንን መጽሐፍ በንቁ አዕምሮህ እያነበብክ፣ በውስጥህ ደም ይዘዋወራል፤ ያለማቋረጥም ትተነፍሳለህ። ድብቁ አዕምሮህ፣ ሳንባዎችህ እንዲተነፍሱ፣ ልብህ ደም እንድትረጭ፣ ጨጓራህ ምግብ እንዲፈጭ እንዲሁም ሌሎች የሰውነት ክፍሎችህ ለሕይወትህ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን እንዲያከናውኑልህ የሚያደርግ የአዕምሮህ ክፍል ነው።

ድብቁ አዕምሮ ለሃያ አራት ሰዓታት፣ ያለ ምንም ዕረፍት፣ በውስጣችን ተዓምር እየሠራ ይገኛል። ለምሳሌ የሆነ ትንሽ ነገር እግርህን ቢቆርጥህ እና ብትደማ፣ ልትደነግጥ ትችላለህ። ነገር ግን ከሳምንት በኋላ እግርህን ተመልሰህ ብታየው፣ አንተ ምንም ባታደርግበት እንኳ ድኖ ታገኘዋለህ። አንዳንዴ "አሞኛል! በደንብ ማረፍ አለብኝ" ብለህ ብትተኛም፣ ድብቁ አዕምሮህ ሌሊቱን ሙሉ አይተኛም። አንተ ተኝተህ እያለ፣ ፈጣሪ የሰጠውን የሕክምና ጥበብ በመጠቀም፣ ህመምህን አክሞ፣ በሽታህን አጥፍቶ፣ ሙሉ ለሙሉ ፈውሰህ ያድራል።

በውስጣችን ያለውን የድብቁ አዕምሯችንን ተዓምር ለመረዳት፣ የሕይወት ዘመናችን በቂ አይደለም። አንድ ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት፣ ድብቁ አዕምሮዋ፣ በውስጧ ልጅ ይሠራላታል። ፈጣሪ ምስጢሩን፣ ዘዴውንና አቅሙን ስለሰጠው፣ ድብቁ አዕምሮ፣ አንድ የማይታይ የነበረን ጽንስ፣ የሚያስፈልገውን ሁሉ ነገር በመስጠት፣ በ280 ቀናት ውስጥ በእናቱ እቅፍ ውስጥ የሚገባ ልጅ ያደርገዋል።

ፈጣሪ ድንቅ አድርጎ ስለሠራን፣ ሁለቱም የአዕምሯችን ክፍሎች፣ የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ቢኖራቸውም፣ አብረው ሲሰሩ ግን ፍጹም ናቸው። አሁን የሁለቱንም ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመመርመር፣ እንዴት እነዚህ የአዕምሮ ክፍሎች እንቅስቃሴዎችህን እንደሚቆጣጠሩና እንዴትም ደካማ ጎኖቹን መቀየር እንደምትችል እንመለከታለን።

ንቁ አዕምሮ፣ በአካባቢያችን ያሉ ነገሮችን በመመልከትና አዳዲስ መረጃዎችን በፍጥነት በመሰብሰብ፣ ወዲያውኑ መረጃውን ወደ ተግባር መቀየር ይችላል። ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ ድንቅ መሆንህንና ትልቁን ሕልምህን እውን ማድረግ እንደምትችል ስታነብ፣ ደስ ካለህና ነገሮችን መቀያየር ከጀመርክ፣ ንቁ አዕምሮህ መልዕክቱን ተቀብሎታል ማለት ነው። ንቁ አዕምሮ በፍጥነት አዲስ መረጃ መማርና መረዳት፣ ከዚያም ወደ ውሳኔና ተግባር መግባት ይችላል። አዲስ መረጃ ሲያገኝ እንደገና ትኩረቱን ወደ አዲሱ ነገር ስለሚያዞር፣ ንቁ አዕምሮ አንድ ጉዳይ ላይ ረጅም ቆይታ አያደርግም።

ከንቁ አዕምሮ በተቃራኒ ድብቁ አዕምሯችን ከአካባቢያችን አዳዲስ መረጃዎችን በፍጥነት አይቀበልም። ነገር ግን አንዴ መልዕክቱን ከተቀበለ፣ የተቀበለውን ነገር አይለቅም።

## የንቁ አተነፋፈስ ምሳሌ

በምሳሌ ለመረዳት፣ አንድ ጊዜ አተነፋፈስህን በጥሞና ረጋ ብለህ ተመልከት። በሚቀጥለው ገጽ ላይ፣ አንድ የተለየ "ንቁ አተነፋፈስ" የተባለ የአተነፋፈስ ዘዴ እንለማመዳለን። ይህንን የአተነፋፈስ ዘዴ ለመለማመድ፣ በመጀመሪያ ሊረብሹህ የሚችሉ ማናቸውንም ዐይነት ነገሮች ሁሉ ከአጠገብህ እና አካባቢህ ብታስወግዳቸው ይመከራል።

ይህንን የንቁ አተነፋፈስ ዘዴ በደንብ ተጠቅመህ፣ በማንኛውም ሰዓት ራስህን ከጭንቀት፣ ከራስ ምታት እና ከተለያዩ ችግሮች ነጻ ማውጣት ትችላለህ።

ንቁ አተነፋፈስ፣ በውስጥህ ከአንድ እስከ አምስት እየቆጠርክ የምታደርጋቸው ሦስት ደረጃዎች አሉት።

- በመጀመሪያ (ከአንድ እስከ አምስት እየቆጠርክ) በአፍንጫህ ንጹህ አየር ከውጪ ወደ ውስጥህ አስገባ።
- በመቀጠል (አሁንም ከአንድ እስከ አምስት እየቆጠርክ) ከውጪ ያስገባኸውን ንጹህ አየር ሳትለቅ፣ በውስጥህ ያዝ አድርግ።
- በመጨረሻም (ከአንድ እስከ አምስት እየቆጠርክ) በውስጥህ ያቆየኸውን አየር ወደ ውጪ ተንፍስ።

አሁን እነዚህን ሦስት ደረጃዎች ደጋግመህ አድርጋቸው። ልምምዱን ለመጀመር፣

- በመጀመሪያ፣ በአካባቢህ ያለ ምንም ነገር እንደማይረብሽህ ርግጠኛ ሁን።
- በመቀጠል ከወገብህ ቀጥ ብለህ ተቀመጥ፤ አልያም ቀጥ ብለህ ቁም።
- በመጨረሻም ዐይንህን በመጨፈን፣ ሳታቋርጥ ሦስቱን የንቁ አተነፋፈስ ዘዴዎች (ከአንድ እስከ አምስት እየቆጠርክ) ደጋግመህ አድርጋቸው።

ልምምዱን አደረግክ? ካደረግክ መልካም። ልምምዱን ካደረግክ በኋላ ምን ተሰማህ? ልምምዱን በደንብ ስትሠራና ረጅም ጊዜ መቆየት ስትጀምር፣ የተሻለ ዕረፍት አልሰጠህም? አሁን አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ። በንቁ የአተነፋፈስ ልምምዱ ውስጥ ለምን ያክል ጊዜ ቆየህ? ስንት ጊዜ ሦስቱን ደረጃዎች በመደጋገም ሠራህቸው? አብዛኛው ሰው ደረጃዎቹን ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ብቻ ከደጋገመ በኋላ፣ በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ልምምዱን ያቋርጣል። ለምንድን ነው ግን አንድ ሰው የንቁ አተነፋፈስን ጥቅምና ዘዴ እያወቀ፣ እየወደደ ደግሞም እየተረዳ፣ ለረጅም ጊዜ በደንብ ዕረፍት እስኪሰማው ድረስ በተደጋጋሚ ልምምዱን የማይቀጥለው? ምክንያቱም ንቁ አተነፋፈስን "በንቁ አዕምሯችን የምንሠራው" በመሆኑ ነው። ንቁ አዕምሯችን ደግሞ ትዕግስት የለውም።

አሁን ይሄኛውን አንቀጽ ስታነብ፣ እየተጠቀምክ ያለህበትን አተነፋፈስ ልብ ካልከው፣ ንቁ አዕምሮህ፣ ንቁ አተነፋፈሱን ትቶ፣ አዲስ ነገር ወደ ማንበብ ሲገባ፣ ድብቁ አዕምሮህ ደግሞ፣ የመተንፈስ ሥራውን ተቀብሎ ሥራውን ቀጥሏል። ሁለቱ የአዕምሯችን ክፍሎች እርስ በርስ ሲነጋገሩ ብንሰማ፣ ድብቁ አዕምሮ፣ ለንቁ አዕምሮ፣ "አሁን ደግሞ በመተንፈስ መጣህብኝ? በል ሌሎች ነገሮችን ሞካክር፤ መተንፈሱን ግን ለኔ ተውልኝ" ሲለው እንሰማ ነበር።

በንቁ አዕምሯችን ብንተነፍስ ኖሮ፣ በአንድ ሰዓት ውስጥ እንሞት ነበር። ፈጣሪ በጥንቃቄ ስለሠራን፣ እነዚህ ትላልቅና ለረጅም ጊዜ የሚቀጥሉ ከባባድ ኀላፊነቶች፣ ለድብቁ አዕምሯችን ነው የተሰጡት። ድብቁ አዕምሮ ኀላፊነቱን ሲወጣ፣ አይሰላችም፤ ደከሞትም አያውቅም። ድብቁ አዕምሮ መተንፈስ የጀመረው፣ ንቁ አዕምሮ መተንፈሱን ባቋረጠበት ሰዓት ሳይሆን፣ በተወለድንባት ዕለት ነው። ድብቁ አዕምሮ፣ ከተወለድንባት ዕለት አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ሥራውን በምንም ዐይነት ምክንያት አቋርጦ አያውቅም። ቢያቋርጥ ኖሮማ በሕይወት አንቀጥልም ነበር።

ስለ አፈጣጠራችን ስንመረምር የምንገነዘበው፣ ንቁ አዕምሮ አዲስ ነገር ለመማር እና በፍጥነት ወደ ተግባር ለመግባት እንደሚችል ነው። ንቁ አዕምሮ ግን ቆይታ የለውም። ድብቁ አዕምሮ፣ አዲስ ነገር በፍጥነት አይቀበልም። ከተቀበለ ደግሞ፣ በቀላሉ አይለቅም። ከዚህ መጽሐፍ የምትማራቸው አዳዲስ ምስጢሮች፣ በንቁ አዕምሮህ ብቻ ከገቡ፣ ምንም ትርጉም አይኖራቸውም። ለተወሰነ ጊዜ ትቀየራለህ፤ ከዚያ ግን ወደነበርክበት የድሮ ኑሮ ትመለሳለህ። በድብቁ አዕምሮህ ከገቡ ግን፣ በሕይወትህ ትክክለኛውንና ዘላቂውን ለውጥ ማምጣት ትችላለህ። ራስህን መቀየር የምትችለው፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ምስጢሮችን በመጠቀም ንቁውን ብቻ ሳይሆን ድብቁን አዕምሮህን ጭምር ስትቀይር ነው።

## ራስህን ለመቀየር ዝግጁ ነህ?

ሕይወትህን ለመቀየር፣ መቀየር ያለብህ ራስህን ነው። ራስህን ለመቀየር ደግሞ፣ አዕምሯዊ አካልህ መቀየር አለበት። ሥጋዊ አካልህ ሁሌም ቢሆን በአዕምሯዊ አካልህ ቁጥጥር ስር ስለሆነ፣ አዕምሯዊ አካልህ ሲቀየር፣ ሥጋዊ አካልህ እና ሕይወትህ ይቀየራሉ። ስለዚህ ሕይወትህን ለመቀየር፣ አዕምሯዊ አካልህ እንዲቀየር መሥራት አለብህ። አዕምሯዊ አካልህን ለመቀየር ደግሞ፣ ሁለቱም የአዕምሮ ክፍሎችህ መቀየር አለባቸው። ሕይወትህን ለመቀየር፣ በንቁ አዕምሮህ አስበህ የምታደርገውንና በድብቁ አዕምሮህ ምንም ሳታስብ የምታደርገውን ሁሉ መቀየር አለብህ። ሁለቱ የአዕምሮ ክፍሎችህ ሲቀየሩ፣ ሙሉ ሕይወትህ ይቀየራል።

በዚህ ሳምንት፣ አንተ ድንቅ መሆንህንና ማድረግ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ እንደምትችል ተመልከተናል። ከነገ ጀምሮ ደግሞ፣ አዳዲስ እና ድንቅ የሕይወት እና ስኬት ምስጢራትን ማጥናት እንጀምራለን። በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት የምታጠናቸው ምዕራፎች ራስህን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብህን፣ መሥሪያ ቤትህን፣ አገርህን፣ አህጉርህን እና ዓለምን ለመቀየር የሚረዱህን ድንቅ የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች የያዙ ምዕራፎች ናቸው። በነዚህ ሦስት ቀናት የምታጠናቸው ምዕራፎች የሚከተሉት ናቸው።

- ትልቅ ሕልም
    - ፓራዳይም እና
        - የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች

በቀጣዮቹ ሦስት ቀናት የምታጠናቸው እነዚህ ሦስት ምዕራፎች፣ የዚህ መጽሐፍ የደም ስሮች ናቸው። እነዚህ ሦስት ምዕራፎች የየራሳቸው የሆነ ልዩ ልዩ ልምምዶች በውስጣቸው ይዘዋል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምታደርገው ጥናት እና ምርምር ውጤታማ የሚሆነው፣ በሦስቱ ምዕራፎች ውስጥ ያሉትን የሕይወት እና ስኬት ምስጢራት በትክክል ስታጠናቸው እና ልምምዶቹን በጥንቃቄ ስትሠራቸው ነው። እነዚህን ሦስት ምዕራፎች በትኩረት ስታጠናቸው እና ልምምዶቹን በጥንቃቄ ስትሠራቸው ሕይወትህን የሚቀይሩ፣ "ትልቅ ሕልም" "ድንቅ ፓራዳይም" እና "የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች" ይኖሩሀል።

እነዚህን ሦስት ምዕራፎች አጥንተህ እንደጨረስክ፣ የሳምንቱን የመጨረሻ "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ጥናት በገጽ 95 ላይ ታገኛለህ። ይህ ልምምድ ለሃያ አንድ ቀናት በተደጋጋሚ በየቀኑ የሚሠራ ልምምድ ነው። ይህንን ልምምድ ለሃያ አንድ ቀናት በተደጋጋሚ ስትሠራው ትልቁን ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህ በርግጠኛነት ይቀየራል። ይህንን ልምምድ በትክክል ለመሥራት፣ በሚቀጥሉት ሦስት ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙትን ልምምዶች፣ በመመሪያዎቹ መሠረት በጥንቃቄ መሥራት አለብህ።

ቀጥሎ አንድ የጥናት ሰሌዳ ቀርቧል። በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ያሉ የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በትኩረት ለማጥናትና ልምምዶቹን በጥንቃቄ ለመሥራት፣ እባክህ ውድ ጊዜህን በዚህ የጥናት ሰሌዳ መሠረት አስቀድመህ አዘጋጅ። ለዘመናት የተደበቁ ጥልቅ የሕይወት እና ስኬት ምስጢራትን በማጥናት፣ በመረዳት እና በመጠቀም እንዲሁም መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል ራስህን፣ ቤተሰብህን፣ መሥሪያ ቤትህን፣ አገርህን፣ አህጉርህንና ዓለምን መቀየር አሁኑኑ ጀምር። ጊዜው አሁን ነው!

| ቀን | ምዕራፍ | ጥናት | ልምምድ | | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ልዩ | ምስጋና | |
| ፩ | ትልቅ ሕልም | 02:00 | 02:00 | 00:30 | 04:30 |
| ፪ | ፓራዳይም | 01:30 | 02:00 | 00:30 | 04:00 |
| ፫ | የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች | 01:15 | 02:00 | 00:30 | 03:45 |
| | ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ | 00:30 | 02:00 | 00:30 | 03:15 |

<u>ማሳሰቢያ፡</u> ከላይ ባለው ሰንጠረዥ የተጠቀሱትን የዚህ መጽሐፍ መሠረታዊ ምዕራፎች በጥልቀት ለማጥናት እና ልምምዶቹን በትኩረት ለመሥራት፣ ግማሽ ቀን እና ከዚያ በላይ ሊያስፈልግህ ይችላል!

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። አባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረክኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*
*
*
*
*
*
*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*
*
*
*
*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*
*
*

**አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሃል!**

# ቀን ፫

*******

# ትልቅ ሕልም

*"የትልቅ ሕልም ዓላማ፣ ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት መቀየር ነው!"*

ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው? ምን መሆን ትፈልጋለህ? ምን ማድረግ ትሻለህ? የት መድረስ ትፈልጋለህ? ምንስ ማግኘት ትፈልጋለህ? ድንቅ የፈጣሪ ልጅ ለሆንከው ለአንተ፣ ሁሉም ነገር የሚቻል ስለሆነ እና የማይቻል ነገርም ስለሌለ፣ ማሳካት የምትፈልገው ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው?

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሕልም ካርድ ታገኛለህ። በዚህ የሕልም ካርድ ላይ ትልቁን ሕልምህን ስትጽፈውና በየቀኑ ደጋግመህ ስታነበው፣ ድንቁና ትልቁ ሕልምህ እውን ይሆናል። ይህንን እየነገርኩህ ያለሁትን እውነት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታነብ፣ የማይሆን ነገር ብቻ ሊመስልህ ይችላል። ነገር ግን ትልቁን ሕልምህን፣ በዚህ የሕልም ካርድ ላይ በመጻፍና በየቀኑ ደጋግመህ በማንበብ፣ በልብህ ስታምነውና በተግባር ስታሳካው፣ የዚህን የሕልም ካርድ ተዓምር ትመሰክራለህ።

ስኬት ሦስት ነገር ነው። ስኬት ማለት አሁን የት እንዳለህ ማወቅ፣ የት መሄድ እንደምትፈልግ መወሰንና ካለህበት የአሁን ሁኔታ በመነሳት፣ መሄድ ወደምትፈልገው ቦታ መሄድ ነው። ብዙ ሰው አሁን የት እንዳለ አያውቅም፤ የት መሄድ እንደሚፈልግም አይወስንም። በዚህም ጥዋት ሲነሳ፣ ወዴት መሄድ እንዳለበት ግራ ይገባዋል። ባለፉት ቀናት ያጠናሀቸውን ዘዴዎች በመጠቀምና ራስህን በጥንቃቄ በመፈተሽ፣ አሁን በየትኛው ደረጃ ላይ እንዳለህ በግልጽ አውቀሀል። ዛሬ በዚህ "ትልቅ ሕልም" የሚል ምዕራፍ፣ የት መሄድ እንደምትፈልግና ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ ትወስናለህ። በሚቀጥሉት ቀናት በምታጠናቸው ምዕራፎች ደግሞ፣ አሁን ካለህበት ደረጃ በመነሳት፣ እንዴት አድርገህ ወደምትፈልገው ትልቅ ሕልም መሄድ እንደምትችል ታጠናለህ።

## ትልቅ ሕልም ምንድን ነው?

ከስኬታማ ሰዎች ጎራ ሻገር ብለህ የሕይወት ሥርዓታቸውን ብትመረምር፣ ሁሉም የሚያመሳስላቸውን አንድ የጋራ ጉዳይ ታገኛለህ፤ "ሕልም" የሚባል ወሳኝ ቁልፍ። "የሕልምህ ምንነት የአንተነትህ ነገነት ነው" ትልቅ ሕልም፣ የማንነትህ መገንቢያ፣ የአኗኗርህ መፈተሻ፣ የነገ ሕይወትህን ማያ መነጽር ነው። ትልቅ ሕልም ለሕይወትህ ወሳኝ ትርጉም የሚሰጥ፣ መሆን የምትፈልገው፣ ማድረግ የምትሻው፣ ልታገኘው የምትቋምጥለት፣ ለመድረስ የምትቸኩልለት የልብህ እውነተኛ ፍላጎት ነው።

ትልቅ ሕልም በዕንቅልፍህ ለጥ ብለህ የምታየው ተራ ሕልም ሳይሆን፣ ከዕንቅልፍህ በጥዋት የሚቀሰቅስህ የስኬት ደውል እና የሕይወት ዓላማ ነው።

አዎ! ትልቅ ሕልም፣ የትም ተውሎ፣ እግር ባደረሰው ደርሶ፣ የባከነ አዕምሮ አልጋ ላይ ሲተኛ የሚታይ የማይጨበጥ የድርጊቶች ጋጋታ፣ አልያም ራስህን አልጋ ውስጥ የምታገኝበት የሌሊት ድራማ አይደለም። ትልቅ ሕልም፣ አዲስ ዓመት ሲገባ "አደርገዋለሁ" ተብሎ የሚፎከርለት፣ በማግስቱ ደግሞ የሚጠፋ ደራሽ ውሃም አይደለም። ብዙ ሰዎች አዲስ ዓመት ሲገባ፣ በዓል ሲመጣ ወይም አንድ ስልጠና ሲወስዱ ወኔያቸውን ያጠረቃቅሙና ትልቅ "ግብ" ወይም "ሕልም" ያስቀምጣሉ። ከዚያም ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ሕልማቸውን ረስተው፣ የተለመደ "ተራ" ሕይወታቸውን በድጋሚ እንደ በፊቱ መኖር ይቀጥላሉ። እንደዚህ ዐይነት ሕልም፣ በምንም አጋጣሚ፣ በማንም ሰው ሕይወት ላይ ትልቅ ለውጥ አያመጣም።

ትክክለኛውንና ትልቁን ሕልምህን ስትይዘው፣ አይደለም ከወኔህ ማግስት አሽቀንጥረህ ልትጥለው ቀርቶ፣ ለደቂቃም ቢሆን ከአዕምሮህ ማውጣት እንኳ ይከብድሀል! ትልቁ ሕልምህ ሲሳካ የምታመጣው እጅግ ድንቅ ለውጥ፣ ሕይወትህን፣ ቤተሰብህን፣ አገርህን እና ዓለምን የመቀየር ሙሉ አቅም አለው። ትልቁ ሕልምህ እንደዚህ ዐይነት ኀይል እንዲኖረው ግን በልብህ የምትወደው፣ ማሳካት የምትፈልገውና በምንም የማትደራደርበት ሕልም መሆን አለበት።

"ትልቅ ሕልም" የሚለው ሀሳብ፣ አሁን እኛ የፈጠርነው ነገር ሳይሆን፣ ከጥንት ጀምሮ፣ ራሳቸውንና ዓለምን ለመቀየር ቆራጥ ከነበሩ ድንቅና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች የተማርነው ነው። "I Have a Dream" ወይም "ሕልም አለኝ" የሚል ቃል ስትሰማ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ትዝ እንደሚልህ ርግጠኛ ነኝ። ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ በዓለማችን ላይ ትልቅ ሕልም ከነበራቸው ድንቅ ሰዎች መካከል አንዱ ሆኖ፣ በትልቅ ሕልሙ ዓለምን የቀየረ ጀግና ነው። ዶ/ር ኪንግ ስለ ሕልሙ ሲናገር፣ "አንድ ቀን አራቱ ሕፃናት ልጆቼ በቆዳቸው ቀለም ሳይሆን፣ በማንነታቸው የሚዳኙበት ቀን እንደሚመጣ ትልቅ ሕልም አለኝ!" ነበር ያለው። በወቅቱ ማርቲን ሉተር ያለመውን ሕልም ለሰዎች ሲያካፍል፣ እንደ እብድና እንደ ቅንጡ ሰው ነበር የታየው።

አንተም ይህንን ምዕራፍ በማጥናት፣ አንድ ትልቅ ሕልም ለራስህ ስታስቀምጥ፣ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ላይቀበሉህ ይችላሉ። ካለመቀበልም አልፈው፣ እንደ እብድ ሊቆጥሩህ ይችላሉ። ምናልባት አሁን ባለንበት ዘመን፣ ማርቲን ሉተር ያለመውን ሕልም ማሰብ በጣም ቀላል ሊሆን ይችላል። በዚያ ጥቁሮች ከነጮች የበታች ተደርገው በሚታዩበት ወቅት ግን "ትልቅ ሕልም አለኝ!" ብሎ የተናገረውን ሕልም መስማት፣ ቀልድ ነበር የሚመስለው። ከዚያ አሳዛኝ የጥቁሮች "ሕይወት" መሰንበቻ ላይ ሆኖ፣ ይህንን ሕልሙን ሲናገር፣ ዶ/ር ኪንግ አዕምሮውን ነካ የሚያደርገው፣ አልያም በማይሆን የቅዠት ዓለም ውስጥ ያለ እብድ የመሰላቸው፣ ብዙዎች ነበሩ።

ሉተር ትልቅ ሕልሙን ሲናገር፣ በዚያን ጊዜ የነበሩ ነጮች፣ "ዶ/ር ኪንግ፣ የማይሆን ሕልም ለምን ታልማለህ?! ከባርነት ነጻ ማውጣታችን ሳይበቃችሁ፣ ጭራሽ ከእኛ እኩል በአንድ ምግብ ቤት መብላት፣ በአንድ አውቶቡስ መጓዝ... አማራችሁ?! 'ጅብ በማያውቁት አገር ሄዶ፣ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ' ይላሉ ይህ ነው..." ብለው እንዳፌዙበት መገመት አይከብድም። ዶ/ር ኪንግ፣ ነጮቹ ከሚያፌዙበት ፌዝ ይልቅ፣ የራሱ ጥቁር ወንድሞች ይመክሩት የነበረው የስንፍና ቃል ነበር ሕልሙን የፈተነው። ጥቁሮቹ "ዶ/ር ኪንግ፣ ይህን የማይሆን የቀን ቅዠትህን ተወው! ነጮቹኮ አሁን ከባርነት ነጻ አውጥተውናል። አሁን ምን አለበት እኛ በራሳችን ምግብ ቤት ብንመገብ? በራሳችንም አውቶቡስ ብንጓዝ?!" ይሉት እንደነበር መገመት አያዳግትም። የራሱን ብቻ ሳይሆን፣ የዓለምን ሕይወት የቀየረው የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ሕልም ግን፣ አሁንም በደማቅ ብዕር በሰው ሁሉ የህሊና ገጽ ውስጥ ተጽፎ ይኖራል። ካለሙ አይቀር እንዲህ ነው!

ማርቲን ሉተር ኪንግ የማንንም ርዳታ ሳይጠብቅ፣ በትልቅ ሕልሙ ስላመነና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ስለከፈለ፣ ሕልሙን እውን በማድረግ የልጆቹን ሕይወት ብቻ ሳይሆን፣ የዓለምን ታሪክ ቀይሯል። ልክ እንዳለመውም፣ አሁን ጥቁሮችና ነጮች እኩል ሆነው፣ ጥቁሮች ነጮችን ሲመሩ አይተናል። ባራክ ኦባማ አርባ አራተኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ሆነው ለሁለት ተከታታይ የምርጫ ዘመናት ማለትም፣ ለስምንት ዓመታት፣ አገራቸውን ሲመሩ ማየት፣ በዚያ በማይመስል ጊዜ፣ ቃዠህ የተባለው የማርቲን ሉተር

ትልቅ ሕልም ውጤት ነው። ትልቅ ሕልም ማሳካት እንደሚቻል ርግጠኛ ለመሆን ግን ሩቅ መሄድ አያስፈልገንም። በአገራችን ያሉትን ባለ ትላልቅ ሕልሞች እና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል ሕልማቸው ያሳኩ ሰዎች መመልከት ራሱ በቂ ነው።

አብዮት ነበር የሕፃንነት ስሙ። ገና የሰባት ዓመት ሕፃን ልጅ እያለ ነበር እናቱ "ንጉሥ ትሆናለህ" ብላ ትልቅ ሕልም እንዲሰንቅ ያደረገችው። እሱም "አንድ ቀን ትልቁ ሕልሜ ይሳካል፤ አገሬም ላይ ንጉሥ እሆናለሁ" ብሎ በማመን፣ ራሱንና ቤተሰቡን፣አገሩን፣ አህጉሩንና ዓለምን ለመቀየር መሆን ያለበትን እየሆነ፣ መሥራት ያለበትን እየሠራ፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነትም እየከፈለ ነው። ወታደር እያለ፣ ጓደኞቹ አብሯቸው ፎቶ እንዲነሳ ሲጠይቁት፣ "አንድ ቀን ንጉሥ ስለምሆን፣ ዝም ብዬ ፎቶ አልነሳም!" ይላቸውም ነበር። ጠ/ሚ/ዶ/ር ዐቢይ አህመድ እናቱ ያለመችለትን ትልቅ ሕልም ለማሳካት መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን፣ የአገራችንን ታሪክ ቀይሯል። እ.ኤ.አ በ2019 "የሰላም ኖቤል" ተሸላሚ መሆን ችሏል። ሌሎች ትላልቅና ድንቅ የሆኑ ሕልሞችን በማለምና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈልም የአህጉራችንን ብሎም የዓለምን ታሪክ ጭምር እየቀየረ ነው።

# ትልቅ ሕልም ለምን ያስፈልጋል?

ትልቅ ሕልም በዓላማ እንድትኖር እና እንድታድግ እንዲሁም እንድትቀየር እና የተሻለ ሰው እንድትሆን የሚረዳህ ወሳኝ የሕይወት ካስማ ነው። ትልቁን ሕልማችንን በጥንቃቄ መርጠን ለማሳካት መኖር ስንጀምር፣ የምናገኛቸው ጥቅሞች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። ትልቅ ሕልም ሲኖረን ከምናገኛቸው ወሳኝ ጥቅሞች መካከል፣ የትልቅ ሕልም ዓላማ የሆኑትንአራት ዓላማዎችብቻ መርጠን፣ በዚህ ምዕራፍ እንወያይባቸዋለን።

## ፩. የትልቅ ሕልም ዋና ዓላማ እድገት ነው

የትልቅ ሕልም ዋና እና መሠረታዊ ዓላማው እድገት ነው። በርግጥ ሕልማችን ሲሳካ በሕይወታችን የምንፈልገውን ውጤትና የሕልማችንን ሽልማት እናገኛለን። የትልቅ ሕልም ዋና ዓላማ ግን እድገት እንጂ፣ የምናገኘው ሽልማት አይደለም። ለምሳሌ አንድ ሰው ወደ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ሄዶ፣ የተለያዩ ክብደት ያላቸውን ብረቶች የሚያነሳው፣ ጡንቻዎቹን መገንባት ስለሚፈልግ ነው። ከአንድ የክብደት ደረጃ ወደ ተሻለ ደረጃ (50 ኪሎ ያነሳ ከነበረ ወደ 70 ኪሎ) ሲያድግ የሚያገኘው ሽልማት፣ አድናቆት እና ተቀባይነት ደስ ቢለውም፣ በየቀኑ ብረቶቹን የሚያነሳበት ዋና ዓላማ ግን የሰውነቱና የጡንቻዎቹ ጥንካሬና እድገት ነው።

ሕይወትም እንዲሁ ነች። ለምሳሌ አንድ በሕዝብ መጓጓዣ የሚጠቀም ሰው፣ "ዛሬ ጥር 15፣ 2013 የራሴ መኪና አለኝ" የሚል ትልቅ ሕልም አለው እንበል። ይህ ሰውዬ ትልቁን ሕልሙን ሲያሳካው፣ በርግጥ መኪና ይሸለማል። የትልቅ ሕልሙ ዋና ዓላማ ግን መኪና መግዛት ሳይሆን፣ የአስተሳሰብ እና የማንነት እድገት ነው። ይህ ሰው በሕዝብ ትራንስፖርት እየተጠቀመ፣ ማንም ሳይረዳው፣ ምንም ሳይኖረው፣ "የራሴ መኪና አለኝ" ብሎ ሲያልምና ሕልሙን ለማሳካት መሥራት ያለበትን ሲሠራ፣ ማድረግ ያለበትን ሲያደርግ፣ መከፈል ያለበትንም መሥዋዕትነት ሲከፍል፣ በመጨረሻ የሚያገኘው ዋና ጥቅም፣ መኪናውን ሳይሆን፣ አዲሱን ማንነቱንና እድገቱን ነው። ይህ ሰው ከባዶ ተነስቶ፣ ራሱን መኪና መግዛት ወደሚችል ሰውነት ስለቀየረ፣ ሽልማቱ ወይም መኪናው በተለያየ ምክንያት ሊጠፋ ቢችል እንኳ አሁንም በድጋሚ ከባዶ ተነስቶ፣ አዲስ መኪና መግዛት ይችላል።

አንተም ለራስህ ትልቅ ሕልም ስትመርጥ፣ ዓላማው እንዲህ ነው መሆን ያለበት። ለራስህ ትልቅ ሕልም መርጠህ፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ስትከፍል፣ ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ቀይራለህ። አሁን ትልቁን ሕልምህን ስትመርጥ፣ እንዴት አድርገህ ልታሳካው እንደምትችል

ላታውቅ ትችላለህ። ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልጉህ ገንዘብ፣ ሰው፣ ዕውቀት፣ ልምድና ሌሎች ነገሮች ላይኖሩህም ይችላሉ። ነገር ግን ይህንን ሕልም እንደምታሳካው በማመን፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ስትከፍል፣ ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ሰውነት ትቀይራለህ። ራስህን፣ ሕልሙን ለማሳካት የሚያስፈልጉት ገንዘብ፣ ሰው፣ ዕውቀት፣ ልምድ እና ሌሎች ነገሮች ሳይኖሩት፣ ሕልሙን ማሳካት ወደሚችለው ሰውነት ትቀይራለህ።

ትልቅ ሕልም የምታስቀምጠው፣ ሕልምህን ለማሳካት በምታደርገው ጉዞ የምታገኛቸውን ዳረጎቶች ወይም ቁሳቁሶች ለመቃረም አይደለም። ዳረጎቶቹና ቁሳቁሶቹ ሕልምህን በማሳካት የምታገኛቸው ተጨማሪ ሽልማቶች እንጂ የሕይወትህ ዓላማዎች አይደሉም። ትልቅ ሕልም የምታስቀምጥበት ዋና ዓላማ፣ ለማደግና ራስህን የተሻለ ሰው ለማድረግ ነው። ጥያቄው፣ "አንተን የሚያሳድግህ እና የተሻለ ሰው እንድትሆን የሚያደርግህ ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው?" የሚለው ነው።

## ፱. ትልቅ ሕልም የሕይወት ጉዞህን አቅጣጫ ይሰጥዋል

ትልቅ ሕልም ያለው ሰው፣ አንዳንዴ ቢከብደውም፣ በማለዳ ተነስቶ፣ ወደ ሕልሙና ሕልሙን ወደሚያሳካበት ቦታ ነው የሚራመደው። ትልቅ ሕልም የሌለው ሰው ግን፣ ማሳካት የሚፈልገው ትልቅ ዓላማ ስለሌለው፣ በጥዋት ተነስቶ፣ ወደተገኘውና ቀለል ወዳለው መንገድ ነው የሚሄደው። አንድ የት እንደሚሄድ ያልወሰነ መንገደኛ፣ ምን ያክል አድካሚና አሰልቺ ጉዞ ሊጓዝ እንደሚችል መገመት አይከብድም! መድረሻውን የማያውቅ ሰው፣ ወዴት እንደሚሄድ አይታወቅም። ለምሳሌ አንድ የሚሄድበትን ቦታ ያልወሰነ ሰው፣ "ወደ ምስራቅ ነው የምሄደው" ብሎ ቢነሳ፣ መድረሻ ቦታውን እስካልወሰነ ድረስ፣ ምስራቅ ምስራቁን ሲሄድ ዓለምን ዞሮ፣ ወደነበረበት ቦታ ሊመለስ ይችላል። ምናልባትም የዓለምን ክብነት የሚነግረን ሌላኛው ፈርዲናንድ ማጄላን ሊሆን ይችላል! ማስታወስ ያለብህ ዋና ቁም ነገር፣ ትልቅ ሕልም ማለዳ ተነስተህ ወዴትና እንዴት መሄድ እንዳለብህ፣ ለሕይወት ጉዞህ አቅጣጫን የሚሰጥ መሆኑን ነው።

አንድ ሰው የሚሄድበትን አቅጣጫ አስቀድሞ ከወሰነ፣ ምንም ዐይነት ዕንቅፋት እና ፈተና ቢያጋጥመው እንኳ፣ መድረስ ያለበት ቦታ ላይ እንደ ምንም ብሎ ይደርሳል። ለምሳሌ ለሁሉም የዚህ መጽሐፍ አንባቢያን፣ "የአንድ ሚልየን ብር ሽልማት ስላዘጋጀን፣ ወደ አዲስ አበባ ከተማ፣ ሃያ ሁለት አካባቢ፣ ባታ ሕንጻ ውስጥ፣ አንደኛ ፎቅ፣ የድሪምስ ቢሮ ቀድመው ለሚደርሱ አስር አንባቢያን፣ ሽልማቱን እናበረክታለን" ብለን ብናስተዋውቅ፣ ከተሸላሚዎቹ አንዱ ለመሆንና ወደ ድሪምስ ቢሮ ለመድረስ ወዲያውኑ ሩጫህን አትጀምርም? ስለ ሽልማቱ እንዳነበብክ፣ "የእናቴ ቀሚስ ጠለፈኝ" የሚል ምንም ዐይነት ሰበብ ሳታሳብብ፣ አንድ ሚልየን ብር ከሚያሸንፉት አስር ሰዎች መካከል አንዱ ለመሆን፣ መጋለብ አትጀምርም?

መኪና ካለህ በመኪናህ፣ ከሌለህ ደግሞ መኪና ተኮናትረህ፣ ምንም ዐይነት የሚያጋጥምህን መሰናክል አሸንፈህ፣ ድሪምስ ቢሮ ትደርሳለህ። መኪናህ ቢበላሽ፣ ተስፋ ሳትቆርጥ ሌላ መኪና ይዘህ፣ በባቡር መሳፈር ካለብህ በባቡር ተሳፍረህ፣ የማሸነፍ ሩጫህን ትቀጥላለህ። መሮጥ ካለብህ ትሮጣለህ፤ መብረር ካለብህ ትበራለህ፤ መዳኸም ካለብህ ትድኻለህ። ይህንን ሁሉ መሥዋዕትነት የምትከፍለው ግን፣ የምትሄድበት ትልቅ ዓላማ ስላለህ ነው፤ አንድ ሚልየን ብር የማግኘት ዓላማ! በግልጽ የሚታይ ትልቅ ሕልም ወይም ዓላማ ከሌለህ ግን፣ ከቤትህ ተነስተህ ሰፈርህ ወዳለ ሱቅ ለመሄድ እንኳ ወኔ ልታጣ ወይም ሊደብርህ ይችላል። አሁን ትልቅ ሕልም አስቀምጠህ፣ ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት የምትከፍል ከሆነ፣ ከማንም ምንም ሳትጠብቅ፣ የሚያስፈልጉህን ገንዘብና ሌሎች ነገሮች ማግኘት ትችላለህ። በርግጥ በስኬት ጉዞህ ያላሰብካቸው የተለያዩ ፈተናዎችና ዕንቅፋቶች ሊያጋጥሙህ ይችላሉ። ነገር ግን ትልቅ ሕልም ሲኖርህና ሕልምህን ለማሳካት ስትወስን፣ መሆን ያለብህን ትሆናለህ፤ ማድረግ ያለብህን ታደርጋለህ፤ መከፈል ያለብህን መሥዋዕትነትም ትከፍላለህ። ለትልቅ ሕልም ይኖራል፤ ?ምታልም።

## ፫. ትልቅ ሕልም ድንቅ አቅምህን እንድትጠቀምበት ይረዳሀል

ትልቅ ሕልም በውስጣችን ያለውን ጥልቅና ዕምቅ አቅም እንድንጠቀምበት በር የሚከፍትልን ልዩ ቁልፍ ነው። ትልቅ ሕልም የሌለው ሰው፣ ጥልቅና ዕምቅ አቅሙን ሳይጠቀምበት ተራ የሆነ ሕይወት እየኖረ ነው የሚሞተው። ተራ ሰው አንድ ለየት ያለ አጋጣሚ ወይም ዝግጅት ሲያገኝ፣ ልክ እንደ ድንቅ ሰው፣ ተራ ሰው መሆኑን ትቶ፣ ድንቅና አስገራሚ ሥራዎችን መሥራት ይጀምራል። ማንም ሰው አንድ ትልቅ ነገር ማሳካት ሲፈልግ፣ በውስጡ ያለውን ድንቅ አቅም በመጠቀም፣ ተዓምር መሥራት ይጀምራል።

የሰው ልጅ ድንቅ አቅሙን የሚጠቀመው፣ ብዙውን ጊዜ፣ እንደ ሰርግ ያለ ልዩ ዝግጅት ሲኖርበት ነው። የሰው ልጅ የራሱ፣ የቤተሰቡ፣ የጓደኞቹ ወይም የወዳጆቹ ሰርግ ሲኖርበት፣ ወደ ድንቅ ሰውነት ይቀየራል። በሰርጉ ዕለት፣ የሚታደሙትን ሰዎችም ሆነ ሰርገኞቹን ለማስደሰት እና ለማኩራት ስለሚፈልግ፣ ሰርጉን ለማሳመር፣ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል። በተለይ የሰርጉ የመጨረሻ ሳምንት ሲደርስ፣ ሰበበኛ መሆኑን ትቶ፣ ወደ ልዩና ድንቅ ሰውነት ይቀየራል። በሰርጉ የመጨረሻ ሳምንት በሥነ-ሥርዓት ለመብላት፣ ለመጠጣት፣ ለመተኛት፣ ለመዝናናት ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማድረግ ጊዜ አያገኝም። ሳምንቱን ሙሉ በሥነ-ሥርዓት ሳይመገብና ሳይተኛ ቢያሳልፍም እንኳ፣ የሰርጉ ዕለት ሲደርስ፣ መሥራት ያለበትን ሥራ በድንቅ መንገድ ይሠራል። ሰርጉ ካለፈ በኋላ፣ በሥነ-ሥርዓት ይበላል፤ ይጠጣል፤ ይተኛል፤ ቴሌቪዥን ላይ ቁጭ ብሎ ያመሻል። ማልዶ፣ ሥራ ቦታ መሄድ ሲኖርበት ግን "ደከሞኛል፤ ደብሮኛል፤ አሞኛል፤ ዕረፍት ያስፈልገኛል፤..." ብሎ ያሳብባል። "የሰው ልጅ ሲፈልግ ተዓምረኛ፣ ካልፈለገ ደግሞ ሰበበኛ ነው!"

ድንቅ እንድትሆን፣ የቤተሰብህ ሰርግ እስኪመጣ መጠበቅ አያስፈልግህም። ድንቅ ለመሆን፣ የምትፈልገውን ትልቅ ሕልም በማስቀመጥ፣ ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት መቀየር ብቻ ነው የሚያስፈልግህ። በሕይወትህ ትልቅ ሕልም አስቀምጠህ፣ ሕልምህን ለማሳካት መሮጥ ስትጀምር፣ በውስጥህ ተደብቆ የነበረውን ጥልቅና ዕምቅ አቅም መጠቀም ትጀምራለህ። ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ስትቀይር፣ ሰበበኛው ከሕይወትህ ይባረራል። ነገር ግን ሰበበኛው ከሕይወትህ ከመባረሩ በፊት፣ አንድ ምክር ሊመክርህ ይችላል። ሰበበኛው "ሕይወትህን ለመቀየር እኮ መቀየር ያለብህ አንተ ነህ። ነገር ግን ችግሩ እሱ አይደለም። ችግሩ፣ ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልግህን ገንዘብ ማግኘት አለመቻልህ ነው" ብሎ ሊያሳንፍህ ይሞክራል። ሰበበኛው እንዲህ ብሎ ሊያሳንፍህ እንዳይሞክር አንድ ምሳሌ ልጨምርልህ።

ለምሳሌ አንድ ወዳጅህ፣ "በዚህ ሳምንት አስር ሺህ ብር ልታገኝልኝ ትችላለህ?" ብሎ ቢጠይቅህ፣ "ይህን ያክል ገንዘብ ከየት ይመጣል ብለህ ነው? አሁን ካለው ኢኮኖሚ አንጻር እኮ አስር ሺህ ብር ማግኘት ከባድ ነው" ብለህ ምንም መፍትሄ ሳትሰጠው ትችላለህ። ነገር ግን አንድ ሰው፣ ወዳጅህን እንደ መያዣ ቢይዝብህና "በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መቶ ሺህ ብር ካላመጣህ፣ ወዳጅህን ድጋሚ አታገኘውም!" ብሎ ቢያስፈራራህ፣ መቶ ሺህ ብሩን ከየትም ብለህ ታመጣዋለህ። እንዴት ነው በመጀመሪያ ለወዳጅህ አስር ሺህ ብር ማግኘት ያልቻልከ ሰውዬ፣ አሁን ጠላት ሲመጣብህ መቶ ሺህ ብር ልታገኝ የቻልከው? ምክንያቱም አሁን ትልቅ ዓላማ ስላለህ ነው። የምትወደውን ሰው ለማዳን መከፈል ያለብትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ የሚያስፈልገውን መቶ ሺህ ብር በሳምንት ጊዜ ውስጥ ታገኛለህ። ራስህን በሳምንት መቶ ሺህ ብር ማግኘት ወደሚችል ሰውነትም ትቀይራለህ።

ራስህን በሳምንት መቶ ሺህ ብር ማግኘት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ለመቀየር ግን፣ ወዳጆችህ ችግር ውስጥ መግባት የለባቸውም። ራስህን በሳምንት መቶ ሺህ ብር ማግኘት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ለመቀየር፣ በሳምንት መቶ ሺህ ብር የሚያስገኝ ትልቅ ሕልም ብቻ ነው የሚያስፈልግህ። ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ስትቀይር፣ ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልግህን ገንዘብ፣ ቦታ፣ ጊዜ፣ ሰው፣ አቅም፣ ችሎታ፣ ትምህርት ወይም ሌላ ነገር ለማግኘት አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ሁሉ ትከፍላለህ።

## ፬. ትልቅ ሕልም ዓለምህን ይቀይረዋል

አንድ ተግባር ላሠራህ ስለሆነ፣ እባክህ የማሠራህን ልምምድ ለመሥራት ተዘጋጅ። በዚህ ተግባር ውስጥ "አቁምና ዐይንህን ጨፍነህ... አስብ" የሚል ትዕዛዝ እስኪታገኝ ድረስ፣ ማንበብህን ቀጥል። "አቁምና ዐይንህን ጨፍነህ... አስብ" የሚለውን ጽሑፍ እንዳገኘህ፣ "ጨፍን" ከመባልህ በፊት የሚሰጥህን ትዕዛዝ ለመሥራት ሞክር። እባክህ በዚህ ልምምድ ውስጥ ያሉትን አስር ርምጃዎች፣ እያንዳንዳቸውን፣ በትኩረት ሥራቸው። (አሁን ቀጥሎ የቀረቡትን ፲ ርምጃዎች ከመውሰድህ በፊት፣ እባክህ ከዚህ በላይ ያነበብከውን መመሪያ ደግመህ አንብበው)

፩. በመጀመሪያ በአካባቢህ ያሉትን ነገሮች በአትኩሮት ከግራ ወደ ቀኝ በማማተር ቃኝ።
፪. በመቀጠል በአካባቢህ ያሉ "ቀይ ቀለም" ያላቸውን ነገሮች ፈልግ።
፫. ከዚያም የተመለከትካቸውን ቀይ ነገሮች አንድ በአንድ ቁጠራቸው።
፬. በአካባቢህ ምን ያክል ቀይ ቀለም ያላቸውን ነገሮች ቆጠርክ?______________
፭. አሁን በአዕምሮህ ስለነዚህ ቀይ ቀለም ያላቸው ነገሮች ብቻ አስብ። ስለነዚህ ቀይ ቀለም ያላቸው ነገሮች ስታስብ ግን፣ ዐይንህን ሙሉ በሙሉ በዚህ መጽሐፍ ላይ ብቻ አሳርፍ። ስለ ቀዮቹ ነገሮች ስታስብ፣ ዐይንህን ከዚህ መጽሐፍ ላይ እንዳትነቅል።
፮. በመቀጠል ዐይንህን እዚህ መጽሐፍ ላይ እንዳደረግክ እና ዐይንህን ከዚህ መጽሐፍ ላይ ሳትነቅል፣ በአካባቢህ "አረንጓዴ ቀለም" ያላቸውን ነገሮች በሀሳብህ ፈልግ። አረንጓዴ ቀለም ያላቸውን ነገሮች ለመቁጠር ስትሞክር ግን፣ ዐይንህን ከመጽሐፉ ላይ ሳትነቅል መሆን አለበት።
፯. ትዕዛዝ፡ አሁን አቁምና ዐይንህን ጨፍነህ ስንት አረንጓዴ ነገሮች እንዳሉ አስብ!
   - ስንት አረንጓዴ ነገሮች እንዳሉ ዐይንህን ጨፍነህ ካሰብክ በኋላ ዐይንህን ገልጠህ ቀጣዮቹን ጥያቄዎች መልስ።
፰. ዐይንህ ተጨፍኖ እያለ ስንት አረንጓዴ ቀለም ያላቸውን ነገሮች ቆጠርክ?______________
፱. አሁን ዐይንህን ስትገልጥስ ምን ያክል ተጨማሪ አረንጓዴ ቀለም ያላቸውን ነገሮች አየህ?________
፲. ዐይንህን ጨፍነህ፣ ያላየሀቸውን ስንት ተጨማሪ አረንጓዴ ቀለም ያላቸውን ነገሮች፣ ዐይንህን ከገለጥክ በኋላ አየህ?______________

እነዚህ አሁን ያየሀቸው አረንጓዴ ቀለም ያላቸው ነገሮች፣ ቀዮቹን ስትፈልግም ነበሩ። ነገር ግን አላየሀቸውም። ቀይ ቀለም ያላቸውን ነገሮች እየፈለግክ፣ አረንጓዴ ቀለም ያላቸውን ነገሮች ማየት ይከብድሀል። ይህ ማለት ግን፣ ቀዩን ቀለም በምታይበት ሰዓት አረንጓዴ ቀለም የለም ማለት አይደለም። ቀይ ቀለም ያላቸው ነገሮች፣ በሕይወታችን የሚያጋጥሙንን የማንፈልጋቸውን ችግሮች የሚወክሉ ሲሆን፣ አረንጓዴ ቀለም ያላቸው ነገሮች ደግሞ፣ በሕይወታችን የምንፈልጋቸውን ነገሮች የሚወክሉ ናቸው።

በሕይወታችን ውስጥ ስላሉ የማንፈልጋቸው "ቀይ" ችግሮችና መከራዎች ብቻ የምናስብ ከሆነ፣ የሚታየን ነገር ሁሉ ችግር እና መከራ ብቻ ነው። ስለነዚህ ችግሮች እና መከራዎች በተደጋጋሚ ስናስብና ስናማርር ደግሞ፣ "መከራ" የማሰብ ውጤት የሆነውን "የባሰ መከራ ነው" የምናጭደው። ይህ ማለት ግን በአካባቢያችን የምንፈልጋቸው "አረንጓዴ" መፍትሄዎች እና አጋጣሚዎች የሉም ማለት አይደለም። ስለ ቀይ ችግሮቻችን እና መከራዎቻችን እያማረርን፣ አረንጓዴ መፍትሄዎች እና አጋጣሚዎች አይታዩንም። አሁን ቀይ የሆኑትን ነገሮች እና ችግሮች፣ ከአዕምሯችን ዘግተን አረንጓዴ ነገሮችን ብቻ በትኩረት መፈለግ ስንጀምር፣ ትልቁን ሕልማችንን የሚያሳኩ የተለያዩ ድንቅ መፍትሄዎችን እና አረንጓዴ አጋጣሚዎችን ማግኘት እንጀምራለን።ለምሳሌ አንድ የራሱን ሥራ የመጀመር ትልቅ ሕልም ያለው፣ ነገር ግን ሁልጊዜ፣ "በአገራችን ላይ የራስን ሥራ መጀመር በጣም ከባድ ነው!" ብሎ የሚያስብ ሰው እንውሰድ። ይህ ሰውዬ በአገሩ ላይ ትልቅ ሥራ ያልሠራው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የራስን ሥራ መሥራት ስለማይቻል ወይም

ሰውዬው የሚያስፈልገውን ነገር ማግኘት ስለማይችል አይደለም። ይህ ሰው ትልቅ ሕልሙን ያላሳካው፣ አገሪቷ፣ እንደ እሱ ዐይነት ድንቅ ሕልም የሚሰንቁ ዜጎቿን የምትበላ ድመት ስለሆነችም አይደለም። ይልቁንም ሕልሙን እንዳያሳካ ስለሚከለክሉት ቀይ ፈተናዎች እና ችግሮች በተደጋጋሚ ስለሚያማርር ነው። ሕልሙን ያላሳካበት ምክንያት፣ ሁሌም ቢሆን "እዚህ አገር እኮ ሥራ የለም! በዚህ ሰዓት ሥራ መሥራት የማይታሰብ ነው! የሚሠራ ሰው የታለና?! የሠራ'ማ መቼ ያልፍለታል?! በዚያ ላይ ልሥራ ቢባል እንኳ፣ ለሥራ የሚሆን ብር በቀላሉ አይገኝም!" ብሎ ስለሚያማርር እና ሕልሙን ማሳካት የማይችልባቸውን ቀይ ነገሮች ብቻ በተደጋጋሚ ስለሚያስብ ነው።

ነገር ግን ይህ ሰውዬ "እኔ በአገሬ ትልቅ ሥራ በመሥራት፣ ሕይወቴን፣ ቤተሰቤን፣ አገሬንና ዓለምን የመቀየር ትልቅ ሕልም አለኝ!" ብሎ ቢወስን፣ ሁሉም ነገር ይቀየራል። ከዚያም አረንጓዴ ነገሮቹን ማየት ይጀምራል። በጥዋት ተነስቶ የሚያስበው፣ ሕልሙንና ሕልሙን የሚያሳካበትን መንገድ ብቻ ከሆነ፣ ሙሉ ቀን የሚታዩት፣ የራሱን ሥራ የሚጀምርበት እና ሕልሙን የሚያሳካበት መንገዶች ብቻ ናቸው የሚሆኑት። በዚህ ድንቅ አስተሳሰቡ ሲንቀሳቀስ፣ ሕልሙን እንዲያሳካ ሊረዱት የሚችሉ ሰዎችን ማግኘት ይጀምራል። በዚህም አረንጓዴ የሆኑ ሀሳቦችን፣ ሰዎችን፣ ቦታዎችንና አጋጣሚዎችን እያገኘ፣ ትልቁን ሕልሙን እውን በማድረግ፣ የራሱንና የቤተሰቡን ሕይወት ይቀይራል።

ራስህን ስትቀይር፣ ሁሉም ነገር ይቀየራል። ራስህን፣ ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ሰውነት ስትቀይር፣ አገርህ ላይም ሆነ በዓለም ዙሪያ፣ የሚያስፈልጉህና የምትፈልጋቸው አረንጓዴ ነገሮች መንገድህ ላይ ይጠብቁሀል። አረንጓዴ ማየት ከፈለግክ፣ አረንጓዴ ታያለህ፤ አረንጓዴውን ማየት ካልፈለግክ ደግሞ፣ በጭራሽ አታየውም። የነገሮች መሳካትና የምትፈልገውን ዐይነት ቅርጽ መያዝ ያለው፣ "ምን ለማየት ፈለግክ?" የሚለው ጥያቄ ውስጥ ባለው መልስህ ተቋጥሮ ነው። አንተ ማለት፣ ለማየት የፈለግከውን የምታይ፣ ያየኸውን ደግሞ የምትወርስ ፍጡር ነህ። ይህ የተፈጥሮ ሂደት ነው።

# የሕልም ዐይነቶች

በዚህ ክፍል፣ የሰው ልጆች ስለሚያስቀምጧቸው የተለያዩ የሕልም ዐይነቶች እንመለከታለን፤ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ በተለያየ የትምህርት እና ማኅበራዊ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ስለሚያስቀምጠው ሕልም። ብዙ ሰው፣ "ትልቅ ነው" ብሎ የሚያስበውን ሕልም በሕይወቱ ለማሳካት ዕቅድ ይይዛል። የሚያሳኩትና ሕልማቸውን ኖረው የሚያልፉት ሰዎች ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። የአብዛኛው ሰው ሕልም የማይሳካበት ምክንያት፣ ገና ከጅምሩ፣ ትክክለኛ የሆነ ሕልም ስለማይመርጥ ነው።

የሰው ልጅ ትልቅ ሕልሙን በማሳካት ሕይወቱን የማይቀይርበት ሌላው ምክንያት፣ የሚፈልገውን ትልቅ ሕልም አስቀምጦ፣ ያንን ትልቅ ሕልም ለማሳካት ስለሚከብደው ሳይሆን፣ ትናንሽ ሕልሞችን አስቀምጦ ስለሚሳካለት ነው። የስኬት ወሳኝ ቁልፍ፣ አስቀድሞ፣ ትክክለኛ ትልቅ ሕልምን በጥንቃቄ መምረጥ ነው። ይህንን የስኬት ቁልፍ ከልጅነታችን ጀምሮ ብናውቀው ኖሮ፣ ሕይወታችን እጅግ በጣም ቀላል ይሆን ነበር። ነገር ግን ቤተሰቦቻችንና ትምህርት ቤታችን ይህን ወሳኝ ምስጢር አላስተማሩንም። ምክንያቱም እነሱ ራሳቸው ይህን የስኬት ቁልፍ ያስተማራቸው ሌላ ሰው ባለመኖሩ ነው።

በትክክለኛ አቅጣጫ መጓዝ እና በስኬት የተሞላ ሕይወት መኖር የምትፈልግ ከሆነ፣ ከዚህ በታች የተገለጹትን አራት የሕልም ዐይነቶች በጥንቃቄ መርምራቸው። ከነዚህ አራት የሕልም ዐይነቶች መካከል አንዱ ሕይወትህን መቀየር የሚችል በመሆኑ፣ እንዴት አድርገህ ትክክለኛ እና ድንቅ የሆነ ትልቅ ሕልም መምረጥ እንደምትችል በጥንቃቄ መርምር። ከዚህ ቀጥሎ አራተኛ የሕልም ዐይነት ከሆነው "የፍራቻ ሕልም" በመነሳት ጥናታችንን እንጀምራለን።

## ፬. የፍራቻ ሕልም

አራተኛው የሕልም ዐይነት የፍራቻ የሕልም ዐይነት ነው። የፍራቻ የሕልም ዐይነት፣ "እንዳልወድቅ" ብለህ ከመፍራትህ የተነሳ የምታስቀምጠው የሕልም ዐይነት ነው። የፍራቻ ሕልም፣ ሆን ብለህ መርጠህ ለሕይወትህ የምታስቀምጠው ዐይነት ሕልም አይደለም። የፍራቻ ሕልም፣ ለሕይወትህ ትክክለኛውን ሕልም በተንቃቄ ባለመምረጥህ፣ ሌሎች ሰዎች ወይም የራስህ ሰበበኛ የሚያስቀምጡልህ የሕልም ዐይነት ነው። ሕልምህን ለማሳካት በራስ መተማመን ከሌለህና፣ መውደቅን ከመፍራትህ የተነሳ የምታስቀምጠው ሕልም ካለህ፣ ሕልምህ "የፍራቻ ሕልም" ይባላል።

ከባድ የጭነት መኪና ገዝቶ የሚሠራ አንድ የማውቀው ሰው ነበረ። አንድ ቀን መኪናው አደጋ አጋጠመውና በጣም ብዙ ብር ከሰረ። በአደጋው ምክንያት በጣም ብዙ ብር ስለከሰረም ተስፋ ቆረጠ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ "ሕልምህ ምንድን ነው?" ብዬ ስጠይቀው፣ "ኧረ ተወኝ ዳዊት! እኔ ሰላም እንጂ ትልቅ ሕልም አያስፈልገኝም!" ብሎ መለሰልኝ። ለራሳችን የፍራቻ ሕልም ማስቀመጥ በጣም ቀላል እና ምንም ሀሳብ የማያስፈልገው ነው። ብዙ ሰዎች አንድ ትልቅ ሕልም ለማሳካት ሞክረው ካልተሳካላቸው፣ ተስፋ በመቁረጥ አልያም በድጋሚ ለመሞከር በመፍራት፣ የፍራቻ ሕልምን አማራጫቸው ሲያደርጉ ይታያሉ። በዚህ የሕልም ምድብ ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ ጥዋት ተነስተው ወደ ድንቅ ሕልማቸው ሳይሆን እግራቸው ወደመራቸው ነው የሚያቀኑት። ብዙ ሰዎች የዚህን ዐይነት ሕልም የሚይዙት፣ የተሻለ አማራጭ እንዳላቸው ስለማያውቁ ነው። ታዲያ በፍራቻ ሕልም እየኖሩ፣ ስኬታማ የሆነ ኑሮን መኖር በጣም ከባድ ነው። የአብዛኛዎቹ ትልቅ ሕልም የሌላቸው ሰዎች ምድብ፣ የፍራቻ ሕልም ነው።

አንተስ ትላልቅ ሕልሞችን ለማሳካት ሞክረህ፣ ስላልተሳካልህ፣ ተስፋ ቆርጠህ በፍራቻ ሕልም ውስጥ እየኖርክ ነው? መልስህ "አዎ" የሚል ከሆነና የፍራቻ ሕልም ውስጥ እየኖርክ ከሆነ፣ ትንሽ ጊዜ ወስደህ ሕይወትህን እና አኗኗርህን መፈተሽ ግድ ይልሃል።

## ፭. የዕውቀት ሕልም

ይህ የሕልም ዐይነት፣ አሳክተኸው የምታውቀው፣ ወይም እንዴት አድርገህ እንደምታሳካው የምታውቀው እና በድጋሚ ለማሳካት የምታስቀምጠው የሕልም ዐይነት ነው። የዕውቀት ሕልም ከፍራቻ ሳይሆን ከዕውቀት ተነስተህ የምታስቀምጠው ስለሆነ፣ ከፍራቻ ሕልም የተሻለ ነው። ነገር ግን የዕውቀት ሕልም ከዚህ በፊት አሳክተኸው የምታውቀው ዐይነት ሕልም ስለሆነ፣ በድጋሚ ብታሳካውም በሕይወትህ ላይ ያን ያክል ትልቅ ለውጥ አያመጣልህም። ሕልም የብቃት ድግግሞሽ ሳይሆን፣ የአዳዲስ ነገሮች ፈጠራ ነው። የትልቅ ሕልም ዋና አስፈላጊነት፣ የተሻለ እድገት ለማግኘት እንጂ፣ ባሉበት ለመዳከር አይደለም። አሳክተኸው የምታውቀውን ሕልም ደግመህ ለማሳካት ካለምክ፣ ሕልምህ የዕውቀት ሕልም ነው። የዕውቀት ሕልም በማስቀመጥ ደግሞ ሕይወትህ ላይ ትልቅ እድገት አታገኝም።

ለምሳሌ ከአንድ ዓመት በፊት አንድ ጥሩ፣ አዲስ ተንቀሳቃሽ ስልክ ገዝተሀል እንበል። አሁን ሌላ የሚያምር አዲስ ተንቀሳቃሽ ስልክ ገበያ ላይ አይተህ፣ "ይህንን አዲስ ተንቀሳቃሽ ስልክ የመግዛት ትልቅ ሕልም አለኝ!" ብለህ ብታልም ይህ ያለምከው ሕልም የዕውቀት ሕልም ይባላል። አዲስ ተንቀሳቃሽ ስልክ መግዛትህ በራሱ ምንም ስህተት የለውም። ነገር ግን "ትልቁ ሕልምህ" ስልክ መግዛት ስለሆነ፣ ምንም የሚያስደንቅ ነገር የለውም። ምክንያቱም አዲስ ስልክ እንዴት እንደሚገዛ፣ የሚሰጠውም ስሜት ምን ዐይነት ሊሆን እንደሚችል፣ ከዛሬ አንድ ዓመት በፊት፣ አሁን ያረጀበትን የዚያን ጊዜ አዲስ ስልክ ስትገዛ ታውቀዋለህ! ሕልም የሚያስፈልግህ ለማደግ እንጂ ተመሳሳይ ነገሮችን ደጋግመህ በማድረግ ለውጥ የሌለው ሕይወት እንድትኖር አይደለም።

አብዛኛው "ትልቅ ሕልም አለኝ!" የሚል ሰው፣ የዕውቀት ሕልም ያለው ነው። አንተም አሁን ያለህን ሕልም አስቀድመህ አሳከተኸው የምታውቅ ከሆነ፣ በሕይወትህ ላይ ምንም እድገት አያመጣልህም። ትልቁ ሕልምህ የዕውቀት ሕልም እንዳይሆን፣ ጊዜ ወስደህ ራስህን መፈተሽ ያስፈልግሃል።

## ፪. የዕቅድ ሕልም

የዕቅድ ሕልም በአብዛኛው ጥሩ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች እና ድርጅቶች የሚጠቀሙበት የሕልም ዐይነት ነው። በዓለማችን ላይ ታሪክ የሚሰሩ እና ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ባለ ራዕዮች የሚጠቀሙበት ዐይነት ሕልም ግን አይደለም።

የዕቅድ ሕልም፣ ቁጭ ብለህ... "እንደዚህ ካደረግኩ፣ ይህንን ነገር ከቀየርኩ፣ እከሌ ከረዳኝ፣ እከሊት አብራኝ ከሠራች ወይም አንድ ነገር ከተቀየረ፣ ሕልሜን አሳካለሁ" ብለህ የምታቅደው ሕልም ነው። የዕቅድ ሕልም፣ ከፍራቻና ከዕውቀት ሕልም በጣም የተሻለ ነው፤ በሕይወትህ ላይም ለውጥ እንድታመጣ ሊረዳህ ይችላል። ይሁን እንጂ የዕቅድ ሕልም እንደ ትልቅ ሕልም አይቆጠርም። የዕቅድ ሕልም፣ ትክክለኛው ትልቅ ሕልምህ ሊሰጥህ የሚችለውን ውጤት እና እድገት አይሰጥህም። በርግጥ የዕቅድ ሕልም ጥሩ የሕልም ዐይነት ስለሆነ፣ ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሱ ብዙ ሰዎች ይጠቀሙበታል። የዕቅድ ሕልም ውሱንነት ግን፣ "ፓራዳይምህን" ወይም ሰበበኛውን የማሸነፍ አቅም አለመኖሩ ነው።

ፓራዳይም ማለት ከልጅነታችን ጀምሮ በአዕምሯችን የተገነባ የልማዶች እና የአስተሳሰብ ድምር ሆኖ፣ ማንኛውንም የሕይወታችንን እንቅስቃሴ እና ውጤት የሚቆጣጠር ፕሮግራም ነው። በመሆኑም ፓራዳይማችን ካልተቀየረ፣ የምናገኘው ውጤትም ሆነ ሕይወታችን አይቀየሩም። የብዙ ሰው ችግርና ውድቀት መነሻም፣ ስለ ፓራዳይም አሠራርና ስውር ኀይል አለመረዳቱ ነው። ፓራዳይም እንዴት እንደሚሠራ በትክክል ስትረዳ፣ ሕይወትህን እንዴት መቀየር እንዳለብህ መረዳት ትጀምራለህ። ፓራዳይምህ ሲቀየር ደግሞ ሕይወትህ ይቀየራል። (ነገ በምናጠናው ምዕራፍ፣ ፓራዳይም ምን እንደሆነ እና እንዴት መቀየር እንደሚቻል እንመለከታለን)

አስቀድሜ እንደገለጽኩልህ፣ የዕቅድ ሕልም ከፍራቻ እና ከዕውቀት ሕልሞች በብዙ መንገድ የተሻለ ቢሆንም፣ ፓራዳይምን ስለማያሸንፍ፣ ሕልሙ በሕይወታችን ትልቅ ለውጥ አያመጣልንም። ለምሳሌ ብዙ ሰዎች አዲስ ዓመት ሲገባ ሕይወታቸውን እና ሥራቸውን መቀየር ስለሚፈልጉ፣ የዕቅድ ሕልም ያስቀምጣሉ። ስለሚያልሙት ሕልም ሲያስቡም "ከአዲሱ ዓመት ጀምሮ፣ እንዲህ አደርጋለሁ፤ እንዲያ እቀይራለሁ፤ ይሄንን አሻሽላለሁ፤ የተሻለ፣ ጠንካራ እና ጎበዝ ሰው እሆናለሁ፤..." ብለው የዕቅድ ሕልማቸውን ያስቀምጣሉ።

ከዚያም አዲሱ ዓመት ሲመጣ፣ እንዳቀዱት፣ ለተወሰኑ ቀናት ወይም ሳምንታት የዕቅድ ሕልማቸውን ለማሳካት ይሠራሉ። ከቀናትና ሳምንታት በኋላ ግን ፓራዳይማቸው ያሸንፋቸውና ወደ ድሮ አኗኗራቸው ይመለሳሉ። ከአንድ ወር በኋላም፣ ሲፎክሩበት የነበረውን "ትልቅ ሕልም" ሙሉ በሙሉ ይረሱና፣ ተራ ሕይወታቸውን በማማረር መኖሩን ይያያዙታል።

በሚቀጥለው ዓመትም በድጋሚ በሕይወታቸው ውስጥ ለውጥ ለማምጣት በመፈለግ፣ የተሻለ የዕቅድ ሕልም ያስቀምጡና የተወሰነ ለውጥ ያመጣሉ። ለተወሰነ ጊዜም ከለውጡ ጋር ይቆያሉ። የተወሰኑ ቀናት ካለፉ በኋላ ግን፣ ፓራዳይማቸው ሕልማቸውን ያሸንፈዋል፤ በዚህም ሕይወታቸው ወደነበረበት ይመለሳል። ሕልም የሚባል ነገርም መረሳት ይጀምራል። ብዙ ሰዎች ሕልማቸው አልሳካ ያላቸው ሲመስላቸው ይቀብሩታል፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ይረሱታል።

የዕቅድ ሕልም አስቀምጠው፣ ለተወሰነ ጊዜ ሕልማቸውን ለማሳካት ከሞከሩ ሰዎች መካከል፣ "ሕልምህ ምንድን ነው?" ብለህ ብትጠይቀው፣ "ምን ማለትህ ነው?" ብሎ ሊመልስልህ ይችላል። በመቀጠልም "ትልቅ ሕልም የሚባል ነገር ለኔ አይሠራም፤ ስንቴ መሰለህ ሕልም፣ ሕልም እያልኩ የባዘንኩት?! ትልቅ ሕልም ማለም፣ ምንም ጥቅም የለውም" ብሎ ሊያሳምንህም ይሞክራል። ስለ ፓራዳይም እና የሕልም ምስጢር በአግባቡ ስላልተረዳ፣ በዕቅድ ሕልሙ ተስፋ ቆርጦ ወደ ፍራቻ ሕልም ይመለሳል። በድርጅቶችም ቢሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ፣ የዕቅድ ሕልም ያለመሳካት አዝማሚያ በስፋት ይስተዋላል። ድርጅቶች ትልቅ ለውጥ ለማምጣት የቀናትና የሳምንታት ስብሰባ አድርገው፣ የሚገርም የዕቅድ ሕልም ወይም ግብ ይመርጣሉ። ከዚያም በአንድ ድምጽ ሁሉም ተስማምተው ያጸድቁታል። የጸደቀው የዕቅድ ሕልማቸውም፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ እሴትና ግብ ተብሎ በወሳኝና ትኩረት በሚስብ ቦታ ላይ በሚገርም ሕትመት ተውቦ ይለጠፋል።

በርግጥ በዚህ የዕቅድ ሕልም፣ የሠራተኞች አሠራር ለተወሰኑ ቀናት ይቀየራል፤ ድርጅቱም ማደግ ይጀምራል። ነገር ግን ከተወሰኑ ቀናት በኋላ፣ ፓራዳይም ብቅ ይልና ከሕልማቸው ይልቅ ተጽዕኖው እየጎላ ይመጣል። ከዚያም፣ ሰው ሁሉ ወደ ድሮ አሠራሩ ይመለሳል። በብዙ ስብሰባና ልፋት የተሠራው ዕቅድም ከሠራተኞቹ አዕምሮ ወጥቶ፣ በወረቀትና ግድግዳ ላይ ብቻ ተለጥፎ ይቀራል። ዳሩ የድርጅቱ ሕልም በሠራተኞቹ ልብ ቢታተም መልካም ነበር እንጂ! የፓራዳይምን አሠራር እና ስውር ኀይል ሳትረዳ፣ ምንም ዐይነት ሕልም ብታቅድ፣ የፓራዳይም መጫወቻ ሆነህ ነው የምትቀረው።

## ፭. የምኞት ሕልም

የምኞት ሕልም ከእውነተኛ ፍላጎትህና ከልብህ ምኞት ተነስተህ የምታስቀምጠው የሕልም ዐይነት ነው። ከልጅነትህ ጀምሮ በአዕምሮህ የተገነባውን ፓራዳይም ማሸነፍ የሚችለው የሕልም ዐይነት፣ የምኞት ሕልም ብቻ ነው።
የምኞት ሕልም፣ እንደ ሌሎቹ የሕልም ዐይነቶች ከፍራቻ፣ ከዕውቀት ወይም ከዕቅድ ተነስተህ ሳይሆን፣ ከእውነተኛ ፍላጎትህ፣ ከልብህ ከምትወደው፣ አልያም ከምታፈቅረው ምኞትህ ተነስተህ የምታስቀምጠው፣ ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ሊቀይር የሚችል ኀይል ያለው የሕልም ዐይነት ነው። ታሪካቸውን የምታነብላቸው፣ ጀብዳቸውን "ብደግመው" ብለህ የምትቋምጥላቸው፣ "አቤት አዕምሯቸው!" ብለህ የምትደመምላቸው ታሪክ ሠሪዎች በሙሉ፣ የምኞት ሕልም ባለቤቶች ናቸው። አንተም ታሪክ አንባቢ ብቻ ሳትሆን፣ ታሪክ ሠሪም ጭምር መሆን ከፈለግክ፣ የምኞት ሕልም ሊኖርህ ይገባል።

ታዲያ ትክክለኛውን ትልቅ ሕልም ወይም የምኞት ሕልም ለማስቀመጥ፣ ራስህን በጥልቀት መፈተሽ አለብህ። "የምመኘው ትልቁ ሕልሜ ምንድን ነው? ምን መሆን፣ ምን ማድረግና የት መድረስ እፈልጋለሁ?" ብለህ፣ በውስጥህ ያሉ ዋና ዋና ፍላጎቶችንና ምኞቶችን መፈተሽ አለብህ። የሰው ልጅ፣ ትልቅ ሕልሙን በአዕምሮው ተመኝቶ፣ በልቡ እንደሚያሳካው ሲያምን፣ ሕልሙን ከማሳካት የሚከለክለው አንዳች ነገር ስንኳ አይኖርም። ችግሩ ግን አብዛኞቻችን ከልጅነታችን ጀምሮ የምንፈልገውን ወይም የምንመኘውን ነገር ማግኘት እንደማንችል በተደጋጋሚ እየተነገረን በማደጋችን፣ የምኞት ሕልም አለማለማችን ነው። ሕፃናት እያለን፣ የምንመኘውን ነገር ለማሳካት፣ አዕምሯችን ብዙም ችግር አልነበረበትም። እያደግን ስንመጣ ግን እንዴት አድርገን የምንፈልገውን ነገር ማግኘት እንደምንችል ካላወቅን፣ የምንፈልገውን ነገር ተመኝተን ለማግኘት መሞከርን እንደ ሞኝነት መቁጠር እንጀምራለን።

ሕፃናት እያለን፣ የምኞት ሕልም ለማለም ብዙ ችግር አልነበረብንም። ሕፃናት ተሰብስበው ዕቃ-ዕቃ ሲጫወቱ፣ የተለያዩ ዕቃዎችን በመጠቀም የሚፈልጉትን ነገር ሲፈጥሩ፣ አውሮፕላን፣ መርከብ ወይም መኪና ሲነዱ፣ ቤተሰቦቻቸው ምንም አይመስላቸውም። እንዲያውም ልጃቸው አዕምሮውን ተጠቅሞ የተለያዩ ጨዋታዎችን በመፍጠር እንዲጫወት ይፈቅዱለታል። ልጆች አዕምሯቸው በጣም ክፍት ስለሆነና

"አይቻልም" በሚል አስተሳሰብ ስላልተሞላ፣ "ምን መሆን ትፈልጋላችሁ...?" ብለህ ስትጠይቃቸው፣ ወዲያውኑ "ዶክተር፣ ፓይለት፣ አስተማሪ፣ ተዋናይ..." ብለው ምኞቶቻቸውን በነጻነት ለመግለጽ ምንም የሚይዛቸው ነገር የለም። እርስ በርሳቸው ሲጫወቱ የሚፈልጉትን ገጸ ባህሪ በመያዝ መጫወትም ምንም አይመስላቸውም።

አንድ ልጅ ትምህርት ቤት መሄድ ሲጀምር ግን አስተማሪው፣ እሱ የሚለውን ብቻ እንዲያዳምጥና እንዲማር ነው የሚፈልገው። ስለዚህ አስተማሪው እያስተማረ፣ ልጁ በአዕምሮው ስለሚፈልገው ነገር ማለም ቢጀምር፣ "አንተ ልጅ! ምን እያሰብክ ነው? ለምንድን ነው ሀሳብህን የማትሰበስበው?" ተብሎ የተለያዩ ቅጣቶችን ሊቀጣ ይችላል። ይሄ ልጅ ወደ ቤት ተመልሶ ሲሄድም፣ በትምህርት ሰዓት "አዕምሮውን ተጠቅሞ ስላለመ" ቅጣቱ በወላጆቹ ሊደገምለት ይችላል።

ወላጆች እና አስተማሪው ያላወቁት ነገር፣ ልጁ ፈጣሪ የሰጠውን ድንቅ የምናብ አቅሙን እየተጠቀመ እንደነበረ ነው። ልጁ ቀን በቀን የመቀጣት ፍላጎት ስሌለው፣ ከተወሰኑ የ"አታልም" ማስጠንቀቂያዎች በኋላ፣ ድንቅ የሆነ ምናባዊ አቅሙን መጠቀም ያቆማል፤ እንዴት እንደሚጠቀምበት እንዲረሳም ይሆናል። ካደገና ብዙ ዕውቀት ከሰበሰበ በኋላ፣ "ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው? ምንስ መሆን ትፈልጋለህ?" ብለህ ብትጠይቀው ግን ምንም መልስ ላይኖረው ይችላል።

በተለያዩ የስልጠና መርሀ ግብሮች ላይ፣ የተለያዩ ሕፃናትን "ነገ ላይ ምን መሆን ትፈልጋላችሁ? ወይም "ትልቁ ሕልማችሁ ምንድን ነው?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ "እኔ እንደዚህ መሆን ነው የምፈልገው" ብለው ወዲያውኑ ፍላጎታቸውን እና ምኞታቸውን ይነግሩኛል። ነገር ግን የተለያዩ "ትላልቅ" ሰዎችን፣ "ትልቁ ሕልማችሁ ምንድን ነው?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ ሕልማቸውን ሳይሆን ፍራቻቸውን ወይም ሕልማቸውን እንዳያሳኩ የከለከላቸውን ችግር ነው የሚነግሩኝ። በርግጥ ትልቁን ሕልማችንን ለማሳካት እና ሕይወታችንን ለመቀየር ስንፈልግ፣ በተለያዩ የሕይወት ፈተናዎች እና ችግሮች እንፈተናለን። ነገር ግን የስኬት የመጀመሪያ ሁለት ርምጃዎች፣ አሁን የት እንዳለህ በግልጽ ማወቅ እና የት መሄድ እንደምትፈልግ መወሰን ናቸው።

ስለዚህ በልብህ የምትፈልገውና የምትመኘው ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ ራስህን ልትጠይቅ ይገባል። አሁን ልክ እንደ ሕፃን ልጅ፣ ሕልምህን እንዴት እንደምታሳካው ሳትጨነቅ፣ ሕልምህ ምን እንደሆነ ወስን። ሁሉም ነገር የሚቻል ስለሆነ፣ የማይቻል ነገርም ስለሌለ፣ ማሳካት የምትፈልገው እና የምትመኘው ሕልምህ ምንድን ነው? የምኞት ሕልምህ ምንድን ነው? ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው?

አሁን መወሰን ያለብህ አንድ ነገር፣ የት መሄድ እንደምትፈልግ እንጂ እንዴት እንደምትሄድ መሆን የለበትም። በዚህ "ትልቅ ሕልም" በሚለው ምዕራፍ፣ የት መሄድ እንደምትፈልግ ከወሰንክ፣ እንዴት ወደ ሕልምህ እንደምትሄድ በሚቀጥሉት ምዕራፎች በደንብ አሳይሀለሁ። በርግጥ ሕልምህን ለማሳካት የምትጓዘው ጉዞ ቀላል አይደለም፤ ጉዞውም ከባድና ትዕግስት የሚያስፈልገው ነው። የምትወደው እና የምትመኘው ትልቅ ሕልም ካለህ ግን፣ በጉዞህ ላይ የሚያጋጥሙህን የተለያዩ ፈተናዎች እንድታሸንፍ፣ ጉልበት ይሰጥሀል።

ሁሉም ሰው በሕይወቱ ይለፋል። ጥያቄው ግን "ለምንድን ነው የሚለፋው?" የሚለው ነው። ትልቅ ሕልም የሌለው ሰው ብዙውን ጊዜ የሚለፋው ለከንቱ ነው። ትልቅ ሕልም ያለው ሰው ግን መክፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ሕልሙን ያሳካል፤ ሕይወቱንም ይቀይራል።

ለሕይወትህ ትርጉም የሚሰጠው፣ የምትፈልገውና የምትመኘው ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው? ምን መሆን ትፈልጋለህ? ምን ማድረግ ትሻለህ? የት መድረስስ ትፈልጋለህ? ራስህን በነዚህ ጥያቄዎች በመፈተሽ ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ አሁኑኑ ወስን።

# ትልቁ ሕልሜ ይቻላል!

አንድሪው ካርኔጊ እ.ኤ.አ. በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ይኖር የነበረ፣ በዓለማችን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢልየነር ከነበሩ ጥቂት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። በዚያ ሰዓት ቢልየነር የነበረ ሰው፣ አሁን ባለው ምንዛሬ፣ ምናልባትም ትሪልየነር ይሆናል። አንድሪው ካርኔጊ ወደዚች ዓለም ከሀብታም ቤተሰብ አልመጣም፤ የዘር ሀረጉም ከቢልየነር ዘመዶች የሚመዘዝ አልነበረም። አመጣጡ ከድሀ ቤተሰብ ነበር። ድህነት ከልጅነቱ ተጠናውቶት ነበር ያደገው። ነገር ግን በሕይወቱ ያጋጠመውን ድህነትና ማጣት በማሸነፍ፣ የዓለማችን ቢልየነር ለመሆን ችሏል። አንድሪው ካርኔጊ ራሱን ብቻ ሳይሆን፣ አገሩንና ዓለምን ጭምር መቀየር ይፈልግ ስለነበር፣ ጊዜውንም ሆነ ገንዘቡን፣ ሰዎችን ለመርዳት ነበር የተጠቀመበት።

አንድሪው ካርኔጊ ራሱን፣ ቤተሰቡን፣ አገሩን እና ዓለምን ለመቀየር ያደረጋቸውን ነገሮች እና ያበረከታቸውን አስተዋጽዖዎች ለመግለጽ፣ ሌላ ሙሉ መጽሐፍ ያስፈልጋል። በዓለማችን ላይ ካበረከታቸው በርካታ አስተዋጽዖዎች መካከል ከ2,800 በላይ የሚሆኑ ቤተ-መጻሕፍት እንዲከፈቱ መርዳቱ ይጠቀሳል። አንድሪው ካርኔጊ፣ ከድህነት ሕይወት በመውጣት፣ የቢልየነርነትን ሕይወት ማጣጣም የቻለው፣ ትክክለኛ ዕውቀት እና መረዳት ስላገኘ ነው። ይህንን ትክክለኛ ዕውቀት በመጠቀም ሕይወቱን ሊቀይር በመቻሉ፣ ሌሎች ሰዎችም ይህንን ትክክለኛ ዕውቀት ተምረው፣ ሕይወታቸውን እንዲቀይሩ ሁሌም ይፈልግ ነበር።

በአንድሪው ካርኔጊ ዘመን ይኖር የነበረ አንድ ወጣት እና ድሀ ጋዜጠኛ ነበር፣ ናፖልዮን ሂል። በአንድ ልዩ አጋጣሚ ናፖልዮን እ.ኤ.አ በ1908 ዓ.ም. አንድሪው ካርኔጊን ቃለ-መጠይቅ የማድረግ ዕድል አገኘ። ድሀውና ወጣቱ ናፖልዮን ሂል፣ በዘመኑ ከነበሩ ቢልየነር ባለ ሀብቶች መካከል ተጽዕኖ ፈጣሪ በነበረው ሰው፣ ቀጥታ የመማር ዕድልን ስላገኘ በጣም ደስ አለው። በተቃራኒው አንድሪው ካርኔጊም በውስጡ የነበረውን ትልቅ ምስጢር ለዓለም እንዲያካፍል በሚያደርገው ጥረት ላይ ሊረዳው የሚችለውን ሰው በማግኘቱ በጣም ደስ አለው። አንድሪው ካርኔጊ በሕይወቱ የተማራቸውን ምስጢሮች ለዓለም ማካፈል እንጂ፣ ወደ መቃብሩ ይዟቸው መሄድን አልመረጠም።

ናፖልዮን ሂል፣ አንድሪው ካርኔጊን ሦስት ሰዓታት የፈጀ ቃለ-መጠይቅ አደረገለት። በነዚህ የሦስት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ፣ አንድሪው ካርኔጊ ትላልቅ የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮቹን በመጠቀም እንዴት አድርጎ ከድህነት በመውጣት፣ ሕይወቱን እንደቀየረ ለናፖሊዮን ሂል አስተማረው። ሆኖም በነዚህ ሦስት ሰዓታት ውስጥ ለናፖሊዮን ሂል ባስተማረው ትምህርት አልረካም። አንድሪው ካርኔጊ "ይህ ቃለ-ምልልስ ተጀመረ እንጂ አላለቀም" በማለት፣ ናፖሊዮን ሂልን ወደ ቤቱ በመውሰድ፣ ቃለ-መጠይቁን ለሦስት ቀናት በቤቱ እንዲቀጥል ወሰነ። ለሆቴል እንኳ የሚከፍለው በቂ ገንዘብ ያልነበረው ናፖልዮን ሂል፣ ለሦስት ቀናት በቢልየነሩ ቤት በመሄድ ጥሩ ጊዜ እንደሚያሳልፍ ሲሰማ፣ የተሰማውን ደስታ መገመት አይከብድም።

በነዚያ ሦስት ቀናት፣ አንድሪው ካርኔጊ የሕይወትን እና የስኬትን ዋና ዋና ቁልፎች እና ምስጢሮች ምንም ሳያስቀር፣ ለናፖልዮን ሂል ካስተማረው በኋላ፣ እንዲህ የሚል ጥያቄ ጠየቀው። "ናፖልዮን ሂል፣ አሁን የማካፍልህን ምስጢራት ለማጥናትና ዓለምን ለማስተማር፣ እስከ ሃያ ዓመታት ድረስ ምንም ነገር ሳይከፈልህ ለመሥራትና ሕይወትህን መሥዋዕት ለማድረግ ዝግጁ ነህ?" ብሎ ጠየቀው። ናፖልዮን ሂል በሃያ ዘጠኝ ሰከንዶች ውስጥ "አዎ!" ብሎ መለሰ። ናፖልዮን ሂል ያላወቀው ነገር፣ አንድሪው ካርኔጊ በእጁ ሰዓት ይዞ ነበር። ናፖልዮን ሂል በአንድ ደቂቃ ውስጥ፣ "አዎ!" ብሎ ባይመልስ ኖሮ፣ ካርኔጊ ሥራውን አይሰጠውም ነበር። በኋላ፣ ናፖልዮን ሂል "ይህ ድንቅ የሕይወት አጋጣሚ ከእጄ ለማምለጥ ሰላሳ አንድ ሰከንዶች ብቻ እንደቀረው አላወቅኩም ነበር" በማለት ተናግሯል።

አንድሪው ካርኔጊ፣ ናፖልዮን ሂልን "ይህንን ሥራ መሥራት ቀላል አይደለም፤ እኔ ደግሞ ይህንን ሥራ ስትሠራ ምንም ነገር አልከፍልህም" ብሎ በመንገር ነበር ሥራውን የሰጠው። ካርኔጊ ለናፖሊዮን የሰጠው

አንድ ነገር ቢኖር፣ በዘመኑ ከነበሩ ስኬታማ ሰዎች ዘንድ በመሄድ፣ ቃለ-መጠይቅ ማድረግ እንዲችል፣ ናፖልዮንን የሚያስተዋውቀውን ደብዳቤ ብቻ ነበር። ናፖልዮን ሂል፣ በዚያ ዘመን የነበሩ፣ ከ500 በላይ የሆኑ የዓለማችን ትላልቅ እና ስኬታማ ሰዎች ዘንድ በመሄድ፣ ስለ ሕይወት እና ስኬት ምስጢራቸው በመጠየቅ፣ ብዙ ቁም ነገሮችን ጨበጠ። ናፖልዮን ሂል ቃለ-ምልልስ ካደረገላቸው ሰዎች መካከል፣ ቶማስ ኤዲሰንን (የመብራት አምፑልና ሌሎች ከአንድ ሺህ በላይ ነገሮችን የፈጠረ)፣ ሄንሪ ፎርድን (የፎርድ ሞተር መኪናን የፈጠረ)፣ አሌክሳንደር ግራሀም ቤልን (ስልክ እና ሌሎች ነገሮችን የፈጠረ)፣ ቴዎድሮስ ሩዝቬልትን (26ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበረ) እና ሌሎች የዘመኑ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል።

አንድሪው ካርኔጊ፣ ናፖልዮን ሂልን ከማሰናበቱ በፊት፣ እንዲህ በማለት አንድ የመጨረሻ ምስጢር ነግሮት ነበር። "ናፖልዮን፣ አሁን የምሰጥህ ሥራ የተወሰነ ሰዓት ሊከብድህ እና ተስፋ እንድትቆርጥ ሊያደርግህ ይችላል። አሁን የምነግርህን ምስጢር ከተጠቀምክበት ግን ሕልምህን ለማሳካት ይረዳሀል። ምስጢሩ ደግሞ በጣም ቀላል ነው። ምስጢሩ፣ አሁን የምነግርህን ቃላት በወረቀት ላይ መጻፍ እና ወረቀቱ ላይ የጻፍካቸውን ቃላት፣ በየቀኑ ደጋግመህ ማንበብ ነው" አለው። ናፖልዮን እነዚህን ሕልሙን ለማሳካት የሚረዱ ቃላት ለመጻፍ እንደተዘጋጀ፣ አንድሪው ካርኔጊ እንደዚህ ብሎ እንዲጽፍ ትዕዛዝ ሰጠው። *"አንድሪው ካርኔጊ፣ በሕይወትህ ያገኘሀቸውን ውጤቶች ሁሉ አገኛቸዋለሁ። እንዲያውም በሩጫው ሜዳ ላይ እፎካከርሀለሁ፤ በሩጫው መጨረሻ ስንደርስ ደግሞ እቀድምሀለሁ!"*

ናፖልዮን ሂል በእጁ ይዞት የነበረውን እርሳስ በመወርወር፣ "ይህማ የማይሆን ነገር መሆኑን አንተም ጠንቅቀህ ታውቃለህ!" ብሎ ተስፋ በመቁረጥ መለሰለት። አንድሪው ካርኔጊም "አዎ! ይህ የማይሆን ነገር ነው። የማይሆነው ግን በልብህ እስካላመንከው ድረስ ብቻ ነው" ብሎ በመመለስ፣ ቃል እንዲገባለት ናፖልዮንን ጠየቀው። "ናፖልዮን፣ አሁን የምሰጥህን ቃላት፣ ሁሌም ጥዋት እና ማታ ሳታቋርጥ ለሰላሳ ቀናት ጮክ ብለህ እንደምታነባቸው ቃል ግባልኝ" አለው። ናፖልዮን፣ የተሰጠውን ትልቅ ሕልም እንዴት አድርጎ እንደሚያሳካው ባይረዳም፣ እነዚህን ቃላት ለመጻፍ እና በልቡ እምነት እስኪፈጠር ድረስ ጥዋት እና ማታ፣ ለሰላሳ ቀናት ለማንበብ ለካርኔጊ ቃል ገባለት። ናፖልዮን ሂል ቃሉን በመጠበቅ፣ ቤት ገብቶ እነዚህን ቃላት ለመጀመሪያ ጊዜ ሊያነብ ሲል፣ ቤት ውስጥ ወንድሙ ቁጭ ብሎ ነበር። እነዚያን አይደለም ከሰው ፊት፣ ለራሱ እንኳ ማመን የከበዱትን ቃላት፣ በወንድሙ ፊት ጮክ ብሎ ማንበብ ስላሳፈረው ወደ መታጠቢያ ቤት ገብቶ፣ በመስታወት ፊት ቆሞ እነዚህን ቃላት ቀስ ብሎ በሹክሹክታ አነበባቸው። *"አንድሪው ካርኔጊ፣ በሕይወትህ ያገኘሀቸውን ውጤቶች ሁሉ አገኛቸዋለሁ። እንዲያውም በሩጫው ሜዳ ላይ እፎካከርሀለሁ፤ በሩጫው መጨረሻ ስንደርስ ደግሞ እቀድምሀለሁ!"*

ናፖልዮን እነዚህን ቃላት ጮክ ብሎ በመስታወት ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያነባቸው፣ ምንም ትርጉም አልሰጡትም ነበር። ነገር ግን የገባውን ቃል በመጠበቅ፣ በየቀኑ ጥዋት እና ማታ ጮክ ብሎ ለአንድ ወር ማንበቡን አላቋረጠም። ለግማሽ ወር ያክል እነዚህን ቃላት ደጋግሞ ማንበቡን ሲቀጥል፣ "ይህ ነገር እኮ ሊሆን ይችላል" ብሎ ማሰብ እና መጠራጠር ጀመረ። አንድሪው ካርኔጊ እንዳዘዘው ለአንድ ወር ሙሉ እነዚህን ቃላት ደጋግሞ ጥዋት እና ማታ መስታወት እያየ ጮክ ብሎ ካነበበ በኋላ ግን፣ "ይህ ነገር መሆን ይችላል!" የሚል እምነት በልቡ ተፈጠረ።

አንድሪው ካርኔጊ በሕይወት እያለ በዓለማችን ላይ አምሳ ሦስት የሚሆኑ ሰዎች ሚልየነሮች እንዲሆኑ ረድቷል። ናፖልዮን ሂል ግን ዓለማችን ላይ በሚልየኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ሚልየነሮች እንዲሆኑ ረድቷል። ናፖልዮን ሂል "Think and Grow Rich" በተባለው መጽሐፉ ብቻ እስከ ዛሬ ድረስ፣ በዓለም፣ በብዙ ቋንቋዎች፣ በአማርኛም ጭምር በመተርጎም፣ ከአንድ ሚልዮን ቅጂዎች በላይ ታትሞ ተሸጦለታል። ዓለምን መቀየር ይፈልግ የነበረው አንድሪው ካርኔጊ ስለ ናፖልዮን ሂል የተናገረው ልክ ነበር። ናፖልዮን ሂል በመጨረሻ በትልቅ ሕልሙ ስላመነ፣ በሚልየኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ትልቅ ደረጃ ላይ እንዲደርሱና ዓለምን እንዲቀይሩ ረድቷል። በርግጥም ናፖልዮን ሂል አንድሪው ካርኔጊን በሩጫው መጨረሻ ቀድሞታል።

ናፖሊዮን ሂል ስለ ሕይወት እና ስኬት ቀመሮች ብዙ ምስጢሮችን ከተማረ በኋላ፣ ለዓለማችን፣ ይህን የስኬት ቀመር አስቀምጧል። "የሰው አዕምሮ መጸነስ እና ማመን የቻለውን ሁሉ ማግኘት ይችላል" ይሄ የስኬት ቀመር፣ በውስጧ ትልቅ ምስጢር ስላላት፣ ደጋግመህ አንብባት። የሰው ልጅ በአዕምሮው አንድ ትልቅ ሕልም ሲያልምና ያለመውን ሕልም እንደሚያሳካው በልቡ ሲያምን፣ በርግጠኛነት ሕልሙን ማሳካት ይችላል። በዓለማችን ላይ ታሪክ የሰሩ ሰዎችን ብትመለከት፣ ሁሉም ይቺን የስኬት ቀመር ተጠቅመውባት እንዳለፉ መረዳት ትችላለህ። በርግጥ አንዳንዶቹ የስኬት ቀመር ምን እንደሚል ቃል በቃል ላያውቁት ይችላሉ። ነገር ግን ይህንን የስኬት ቀመር ቃል በቃል ምን እንደሚል አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት የስኬት ቀመርን በመጠቀም ሕልማቸውን አሳክተዋል።

በዓለማችን ላይ ታሪክ የሰሩ ሰዎች በሙሉ በመጀመሪያ አንድ ትልቅ ሕልም እንደሚያሳኩ በአዕምሯቸው በማሰብ እና በመወሰን፣ ሕልማቸውን እንደሚያሳኩ በልባቸው ያመኑ ናቸው። ትልቅ ሕልማቸውን በልባቸው እንደሚያሳኩት እምነት ስላላቸው፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ በዓለማችን ላይ ታሪክ መሥራት የቻሉም ናቸው። አንተስ ይህንን የስኬት ቀመር በመጠቀም፣ ትልቁን ሕልምህን በአዕምሮህ በተደጋጋሚ በማሰብ እና እንደምታሳካው በልብህ በማመን፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት ዝግጁ ነህ?

ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው? አሁን ያለህ የሕልም ዐይነት የምትፈልገው የምኞት ሕልም ነው ወይስ የፍራቻ፣ የዕውቀትና የዕቅድ ሕልም? በሕይወቴ ያስቀመጥኳቸውና ያሳካኋቸው ሕልሞች እንደ ትክክለኛውና ዋናው ትልቅ ሕልሜ ቢመስሉኝም እንኳ፣ አሁን መለስ ብዬ ራሴን ስፈትሽ ግን በሕይወቴ ያሳካኋቸው ሕልሞች የዕቅድ፣ የዕውቀትና የፍራቻ ሕልሞች መሆናቸውን ተረድቼአለሁ። ወደ ኢትዮጵያ በመጣሁበት የመጀመሪያ ሰሞን የነበረኝ ሕልም "የፍራቻ ሕልም" ነበር። (ወደ ኢትዮጵያ ከመጣሁበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የነበሩኝን ሕልሞች እንዲሁም በሕይወቴ የተማርኳቸውን ትምህርቶችና ምስጢሮች ለመረዳት፣ "ዳዊት ድሪምስ" የሚለውን የዚህ መጽሐፍ "መግቢያ" መመልከት ትችላለህ። ሆኖም በሕይወቴ ያስቀመጥኳቸውን ሕልሞች፣ የተማርኳቸውን ትምህርቶችና ምስጢሮች ከዚህ "ትልቅ ሕልም" የሚል የዛሬው ምዕራፍ ጋር በማያያዝ አሳጥሬ እደግመዋለሁ)

ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቴ በፊት ባጋጠሙኝ የተለያዩ ፈተናዎችና ችግሮች ምክንያት፣ አፍሪካ ውስጥ መሥራትም ሆነ መኖር በጣም አስጠልቶኝ ስለነበረ፣ "ትልቁ ሕልሜ" በድጋሚ ወደ እንግሊዝ አገር መሄድ ነበር። በዚያ ሰዓት ትልቅ ሕልም የነበረኝ ቢመስለኝም እንኳ፣ የነበረኝ ሕልም የፍራቻ ሕልም መሆኑን የተረዳሁት ግን አሁን ነው። ኢትዮጵያ እንደገባሁ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅር በጣም ስለማረከኝ፣ የፍራቻ ሕልሜን በማባረር፣ ዋናውንና ትልቁን ኢትዮጵያንና አፍሪካን የመቀየር ሕልሜን ለማሳካት ወሰንኩ።

በዚያ ሰዓት፣ "ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት የሚያስፈልገኝ ገንዘብ፣ ሰው፣ የቋንቋ ችሎታ ወይም ሌላ ነገር አለኝ" ብዬ ስላላመንኩ፣ ከዋናው ሕልሜ አነስ ያለ ሌላ ሕልም አስቀመጥኩ። በሰዓቱ "በኮምፒዩተር ጥገና እና ኢንተርኔት ሥራዎች በቀን አንድ ሺህ ብር እየሠራሁ ነው" ብዬ ያስቀመጥኩትን ሕልም "በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አሳካዋለሁ" ብዬ ባቅድም እንኳ፣ በሚገርም የጊዜ ፍጥነት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በቀን አንድ ሺህ ብር የማግኘት ሕልሜን ማሳካት ቻልኩ። በወቅቱ ያስቀመጥኩት ሕልም፣ ትልቁ ሕልሜ መስሎ ቢታየኝም፣ አሁን ሳስበው ግን የዕውቀት ሕልም መሆኑን ነው የተረዳሁት። ከዚህ በመቀጠልም "በኮምፒዩተር ጥገና እና ኢንተርኔት እንዲሁም በካፌና ምግብ ቤት ሥራዎች በቀን አስር ሺህ ብር እየሠራሁ ነው" ብዬ በሁለት ዓመታት የሚሳካ ሕልም ባስቀምጥም፣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አሳካሁት። ይህንንም ሕልም አሁን ላይ የኋሊት ስመለከተው፣ የዕቅድ ሕልም እንዳስቀመጥኩ ነበር የተረዳሁት። እነዚህ በዚያ ሰዓት "ትልቅ ሕልም" ብዬ ያስቀመጥኳቸው ሕልሞች፣ እንደ ትልቅ ሕልሜ ባይሆኑም ሕይወቴን ግን ቀይረውታል። በመሆኑም እነዚህን ሕልሞች በማስቀመጤና በማሳካቴ ፈጣሪን አመሰግናለሁ።

እነዚህ ሕልሞች ሕይወቴን በወቅቱ በርግጠኛነት ቀይረውታል። ነገር ግን በሰዓቱ እነዚህን ሕልሞች ያስቀመጥኳቸው "ዋናውንና ትልቁን ሕልሜን ማሳካት ይከብደኛል" ብዬ ስላመንኩና ስለፈራሁ ነበር። "ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት የሚያስፈልገኝ ሰው፣ የቋንቋ ችሎታ፣ ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር የለኝም" ብዬ ስላመንኩና ስለፈራሁ፣ የዕውቀትና የዕቅድ ሕልሞችን ለማሳካት ወሰንኩ። ነገር ግን ልቤ ከትልቁ ሕልሜ ጋር ስለነበር ዕረፍት አልሰጠኝም። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም የቀን ገቢዬ ወደ አስራ አምስት ሺህ ብር ሲያድግ፣ ሙሉ በሙሉ ወደ ትልቁ ሕልሜ በመመለስ፣ "እኔ ዳዊት ድሪምስ ነኝ! ኢትዮጵያን እና አፍሪካን እየቀየርኩ ነው፤ በወርም አንድ ሚልየን ብር እያገኘሁ ነው" የሚለውን ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት ወሰንኩ። ኢትዮጵያን እና አፍሪካን ለመቀየር፣ በተለያዩ ቦታዎችና የመገናኛ ብዙኀን የነጻ ስልጠናዎችንና የምክር አገልግሎቶችን መስጠት ጀመርኩ። በወር አንድ ሚልየን ብር ለመሥራት ደግሞ ሥራዎቼን በደንብ ማስፋፋትና ማጠናከር ጀመርኩ።

ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት እሠራ የነበርኩበት ቦታ ግን ከሦስት ዓመት በላይ ለልማት ስለተቆፈረ፣ "በሚልየኖች እሠራበታለሁ" ብዬ ያሰብኩት ቦታ በሚልየኖች የሚቆጠር ብር አከሰረኝ። ይህ ወቅት በሕይወቴ ከባድ ጊዜና ጨለማ የነበረበት እንዲሁም የፈተናና የችግር ወቅት ነበር። ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እንደምችል ሙሉ እምነት ቢኖረኝም፣ እንደዚያ ወቅት ተፈትኜ አላውቅም። በዚያ ሰዓት የነበሩኝ አማራጮች ሁለት ነበሩ። ተስፋ በመቁረጥ ወደ ፍራቻ ሕልሜ መመለስ፤ አልያም መሥዋዕትነት በመክፈል ከዜሮና ከኪሳራ ተነስቶ ትልቁን ሕልሜን ማሳካት። የቅርብ የምላቸው አጠገቤ የነበሩ ሰዎች ጭምር ግን፣ ሥራዎቼን ወደ ሌሎች ቦታዎች በማዞር፣ ሌላ የዕውቀትና የዕቅድ ሕልሞችን እንዳሳካ ወይም የፍራቻ ሕልሜን በቀላሉ እንዳጣጥም ይመክሩኝ ነበር።

እኔ የምፈልገው ትልቁን ሕልሜን ማሳካት ቢሆንም፣ አሁንም ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት የሚያስፈልጉኝ በቂ ገንዘብ፣ የቋንቋ ችሎታ፣ ሰውና ሌሎች ነገሮች አልነበሩኝም፤ እንዲያውም ከአምስት ሚልየን ብር በላይ ዕዳና ኪሳራ ተሸክሜ ነበር። በዚያ ከባድ ሰዓት ግን አንድ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ለማድረግ ወሰንኩ። ከዚያም አሁን በዚህ መጽሐፍ የምጽፋቸውን የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች እንደ ሳይንቲስት ሆኜ በማጥናት ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እንደምችል ተረዳሁ።

የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በጥንቃቄ ሳጠና፣ ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ባይኖሩም እንኳ እኔ ድንቅ የፈጣሪ ልጅ መሆኔን ደግሞም ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እንደምችል በትክክል ተረዳሁ። የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በትክክል ስረዳ፣ ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት የሚያስፈልገኝ ሰው፣ የቋንቋ ችሎታ፣ ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ድንቅ ውሳኔ መወሰን ብቻ መሆኑን ተረዳሁ። በዚያ ሰዓት ከማንም ምንም ነገር ሳልጠብቅ፣ ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት ወሰንኩ። አዎ! ራሴንና ቤተሰቤን ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያን እና አፍሪካን ለመቀየር፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ለመክፈል ወሰንኩ።

በወቅቱ ያደረግኩት የመጀመሪያው ነገር፣ ትልቁን ሕልሜን በሕልም ካርዴና በልቤ ላይ በደማቁ መውቀር ነበር። ትልቁ ሕልሜ "እኔ ዳዊት ድሪምስ ነኝ! ኢትዮጵያንና አፍሪካን እየቀየርኩ ነው! በወር አንድ ሚልየን ብር እያገኘሁ ነው" የሚል ነበር። ሕልሜን ከጻፍኩበት ቅጽበት አንስቶም የሕልም ካርዴ ከእኔ ተለይቶ አያውቅም። ትልቁን ሕልሜን ማሳካት እንደምችል በልቤ ማመን ቀላል ባይሆንም፣ የሕልም ካርዴን ጥዋት ከተነሳሁበት ሰዓት አንስቶ ማታ እስከምተኛበት ጊዜ ድረስ ደጋግሜ በማንበብ፣ በልቤ ወቀርኩት። ትልቁን ሕልሜን ለማሳካት የተለያዩ ሥራዎችን ስሠራና ለሕልሜ የሚከፈለውን መሥዋዕትነት ስከፍል፣ የተለያዩ ችግሮችና ፈተናዎች ያጋጥሙኛል። ችግሮች ባጋጠሙኝ ቁጥር ግን ትልቁን ሕልሜን ደግሜ ደጋግሜ በማንበብ፣ እምነቴን አጠነክራለሁ፤ ትልቅ ሕልሜን የማሳካት ፍላጎቴንም በትጋት እቀጥላለሁ።

በአካባቢዬ የነበሩ ሰዎች ትልቁን ሕልሜን በአጋጣሚ ሲያነቡ ወይም ጮክ ብዬ ሳነብ ሲሰሙ፣ በጣም ይስቁና ይቀልዱ ነበር። ትልቁ ሕልሜ ሲሳካ በዐይናቸው ሲመለከቱ ግን በራሳቸው ላይ እንደሳቁና እንደቀለዱ እየገባቸው ነው።

ትልቁ ሕልሜ በጣም የሚያስደስተኝ ሕልም ቢሆን እንኳ፣ በመጀመሪያ ግን እኔም ራሴ ሳስበው በጣም ያስፈራኝ ነበር። አሁን የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በመጠቀምና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል ራሴን ስቀይር፣ ትልቁ ሕልሜ እየቀለለኝና እያነሰብኝ መጣ። አሁን ያለኝን ትልቅ ሕልም ሙሉ በሙሉ በማሳካት፣ ሌላ አዲስ የሚያስደስተኝን፣ ነገር ግን ሊያስፈራኝ የሚችልን ትልቅ ሕልም በማስቀመጥ፣ ዓለምን ለመቀየር በጉጉት እየጠበቅኩ እና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት እየከፈልኩ ነው።

አንተም ትልቁን ሕልምህን ልታሳካ ስትፈልግ፣ ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልግህ ሰው፣ ገንዘብ፣ ቦታ፣ የትምህርት ደረጃ ወይም ሌላ ነገር ላይኖርህ ይችላል። ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት የሚያስፈልግህ፣ አሁኑኑ ድንቅ ውሳኔ መወሰን ብቻ ነው። ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት ስትወስን፣ የሚያስፈልግህን ሰው፣ ገንዘብ፣ ቦታ፣ የትምህርት ደረጃ ወይም ሌላ ነገር ማግኘት ትጀምራለህ። አሁን የሚያስፈልግህ፣ ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት በአዕምሮህ መወሰንና እንደምታሳካው በልብህ ማመን ነው። አሁን ትልቁን ሕልምህን በሕልም ካርድህ ላይ አስቀድመህ በማስፈር፣ በየቀኑ ጮክ ብለህ እያነበብክ በአዕምሮህና በልብህ ውቀር።

# ትልቅ ሕልም መውቀር

ከዚህ መጽሐፍ ጋር የሕልም ካርድ ታገኛለህ። በዚህ የሕልም ካርድ፣ ትልቁን ሕልምህን በጥንቃቄ በመምረጥ ጻፍ። ይህንን ካርድ ከራስህ ሳትለይ፣ በየቀኑ ጥዋት እና ማታ እንዲሁም ጊዜ ባገኘህ ቁጥር በተደጋጋሚ ስታነበው፣ ሕልምህን ታሳካዋለህ። በስኬት ቀመር መሠረት፣ ትልቁን ሕልምህን በዚህ ካርድ ላይ ከጻፍክ በኋላ፣ በየቀኑ በተደጋጋሚ በማንበብ፣ በአዕምሮህ ማሰብ አለብህ። በአዕምሮህ በየቀኑ በተደጋጋሚ ስታስበው ደግሞ፣ ሕልምህን እንደምታሳካ በልብህ እምነት ይፈጠራል። ሕልምህን እንደምታሳካ በልብህ እምነት ሲፈጠር ደግሞ፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ በሕይወትህ ተዓምር መሥራት ትችላለህ።

ይህንን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰማው፣ ቀንጆ ተስፋ ብቻ ሊመስልህ ይችላል። ነገር ግን ሕልምህን በዚህ ካርድ ጽፈህ፣ ጥዋት እና ማታ ለሃያ አንድ ቀናት ደጋግመህ በማንበብ፣ የምታነበውን ነገር በልብህ ስታምንና ሕልምህን ማሳካት ስትጀምር፣ እያካፈልኩህ ያለሁት ምስጢር፣ ደስ የሚል ተስፋ ብቻ እንዳልሆነ ትረዳለህ። "ራስህን መቀየር ትችላለህ!" ብዬ እየነገርኩህ ያለሁት ሀሳብ ካላሳመነህ፣ ምንም ችግር የለውም። አንድ ቃል እንድትገባልኝ የምፈልገው ነገር፣ በዚህ ካርድ ላይ በጥንቃቄ መርጠህ የጻፍከውን ትልቁን ሕልምህን ለሃያ አንድ ቀናት ጥዋት እና ማታ በተደጋጋሚ እንድታነብ ብቻ ነው።

እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ትልቁን ሕልሜን በትንሽዬ ወረቀት ላይ ስጽፈው፣ የሚሳካ አልመሰለኝም ነበር። ነገር ግን ትልቁን ሕልሜን በዚያች ትንሽዬ ወረቀት ላይ በመጻፍ፣ በተደጋጋሚ ሳነበው፣ ሕልሜን እንደማሳካው አመንኩ። ሕልሜን በወረቀት ላይ በጻፍኩበት ሰዓት፣ እንዴት አድርጌ ላሳካው እንደምችል ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም። ነገር ግን ሕልሜን በየቀኑ ጥዋት እና ማታ እንዲሁም ጊዜ ባገኘሁ ቁጥር በተደጋጋሚ ሳነብ፣ ትልቁን ሕልሜን እንደማሳካው በልቤ ላይ ትልቅ እምነት ተፈጠረ። ሕልሜን እንደማሳካው ሙሉ እምነት ስለነበረኝ፣ ሕልሜን ለማሳካት የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ በሰዓቱ ማግኘት ጀመርኩ። አሁን ሕልሜን በምፈልገው ደረጃ በማሳካትና ራሴን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ሰውነት በመቀየር፣ ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ቀይሬያለሁ። ራሴን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ሰውነት በመቀየር፣ ሕይወቴን ለመቀየር የቻልኩት፣ ትልቁ ሕልሜ ምን እንደሆነ ጊዜ በመውሰድ በጥንቃቄ ስለመረጥኩ ነው።

አንተም ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ድንቅ ሰውነት በመቀየር፣ ሕይወትህን እንድትቀይር፣ አሁን ጊዜ ወስደህ፣ ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ በጥንቃቄ መምረጥ አለብህ። ስለዚህ አሁን ትልቁን ሕልምህን በትክክል መምረጥ እንድትችል የሚረዳህን ልምምድ እንሠራለን። በሚቀጥለው ገጽ የቀረበውን ልምምድ በጥንቃቄ መሥራት፣ ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይረዳሃል።

## ፩. ቅድመ ዝግጅት

በዚህ የቅድመ ዝግጅት ደረጃ፣ ትልቁ ሕልምህ ምን መሆን እንዳለበት በመወሰን፣ ሕልምህን በሕልም ካርድህ ላይ ከመጻፍህ በፊት፣ ራስህን በነዚህ አምስት የቅድመ ዝግጅት መመሪያዎች አዘጋጅ።

፩.፩ **ምቹ ቦታ መምረጥ:** በመጀመሪያ ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ በትክክል እንድትፈልግና እንድትወስን ሊረዳህ የሚያስችል ትክክለኛ ቦታ ምረጥ። ለዚህ ልምምድ የምትመርጠው ቦታ፣ በጥሞና ለማሰብ ምቹ የሆነና ከተለያዩ ሊረብሹህ ከሚችሉ ነገሮች ነጻ የሆነ መሆን አለበት።

፩.፪ **ምቹ ጊዜ መምረጥ:** ይህንን ልምምድ ለመሥራት፣ ትክክለኛ ቦታ ብቻ ሳይሆን፣ ትክክለኛ ጊዜም ጭምር መምረጥ አለብህ። ለዚህ ልምምድ የሚሆን ጊዜ ስትመርጥ፣ በትኩረት ለማሰብና ለመወሰን የሚረዳህ መሆኑን እንዲሁም የሚረብሽህ ምንም ነገር እንደሌለ፣ አስቀድመህ ማረጋገጥ አለብህ።

፩.፫ **አስፈላጊ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት:** ልምምዱን ለመሥራት እንዲረዳህ፣ ማስታወሻ መያዣና ብዕር እንዲሁም በትኩረት ለማሰብ የሚረዳህን ምቹ ጠረጴዛና ወንበር አስቀድመህ አዘጋጅ። ከዚህ መጽሐፍ ጋር ተያይዞ ያለውን "ትልቅ ሕልም አለኝ!" የሚለውን የሕልም ካርድህንም ዝግጁ አድርግ።

፩.፬ **ከሰበበኛው መጠንቀቅ:** ይህንን ልምምድ ስትሠራ፣ ከውጪው ዓለም ከሚመጡ የተለያዩ ችግሮች ይልቅ፣ በውስጥህ ያለው የራስህ ሰበበኛ እንዳይረብሽህ መጠንቀቅ አለብህ። ስለዚህ ትልቁ ሕልምህ ምን መሆን እንዳለበት ራስህን ስትፈትሽ፣ የውስጥህ ሰበበኛ የተለያዩ ሀሳቦችንና ጉዳዮችን በማንሳት ሀሳብህን እንዳይከፋፍለው፣ መጠንቀቅ አለብህ።

፩.፭ **አዕምሮን ማዘጋጀት:** ሕልምህን ለመፈለግም ሆነ ለመወሰን የምትጠቀመው አዕምሮህን ስለሆነ፣ አዕምሮህን ለዚህ ድንቅ ልምምድ ንቁና ዝግጁ ማድረግ ይገባሀል። የአዕምሮ መሣሪያ የሆነው ምናብህ፣ ትልቁን ሕልምህን እንድትፈልግና እንድታገኝ የሚያደርግህ ድንቅ የአዕምሮ መሣሪያ ነው። ስለዚህ ትልቁን ሕልምህን ለመፈለግ እና ለማግኘት አስቀድመህ ምናብህን ማዘጋጀት ያስፈልግሀል። (የአዕምሮ መሣሪያ የሆነውን ምናብህን እንዴት እንደምትጠቀምበት ለመረዳት፣ በዚህ መጽሐፍ ፪ኛ ሳምንት፣ ፲፪ኛ ቀን ያለውን "ምናብ የአዕምሮ መሣሪያ" የሚል ምዕራፍ መመልከት ትችላለህ) ከምናብህ በተጨማሪ፣ ሙሉ ሰውነትህን መጠቀም፣ ለምታደርገው ልምምድ ውጤታማነት ትልቅ አስተዋጽዖ ስላለው፣ ቀጥሎ የቀረበውን ልምምድ ለመሥራት፣ ራስህን አዘጋጅ።

## ፪. ሕልምን መፈለግ እና መወሰን

ሕልምህን ለመፈለግ፣ ለመምረጥና ለመወሰን፣ ከላይ ያሉትን አምስት ልምምዶች በመጠቀም ራስህን ስላዘጋጀህ በጣም ደስ ብሎኛል። አሁን ወደ ዋናው ሥራ እንግባ። አሁን፣ በዚህ ክፍል ያሉትን አምስት ልምምዶች በመጠቀም፣ ማሳካት የምትፈልጋቸውን ነገሮችና ማግኘት የምትሻቸውን ውጤቶች ትዘረዝራለህ። ማሳካት እና ማግኘት የምትፈልጋቸውን ነገሮችና ውጤቶች ከዘረዘርክ በኋላ ደግሞ፣ ትልቁን ሕልምህን ከዝርዝሮቹ መካከል በጥንቃቄ ትመርጣለህ።

፪.፩ **ፍላጎትን መዘርዘር:** በቅድመ ዝግጅት ወቅት ባዘጋጀኸው ማስታወሻ ላይ፣ በሕይወትህ ማሳካትና ማግኘት የምትፈልጋቸውን ውጤቶች በዝርዝር ጻፍ። የምትፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝረህ ስትጽፍ፣ አዕምሮህ ትልቅ ሕልም ለማለም ዝግጁ ይሆናል። አዕምሮህ ትልቁን ሕልምህን ለማሰብና ለመፍጠር ዝግጁ ሲሆን ደግሞ፣ ዋናውን እና የምትፈልገውን ትልቁን ሕልምህን ማግኘት ይቀልሀል። ስለዚህ አሁን ልክ እንደ ሕፃን ልጅ ሆነህ፣ በሕይወትህ ማሳካት የምትፈልጋቸውን ነገሮችና ማግኘት የምትሻቸውን ውጤቶች በሙሉ፣ አንድም ሳታስቀር በዝርዝር ጻፋቸው።

፪.፪ **የሕይወት ዘርፎችን በትክክል መረዳት፡** በሕይወታችን ውስጥ ሰባት የሕይወት ዘርፎች አሉ። እነዚህ ሰባት የሕይወት ዘርፎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። የምትፈልጋቸውን ነገሮች በነዚህ ሰባት የሕይወት ዘርፎች ስትመድብ፣ በሁሉም የሕይወት ዘርፎችህ ላይ ሚዛናዊ የሆነ ድልድል ይኖርሀል። ይህም ሕይወትህ የተስተካከለ እንዲሆንና፣ ማስተካከል ያለብህ ጉዳይ ምን እንደሆነ እንድትመረምር ይረዳሀል። የምትፈልጋቸውን ነገሮች ከነዚህ የሕይወት ዘርፎች ጋር ስታነጻጽር፣ በተወሰኑ የሕይወት ዘርፎች ላይ ብቻ በማተኮር፣ አንዳንድ የሕይወት ዘርፎችን እንዳትረሳቸው ይረዳሀል። አሁን ማሳካት የምትፈልጋቸውን ነገሮች እና ማግኘት የምትሻቸውን ውጤቶች በነዚህ ሰባት የሕይወት ዘርፎች እየመደብክ ጻፍ።

፩. መንፈሳዊ ዘርፍ

፪. የጤንነት ዘርፍ

፫. የመልካም ግንኙነት ዘርፍ

፬. የትምህርት ዘርፍ

፭. የሙያ ዘርፍ

፮. የሀብት ዘርፍ

፯. የመዝናናት ዘርፍ

፪.፫ **ቀዳሚ መሆን የሚገባውን ማስቀደም፡** እስከ አሁን ድረስ በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ዙሪያ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ምንም ሳታስቀር በመጻፍ፣ አዕምሮህን ለትልቁ ሕልምህ አዘጋጅተሀል። አሁን ከነዚህ ዝርዝሮች መካከል ዋናውንና ከሁሉም በላይ ቀዳሚ ሊሆን የሚገባውን ማሳካት የምትፈልገውን ነገር በጥንቃቄ መምረጥ ነው። ከመረጥካቸው ምርጫዎች ሁሉ በሕይወትህ ላይ ልዩ ትርጉም ያለውና ትልቅ ልዩነት መፍጠር የሚችለው ምርጫህ የቱ ነው? ከምርጫዎችህ መካከልስ በሕይወትህ ላይ ቀዳሚ መሆን ያለበት ምርጫ የትኛው ነው? በሕይወትህ ላይ ትልቅ ልዩነት መፍጠር የሚያስችልህንና ማግኘት የምትፈልገውን ውጤት ሊያስገኝልህ የሚችለውን ነገር በጥንቃቄ ምረጥ። ይህ በጥንቃቄ የመረጥከው ልዩ ነገር ትልቅ ሕልምህ ነው።

፪.፬ **መደመር፡** በሕይወትህ ከምትፈልጋቸው ነገሮች መካከል "ቀዳሚ መሆን አለበት" ብለህ የወሰንከውን ትልቁን ሕልምህን ስትመርጥ፣ አንዳንዴ ከአንድ በላይ የሆኑ ምርጫዎችን ልታገኝ ትችላለህ። እነዚህ "ቀዳሚ መሆን አለባቸው" ብለህ የመረጥካቸው ነገሮች፣ ከአንድ በላይ ከሆኑብህ፣ ወደ አንድ ሕልምነት ደምራቸው። አሁን የመረጥካቸውን ነገሮች ወይም ውጤቶች በጥንቃቄ በመመልከት፣ እንደ አንድ ሕልም የሚጣመሩበትን ወይም የሚደመሩበትን መንገድ በመፈለግ፣ ወደ አንድ ሕልምነት ደምራቸው። ይህ የፍላጎቶችህ ድምር፣ ስም ሲሰጠው፣ "ትልቅ ሕልም" ይባላል።

፪.፭ **መወሰን፡** አሁን ለመጨረሻ ጊዜ የጻፍካቸውን ዝርዝሮች ደግመህ በመፈተሽ፣ መጨመር የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ጨምር። ከነዚህ ዝርዝር ፍላጎቶችህ መካከል፣ ቅድሚያ መስጠትና መደመር የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ቅድሚያ በመስጠትና በመደመር፣ ዋናውን ምርጫህን ለይተህ ጻፍ። አሁን ትልቁን ሕልምህን በሕልም ካርድህ ላይ በመጻፍ፣ ሕልምህን እንደምታሳካው ወስን።

ትልቁን ሕልምህን፣ በሕልም ካርድህ ላይ ስትጽፈው፣ ማሰብ ያለብህ አንድ ነገር፣ ማሳካት የምትፈልገው ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ ብቻ ነው። በዚህ ደረጃ፣ ሕልምህን እንዴት እንደምታሳካው ምንም አታስብ። ማሰብ ያለብህ የት መሄድ እንደምትፈልግ እንጂ እንዴት እንደምትሄድ መሆን የለበትም። የት መሄድ እንደምትፈልግ በትክክል ከመወሰንህ በፊት፣ እንዴት እንደምትሄድ መጨነቅ ከጀመርክ፣ የትም አትሄድም። ስለዚህ አሁን ሕልምህን እንዴት እንደምታሳካው ሳታስብ፣ ማሳካት የምትፈልገውን ትልቁን ሕልምህን በሕልም ካርድህ ላይ ጻፈው።

## ፫. መመሪያዎች

ትልቁን ሕልምህን ከመጻፍህ በፊት፣ በሕልም ካርድህ ላይ በትክክል መጻፍ ያለብህን ትልቁን ሕልምህን እንዴት አድርገህ መጻፍ እንዳለብህ የሚያሳዩህን ቀጣይ መመሪያዎች በጥንቃቄ ተከተላቸው።

፫.፩ **ትክክለኛ ሕልም፡** በሕልም ካርድህ ላይ የምትጽፈው ሕልምህ፣ ዋናው ትልቁ የምኞት ሕልምህ መሆኑን ርግጠኛ ሁን። በሕልም ካርድህ ላይ የምትጽፈው ትልቅ ሕልም፣ ወደ ሕልምህ የሚወስድ መንገድ ሳይሆን፣ ማሳካት የምትፈልገውና ሕይወትህን የሚቀይር ብቻ መሆን አለበት።

፫.፪ **አሁንነት፡** ትልቁን ሕልምህን በሕልም ካርድህ ላይ ስትጽፈው፣ አሁን እንደተሳካ ወይም አሁን እየተሳካ እንዳለ አድርገህ ጻፈው። ሕልምህን የምትጽፍበት ጊዜም፣ የዋህ ኀላፊ (Past tense)፣ ወይም የአሁን ጊዜ (Present tense) መሆን አለበት። በሕልም ካርድህ ላይ የምትጽፈው ሕልም፣ የተስፋ መንፈስ ያለው ሳይሆን፣ የርግጠኛነት መንፈስ ያለው መሆን አለበት። ሕልምህን እንደ ተስፋ ወይም ወደ ፊት ለማሳካት የምታስበው ሕልም አድርገህ ከጻፍከው፣ ሕልምህ ተስፋ ብቻ ሆኖ ሊቀር ይችላል። ስለዚህ ትልቁን ሕልምህን አሁን እንዳሳካኸውና እንዳገኘኸው አድርገህ መጻፍ አለብህ።

በአገር ደረጃ የምናልመው ትልቅ ሕልም *"ድህነትን ከኢትዮጵያ እናጠፋለን"* የሚል ሳይሆን፣ *"ድህነትን ከኢትዮጵያ አጥፍተናል"* የሚል መሆን አለበት። ይህም እምነት ይባላል። እምነት "ነገ ይሆንልኝ ይሆናል" ብለህ የምትመኘው ሳይሆን፣ በእጅህ ሳይገባ፣ ሳትጨብጠው፣ አጠገብህ ሳይኖር፣ እንደጨበጥከው መቁጠር ነው። "አማኝ ነኝ" ካልክ፣ ሕልምህ እንደተሳካ ካመንክ፣ የምትናገርበት ጊዜ አሁን፣ የምትናገርበትም ቦታ እዚህ መሆን አለበት። የወሬዬ ማሰሪያ ልጥ አማኝ ሁን የሚል ነው።

፫.፫ **አዎንታዊነት፡** በሕልም ካርድህ ላይ የምትጽፈው ሕልም አዎንታዊ ብቻ መሆን ያለበት። አሉታዊ መልዕክት ያለውን ምንም ዐይነት ቃል ተጠቅመህ በካርድህ ላይ ጽፈህ፣ በየቀኑ ብታነበው፣ ይህ አሉታዊ መንፈስ በውስጥህ ስለሚገባ፣ ሕልምህን የምትገልጽባቸው ቃላት አዎንታዊ ብቻ መሆን አለባቸው። ስለዚህ በአገር ደረጃ የምናልመው ሕልም *"ድህነትን ከኢትዮጵያ አጥፍተናል"* ሳይሆን *"ኢትዮጵያ ሀብታም አገር ናት"* የሚል መሆን አለበት። አዎንታዊነት ማለት ይህ ነው።

፫.፬ **ቁጥርና ቀን፡** ትልቁ ሕልምህ ቁንጅ ተስፋ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር፣ እንዲሳካ የምትፈልገውን ሕልም በሚለካ ቁጥርና ቀን አስቀምጠው። በአገር ደረጃ ያለን ትልቅ ሕልም *"ኢትዮጵያ ሀብታም አገር ናት"* የሚል ብቻ ሳይሆን፣ *"ኢትዮጵያ ሀብታም አገር ናት፤ ዛሬ መስከረም 1፣ 2022 ዓ.ም. አንድ ብር ከአንድ ዶላር እኩል ነው!"* የሚል መሆን አለበት።

፫.፭ **ማራኪነት፡** ሕልምህን በሕልም ካርድህ ላይ ስትጽፍ፣ ወደ ልብህ በቀላሉ እንዲገባ፣ ስሜት ጨምረህ ማራኪ በሆነ መንገድ ጻፈው። ትልቁን ሕልምህን በቀላሉ ማስታወስ እንድትችል አድርገህ፣ በአንድ አረፍተ ነገር መጻፍ አለብህ። ቀጥሎ የቀረበው ምሳሌ ማራኪ የሆነ ትልቅ ሕልም እንዴት እንደሚጻፍ ያስረዳል። **"አገሬ በጤንነት፣ በስኬትና በፍቅር የተባረከች አገር ናት! ዛሬ አንድ ብር ከአንድ ዶላር እኩል ነው"**

*ሕልምህን በመጀመሪያ ስታነበው፣ መሠረት የሌለው ተስፋ ሊመስልህ ይችላል። ነገር ግን ደጋግመህ ስታነበው በልብህ ታምነዋለህ። ሕልምህን እንደምታሳካው ስታምን፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ትከፍላለህ። መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ስትከፍል ደግሞ፣ ትልቁ ሕልምህ እውን ይሆናል። ትልቁ ሕልምህ ሲሳካም፣ የበለጠ ትልቅ ሕልም ታስቀምጣለህ።* **አንድ ብር = አንድ ዶላር!**

**"አገሬ በጤንነት፣ በስኬት እና በፍቅር የተባረከች አገር ናት! ዛሬ 01/01/2022 አንድ ብር ከአንድ ዶላር እኩል ሆኗል!"**

******

# የሕልም ካርድ

*ትልቁ ሕልምህ ምን እንደሆነ በመወሰንህ እንኳን ደስ አለህ!*

ከዚህ መጽሐፍ ጋር የሕልም ካርድ ታገኛለህ። ትልቁን ሕልምህን በዚህ የሕልም ካርድ ላይ ለመጻፍና በተደጋጋሚ ሕልምህን ለማንበብ ዝግጁ ነህ? ትልቁን ሕልምህን በጥንቃቄ በመምረጥ፣ በዚህ ካርድ ላይ ስትጽፈውና በየቀኑ ደጋግመህ ስታነበው፣ ሕልምህን እንደምታሳካው በልብህ ታምናለህ። ትልቁን ሕልምህን እንደምታሳካው በልብህ ስታምን ደግሞ፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል በርግጠኛነት ሕልምህን ታሳካዋለህ።

ሕይወትህን ሊቀይር የሚችለው ትልቁ ሕልምህ ምንድን ነው? ከላይ የተወያየንባቸውን ምስጢሮች እና መመሪያዎች በመከተል የመረጥከውን ትልቁን ሕልምህን፣ አሁን በሕልም ካርድህ ላይ ጻፈው። ትልቁን ሕልምህን በዋናው የሕልም ካርድህ ላይ ከመጻፍህ በፊት፣ ከዚህ በታች ባለው የሕልም ካርድ ሳጥን ውስጥ ጻፈው።

ትልቁን ሕልምህን በዚህ ሳጥን ውስጥ ከመጻፍህ በፊት ግን፣ ትልቁን ሕልምህን ውጤታማ በሆነ መልኩ መጻፍ እንድትችል፣ "ሕልምን በሕልም ካርድ ላይ መውቀር" የሚለውን የቀጣይ ገጽ ክፍል አስቀድመህ አንብብ።

## ትልቅ ሕልም አለኝ!

ተመስገን! ዛሬ ____/____/________ እጅግ በጣም ደሰሰሰ... ብሎኛል!
አዎ! ትልቁ ሕልሜ ሰለተሳካ...

## ፱. ሕልምን በሕልም ካርድ ላይ መውቀር

፱.፩ ከዚህ መጽሐፍ ጋር የሕልም ካርድ ታገኛለህ። ትልቁን ሕልምህን ከዚህ መጽሐፍ ጋር ባለው ዋናው የሕልም ካርድህ ላይ ከመጻፍህ በፊት፣ በቀዳሚው ገጽ ባለው "የሕልም ካርድ ሳጥን" ውስጥ ትጽፋለህ።

፱.፪ በቀዳሚው ገጽ ባለው የትልቅ ሕልም ሳጥን ውስጥ፣ "ተመስገን! ዛሬ___|___|______" ብሎ የሚጀምር የቀን መጻፊያ መስመር ታገኛለህ። በዚህ የቀን መጻፊያ መስመር ላይ የምትጽፈው ቀን "ሕልሜ ይሳካል" ብለህ የምታቅድበትን ቀን መሆን አለበት። በቀን መጻፊያ መስመሩ ላይ የምትጽፈው ቀን፣ "ሕልሜ ይሳካል ብለህ የምታቅድበት ቀን" እንጂ "ሕልምህን በካርዱ ላይ የምትጽፍበት የዛሬውን ቀን" አይደለም።

፱.፫ በቀዳሚው ገጽ፣ ባለው ሳጥን ውስጥ "አዎ! ትልቁ ሕልሜ ስለተሳካ..." ከሚለው ክፍት ቦታ ሥር ትልቁን ሕልምህን በጥንቃቄ፣ ድንቅ ስሜት እና ሙሉ እምነት ጨምረህ ውቀረው።

፱.፬ በቀዳሚው ገጽ፣ ትልቁን ሕልምህን ለመጻፍ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ፣ ማራኪ በሆነ መንገድ ሕልምህን መጻፍህን ርግጠኛ ሁን።

፱.፭ ሕልምህን በቀዳሚው ገጽ የትልቅ ሕልም መጻፊያ ሳጥን ውስጥ በጥንቃቄ ከወቀርክ በኋላ፣ የልብህ እውነተኛ ፍላጎት የሆነውን ትልቁን እና የምኞት ሕልምህን፣ በዋናው የሕልም ካርድህ ላይ በእምነት ውቀረው።

## ፲. ሕልምን በልብ መውቀር

ጊዜ ወስደህ እንደ ተመራማሪ በመመራመር፣ ሕልምህ ምን ሊሆን እንደሚገባው በመወሰን፣ ትልቁን ሕልምህን በዋናው ካርድህ ላይ ስለጻፍክ ደስ ይበልህ። ይህ ለስኬት ዋናው ቁልፍ ነው። አሁን ትልቁን ሕልምህን እንደምታሳካ በልብህ ማመን አለብህ። እነዚህን ከታች የተዘረዘሩ አምስት መመሪያዎች በመተግበር፣ ትልቁን ሕልምህን ከወረቀት ባሻገር በልብህ ውቀረው።

፲.፩ የሕልም ካርድህ ሁሌም ቢሆን ከአንተ ጋር አብሮ ይሁን፤ ይዋል፤ ይደር። የሕልም ካርድህ በምንም ምክንያት ከአንተ መለየት የለበትም።

፲.፪ ጥዋት ልክ ከዕንቅልፍህ እንደተነሳህ፣ ቀንህን በምስጋና እንደጀመርክ፣ ትልቁን ሕልምህን ስሜት ጨምረህ በተደጋጋሚ አንብብ። እንደዚህ ማድረግህ፣ አዕምሮህ ሙሉ ቀን ሕልምህን ለማሳካት እንዲሠራ ያደርገዋል።

፲.፫ ሙሉ ቀን፣ ጊዜ ባገኘህ ቁጥር፣ ትልቁን ሕልምህን ደጋግመህ በማንበብ፣ ያለምከውን ሕልም እንደምታሳካው በልብህ እመን።

፲.፬ የማትፈልገውና አሉታዊ ነገር ሲያጋጥምህ፣ ትልቁን ሕልምህን ደጋግመህ አንብበው። ትልቁ ሕልምህ፣ ከተለያዩ አሉታዊ ስሜቶች አውጥቶ፣ ወደ አዎንታዊ እና ሕልምህን ወደምታሳካበት አስተሳሰብ ይመልስሀል።

፲.፭ ማታ ከመተኛትህ በፊት፣ ትልቁን ሕልምህን ስሜት ጨምረህ በተደጋጋሚ አንብበው። አዕምሮህ አንተ ስትተኛ፣ ሌሊቱን ሙሉ ሕልምህን የሚያሳካበትን መንገዶች በመፈለግ፣ ሕልምህን የምታሳካበትን መንገድ ይቀምርልሀል።

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። አባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረክኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋናና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሀል!

## ቀን ፮

*******

# ፓራዳይም

*"ፓራዳይምህን ስትቀይር፣ ሕይወትህ ሙሉ በሙሉ ይቀየራል፤ መቀየሩ ደግሞ ዘለቄታዊ ነው!"*

አንድ ሕፃን ልጅ በእስር ቤት ውስጥ ተወልዶ፣ እዚያው እስር ቤቱ ውስጥ ቢያድግ፣ ከእስር ቤቱ ውጪ ሌላ ሕይወት እንዳለ ስለማያውቅ፣ ሕይወቱ "የነጻነት" ሳይሆን "የባርነት" ነው የሚሆነው። ይህ ልጅ በእስር ቤት እንደተወለደ፣ ከእስር ቤቱ ውጪ ደግሞ ሌላ ሕይወት እንዳለ ያወቀ ዕለት ግን፣ ከባርነት ነጻ የመውጣት ዕድል እንዳለው ማሰብ ይጀምራል፤ በነጻነት ለመኖርም ይሞክራል። ከሚኖርበት የባርነት ሕይወት ውጪ ሌላ የነጻነት ሕይወት መኖር እንደሚችል ማወቁ ደግሞ፣ ነጻነትን እንዲፈልግ፣ ለነጻነቱ እንዲታገልና ነጻ እንዲወጣ አቅም ይሰጠዋል።

ሁላችንም፣ ምንም እንኳ በተለየ ቅርጽ ይሁን እንጂ፣ በእስር ቤት ተወልዶ እንዳደገው ልጅ፣ በአንድ ዐይነት እስር ቤት ውስጥ ነው ያደግነው። ይህ ያደግንበት እስር ቤት ግን በብረት የታጠረ አይደለም፤ ይልቁንም ስውር እና ረቂቅ ነው። ከዚህም የተነሳ መውጫ መንገዱን እስካላወቅን ድረስ፣ ከእስር ቤቱ መውጣት እጅጉን ከባድ ነው። ካለንበት እስር ቤት "ምህረት ይሰጠናል" ብለን ተስፋ የምናደርግበት ስላልሆነም፣ መውጫ መንገዱን ማግኘት ወሳኝ ነው። በርግጥ ከእስር ቤቱ ለመውጣት ከፈለግን፣ መውጣት እንችላለን። መውጫው መንገድ ግን አንድና አንድ ብቻ ነው። ከእስር ቤት ስለ መውጫው መንገድ ከመነጋገራችን በፊት፣ ይህ እስር ቤት ምን እንደሆነና በዚህ እስር ቤት እንዴት እንደታሰርን እንመልከት።

ያደግንበት እስር ቤት የአዕምሮ እስር ቤት ነው። ይህ የአዕምሮ እስር ቤት "ፓራዳይም" ወይም "የልቦና ውቅር" ይባላል። ሁላችንም የሰው ልጆች ታስረን የኖርንበት የየራሳችን የአዕምሮ እስር ቤት አለን። ፓራዳይም፣ ከልጅነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በአዕምሯችን የተገነባ የልማዶች፣ እምነትና አስተሳሰብ ድምር ሆኖ፣ ማንኛውንም በሕይወታችን የምናደርገውን እንቅስቃሴና ውጤት የሚቆጣጠር፣ በድብቁ አዕምሯችን የተገነባ የአዕምሮ ፕሮግራም ነው። በመሆኑም ፓራዳይማችን ወይም የአዕምሮ ፕሮግራማችን ካልተቀየረ፣ በሕይወታችን የምናደርገው እንቅስቃሴና የምናገኘው ውጤት፣ እንዲሁም ሕይወታችን ራሱ አይቀየርም፤ ቢቀየር እንኳ፣ መቀየራችን ዘለቄታነት አይኖረውም። ፓራዳይማችን ሲቀየር ግን ሕይወታችን ይቀየራል፤ መቀየራችንም ዘለቄታነት ይኖረዋል። ማንኛውም ሰው ፈጣሪ የሰጠውን ድንቅ አቅምና ችሎታ በመጠቀም፣ ድንቅ ሕይወት በመኖር፣ ትልቅ ሕልሙን ማሳካት ይችላል። የአብዛኛው ሰው ስኬት ግን፣ በሰውዬው ውስጥ በተገነባው ፓራዳይም ቁጥጥር ሥር ያለ ነው። ማንኛውም ሰው የሚያደርገውን ነገር ሁሉ የሚያደርገው፣ አሰበውም አላሰበውም፣ በፓራዳይሙ ቁጥጥር ስር ነው። በዚህም ማንኛውም ሰው የሚኖረው ኑሮ፣ ፓራዳይሙ በተገነባበት የሕይወት ልክ ነው። በፈጣሪ አምሳል የተፈጠረው ድንቅ ሰው የሚኖረው፣ እንደ "ድንቅ አፈጣጠሩና አቅሙ" ሳይሆን እንደ "ፓራዳይሙ" ነው።

የሰው ልጅ በብዙ ጉዳዮች ላይ የአቅምም ሆነ የዕውቀት ችግር የለበትም። ሰው የብዙ ነገሮችን ምንነት፣ የአሠራር ሂደት፣ ጥቅምና ጉዳት በደንብ ያውቃል። ችግሩ የሚያውቀውን ዕውቀት በተግባር ላይ አለማዋሉና አለመጠቀሙ ላይ ነው። ድርጊቶቻችንና ተግባሮቻችን በፓራዳይሞቻችን ቁጥጥር ሥር ስለሆኑ፣ ዕውቀታችን በጨመረ ቁጥር፣ ድርጊቶቻችንና ተግባሮቻችን በዚያው ልክ ሲቀየሩ አይታይም። የሰው ልጅ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዙ ዕውቀት ያከማቻል፤ ያከማቸውን ዕውቀት ግን ባከማቸው ልክ አይጠቀምበትም። የሰው ልጅ መቀየር የሚችለውና በሕይወቱ ላይ ትልቅ ለውጥ ማምጣት የሚችለው ግን፣ ተጨማሪ ዕውቀትን በመሰብሰብ ሳይሆን፣ ፓራዳይሙን በመቀየር ነው።

ይህን እውነት ለመረዳት ብዙ ሩቅ መሄድ አያስፈልግህም። በዙሪያህ ያሉ ሰዎችን "ደስተኛና ስኬታማ የሆነ ሕይወት ለመኖር ምን ያስፈልጋል?" ብለህ ብትጠይቃቸው፣ ከሚመልሱት መልስ፣ ከምትጠብቀው በላይ ዕውቀት እንዳላቸው ትገነዘባለህ። ነገር ግን ያንን ዕውቀት ተጠቅመው ሕይወታቸውን ሲለውጡ አታይም። የሰው ልጅ የሚፈልገውን ደስተኛና ስኬታማ ሕይወት ለመኖር የሚያስችለው ዕውቀትና አቅም እያለው፣ የሚፈልገውን ሕይወት አይኖርም። "ለምን?" ቢባል ለውጥ ከዕውቀት ያለፈ ነገር ስለሚጠይቅ ነው።

ለምሳሌ "ጤናማና ጠንካራ ሰውነት እንዲኖረኝ ምን ማድረግ አለብኝ?" ብለህ ሰዎችን ብትጠይቃቸው፣ ካላቸው ዕውቀት ተነስተው፣ ብዙ ነገር ሊያስተምሩህ ይችላሉ። "በቀን ሁለት ሊትር ውሃ መጠጣት አለብህ፤ በሳምንት ለአምስት ቀናት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ አለብህ፤ የተመጣጠነ ምግብ መመገብ አለብህ፤ በቀን ከስድስት እስከ ስምንት ሰዓታት መተኛት አለብህ..." በማለት ጠንካራና ጤናማ ሰውነት እንዲኖርህ የሚያደርግህን ዕውቀት ያካፍሉሀል። ዕውቀቱን ያካፈለህን ሰው ግን፣ "አንተ እነዚህን የነገርከኝን ነገሮች ታደርጋቸዋለህ?" ብለህ ብትጠይቀው፣ "ውይ! እኔ እንኳን አላደርጋቸውም" ብሎ ሊመልስልህ ይችላል። ለዚህ ነው "ሰው ያለበት የዕውቀት ሳይሆን የድርጊት ችግር ነው" የምለው።

ማንኛውም ተማሪ፣ አስተማሪ፣ ነጋዴ፣ ሸማች፣ አለቃ፣ ምንዝር፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ጸሐፊና ሠራተኛ ባለበት የሥራ መስክ፣ በሕይወቱ የተሻለ ውጤት እንዲያገኝ የሚያስችለው በቂ ዕውቀትና አቅም አለው። ቢጠየቅም፣ የሚያውቀውን ለሌሎች ሰዎች በማስተማር፣ ሙሉ ቀን ዕውቀቱን ማካፈል ይችላል። ይህንን ትምህርትና ዕውቀት ግን ወደ ተግባር በመቀየር የተሻለ ውጤት ሲያገኝ አይታይም። ሕይወታችን የሚቀየረው ዕውቀታችንን በማሳደግ ሳይሆን፣ ድርጊታችንንና ተግባራችንን በመቀየር ነው። መርሳት የሌለብን ወሳኝ ነጥብ፣ ተግባርና ድርጊታችን ሁሌም ቢሆን በፓራዳይማችን ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ነው። ታዲያ ተዓምር መሥራት የምንችለው፣ ከፓራዳይም እስር ቤት ነጻ ስንወጣ ብቻ ነው።

ሕጻናት እያለን ፓራዳይም ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚሠራ እያወቅን አድገን ቢሆን፣ በጣም ውጤታማ እንሆን ነበር። ነገር ግን የፓራዳይም ጽንሰ ሀሳብ ለዘመናት ከብዙ ሰዎች የተደበቀ ምስጢር ሆኖ ስለቆየ፣ ወላጆቻችን፣ አስተማሪዎቻችን፣ አለቆቻችንና ሌሎች ሕይወታችንን እንድንቀይር የሚመከሩን ሰዎች፣ ፓራዳይማችንን እንድንቀይር ሳይሆን፣ ባለን ዕውቀት ላይ ሌላ ዕውቀት እንድንጨምር ነው የሚረዱን። የሰው ልጅ ሕይወቱን ለመቀየር፣ አዳዲስ ዕውቀቶችን መጨመር ሳይሆን፣ የሚያውቀውን ዕውቀት በመጠቀም ድርጊቶቹንና ልማዶቹን መቀየር ነው የሚያስፈልገው።

በፓራዳይም ቁጥጥር ሥር ያሉ ድርጊቶቻችንና ልማዶቻችን ሲቀየሩ ብቻ ነው፣ ሕይወታችን ሊቀየር፣ ውጤታችንም ሊያምር የሚችለው። ነገር ግን አስተዳደጋችን ድርጊቶቻችንን፣ ልማዶቻችንንና ፓራዳይማችንን እንድንቀይር ሳይሆን፣ ባለን ዕውቀት ላይ ሌላ ዕውቀት እንድንጨምር ብቻ ነው የሚያደርገው። ያለህን ዕውቀት ሳትጠቀምበት ሌላ ዕውቀት መጨመር ብቻውን ደግሞ ዘለቄታ ያለው ለውጥ አያመጣልህም።

አንድ ሕፃን ልጅ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ ሁልጊዜ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ፣ ከመምህራኑ የሚሰጠው ዕውቀት ነው። ከአንድ ክፍል ወደሚቀጥለው ደረጃ ሲሻገርም፣ ባለው ዕውቀት ላይ ተጨማሪ

ዕውቀት ነው የሚጨመርለት። የትምህርት ቤቶችን የአሠራር ሥርዓት ስንመለከትም፣ ትኩረታቸው የተማሪዎችን ተግባርና ድርጊት መቀየር ላይ ሳይሆን፣ ዕውቀታቸውን መጨመር ላይ ነው። አንድ ተማሪ ዓመቱን ሙሉ ዕውቀት ከሰበሰበ በኋላ ፈተና ይሰጠዋል። ፈተናው ዕውቀት ተኮር ስለሆነ፣ ተማሪው የፈተናውን ጥያቄዎች መመለስ የሚያስችለው ዕውቀት ካለው፣ በቂ ነጥብ በማግኘት ወደሚቀጥለው ክፍል ይዛወራል። በዚህ መንገድም ከክፍል ወደ ክፍል እየተሻገረ ብዙ ዕውቀት በመሰብሰብ፣ በየክፍሉ የሚቀርቡለትን የፈተና ጥያቄዎች መመለስ ሲችል፣ በስተመጨረሻ ይመረቃል።

ትምህርቱን ጨርሶ፣ ተመርቆ ከወጣ በኋላ ግን፣ የሚወደውን ሥራ ማግኘት በጣም ይከብደዋል። በአንጻሩ አንድ ስምንተኛ ክፍል ያልጨረሰ ሰው፣ የሚገርም ሥራ በመሥራት፣ የሚፈልገውን ሕይወት ይኖራል። በርግጥ ስምንተኛ ክፍል ያልጨረሰ ሰው ሥራ ሊያጣ፣ የተመረቀ ሰውም የሚፈልገውን ሥራ ሊሠራ ይችላል። ዋናው ቁም ነገር "ለብዙ ዓመታት ዕውቀት በመሰብሰብ ብቻ የስኬት ቁልፍ አይገኝም" የሚለውን እውነት ማስተዋል ነው። የስኬት ውጤት፣ በዕውቀት ብቻ ሳይሆን በድርጊትና በተግባር ጭምር የሚታይ ነው። ትምህርት ቤት የሚረዳን፣ ድርጊቶቻችንንና ተግባሮቻችንን በመቀየር፣ ማንነታችንንና አስተሳሰባችንን እንድንቀይር ሳይሆን፣ በዕውቀት ላይ ሌላ ዕውቀት እንድንጨምር ነው።

ከትምህርት ቤት ከወጣን በኋላም ከቤተሰቦቻችን፣ ጓደኞቻችንና አለቆቻችን ብዙ ምክርና ዕውቀት እንሰበስባለን። ነገር ግን ዕውቀታችን እንጂ ተግባራችን ሲቀየር አይታይም። ምናልባት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመውሰድ ትንሽ ልንቀየር እንችላለን። ከሳምንት በኋላ ግን ወደነበርንበት እንመለሳለን። አንዳንድ ሰው የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ ብዙ ዕውቀት ይሰበስብና ትላልቅ ለውጦችን ማድረግ ይጀምራል። ከወር በኋላ ግን ወደ ተለመደው ሕይወቱ ይመለሳል። የዚህ ሁሉ ዙረት ማረፊያ፣ "የምንፈልገውን ሕይወት ለመኖር፣ ራሳችንንም ለመቀየር ቀዳሚው፣ ዋናውና አስፈላጊው ነገር ዕውቀት ሳይሆን፣ የፓራዳይም መቀየር ነው" የሚለው ነው። አንተነትህን ፈልገህ የምታገኘውና የሚገባህን ኑሮ የምትኖረው፣ የሕይወት ከህሎት የሆነውን የመኖሪያ ጥበብ፣ ፓራዳይምህን፣ ቀይረህ ስትገኝ እንጂ፣ ዕውቀት ስትቃርም አይደለም። ማወቅ፣ ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ ዋስትና አይደለም፤ ማወቅ ላደረግከው ወይም ላላደረግከው ነገር ራስህን መገምገሚያ፣ መመልከቻና መፈተሻ መሣሪያ እንጂ።

ይህን መጽሐፍ ስታነብ ዕውቀት ነው የምትጨምረው። በዚህ መጽሐፍ የምትማራቸው ምስጢራት ግን፣ ብዙ ሰው በፓራዳይሙ ምክንያት ወደ መቃብሩ ይዞት የሚሄደውን ችግር ይፈቱልሀል። በርግጥ በዚህ መጽሐፍ በርካታ የሚጠቅሙህን ምስጢሮች ትማራለህ። የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ግን ባለህ ዕውቀት ላይ ሌላ ዕውቀት መጨመር ሳይሆን፣ ከዚህ በፊት የምታውቃቸውን ዕውቀቶችና ከዚህም በኋላ የምትማራቸውን ዕውቀቶች ወደ ተግባር በመቀየር፣ በሕይወትህ ላይ የምትፈልገውን ውጤት ማስጨበጥ ነው። የመጽሐፉ ዋና ትኩረትም ፓራዳይምህን መቀየር ላይ ነው። ምክንያቱም ፓራዳይምህ ሲቀየር ድርጊትህ፣ እምነትህ፣ አስተሳሰብህና ውጤትህ ይቀየራል። በሕይወትህ ስኬታማ ለመሆን፣ በፓራዳይምህ ተጣርቶ የሚያልፈውን ዕውቀት ሳይሆን፣ ማጣሪያውን ፓራዳይምህን ራሱን ነው መቀየር ያለብህ።

ስለ ፓራዳይም በደንብ መረዳት ያለብህ ወሳኝ ነገር፣ በውስጥህ ያለ ጠላት መሆኑን ነው። ፓራዳይም አቅምህን፣ ዕውቀትህን፣ ድርጊትህንና ተግባርህን ብቻ ሳይሆን በውስጥህ ያለውን የሚገፋፋህን ስሜትና ቀልብህን የሚቆጣጠር ፕሮግራም ነው። ብዙ ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ "ዳዊት ድሪምስ፣ የምትለው ነገር ገብቶኛል። የፓራዳይም ችግሬንም አውቄዋለሁ፤ ከዚህ በኋላ ፓራዳይሜን በመቀየር ሕይወቴን እቀይራለሁ" ይላል። ነገር ግን ፓራዳይም ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚሠራ ካልተረዳ፣ ፓራዳይሙ ሀሳቡንና ስሜቱን በመቆጣጠር፣ የሰውዬው ሕይወት እንዳይቀየር፣ ወደነበረበት ሊመልሰው ይችላል። ስለዚህ ከልጅነትህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትፈልገውንና የሚያሳድግህን ነገር ሳይሆን፣ ፓራዳይምህ የሚያዝህን ነገር ለምን እንደምታደርግ መፈተሽህ፣ የአዕምሮህን እስር ቤት በትክክል እንድትረዳውና ከፓራዳይምህ ለአንዴና ለዘለዓለም ነጻ እንድትወጣ ይረዳሃል።

# የፓራዳይም ስውር ኀይል

ፓራዳይም ሕይወታችንን የሚቆጣጠር ስውር ኀይል አለው። የፓራዳይምን በዐይን የማይታይ ስውር የመቆጣጠር ስልት ስንረዳ፣ ፓራዳይማችንን ማሸነፍ እንችላለን። አሁን ፓራዳይም ከልጅነታችን ጀምሮ እንዴት አድርጎ በዚህ ስውር ስልቱ እንደሚቆጣጠረን የተለያዩ ምሳሌዎችን በማጣቀስ እንመለከታለን።

**ሕፃን ልጅ፡** ለምሳሌ አንድ ሕፃን ልጅ፣ ወላጆቹ ቤት ውስጥ በሌሉበት ሰዓት ዘና ብሎ ሲጫወት፣ በጨዋታው ይመሰጥና ቤት ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች፣ ምናልባት ሊበላሹ ቢችሉ እንኳ፣ እንደሚመቸው አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። ከዚያም ወላጆቹ ወደ ቤት ሲመለሱ፣ ቤቱ ተበለሻሽቶ ሲያገኙት በብስጭት፣ "ለምንድን ነው ቤቱን እንደዚህ ያበላሸሽው? ለምን እንደዚህ አደረግክ?" ብለው ሲጠይቁት፣ የሚመልስላቸው መልስ እና ሰበብ፣ እነሱ ባላቸው ዕውቀት፣ አጥጋቢና አስደሳች ስለማይሆን፣ የተለያየ ምክር፣ ዕውቀት፣ ቅጣትና ማስጠንቀቂያ ለልጁ ይሰጠዋል። ልጁም የተሰጠውን ምክር በመቀበል፣ በድጋሚ ላለመቀጣት፣ ከወላጆቹ ጋር ተስማምቶ ማስጠንቀቂያውን በመቀበል፣ ከዚህ በኋላ ሲጫወት ቤት ላለማበላሸት ቃል ይገባል። በሚቀጥለው ቀን፣ በድጋሚ በጨዋታው ሲመሰጥ ግን የትናንቱን ምክርና ቅጣት ረስቶ፣ እንደገና ቤቱን ያበላሻል። ከዚያም ወላጆቹ "ለምንድን ነው እንደዚህ ያደረግከው?" ብለው ሲጠይቁት አሁንም የማያረካ መልስ ነው የሚመልሰው።

ልጁ፣ ቤት ውስጥ ሲጫወት፣ ቤቱን ማበላሸት እንደሌለበት ያውቃል። ቤቱን ማበላሸትም ሆነ ቤቱን የሚያበላሽ ነገር መንካትም አይፈልግም። ነገር ግን እየተጫወተ እያለ፣ የሆነ ውስጣዊ ድምጽ፣ አንዳንድ ቤቱን ሊያበላሹ የሚችሉ ነገሮችን እንዲያደርግ ያሳምነዋል። ከዚያም ወደተለመደው ቤት የሚያበላሽ ጨዋታው ይገባል። "ለምንድን ነው ስትጫወት ቤቱን ያበላሸሽው?" ተብሎ ሲጠየቅ፣ አሁንም እንደ ትናንቱ ይመልሳል። ልጁ ቤቱን ሳያበላሽ መጫወት እየፈለገ፣ ለምን እንደሚያበላሽ አያውቅም። ምክር የሚሰጡት ወላጆቹም ምክንያቱን አያውቁም። አየህ! ፓራዳይም በጣም ስውርና ኀይለኛ ነው!

**ትምህርት ቤት፡** ይህ ልጅ፣ ትምህርት ቤት ሄዶ ከረበሸ ወይም ማድረግ የሌለበትን ነገር ካደረገ፣ አስተማሪው አስፈላጊ የሚለውን ምክር ሰጥቶ፣ ያስጠነቅቀዋል፤ አልያም ይቀጣዋል። ልጁም "ከዛሬ በኋላ አልረብሽም፤ ማድረግ የሌለብኝንም ነገር አላደርግም" ብሎ ምሎ ተገዝቶ፣ ከቅጣቱ ይተርፋል። በሚቀጥለው ቀን ግን፣ ወደ መረበሹና ማድረግ የሌለበትን ነገር ወደ ማድረጉ ይመለሳል። አስተማሪው "ለምንድን ነው እንደዚህ የምታደርገው?" ብሎ በድጋሚ ሲጠይቀው፣ ልጁ በዝምታ ይዋጣል። ልጁ ራሱ መረበሽ ሳይፈልግ፣ ለምን እንደሚረብሽ አያውቅም። ምክር የሚሰጡት አስተማሪዎቹም ለምን እንደሚረብሽ አያውቁም። የሁሉም ሰዎች መፍትሄ ማግኘት አለመቻል ምክንያት ግን፣ ውስጣቸው የተመሸገው "ፓራዳይም" የሚባለው ጠላት ነው!

**ውፍረት፡** አንድ ውፍረቱን በጣም መቀነስ የሚፈልግ ሰው፣ "ከዛሬ ጀምሮ የሚያስወፍሩኝን ምግቦች አልበላም! ቴሌቪዥን ላይ ቁጭ ብዬ ማምሸቱን ትቼ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አደርጋለሁ" ብሎ ይወስንና ለቤተሰቦቹ ይነግራቸዋል። ድንገት ከተወሰኑ ቀናት በኋላ፣ ቴሌቪዥን ፊት ቁጭ ብሎ የሚያወፍረውን ምግብ ሲመገብ ቤተሰቦቹ አግኝተውት "ለምንድን ነው እንደዚህ የምታደርገው? 'ከአሁን በኋላ ሕይወቴ ተቀይሯል!' ብለህ አልነበር እንዴ?" ብለው ቢጠይቁት፣ የሚመልሰው መልስ፣ ሕፃኑ ልጅ ከመለሰው መልስ የሚለይ አይደለም። ሰውዬው መወፈር ሳይፈልግ፣ በተደጋጋሚ የሚያስወፍረውን ምግብ እንዲበላ የሚያስደርገውን ምክንያት እሱም እንደ ሕፃኑ አያውቅም። ፓራዳይም ሰውዬው ማድረግ የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ በመገፋፋት፣ የማይፈልገውን ውጤት እንዲያገኝ ያስገድደዋል!

**ሱስ፡** አንድ በሱስ የተጠመደ ሰው ሱሱ እንደሚጎዳውና ሕይወቱን አደጋ ውስጥ ሊከትበት እንደሚችል በማወቅ፣ "ከዛሬ በኋላ በጭራሽ አልጠጣም! አላጨስም! አልቅምም! ሱስ ወደተባለ ነገር ፊቴን አላዞርም"

ብሎ ይወስናል። እንዲያውም ሱሰኛ ወደሆኑ ጓደኞቹና የሱስ ቦታዎች ጭምር እግሩ እንደማይረግጥ ይወስናል። ከቀናት በኋላ ግን ከሱሰኛ ጓደኞቹ ጋር ሱሳቸውን ወደሚያጧጡፉበት፣ "በጭራሽ ድርሽ አልልም!" ብሎ ወደ ሸለለበት፣ የተዋቸውን ጓደኞቹንና የተወውን ሱሱን ወደሚያገኝበት ቤት ተመልሶ ይሄዳል። ከዚያም ራሱን ሱስ ውስጥ ተመልሶ ሲያገኘው ግራ ይገባዋል። "እኔ ግን ለምንድን ነው የማልቀየረው?" ብሎ መቀየር ባለመቻሉ ያዝናል፤ ይጸጸታልም። ፓራዳይም ሰውን ወደለመደው፣ ነገር ግን ወደሚጎዳው ቦታና ሁኔታ እንዲሄድ ይገፋፋል! ለምን ቢባል ፓራዳይም ምክንያታዊ ሳይሆን፣ ልማዳዊ በመሆኑ ነው።

ማርፈድ፡ ፓራዳይምን ለመረዳት አንድ ሁሌም ወደ ቢሮ አርፍዶ ስለሚገባና አለቃው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ስለሰጠው ሰው ምሳሌ ልጨምርልህ። ይህ አርፋጅ ሰውዬ ድጋሚ ማርፈድ ስለማይፈልግ፣ "ከነገ ጀምሮ በጥዋት እነሳለሁ፤ ከሥራ ባልደረቦቼም ቀድሜ ሥራ ቦታዬ ላይ እደርሳለሁ" ብሎ ይወስናል። በሚቀጥለው ቀን ግን፣ ልክ እንደ ትናንቱ አርፍዶ ይገባል። ከዚያም አለቃው "ለምንድን ነው ያረፈድከው?" ብሎ ሲጠይቀው፣ የተለያዩ ሰበቦቹን ይደረድራል። ሁሌም የሚያረፍድበት ምክንያት ግን ፓራዳይም መሆኑን እሱም ይሁን ምክር፣ ማስጠንቀቂያና ቅጣት የሚሰጠው አለቃው አያውቁም። ግለሰቦች፣ ድርጅቶችም ሆኑ አገር የማይቀየሩበት ምክንያት ፓራዳይም የሚሠራውን ሥራ ጠንቅቆ ባለመረዳት ነው።

ብዙ ሰው የማይፈልገውን ነገር በማድረግ የሚፈልገውን ውጤት ባለማግኘቱ ይቆጨዋል። ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን የማይፈልገውን ውጤት የሚያስገኘውን ነገር በድጋሚ ያደርጋል። ወደ ስኬት እና ደስታ የሚወስደውን፣ ማድረግ የሚገባውን ነገር እያወቀ ስለማይተገብረው፣ የማይፈልገውን ውጤት እያጨደ፣ የማይፈልገውን ሕይወት ይኖራል። ቅሉ "ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል!" አይደል ተረቱስ። አንተም በዚህ ዐይነት ተመሳሳይ ሕይወት ውስጥ ካለህ፣ "ለምንድን ነው እያወቅኩ የምታበላሸው?" ተብለህ ብትጠየቅ የምትመልሰው ግራ ሊገባህ ይችላል። የፓራዳይምን የአሠራር ምስጢር ካላወቅን፣ ሕይወት እንቆቅልሽ ስለምትሆንብን፣ ፓራዳይም ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚሠራና እንደሚቀየር ጊዜ ወስደን እንመርምር።

# ፓራዳይም ምንድን ነው?

አስቀድመን፣ ፓራዳይም ከልጅነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በአዕምሯችን የተገነባ፣ የልማዶቻችን፣ እምነቶቻችንና አስተሳሰባችን ድምር ሆኖ፣ ማንኛውንም በሕይወታችን የምናደርገውን እንቅስቃሴና ውጤት የሚቆጣጠር የአዕምሮ ፕሮግራም መሆኑንና ፓራዳይማችን ካልተቀየረ፣ ሕይወታችንና በሕይወታችን የምናገኘው ውጤት እንደማይቀየር፣ ቢቀየርም ዘለቄታነት እንደማይኖረው አይተናል።

በመሠረቱ ፓራዳይም መጥፎ ነገር አይደለም። ትክክለኛ ፓራዳይም ሲኖረን፣ ሕይወታችን በጣም ቀላል እና ስኬታማ መሆን ይችላል። መጥፎ ፓራዳይም ካለን ደግሞ ሕይወታችን በተቃራኒው ከባድ፣ አድካሚ፣ ስኬት የናፈቀው እና ውጣ ውረድ የበዛበት ነው የሚሆነው። አሁን ሕይወትህ በከባድና በማትፈልጋቸው ውጤቶች የተሞላ ከሆነ፣ ችግሩ የፓራዳይምህ መሆኑን መገንዘብ አለብህ። አሁን እያገኘህ ያለህቸውን ውጤቶች መቀየር የምትፈልግ ከሆነ፣ ፓራዳይምህን መቀየር አለብህ። በአዕምሮህ ድንቅ ፓራዳይም በጥንቃቄ ስትገነባ፣ ሕይወትህ ስኬታማና በምትፈልጋቸው ውጤቶች የተሞላ ይሆናል።

ፈጣሪ ሲፈጥረን፣ ፓራዳይማችን ጥሩ እንዲሆንና ለእድገታችን እንዲያመች አድርጎ ነው የፈጠረን። በየቀኑ በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን እንደ መተንፈስ ያሉ መሠረታዊና በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን ነገሮች፣ እያንዳንዳቸውን እያሰብን እና እያሰላሰልን ብናደርጋቸው፣ እጅግ በጣም ያደክሙን ነበር። ፓራዳይም የሚጠቅመን፣ በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን ነገሮች፣ በተደጋጋሚ አስበንና ሆን ብለን ከምናደርጋቸው ይልቅ፣ ያለ ብዙ ሀሳብ፣ ቀሎን እንድናደርጋቸው ለማድረግ ነው።

ፓራዳይም ነገሮችን እንዴት አድርገን እንደምናደርጋቸው ከመጀመሪያ ጀምሮ ያጠናል። ከዚያም እነዚህን በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን ነገሮች ለማድረግ የምንጠቀምባቸውን ዘዴዎች፣ በድብቁ አዕምሯችን ይመዘግባቸዋል። ፓራዳይም፣ እነዚህን ሁሌም ማድረግ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ደጋግመን ማድረግ ስንፈልግ፣ ያለ ምንም ሀሳብ፣ ከድብቁ አዕምሮ መዝገብ አንስቶ፣ በቀላሉ እንድናደርጋቸው ይረዳናል። ልብ ብለህ ራስህን ከታዘብከው፣ ከጥዋት እስከ ማታ በየቀኑ ስትነሳ፣ ስትበላ፣ ስትጠጣ፣ ስትተነፍስ፣ ስትራመድ፣ መኪና ስትነዳና ስትተኛ የምታደርገውን ሁሉ የምታደርገው፣ አስበህ ሳይሆን ፓራዳይምህ ውስጥ የተመዘገበው ፕሮግራም ነገሮችን ወዲያውኑ (Automatically) ስለሚያደርግልህ ነው።

የፓራዳይም ጥቅምም ችግርም አንድ ነው። ፓራዳይም አንድ ነገር ከለመደ፣ ከለመደው ነገር ውጪ ያለ ሌላ ነገር አይፈልግም። ድንቅ ፓራዳይም ካለህ፣ እንቅስቃሴዎችህ ሁሉ ድንቅ እንዲሆኑ በማድረግ ድንቅ ውጤት እንዲኖርህ ያደርጋል፤ በምንም ተዓምር ወደ ተራ ሰውነት እንድትቀየርም አይፈልግም። በአንጻሩ ተራ ፓራዳይም ካለህ ደግሞ፣ እንቅስቃሴዎችህ ሁሉ ተራ እንዲሆኑ በማድረግ፣ ተራ ውጤት እንዲኖርህ ያደርጋል፤ በምንም ተዓምር ወደ ድንቅነት እንድትቀየርም አይፈልግም። ተራ ፓራዳይም፣ በምኞት የሚወጠር የስኬት ዘሀ ሳይሆን፣ በድግግሞሽ የሚገነባ የአንተነትህ መሠረት፣ የነፍስህም መጠሪያ ነው።

ፓራዳይም ከልጅነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወታችን ትልቅ ተጽዕኖ የነበራቸው ሰዎች፣ እኛ ምንም ሳናስብ በአዕምሯችን የገነቡት፣ ድብቁ አዕምሯችን ውስጥ የተቀመጠ የልማዶቻችንና ውጤቶቻችን ድምር ነው። አሁን መጠየቅ ያለብህ ዋናው ጥያቄ "በአዕምሮዬ ምን ዐይነት ፓራዳይም ነው የተገነባው?" የሚል መሆን አለበት። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፣ አሁን እየኖርከ ያለኸውን ሕይወትና የምታገኘውን ውጤት በጥንቃቄ መመልከት ነው የሚያስፈልግህ። እያገኘህ ያለኸው ውጤት እና የምትኖረው ሕይወት ድንቅ ከሆነ፣ ድንቅ ፓራዳይም አለህ ማለት ነው። ነገር ግን ሕይወትህ ተራ፣ እያገኘህ ያለኸው ውጤትም ተራ ከሆነ፣ ተራ ፓራዳይም አለህ ማለት ነው።

በአዕምሮህ የተገነባው ፓራዳይም ተራ ከሆነ፣ ፓራዳይምህን በፍጥነት መቀየር አለብህ። አሁን ያለህን ተራ ፓራዳይም በማሸነፍ በአዕምሮህ እንዴት አድርገህ ድንቅና አዲስ ፓራዳይም መገንባት እንደምትችል አሳይሀለሁ። በአዕምሮህ አዲስና ድንቅ ፓራዳይም እንዴት አድርገህ መገንባት እንደምትችል ለመረዳት፣ የድሮ ፓራዳይም በአዕምሮ ውስጥ እንዴት አድርጎ እንደሚገነባ መረዳት ያስፈልግሀል። ስለዚህ የድሮ ፓራዳይምህ እንዴት አድርጎ በአዕምሮህ ውስጥ እንደተገነባ በመፈተሽ፣ እንዴት አድርገህ ሕይወትህን የሚቀይርና ሕልምህን የሚያሳካ ድንቅ ፓራዳይም በአዕምሮህ መገንባት እንደምትችል እንመረምራለን።

# ፓራዳይም እንዴት ነው የተገነባው?

ወደዚች ዓለም ስንመጣ፣ ምንም ዐይነት ተራም ሆነ ድንቅ ፓራዳይም አልነበረንም። አንዳች "አይቻልም" ብለን የምንፈራው ነገርም አልነበረንም። ከዚያ ግን እናት አባታችን፣ እህት ወንድማችን፣ ዘመድ አዝማዶቻችን፣ ጓደኛ ጎረቤታችን፣ አለቃ ምንዝሮቻችንና ሁሉም በሕይወት ዘመናችን ተጽዕኖ የፈጠሩብን ሰዎች፣ ከራሳቸው ልምድና ተሞኩሮ ተነስተው ቀርጸውናል። ከተወለድንበት ዕለት አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ በአካባቢያችን ካሉ ሰዎችና ነገሮች፣ ብዙ መረጃዎችን በተደጋጋሚ በመሰብሰብ፣ በድብቁ አዕምሯችን፣ የኛ ብለን የምናምነውን የራሳችንን ማንነት ወይም ፓራዳይም ቀርጸናል። እየበሰልን ስንመጣም ሀሳቦቻችንና ድርጊቶቻችን በዚሁ በልጅነታችን የተገነባ ፓራዳይም ቁጥጥር ሥር ስለሚሆኑ፣ በሕፃንነታችን የተቀረጸብንን ፓራዳይም እያፈረስን ሳይሆን እያጠነከርን ነው የምናድገው።

በዚህም ብዙ ሰው ምንም ሳይቀየር፣ ሕይወቱ በዚሁ በተገነባበት፣ ነገር ግን በማይጠቀመው ፓራዳይም ቁጥጥር ሥር ሆኖ ዘላለሙን ይኖራል። ፓራዳይም መልኩ ብዙ፣ መገለጫውም የትዬለሌ ነው። የፓራዳይም መገለጫ ከሆኑ መልኮች መካከል የተወሰኑትን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

የመጀመሪያው ፓራዳይም ስማችን ነው። አንድ ሕፃን ልጅ ወደዚች ዓለም በመጣበት ወቅት፣ የራሱ መጠሪያ ስም አልነበረውም። ከተወለደ በኋላ አልጋው ላይ ተኝቶ አካባቢውን በመመልከትና በማዳመጥ፣ ብዙ መረጃዎችን መማርና በአዕምሮው ውስጥ መመዝገብ ይጀምራል። በሕፃኑ ልጅ አዕምሮ የሚመዘገበው የመጀመሪያው ነገር ደግሞ መጠሪያ ስሙ ነው። ይህ ልጅ "አከሌ" ተብሎ በስሙ ሲጠራ፣ ምንም የሚያውቀው ነገር ስለሌለ፣ እየተጠራ ያለው እሱ መሆኑን አያውቅም። የሚጠራው ስምም፣ የራሱ መሆኑን አይለይም። ልጁ ከተወለደባት ቅጽበት አንስቶ እንደሚያደርገው ይጠባል፤ ይተኛል፤ ይስቃል፤ ያለቅሳል፤... ነገር ግን የሚጠራበትን ስም አያውቅም።

ቀናት ሲቆጠሩ፣ ልጁም እያደገ ሲመጣ፣ የተለያዩ ድምጾችን ከትናንቱ በተሻለ ትኩረት ማዳመጥ ይጀምራል። ከሚሰማቸው ድምጾች መካከል ግን አንድ ድምጽ ለየት ያለ ቅርበት እየሰጠው ይመጣል። ልጁ ቤተሰቦቹን ሲመለከት፣ ብዙ ነገሮች ያወራሉ፤ አንድ ቃል ሲጠሩ ግን፣ (ስሙን ማለት ነው) እሱን እያዩ ስለሚጠሩት፣ ከሌሎች ድምጾች ይልቅ ትኩረቱ በቃሏ ላይ ይሳባል፤ ድምጿንም በትኩረት ማዳመጥ ይጀምራል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ቤተሰቦቹ ይቺን ቃል ሲጠሯት ለየት ያለ ስሜት እየሰጠችው ትመጣለች። ይቺ ተደጋግማ የምትጠራ ቃል የተለየ ትርጉም እንዳላት ስለሚያስብ፣ ስሙን ወደሚጠራው ሰው ሁሉ ዞር ብሎ የጥሪውን ምላሽ ፈገግ በማለት ይሰጣል። ቤተሰቦቹ ይቺን ቃል ሲጠሯት እና ልጁ ዞር ብሎ ሲያያቸው፣ "አ! ስሙን ዐወቀው!" ብለው በጣም ይደሰታሉ። ልጁ ያቺን ሁሌም የምትደጋገም ቃል "ስማኝት" ብሎ ሲዞር፣ ቤተሰቦቹ ደግሞ፣ "ልጃችን ስሙን ዐወቀ" ብለው በደስታ ያቅፉታል።

በዚህ መንገድ ልጁ ስሙን ባያውቀውም፣ "ስም" የሚባል ፓራዳይም በአዕምሮው ውስጥ እየተገነባ ይሄዳል። ልጁ የሚገባው አንድ ነገር ቢኖር፣ ይቺ ለየት ያለች ቃል ስትጠራ፣ የሚጠሩትን ሰዎች ዞር ብሎ ካያቸው፣ የሚጠሩት ሰዎች እንደሚደሰቱና እሱንም እንደሚያጫውቱት ነው። በዚህ መንገድ፣ ልጁ ይቺን ተደጋግማ የምትጠራ ድምጽ ሲሰማ፣ ዞር ብሎ የማየት ልማድ ያዳብራል። ከዚያም "ስም" የሚባለው ነገር ምን እንደሆነ ከማወቁ በፊት፣ "ስም" የሚባል ፓራዳይም በአዕምሮው ይገነባል። ልጁ ሁለት ዓመት እየሞላው ሲመጣ፣ የማዳመጥና የመናገር ክህሎቱን በደንብ ማዳበር ይጀምራል። "ስምህ ማን ነው?" ተብሎ ሲጠየቅም፣ ስሙን መናገር ይጀምራል። ትምህርት ቤት ሲገባ ደግሞ ስሙን የመጻፍ ፓራዳይም በአስተማሪው ይቀረጽበታል።

በልጅነት አዕምሯችን ውስጥ የገባው ስም በራሱ ምንም ችግር የለውም። አሁን ስለ ስም ፓራዳይም እያወራን ያለነው፣ እንደ ስማችን ሁሉ ገና በልጅነት ዕድሜያችን የተለያዩ ፓራዳይሞች በአዕምሯችን ስለገቡና ከስም ፓራዳይማችን ጋር ተመሳሳይ ይዘት ስላላቸው ነው። ወደ ልጁ ብንመለስ፣ ይህ ልጅ እያደገ ሲሄድ ስሙን ብቻ ሳይሆን ከስሙ ጋር የተሳሰሩ ማንነቶችንና አምነቶችን ጭምር እየተማረና በአዕምሮው እየመዘገበ ይሄዳል። አካባቢውን በማየትም ማን እንደሆነ እንዲሁም ምን ማድረግ እንደሚችልና "እንደማይችል" ይማራል። አዕምሮው ገና ለጋ እያለ ልጁ ድንቅ እንደሆነ፣ በፈጣሪ ምስል እንደተሠራና ያሰበውን ሁሉ ማሳካት እንደሚችል ወላጆቹ በተደጋጋሚ በፍቅር ሲያስተምሩት፣ ድንቅ የሆነ ፓራዳይም በአዕምሮው ይፈጠራል። ይህ ፓራዳይም እያደገና እየተጠናከረ ሲሄድ፣ ልጁ በድንቅ ውጤት የተሞላ ድንቅ ሕይወት መኖር ይጀምራል። በተቃራኒው ወላጆቹ ይህንን ልጅ በተደጋጋሚ የሚቆጡትና የሚፈልገውን ነገር ሲጠይቅ ሁሌም "አይቻልም!" የሚሉት ከሆነ፣ "አይቻልም!" የሚል ፓራዳይም በውስጡ ይገነባል። ይህን "አይቻልም!" የሚል ፓራዳይም እያጠናከረ ሲሄድ ደግሞ፣ ሕልሙ ጭራሽ የማይቻል ሆኖ በአዕምሮው ይሳልበታል።

አንድ ሕፃን ልጅ "ፈረንጅ አድርጎ ቢፈጥረን ምን ነበረበት?!... ጥቁር የሚባል ፍጥረት እኮ አይገባውም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሠርቶ ማደግማ ጭራሽ አይታሰብም፤ እኛ እኮ ምንም የለንም፤ ብር ማግኘት በጣም ከባድ ነው፤..." የሚሉ ፍሬ ቢስና የውሸት ሀሳቦችን ወላጆቹ በልጅነት ዕድሜው ደጋግመው ሲያወሩ ሲሰማ፣ ውሸቱን እንደ እውነት አድርጎ ይቀበላል።

በጣም የሚገርመኝ ነገር፣ ብዙ ልጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቃላታቸው፣ ስማቸው ወይም "እማዬና አባዬ" የሚሉት ቃላት ሳይሆኑ፣ "ኖ!" ወይም "አይ!" የሚሉት አሉታዊ ቃላት መሆናቸው ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን በተደጋጋሚ "ኖ" ሲሏቸው፣ በልጆቻቸው ላይ የ"ኖ" ፓራዳይም ይቀረጻል። ወላጆች፣ ልጆቻቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉት ጥንቃቄ መልካም ሆኖ ሳለ፣ በልጆቻቸው የልጅነት አዕምሮ ውስጥ የሚገነቡት "ኖ" ወይም "አይቻልም" የሚል ፓራዳይም እንዳይሆን በጣም መጠንቀቅ ይገባቸዋል።

**ሌላው ፓራዳይም ቋንቋችን ነው።** ዓለም ላይ ከባድ የሚባለው ቋንቋ ምንድን ነው? ይህንን ጥያቄ የሚመልስ ብዙ ሰው "ቻይንኛ" ወይም "ማንደሪን" ብሎ ሊሆን ይችላል። ለአንድ ነጥብ አራት ቢልየን የቻይና ሕዝብ ግን አይደለም። የሰው ልጅ "ከባድ" የሚለው ያልለመደውን ነገር ወይም በፓራዳይሙ ውስጥ ያልገባን ነገር ነው። የአማርኛ ቋንቋ ላንተ ቀላል የሆነው፣ በልጅነት አዕምሮህ እንደ አንድ የቋንቋ ፓራዳይም ሆኖ በአዕምሮህ ስለገባ ብቻ ነው። የተወለድከው ቻይና ውስጥ ቢሆንና ከቻይናዎች ጋር ብታድግ፣ ላንተ ቻይንኛ የዓለማችን ቀላል ቋንቋ ይሆንልህ፣ የቤተሰቦችህ አማርኛ ደግሞ በጣም ከባድ ይሆንብህ ነበር። የሰው ልጅ ቋንቋውን፣ ልማዶቹንና ማንነቱን ወይም በአጠቃላይ ፓራዳይሙን፣ ከደሙና ከዘር ግንዱ ከሚወርሰው በላይ ከአካባቢው የሚወርሰው ይበልጣል።

የአንድ ህንዳዊ ጓደኛዬ ልጆች አምስት ቋንቋዎችን መናገር ይችላሉ። እነዚህ ልጆች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፣ አንድ የእናታቸውን፣ አንድ የአባታቸውንና አንድ የአገራቸውን ብሔራዊ ቋንቋ መናገር ይችሉ ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ደግሞ፣ አማርኛንና እንግሊዝኛን አቀላጥፈው መናገር ለመዱ። እነዚህ ልጆች፣ "አትችሉም!" ያላቸው ሰው ስላልነበረ፣ አምስት ቋንቋዎችን መናገር ችለዋል። አንድ ቋንቋ ብቻ የሚናገር ሰው ግን፣ ሁለተኛ ቋንቋ ለመልመድ ትልቅ ዳገት ሊሆንበት ይችላል። የሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ፣ "ይቻላል!" የሚል ፓራዳይም ከተገነባ፣ ምንም ይሁን ምን፣ የሚፈልገውን ነገር ማሳካት ይችላል።

**ፊደልም ፓራዳይም ነው።** እንደ ቋንቋ ሁሉ፣ ፊደልም ፓራዳይም ነው። ይቺ "O" ትዕምርት ምንድን ናት? የአማርኛ ፓራዳይም ካለህ ይቺ ትዕምርት "0" ናት ወይም "ዜሮ" ናት ብለህ ልትመልስ ትችላለህ። የአረብኛ ፓራዳይም ካለህ ደግሞ "አምስት ቁጥር" ናት ብለህ ልትመልስ ትችላለህ። ይቺው ትዕምርት የግዕዝ ፓራዳይም ላለው ሰው "አራት ቁጥር" ትሆናለች። በየአገሩና በየቋንቋው ብንሄድ፣ ይቺ ፊደል የተለያየ ትርጉም ያላት ፊደል፣ ቁጥርና ቃል ልትሆን ትችላለች። የፊደሏ ዘረ ድምጽ በየቋንቋው ዐይነት፣ የተለያየ ትርጉምና ፍቺ ሊኖረው ይችላል። ሌላ ሰው ደግሞ ይቺን ትዕምርት፣ "የከብ ቅርጽ ናት" ወይም "ቀለበት ናት" ሊለን ይችላል። "ታዲያ ይቺ ትዕምርት እንዴት ይህን ያክል ብዙና የተለያየ መጠሪያ እንዲሁም ትርጉም ሊኖራት ቻለ?" ብለህ ብትጠይቅ፣ መልሱ አንድና አንድ ነው፤ ፓራዳይም!

በምሳሌ ለማስረዳት፣ አንድ የሂሳብ አስተማሪ ይቺኑ ትዕምርት 'O' በሰሌዳ ላይ ይጽፏትና ለተማሪዎቹ "ይቺ ትዕምርት ዜሮ ናት" ብሎ ያስተምራቸዋል። ከዚያም በየቀኑ ይቺን ትዕምርት ለተማሪዎቹ እያሳየ ደጋግመው ጮክ ብለው "ዜሮ" ብለው፣ እንዲጠሯት ያስተምራቸዋል። ተማሪዎቹ "ትዕምርቷ ምንድን ናት?" ተብለው በሒሳብ ክፍለ ጊዜ ሲጠየቁ፣ "ዜሮ" ብለው መጥራት ይጀምራሉ። ከተወሰነ ድግግሞሽ በኋላም፣ ይቺ ትዕምርት በተማሪዎቹ አዕምሮ ውስጥ "ዜሮ" ሆና ትመዘገባለች፤ ፓራዳይም ሆነች ማለት ታዲያ እንዲህ ነው። ተማሪዎቹ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት ይቺ ትዕምርት ምንም ዐይነት ትርጉም አልነበራትም። ትምህርት ቤት ሄደው ከተማሩ በኋላ ግን፣ ይቺን ትዕምርት "ዜሮ" ናት ብለው ማመን ይጀምራሉ። በአረብኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ ይቺ ትዕምርት "ዜሮ" ብቻ ሳትሆን "አምስት" ናት። ትዕምርቷን አንተ "ዜሮ" ማለትህ ልክ ነው፤ እነሱም "አምስት" ማለታቸው ልክ ነው። ለትዕምርቷ ያለን ትርጉምና አጠራር የተለያየው በፓራዳይማችን ምክንያት ነው።

ፓራዳይም በአዕምሯችን እንዴት እንደተቀረጸ ስንረዳ፣ ሕይወት በጣም ቀላል ነው የሚሆነው። ወደዚች ዓለም ስንመጣ፣ ሁላችንም ምንም ዐይነት ቋንቋ፣ ፊደል፣ ብሔር፣ ባህል፣ ፖለቲካዊ አቋምና ሃይማኖት አልነበረንም። ከዚያ ግን ከቤታችንና ከትምህርት ቤታችን ጀምሮ መቀረጽ እንጀምራለን። ወላጆቻችን፣

ቤተሰቦቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ አስተማሪዎቻችን፣ አለቆቻችን፣ የሥራ ባልደረቦቻችን፣ የሃይማኖት አባቶቻችን፣ የፖለቲካ መሪዎቻችን፣ መገናኛ ብዙኃኖቻችንና ሌሎች በሕይወታችን ተጽዕኖ የፈጠሩ ሰዎች እንደየ አስተሳሰባቸውና እምነታቸው ይቀርጹናል። እነዚህ ሰዎች ሕፃን ልጅ ሆነን ሲቀርጹን፣ ከነሱ የተሻለ መረጃ ከልነበረን፣ የሚሉንን ሁሉ ነገር እንደ እውነት ነው የምንቀበለው።

አሁን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ፣ "እኔ ለራሴ ማሰብ ከመጀመሬ በፊት፣ በሕይወቴ ላይ ተጽዕኖ በነበራቸው ሰዎች በአዕምሮዬ የተቀረጸው ፓራዳይም እየጠቀመኝ ነው ወይስ እየጎዳኝ?" የሚለውን ነው። ፓራዳይሞቻችን ሕይወታችንን እየተቆጣጠረና እየመራ ያለበት መንገድ የፍቅር፣ እድገት፣ ሰላምና ስኬት ካልሆነ፣ ፈጥነን አሁኑኑ ልንቀይረው ይገባል። በአዕምሯችን የተገነባው ፓራዳይም የጥላቻ፣ ድህነት፣ ምቀኝነትና ስንፍና ከሆነ አሁኑኑ ከአዕምሯችን ማባረር አለብን።

የዓለማችን ዋናው ችግር መጥፎ ፓራዳይም ነው። ፈጣሪ ሁላችንንም የሰው ልጆች በምሳሌው ድንቅ አድርጎ ነው የፈጠረን። ከውጪ ስንታይ እንዳደግንበት አካባቢ የተለያየ ቋንቋ፣ ምግብ፣ ባህል፣ ዳራ፣ እምነት፣ ሥራ፣ የኑሮ ደረጃ ወዘተ... አለን። በውስጣችን ያለውን ተዓምር ስንመለከት ግን፣ ሁላችንም አንድ እና ድንቅ ነን። "ፈጣሪ የሰውን ልጅ በምሳሌው ፈጠረው" ሲባል ለቀልድ አይደለም። ልዩነት ሲያጋጥመን፣ ልዩነታችን የሚፈጠረው፣ ልዩ ልዩ አፈጣጠር ስላለን ሳይሆን፣ ልዩ ልዩ ፓራዳይም ስላለን ነው። ፓራዳይም ደግሞ ብዙውን ጊዜ እኛ ምንም ምርጫ ሳይኖረን፣ አካባቢያችን እኛ ላይ የቀረጸብን ፕሮግራም ነው። ከኛ የሚጠበቀው፣ የልዩነታችን ምንጭ ፓራዳይሞቻችን እንደሆነ አምነን፣ ማስተካከል የሚገባውን ነገሮች ማስተካከል ነው። ለምሳሌ የጥላቻ ፓራዳይም ካለን ወደ ፍቅር፣ የድህነት ፓራዳይም ካለን ደግሞ ወደ ሀብት እንቀይር። ሌሎች ሰዎችም ፓራዳይማቸውን በመቀየር ሕይወታቸውን እንዲቀይሩ እንርዳቸው። በዚህ መንገድም ድንቅ ፓራዳይም በአዕምሯችን በመገንባት ድንቅ ሕይወት እንኑር።

የፓራዳይምን ምስጢር ስናውቀው፣ እኛ ሰዎች አንድ መሆናችንን እንረዳለን። "እኛና እነሱ" ብለንም አንለያይም። በፈጣሪ ፕሮግራም መሠረት፣ **"እኛ" የምንባል የፈጣሪ ልጆች እንጂ፣ "እነሱ" የሚባሉ ሰዎች የሉም።** ከዚህ በኋላ በቋንቋ፣ በብሔር፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ አንለያይም። ያለን ምርጫ በፍቅርና በአንድነት መኖር ነው። በተቀረጸብን ፓራዳይም ምክንያት ስንለያይ፣ ሁላችንም በመቀናነስ "ዜሮ" እንሆናለን። ያለንን ልዩነት በመርሳት ስንደምር ደግሞ አንድ እንሆናለን፤ ዓለምንም እንቀይራለን። ከዚህ በኋላ "የኛ ብሔር እንደዚህ ነው፣ የነሱ ደግሞ እንደዚያ ነው" የሚል የኋላ ቀርነት አስተሳሰብ ማስቀረት ይገባናል።

ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር ዐቢይ እንዳሉት "ስንኖር ኢትዮጵያዊ፣ ስንሞት ኢትዮጵያ" ከዚህም አልፈን "ስንኖር አፍሪካዊ፣ ስንሞት አፍሪካ" የሚል እምነት በውስጣችን ልናሳድር ይገባል። አፍሪካዊነታችን ብቻውን በቂና ሁላችንን የሚያቅፍ መዋቅር ስላልሆነ፣ ሁላችንም የሰው ልጆች በፈጣሪ ምስል እንደተፈጠርን በመረዳት፣ ሌላውን በፈጣሪ ምስል የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ እንደ ነፍሳችን ማፍቀርን መማር አለብን። በመጨረሻም፣ የሰውን ልጆች ብቻ ሳይሆን፣ እንስሳትን፣ እጽዋትን፣ ተፈጥሮን፣ በአጠቃላይ በፍጥረተ ዓለሙ ያሉ ነገሮችን ሁሉ መውደድ እና መንከባከብ ይገባናል።

ፈጣሪ በሕይወት ዘመናችን ከምንጠቀምበት በላይ አቅም እና ችሎታ ሰጥቶናል። ለፈጣሪ ስጦታ ውለታ እንዲሆን መልሰን የምንሰጠው ነገር ባይኖረንም፣ ማመስገን ግን እንችላለን። ፈጣሪያችንን የምናመሰግነው ደግሞ፣ እርስ በርሳችን ተፋቅረን በመኖርና ይቺን ዓለም በፍቅር በመያዝ ስንኖርባት ብቻ ነው።

**እንጀራም ፓራዳይም ነው።** "የምትወዱት ምግብ ምንድን ነው?" ብዬ የምጠይቃቸው በስልጠናችን የሚሳተፉ ብዙ ሰዎች፣ ሙሉ ለሙሉ በሚያስብል ሁኔታ፣ "እንጀራ" ብለው ነው የሚመልሱልኝ። አንተ የምትወደው ምግብም እንጀራ ሊሆን ይችላል። እንጀራ የምንወደው ግን ለምንድን ነው? እንጀራ ከግሉተን ነጻ ስለሆነ፣ ከፍተኛ የፋይበር፣ ካልሺየም፣ ፖታሺየም እና ፕሮቲን ይዘታ ስላለው ነው? በጭራሽ

አይደለም! እንጀራ በፍቅር የምንወደው፣ በልጅነታችን አብዛኛውን ጊዜ ወላጆቻችን ደጋግመው እንጀራ ስለሰጡን ነው። ለምንድን ነው ወላጆቻችን እንጀራን ደጋግመው እንድንበላ ያስለመዱን? ምክንያቱም የነሱ ወላጆች እንጀራ እንዲበሉ ስላስለመዷቸው ነው። እኔና አንተ ለምን የእንጀራ ፍቅር እንዳለን ለመረዳት ወደ ኋላ ብዙ መቶ ዓመታት ተመልሰን፣ የመጀመሪያዎቹን እንጀራን ከጤፍ የጋገሩ ሰዎች መጠየቅ ያስፈልገናል።

ቅድመ አያቶቻችን የሠሩትና የወደዱት እንጀራ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሻገረ፣ ዛሬ የኛ የምግብ ፓራዳይም ሊሆን በቅቷል። አያቶቻችን የሠሩት ባህላዊ ምግብ እንጀራ ሳይሆን ሩዝ ቢሆን ኖሮ፣ ሁላችንም የሩዝ አፍቃሪዎች እንሆን ነበር። በየቀኑ ቤት ገብተን ሩዝ ካላገኘንም ይደብረን ነበር። ፓራዳይም የምንወደውንና የምንጠላውን ምግብ ጭምር ይቆጣጠራል።

ትዝ ይለኛል በአስራ ሁለት ዓመቴ ከእናቴ ጋር ወደ እንግሊዝ አገር ስንሄድ ብዙም የእንጀራ ፍቅር አልነበረኝም። በዚያ ዕድሜዬ ከእንጀራ ይልቅ ዳቦ፣ ፓስታና ቾኮሌት የምወድ ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን በእንግሊዝ አገር ለሁለትና ሦስት ሳምንታት ዳቦ፣ ፓስታና ቾኮሌት በተደጋጋሚ ስበላ፣ በፓራዳይሜ የተቀረጸው እንጀራ ናፈቀኝ። ከዚያም በእንግሊዝ አገር ለሚኖሩት አያቴ፣ እህቶቼና ወንድሞቼ የወሰድነውን እንጀራና ዶሮ ወጥ፣ እኔና እናቴ ትንሽ ትንሽ እየበላን ጨረስንባቸው። በፓራዳይማችን ውስጥ የተገነባው ፍላጎት ሁሌም ያሸንፋል።

እንጀራን ከአያቶቻችን መውረሳችን ጥሩ ነገር ነው። ዋናው ቁም ነገር "እኛ ምንም ሀሳብ ሳንሰጠው እንደ እንጀራ ያሉ ሌሎች ነገሮችን ከወላጆቻችን በመውረስ፣ ፓራዳይም አድርገናቸዋል" የሚለው ነው። አካባቢያችን ስለ ሥራ፣ ፍቅር፣ እድገት፣ ሀብትና ስኬት ምን ዐይነት ፓራዳይም እንደቀረጸብን መፈተሽ ያስፈልገናል። በአዕምሯችን ያለው ፓራዳይም የምንፈልገውን ሕይወት እንድንኖር እየረዳን ነው? ካልሆነ መቀየር አለበት።

ድህነትም ፓራዳይም ነው። ድህነት ልክ እንደ ስማችን፣ ቋንቋችንና ምግባችን በልጅነታችን በአዕምሯችን የተገነባ ፓራዳይም ነው። ወላጆቻችን ድህነትን የሚያበረታቱ ወይም "አሜን" ብለን እንድንቀበል የሚያደርጉ ንግግሮችን ደጋግመው ያወሩ ከነበሩ፣ የድህነት ፓራዳይም ቀርጸውብን እናድጋለን። በጣም የምወዳቸው እና የማመሰግናቸው ወላጆቼ እጅግ በጣም ብዙ መልካምነቶችን እያሳዩና እያደረጉ፣ እኔንና እህት ወንድሞቼን፣ የሚያስፈልገንን ሁሉ ነገር አሟልተው ነው ያሳደጉን። ወደ ኋላ ተመልሼ ልጅነቴን ስፈትሸው ግን፣ ከሚወዱን ወላጆቻችን ጠቃሚ የሆኑ ፓራዳይሞችን ብቻ ሳይሆን፣ አንዳንድ ጎጂ የሆኑ የድህነት ፓራዳይሞችን እንደወረስን ነው የተረዳሁት።

ለምሳሌ እናቴ በዓለም ካሉ እናቶች በፍቅር አንደኛ መሆኗን፣ እኛ ልጆቿ ብቻ ሳንሆን የሚያውቋት ብዙ ሰዎች ነው የሚመሰክሩት። በእናቴ በኩል "የአየለ ፋሚሊ" የሚባል ቤተሰብ አለን። ይህ ቤተሰብ በሄደበት ቦታ ሁሉ ባለው ፍቅር የታወቀ ነው። እናቴ፣ አያቴና ቅድመ አያቴ አሁን ደግሞ ታላቋ እህቴ የዚህ ቤተሰብ የፍቅር ማግኔት ናቸው። ከወላጆቼ እና ከሁሉም ቤተሰቦቼ ጋር ይህንን ድንቅ እና ትልቅ የፍቅር ሕይወት መቅመስ እና መኖር ስለቻልኩ፣ ፈጣሪዬን ሁሌም አመሰግናለሁ። ወላጆቼ በልጅነቴ የቤተሰብ እና የሰውን ልጅ ፍቅር እንደ ፓራዳይም በአዕምሮዬ ስለገነቡ፣ በጣም አመሰግናቸዋለሁ።

ነገር ግን እናቴ "እኛ የንግድ ሰዎች አይደለንም፣ ከኛ ቤተሰብ ንግዶ የተሳካለት ሰው የለም፤ ወደ ንግድ ዓለም ውስጥ ከገባን በጣም እንከስራለን" የሚል ፓራዳይም በውስጧ ነበራት። ይህ ፓራዳይም ውሸት እንደሆነ ስላላወቀች ደግሞ፣ ለኛ ለልጆቿ የነበራትን ፓራዳይም ሳታስበው አወረሰችን። ታዲያ እኔ መጀመሪያ ወደ ንግድ ዓለም ስገባ፣ ማገፍረስ የነበረብኝ ፓራዳይም ይህንኑ ነበር። አንተስ ከቤተሰቦችህ የማትፈልገው፣ ነገር ግን ሳታስበው የወረስከው ምን ዐይነት ፓራዳይም አለህ? እነዚህን ፓራዳይሞች ፈልገህ ካላጠፋሃቸው፣ ሕይወትህን ሊሚወቁበት ይችላሉ።

አባታችንም የፍቅር አባት ነው። ነገር ግን እሱም ምንም ሳይረዳው አንዳንድ የድህነት ፓራዳይም በአዕምሯችን ገንብቷል። ለምሳሌ ማታ ማታ ቤተሰብ ተኮር የሆኑ ተረቶች ይነግረን ነበረ። በየምሽቱ ደጋግሞ ይነግረን ከነበሩ ተረቶች መካከል ስለ አንድ ሀብታምና ድሀ ጎረቤታማቾች የሚነግረን ትዝ ይለኛል። ተረቱ እንዲህ ነው...

*አንድ በጣም ሀብታም እና አንድ በጣም ድሀ ጎረቤታማቾች ነበሩ። ሀብታሙ ሰውዬ በጣም ባለ ፀጋ ቢሆንም፣ ሌሊቱን ሙሉ ብሩን ሲቆጥር እና ሲጨነቅ ነበር የሚያድረው። ድሀው ሰውዬ ግን ምንም እንኳ ገንዘብ ባይኖረው፣ ሌሊቱን በሙሉ ሲደሰት እና ሰላም ሲሰማው ነበር የሚያድረው። አንድ ቀን ታዲያ ሀብታሙ ሰውዬ ወደ ድሀው ጎረቤቱ ሄደና... "እኔ ይህ ሁሉ ሀብት እያለኝ ያልተደሰትኩ፣ አንተ እንዴት ነው ምንም ሳይኖርህ ደስታ በደስታ ልትሆን የቻልከው?" ብሎ ጠየቀው። ድሀው ሰውዬ መልሶ "እኔ ምንም አልጨነቅም! ስላለኝ ነገር ፈጣሪዬን በጸሎት እና በዝማሬ አመስግኜ ሰላም ተሰምቶኝ ነው የምተኛው" ብሎ ይመልስለታል። ሀብታሙ ሰውዬም በጣም ተደነቀ እና "አንተ ምንም ሳይኖርህ እንደዚህ ከተደሰትክ፣ የበለጠ እንድትደሰት ግማሹን ሀብቴን እሰጥሀለሁ" ብሎ በሚቀጥለው ቀን ግማሽ ሀብቱን ሰጠው። ቀናት መቆጠር ሲጀምሩ ግን፣ ድሀው ሰውዬ ልክ እንደ ሀብታሙ ሰውዬ ድምጹን አጥፍቶ ሌሊቱን ሙሉ ብር መቁጠርና መጨነቅ ጀመረ። ድሀው ሰውዬ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደስታውን እያጣ በመምጣቱ፣ ወደ ሀብታሙ ሰውዬ ሄዶ የሰጠውን ገንዘብ በሙሉ መለሰለት። ከዚያም ድሀው ሰውዬ ወደ ተለመደው ድህነቱና ደስታው ተመለሰ። ሀብታሙ ሰውዬም ወደ ብር መቁጠሩ እና መጨነቁ ተመለሰ። ተረቴን መልሱ...*

በርግጥ ይህ ተረት የብር ተገዢዎችና ባሪያዎች እንዳንሆንና ባለን ነገር እንድንደሰት ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል። ነገር ግን ይህንን ተረት በጥንቃቄ ስንመለከት፣ ዋና የድህነት ፓራዳይም የሚቀርጽ ተረት ሆኖ ነው የምናገኘው። እንዴ ቆም ብለህ ስታየው፣ ታሪኩ የተሳሳተ መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ትረዳለህ። ድሀው ሰውዬ ከሀብታሙ ሰውዬ ብዙ ብር ካገኘ፣ ለምን ሌሊቱን ሙሉ ይቆጥራል? ያገኘውን ብር ለምን መኪና ወይም ቤት ወይም ሌላ ነገር አይገዛበትም? በመሠረቱ ማንም ሀብታም ብሩን ባንክ አስቆጥሮ ነው የሚያስቀምጠው እንጂ ሌሊቱን ሙሉ ሲቆጥር እና ሲጨነቅ አያድርም።

እንደነዚህና ሌሎች የነዚህ መሰል ተመሳሳይ ታሪኮች ሲደጋገሙብን፣ ሆነ ብለን ሳይሆን፣ ሳናስበው ሀብታምነትን ልንጠላ እና ድህነትን ልንወድ እንችላለን። በሕይወት ዘመናችን እኛን በጣም ሀብታም እንድንሆን ሊያደርገን የሚችል የሥራ ዕድል ቢገኝ እንኳ ልንፈራ እንችላለን። በድህነት ውስጥ ያደገ ሰው የድህነት ሕይወት ወደ ውስጡ ከገባ፣ ድህነቱ ስለሚመቸው፣ ሀብትን ሊፈራ እና ሊጠላ ይችላል። ከልጅነታችን ጀምሮ በአዕምሯችን ድህነትን የሚያበረታታ ፓራዳይም ካለን፣ ያስንፈናል። በርግጥ የገንዘብ ባሪያ እንዳንሆን መጠንቀቅ አለብን። ሀብታም መሆን ግን ጎጂ ሳይሆን ጠቃሚ ነው። ሀብታም ስንሆን ለራሳችንና ለቤተሰባችን ብቻ ሳይሆን ለወገናችንም መትረፍ እንችላለን።

ስለ ፓራዳይም ዋናውን ቁም ነገር የጨበጥክ ይመስለኛል። ከልጅነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣ በሕይወታችን ተጽዕኖ የፈጠሩ ሰዎች፣ እኛነታችንን ቀርጸውታል። ይህ በውስጣችን የተቀረጸው ነገር ነው ፓራዳይም የሚባለው። ፓራዳይም ሀሳባችንንና ድርጊታችንን ብቻ ሳይሆን፣ ስሜታችንን፣ እምነታችንንና ማንነታችንን በመቆጣጠር አሁን የምናገኘውን ውጤት እንድናገኝና አሁን የምንኖረውን ሕይወት እንድንኖር እያደረገን ነው። አሁን በምናገኘው ውጤትና በምንኖረው ሕይወት ደስተኛ ካልሆንን፣ አሁን ያለንን ፓራዳይም በአዲስና ድንቅ ፓራዳይም በመቀየር፣ የምንፈልገውን ውጤት እና ሕይወት ማግኘት ደግሞም መኖር እንችላለን።

# ድንቅ ፓራዳይም

ፓራዳይም ብዙውን ጊዜ አይቀየርም። ከተቀየረ ደግሞ፣ የተቀየረው አዲስ ፓራዳይም ቶሎ አይቀየርም። ብዙ ሰው ያልተቀየረውን፣ የማይወደውንና የማይፈልገውን ፓራዳይሙን ወደ መቃብሩ ይዞት ነው የሚሄደው። ይህ ማለት ግን፣ ፓራዳይም አይቀየርም ማለት አይደለም። አሁን ያለህን የማትፈልገውን የድሮ ተራ ፓራዳይም በምትፈልገው አዲስ ድንቅ ፓራዳይም ለመቀየር እንድትችል፣ ቀጥለው የቀረቡት ሁለት ዘዴዎች ይረዱሀል።

፩. የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ
፪. የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ

## ፩. የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ

የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ አብዛኛውን ጊዜ አያጋጥምም፤ ካጋጠመ ደግሞ ብዙውን ጊዜ አሉታዊ በሆነ መንገድ ነው። የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ፣ አንድ የሚያስደነግጠን ነገር በድንገት ሕይወታችን ላይ ሲከሰት፣ ወዲያውኑ በመደንገጥ የምናደርገው የፓራዳይም ለውጥ ነው። በዚች ልዩ ክስተት ከልጅነታችን ጀምሮ በአዕምሯችን የተገነባው የድሮ ፓራዳይም ወዲያውኑ በአዲስ ፓራዳይም ይተካል።

የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥን ለመረዳት ስለ አንድ ችኩል እና ሞገደኛ ሹፌር ምሳሌ አንስተን እንነጋገር። ይህ ሹፌር ሁልጊዜ በፍጥነት፣ በግድ የለሽነት እንዲሁም በቸልተኛነት ነው የሚነዳው። እንደዚህ ዐይነት ባህሪው ደግሞ አደጋ ላይ እንደሚጥለው ብዙ ሰው ነግሮታል፤ እሱ ራሱም ያውቃል። ይህ ሹፌር አነዳዱ በራሱም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ አደጋ ሊፈጥር እንደሚችል በመረዳትና አነዳዱን በማስተካከል፣ ንቡዝ እና የተረጋጋ ሹፌር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በአዕምሮው የተገነባው የችኮላና የግድ የለሽነት የመንዳት ፓራዳይም፣ ዞሮ ዞሮ ወደለመደው አነዳዱ ይመልሰዋል። በዚህ የለመደው የቸልተኛነት የአነዳድ ፓራዳይሙ፣ አንድ ቀን ራሱን በድንገታዊ እና አስደንጋጭ አደጋ ውስጥ ሲያገኘው፣ ድንገታዊ የሆነ የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ ያደርጋል። ከዚያች ከደነገጠባት ዕለት አንስቶም ይህንን የመጥፎ አነዳድ ፓራዳይሙን፣ ከልቡ ይጠላዋል። ከዚያም አዲስና ሥርዓት ያለው የአነዳድ ፓራዳይም በአዕምሮው መገንባት ይጀምራል።

በልጅነቴ፣ አባቴ አንድ የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ ሲያደርግ ትዝ ይለኛል። አባቴ በዚያ ሰዓት፣ ከጓደኞቹ ጋር የመጠጥ ፓራዳይም መገንባት ጀምሮ ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፣ ይህ የመጠጣት እና የመስከር ፓራዳይም፣ በሥራውና በእኛ ላይ ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን መፍጠር ጀመረ። እናቴና ሌሎች ቤተሰቦቻችን በተደጋጋሚ ሲመክሩት ለተወሰኑ ቀናት መጠጥ ያቆምና፣ ከጓደኞቹ ጋር ሲገናኝ በድጋሚ ወደ መጠጣቱ ይመለስ ነበር። በሥራ ሰዓት ሥራውን በደንብ ይሠራና በመጠጥ ሰዓት ደግሞ በደንብ ይጠጣ ስለነበር፣ ከሱሱ የመላቀቅ ብዙ ተስፋ አልነበረውም።

አንድ ጊዜ በተደጋጋሚ ከመጠጣቱ የተነሳ፣ በጣም ታመመ እና ለሕክምና ሆስፒታል ገባ። ሐኪሞቹ በመጠጣቱ ከቀጠለ፣ ራሱን እና ቤተሰቡን እንደሚጎዳ፣ ሕይወቱንም ሆነ ሌሎች ብዙ ነገሮችን ሊያጣ እንደሚችል በመንገር ሲያስደነግጡት፣ በድንገት ማንም ሰው ያልጠበቀውን የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ አደረገ። ከዚያች ቀን ጀምሮ፣ በሕይወት በነበረባቸው ከሰላሳ በላይ የሚሆኑ ዓመታት፣ ምንም ዐይነት መጠጥ ቀምሶ አያውቅም ነበር። አባቴ ከዚያች ቀን አንስቶ ምንም ዐይነት መጠጥ፣ በፊት ይወዳቸው የነበሩትን ቢራ እና ጠጅ እንኳ፣ አንድ ጉንጭ ፉት ብሎ አያውቅም። የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ ብዙውን ጊዜ አያጋጥምም፣ ሲያጋጥም ደግሞ አሉታዊ የሆነ ነገር ሲደርስ ወይም ሲያጋጥም ነው።

ምንም እንኳ የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው አሉታዊ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙ፣ እነሱን ለመቀየር ቢሆንም፣ አዎንታዊ የሚሆንባቸው ውሱን አጋጣሚዎች ግን አሉ። ለምሳሌ አንድ "እኔ ድሀ ነኝ፤ በምንም ተዓምር ደግሞ ሀብታም ልሆን አልችልም" የሚል ሰው፣ ያልጠበቀውን ብዙ ገንዘብ ቢያገኝ አልያም ሎተሪ ቢደርሰው፣ የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ ሊያደርግ ይችላል። ገንዘቡን በአግባቡ ሲጠቀምበት፣ ባላሰበው ድንገታዊ አጋጣሚ፣ ከድህነት ወጥቶ የሀብትን ሕይወት ሊጀምር ይችላል። የመደንገጥ የፓራዳይም ለውጥ በድንገት ስለሚመጣ፣ እንደዚህ ዐይነት ድንገታዊ የፓራዳይም ለውጥ እንዲያጋጥመን መጠበቅ ጊዜያችንን ማባከን ነው የሚሆነው። ስለዚህ ወደ ሁለተኛውና አሁን ያለንን ፓራዳይም ለመቀየር፣ በድንገት ሳይሆን በዓላማ ልንጠቀም የምንችልበት፣ የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ውስጥ እንግባ።

## ፪. የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ

ሕልምህን ማሳካት የሚችል ድንቅ ፓራዳይም በአዕምሮህ በመገንባት፣ ሕይወትህን ለመቀየር ዝግጁ ነህ? የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ፣ የማትፈልገውን፣ ነገር ግን አሁን ያለህን ተራ ፓራዳይም፣ በምትፈልገው ድንቅ ፓራዳይም የምትቀይርበት ዘዴ ነው። የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥን በመጠቀም ሕይወትህን ለመቀየር ግን ይህ ዘዴ እንዴት አድርጎ እንደሚሠራ በጥንቃቄ መረዳት አለብህ። የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ዘዴን በመጠቀም፣ አዲስ ፓራዳይም ለመገንባት ቀጥለው የቀረቡትን ሦስት ደረጃዎች በጥንቃቄ ተጠቀምባቸው።

፩. በመጀመሪያ አሁን ያለህን፣ መቀየር የምትፈልገውን ተራ ፓራዳይም በግልጽ እወቀው።
፪. አሁን ያለህን ተራ ፓራዳይም በምን ዐይነት አዲስና የምትፈልገው ድንቅ ፓራዳይም መቀየር እንደምትፈልግ ወስን።
፫. አዲሱና ድንቅ ፓራዳይምህን በአዕምሮህ ውስጥ በድግግሞሽ በመገንባት፣ የአዕምሮህ ዋና ፓራዳይም አድርገህ ውቀረው።

የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ዘዴን በመጠቀም፣ አሁን ያለህን ተራ ፓራዳይም በአዲስ ፓራዳይም ለመተካት፣ በመጀመሪያ አሁን ያለህ ፓራዳይም ምን እንደሆነና ለምን መቀየር እንደፈለግከ በግልጽ ማወቅ እና መረዳት ያስፈልግሀል። በመቀጠል አሁን ምን ዐይነት አዲስና ድንቅ ፓራዳይም መገንባት እንደምትፈልግ በማሰብ መወሰን ያስፈልግሀል። በመጨረሻም የመደጋገም ዘዴን በመጠቀም፣ ይህንን አዲሱንና ድንቅ ፓራዳይምህን በአዕምሮህ መገንባት አለብህ። ይህንን የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ዘዴ በመጠቀም ሕይወትህን ለመቀየር እንዲቀልህ፣ አንድ ቀለል ያለ የፓራዳይም ለውጥ ምሳሌ ልስጥህ። ይህ ምሳሌ የስም ፓራዳይም ለውጥ ምሳሌ ነው።

# የስም ፓራዳይም ለውጥ

አንድ ሰው ስሙን መቀየር ይፈልጋል እንበል። ስም፣ በልጅነታችን ከሚገነቡ መሠረታዊ ፓራዳይሞች መካከል አንዱ መሆኑን አስቀድመን ተመልክተን ነበር። አሁን የማይፈልገውን ስሙን በአዲስ እና በሚፈልገው ስም ለመቀየር አንድ ሰው መጠቀም የሚችለውን ዘዴ በመመርመር፣ እንዴት አድርገህ የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ዘዴን በመጠቀም፣ የማትፈልገውን ተራ ፓራዳይም በምትፈልገው ድንቅ ፓራዳይም መቀየር እንደምትችል እንመለከታለን።

አሁን ያለውን የማይፈልገውን ስም ወደሚፈልገው አዲስ ስም ለመቀየር የፈለገ ሰው፣ በመጀመሪያ አሁን ያለው ስም ምን ዐይነት ትርጉም እንዳለው እና ለምን መቀየር እንደፈለገ፣ በግልጽ መረዳት አለበት።

፮. ፓራዳይም

ከዚያም አዲስና የሚፈልገውን ስሙን በጥንቃቄ መምረጥ እና መወሰን አለበት። የሚወደውንና ሊጠራበት የሚፈልገውን አዲሱን ከመረጠ በኋላ፣ ይህንን አዲሱን ስሙን በመደጋገም አዕምሮው ውስጥ መገንባት አለበት። አሁን ትኩረት መስጠት የምንፈልገው ነገር፣ አዲስ ስሙን በአዕምሮው ውስጥ እንዴት በመደጋገም እንደሚቀርጽ ነው።

አዲስ እንዲጠራበት የሚፈልገውን ስሙን ከወሰነ በኋላ፣ ይህንን አዲሱን ስሙን፣ በተደጋጋሚ እና በመደጋገም ብቻ ነው በአዕምሮው የሚገነባው። ይህ ሰውዬ አሁን ያለውን ስም በአዲስ ስም ለመቀየር የሚጠቀምበትን የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ዘዴ ለመረዳት የድሮ ስሙ እንዴት አድርጎ በአዕምሮው እንደተገነባ መለስ ብለን እንመልከት።

ወላጆች ለልጃቸው "ይመጥናል!" ብለው ያሰቡትን ስም በመምረጥ፣ የልጃቸውን ስም ይወስናሉ። ይህንን ስም በልጃቸው አዕምሮ ውስጥ ለመቅረጽ የሚጠቀሙበት ዘዴም የመደጋገም ዘዴ ነው። አንድ ሕፃን ልጅ ሲወለድ፣ ወላጆቹ "ልጄ፣ አሁን አንድ ወሳኝ እና በሕይወትህ ሙሉ የሚጠቅምህን ነገር እንነግርሀለን፤ ስምህ አከሌ ነው፤ ከአሁን በኋላ በዚህ ስም ነው የምትጠራው" ብለው አይደለም ስሙን በአዕምሮው ውስጥ የሚቀርጹት። ወላጆች በልጃቸው አዕምሮ ውስጥ ስሙን የሚቀርጹት በመደጋገም ነው። ሕፃን ልጅ ስሙ እንደ ፓራዳይም ሆኖ የሚቀረጸው፣ ከሁለት ዓመት በላይ ከተደጋገመለት ነው። መሠረታዊ የሆነ የስም ፓራዳይም፣ በመስማት ብቻ ሳይሆን በመናገር እና በመጻፍ ደረጃ፣ በሕፃን ልጅ አዕምሮ ውስጥ ለመቀረጽ፣ እስከ አራት እና አምስት ዓመታት ያስፈልገዋል። ፓራዳይም በአዕምሯችን ውስጥ በዋናነት የሚወቀረው በድግግሞሽ ነው።

ልጁ ካደገና ዕድሜው ሃያ አምስት ከሞላ በኋላ ስሙን መቀየር ቢፈልግ፣ በመጀመሪያ በአዕምሮው ለሃያ አምስት ዓመታት የተገነባው ስሙ ምን እንደሆነና ለምን መቀየር እንደፈለገ ማወቅ እና መረዳት አለበት። ከዚያም አዲስ እንዲጠራበት የፈለገው ስም ምን እንደሆነ መምረጥ እና መወሰን አለበት። ስሙን ለመቀየር የሚፈልግ ሰው፣ በቂ ስሙን እንዲቀይር የሚያደርግ ምክንያት ካለው ስሙን መቀየር ይችላል። ስሙን ለመቀየር የሚፈልግ ሰው በጣም ወሳኝ የሆነውን የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ዘዴ በመጠቀም፣ ስሙን በአዕምሮው ውስጥ መውቀር አለበት። ታዲያ አዲሱ ስሙ የራሱ እንዲሆን፣ ከማንነቱ ጋርም እንዲዋሀድ ሁሌም መደጋገም አለበት። ትኩረት መስጠት ያለበት ወሳኙ ነገር ድግግሞሹ ላይ ነው።

አስቀድመን አንድ ሕፃን ልጅ ምንም ሌላ ስም ሳይኖረው አዲስ ስሙን ለመልመድ ምን ያክል ጊዜ እንደሚያስፈልገው አይተናል። ይህ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት የደረሰ ልጅ፣ አሁን ማድረግ የሚፈልገው ለሃያ አምስት ዓመታት በአዕምሮው ውስጥ በተደጋጋሚ የተቀረጸውን ስሙን በአዲስ ስም መተካት ነው። ዕድሜውን ሙሉ የተጠቀመበትን ስም፣ በአዲስ ስም ለመተካት ብዙ ጊዜ መደጋገም እንደሚያስፈልገው መገመት አይከብድም።

አሁን ስምህን ብትቀይረውም ባትቀይረውም በሕይወትህ ላይ ብዙ ለውጥ ሊያመጣልህ ወይም ላያመጣልህ ይችላል። ስለ ስም እያወራን ያለነው፣ ይህንን ዘዴ በመጠቀም፣ አሁን ያለንን የማንፈልገውን ተራ ፓራዳይም እንዴት አድርገን በምንፈልገው ድንቅ ፓራዳይም መቀየር እንደምንችል ለመረዳት ነው። ብዙ ሰው እንዴት አድርጎ የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥን በመጠቀም፣ የድሮ ተራ ፓራዳይሙን በአዲስና ድንቅ ፓራዳይም እንደሚቀይር ስለማያውቅ፣ ብዙውን ጊዜ የፓራዳይም ለውጥ ሙከራው ሲሳካለት አይታይም።

አንተም ከዚህ በፊት የድሮ ተራ ፓራዳይምህን በአዲስ እና ድንቅ ፓራዳይም ለመቀየር ሞክረህ ሳይሳካልህ ቀርቶ ሊሆን ይችላል። በዛሬው ጥናታችን የድሮ ፓራዳይማችን ምን እንደሆነ፣ በአዕምሯችን ውስጥ እንዴት ሊገነባ እንደቻለና ምን ያክል ኀይል እንዳለው ተረድተናል። ቀጥሎ አሁን ያለንን፣ ነገር ግን የማንፈልገውን ተራ ፓራዳይም በምንፈልገው ድንቅ ፓራዳይም የምንቀይርበትን ምስጢር እንማራለን።

# የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ልምምድ

የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥን በመጠቀም፣ በአዕምሮህ የተገነባውንና የማትፈልገውን የድሮ ተራ ፓራዳይም፣ በአዲስና በምትፈልገው ድንቅ ፓራዳይም ለመቀየር የሚረዱህን ልምምዶች አሁን እንሠራለን። እነዚህን አስር የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ልምምዶች በመጠቀም፣ የድሮ ተራ ፓራዳይምህን በአዲስና ድንቅ ፓራዳይም በመተካት፣ ሕይወትህን ለመቀየር ራስህን አዘጋጅ።

፩. **ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፡** ትናንት ትልቅ ሕልም በሚለው ምዕራፍ፣ ትልቅ ሕልምህን ለመወሰን፣ ራስህን ለማዘጋጀት የተጠቀምካባቸውን ዘዴዎች በመጠቀም፣ ራስህን ለዚህ ድንቅ የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ልምምድ አዘጋጅ።

ይህንን ልምምድ ለመሥራት ትክክለኛ ሰዓት፣ ቦታ እና በትኩረት ለመሥራት የሚረዱህን ምቹ ወንበርና ጠረጴዛ አስቀድመህ በመምረጥ አዘጋጅ። ከሁሉም በላይ ግን አካልህንና አዕምሮህን ለዚህ ልምምድ አዘጋጅ።

፪. **አስፈላጊ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፡** ይህንን ልምምድ ለመሥራት የሚረዱህን ብዕር፣ ማስታወሻ እና አንድ *"ቀይ ወረቀት"* አስቀድመህ አዘጋጅ።

፫. **ፓራዳይምህን መጻፍ፡** በአዕምሮህ ውስጥ ያሉትን ተራ እና ድንቅ ፓራዳይሞች አስቀድመህ ባዘጋጀኸው ማስታወሻ ላይ ጻፋቸው። ድንቅ ፓራዳይም፣ አሁን የምትፈልገውን ውጤት እየሰጠህ ያለና ወደ ሕልምህ እንድትሄድ የሚረዳህ ፓራዳይም ነው። ተራ ፓራዳይም ደግሞ የማትፈልገውን ውጤት እየሰጠህ ያለና ወደ ሕልምህ እንዳትሄድ ዕንቅፋት የሚሆንብህ ፓራዳይም ነው። አሁን ሁለቱንም ውጤቶች እየሰጡህ ያሉ ድንቅና ተራ ፓራዳይሞችህን፣ ከነ ጥቅም እና ጉዳታቸው በማስታወሻህ ላይ ጻፋቸው።

ይህንን ልምምድ ስትሠራ፣ አሁን ያለህ ፓራዳይም ምን ዐይነት ፓራዳይም መሆኑን፣ በሕይወትህ ምን ዐይነት ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑንና ሕይወትህን ወደ የትኛው አቅጣጫ እየወሰደ መሆኑን በደንብ መገንዘብ አለብህ።

፬. **በቀይ ወረቀት ላይ መጻፍ፡** በቅድመ ዝግጅት ወቅት ባዘጋጀኸው ቀይ ወረቀት ላይ ለመጻፍ ተዘጋጅ። በዚህ ቀይ ወረቀት ላይ የምትጽፈው፣ አሁን ያለህን የማትፈልገውን ተራ ፓራዳይም ነው።

አሁን ያለህን የማትፈልገውን ውጤት እየሰጠህ ያለውን እና ወደ ሕልምህ እንዳትሄድ ዕንቅፋት የሆነብህን ተራ ፓራዳይም ከነ ሙሉ ችግሩ እና ዕንቅፋቱ በዚህ ቀይ ወረቀት ላይ በዝርዝር አንድም ሳታስቀር በግልቀት ጻፍ። ተራ ፓራዳይም ወይም የራስህ ሰበበኛ፣ የምትፈልገውን ውጤት እንዳታገኝ፣ ሕልምህን እንዳታሳካ እና ሕይወትህን እንዳትቀይር፣ የሚደረድርልህን ችግሮች፣ ዕንቅፋቶች፣ ሰበቦች እና ውሸቶች በዝርዝር ጻፋቸው።

ተራ ፓራዳይምህን ባዘጋጀኸው ቀይ ወረቀት ላይ ስትጽፈው፣ ከነ ሙሉ ስሜቱ አብራርተህ ጻፈው። ተራ ፓራዳይምህ ሕልምህን እንዳታሳካ እና የምትፈልገውን ዐይነት ድንቅ ሕይወት እንዳትኖር ዕንቅፋት በመሆን ደስታህን እየሰረቀብህ ነው። አሁን የማትፈልገውን አሉታዊ ውጤት እና ስሜት የሚሰጥህን ተራ ፓራዳይም፣ ያለመፈለግህ ጥግ ድረስ፣ በዚህ ቀይ ወረቀት ላይ ጻፈው።

፭. **ቀይ ወረቀቱን ማቃጠል፡** አሁን ይህንን ለረጅም ጊዜ ያደከመህን እና አንዳንዴም ውስጥህን ያቃጠለውን፣ የማትፈልገውን ተራ ፓራዳይም፣ በቀይ ወረቀት ላይ ጽፈህ በእሳት አቃጥለው።

- እነዚህን የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ርምጃዎች አንብበሀቸው ብቻ ካለፍክ፣ በአዕምሮህ ዕውቀት ብቻ ነው የምትጨምረው እንጂ ሕይወትህን አትቀይርም። ሕይወትህን ለመቀየር የምትፈልግ ከሆነ፣ እነዚህን መመሪያዎች በጥንቃቄ መከተልና ማድረግ አለብህ።

አሁን በቀይ ወረቀት ላይ የጻፍከውን የማትፈልገውን ፓራዳይም በእሳት አቃጥለኸዋል። ተራ ፓራዳይምህን፣ ቀይ ቀለም ባለው ወረቀት ላይ ጽፈህ በእሳት ስታቃጥል፣ ለአዕምሮህ አንድ ትዕዛዝ እየሰጠኸው ነው። አደጋን በሚያመለክተው ቀይ ቀለም ባለው ወረቀት ላይ የድሮ ፓራዳይምህን ጽፈህ ስታቃጥል፣ ለአዕምሮህ "ከዚች ቅጽበት ጀምሮ፣ በዚህ ተራ ፓራዳይም አልመራም!" የሚል ትዕዛዝ እየሰጠኸው ነው። በቀይ ወረቀት ላይ የድሮ ፓራዳይምህን ጽፈህ ስታቃጥል ራስህን ከፓራዳይም የአዕምሮ እስር ቤት ነጻ እያወጣህ ነው።

፮. **የምትፈልገውን አዲስ ፓራዳይም መዘርዘር፡** አስቀድመህ ባዘጋጀኸው ማስታወሻ ላይ ለመጻፍ ተዘጋጅ። በዚህ ማስታወሻ፣ አዲሱንና የምትፈልገውን ድንቅ ፓራዳይም ጻፍ። የምትፈልገውን ውጤት ለማግኘት፣ ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር የሚረዳህን ፓራዳይም በዝርዝር ጻፍ።

በዚህ ደረጃ በሕይወትህ እንዲኖርህ የምትፈልገውንና የሚያጠነክርህን ድንቅ ፓራዳይም በዝርዝር መጻፍ አለብህ። በዚህ ማስታወሻ ላይ የምትጽፈው የአዲሱ ፓራዳይምህ ዝርዝር፣ በቀዩ ወረቀት ላይ ከጻፍከው ዝርዝር ተቃራኒ መሆን አለበት።

፯. **ቀዳሚውን አዲስ ፓራዳይም መምረጥ፡** በአምስተኛ ደረጃ ከዘረዘርካቸው ዝርዝሮች መካከል፣ አሁን ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር በጣም የሚረዳህንና በቀዳሚነት የሚጠቅምህን ፓራዳይም በመምረጥ፣ ገጽ 76 ላይ በሚገኘው "አዲስ ድንቅ ፓራዳይም" የሚል ርዕስ ባለው ገጽ ላይ ጻፍ። በዚህ ገጽ ላይ የምትጽፈው የፓራዳይም ዝርዝር፣ መሆን ያለብህን እንድትሆንና መሥራት ያለብህን እንድትሠራ የሚረዳህ የፓራዳይም ዝርዝር መሆን አለበት። ትልቁን ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ የሚያጠነክርህን አዲሱን ፓራዳይም በጥንቃቄ እና በትኩረት ጻፍ።

፰. **አዲሱን ፓራዳይም መደጋገም፡** ፓራዳይም በአዕምሯችን ውስጥ የሚገነባው በድግግሞሽ መሆኑን በተደጋጋሚ አይተናል። ለዓመታት በአዕምሮህ የተገነባውን እና የማትፈልገውን የድሮ ተራ ፓራዳይም፣ በአዲስና ድንቅ ፓራዳይም ለመተካት የሚረዳህ ዋናው ምስጢር ድግግሞሽ ነው። ፓራዳይምህ እንዲሆን የመረጥከውን አዲስ የፓራዳይም ዝርዝር፣ በየቀኑ በተደጋጋሚ እየጻፍክ እና እያነበብክ፣ በልብህ ውቀረው። ይህንን ዝርዝር ለሃያ አንድ ቀናት፣ ሳታቋርጥ በየቀኑ ደጋግመህ ስትጽፈው እና ጮክ ብለህ ስታነበው፣ ዋና የአዕምሮህ ፓራዳይም ሆኖ ይወቀራል። ይህ ድንቅ ፓራዳይም ዋና የአዕምሮህ ፓራዳይም ሆኖ ሲወቀር ደግሞ የምትፈልገውን ውጤት እንድታገኝ ይረዳሃል። ይህ አዲሱ በአዕምሮህ ውስጥ የተገነባ ድንቅ ፓራዳይም፣ ትልቁን ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር በምታደርገው ጉዞ ላይ፣ ምሪት ይሰጥሀል፤ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት እንድትከፍልም ጥንካሬውን ይሰጥሃል። መገንባት የምትፈልገውን አዲስ እና ድንቅ ፓራዳይም በልብህ ለማኖር ፓራዳይምህን በድግግሞሽ ወ ትረው። አዲስና ድንቅ ፓራዳይም በልብህ ስትወቅር፣ ሕይወትህ በቀላሉ ይቀየራል። ድግግሞሽ ለዘላቂነት መቀየር ለምትፈልጋቸው ልማዶችና ፓራዳይሞች ዋና መፍትሄ ነው።

    - ነገ ማጥናት ከምንጀምረው "የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች" ምዕራፍ ቀጥሎ፣ "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መሥራት እንጀምራለን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተዘጋጀው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መሥሪያ በተጨማሪም፣ አንተ በምታዘጋጃቸው አርባ ሁለት የመለማመጃ አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ፣ በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ፣ የድሮ ተራ ፓራዳይምህን በአዲስና ድንቅ ፓራዳይም የምትተካበትን የመጻፍ ልምምድ መሥራት ትጀምራለህ።

፱. **ምናብህን መጠቀም፡** ምናብ በአዕምሯችን ወደምንፈልገው ጊዜና ቦታ ለመሄድ የሚጠቅመን የአዕምሮ መሣሪያችን ነው። (የአዕምሮ መሣሪያህ የሆነውን ምናብ እንዴት በትክክል መጠቀም እና ማጠንከር እንደምትችል ለመረዳት፣ በዚህ መጽሐፍ ፪ኛ ሳምንት ፲፪ኛ ቀን ላይ ያለውን ምዕራፍ ተመልከት)

ምናብህን በመጠቀም፣ የጻፍከው ድንቅ ፓራዳይም፣ እውን ወደሚሆንበት ቀን መጥቀህ ተጓዝ። በአዕምሮህ የተገነባው ድንቅ ፓራዳይምህ፣ ሕይወትህን ሲመራ በምናብህ አሻግረህ ተመልከት። አዲሱና ድንቁ ፓራዳይምህ ወደ ሕልምህ ሲወስድህ እንዲሁም ሕይወትህን ሲቀይር፣ የሚኖርህን ደስታ እና ስኬት፣ ሙሉ ስሜት ጨምረህ በምናብህ ተመልከተው። ነገ የምትሆነውን አንተ፣ የምትኖረውን ድንቅ ሕይወት፣ የምታመጣውን ተጽዕኖ፣ በአጠቃላይ ለአንተ እና ለምትፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ፣ ከገደብ ነጻ ሆነህ፣ በደስታ ማድረግ የምትፈልገውን ሁሉ ስታደርግ፣ በዐይነ ሕሊናህ ተመልከተው። ብሩሽ እንደያዘ ሰዓሊ፣ ነገህን በምናብ ብሩሽህ ቀባው። ከልካይ እና ገዳቢ ሳይኖርብህ፣ ያሻህ ቦታ ደርሰህ የምትመጣው፣ በሽርፍራፊ ሰከንዶች ወይም ደቂቃዎች ውስጥ ማንም ሊያሳካው የሚከብደውን ነገር አሳክተህ የምትመለሰው በምናብህ ነው።

፲. **ወደ ድርጊት መግባት፡** ሥጋዊ አካላችን በአዕምሯዊ አካላችን ቁጥጥር ሥር እንደሆነው ሁሉ፣ ድርጊቶቻችንና ተግባሮቻችንም በፓራዳይማችን ቁጥጥር ሥር ናቸው ያሉት። በድንቁ አዕምሯዊ አካልህ የሚመራውን ድንቁን ሥጋዊ አካልህን በመጠቀም፣ ድንቅ የሆኑ ድርጊቶችንና ተግባሮችን ብቻ ፈጽም። በድንቅ ፓራዳይምህ የጻፍካቸውን ነገሮች ሁሉ አሁን በተግባር ማድረግ ጀምር። ከዚህ በኋላ ድንቅ ፓራዳይም ያለው ድንቅ የሰው ልጅ እንደሚያስበው አስብ፤ እንደሚሠራው ሥራ፤ እንደሚንቀሳቀሰው ተንቀሳቀስ፤ እንደሚሯሯጠው ተሯሯጥ፤ ማድረግ እና ማሳካት ያለብህን ነገር ሁሉ፣ ማድረግህንና ማሳካትህን ጀምር፤ ትልቅ ሕልምህንም አሳካ።

እነዚህን አስር የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ ልምምድ መመሪያዎች በመጠቀም፣ ትልቁን ሕልምህን ማሳካት የሚችል ድንቅ ፓራዳይም በአጽንዖት በማሰብ፣ በመጻፍ እና በማንበብ፣ በአዕምሮህ በመቅረጽ ገንባ። በዚህም አዲሱና ድንቁ ፓራዳይምህ በድብቁ አዕምሮህ በመወቀር ሕይወትህን ይቀይረዋል።

## መመሪያዎች

ድንቅ ፓራዳይምህን በሚቀጥለው ገጽ ከመጻፍህ በፊት፣ እባክህ እነዚህን መመሪያዎች በማንበብና በመከተል፣ ሕይወትህን መቀየር የሚችል አዲስና ድንቅ ፓራዳይም በዚህ መጽሐፍና በልብህ በጥንቃቄ ውቀር።

፩. **ግልጽነት፡** በሚቀጥለው ገጽ ላይ የምትጽፈው አዲስ ድንቅ ፓራዳይም አጭር እና ግልጽ የሆነ መሆን አለበት። ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር የሚረዳህን ድንቅ ፓራዳይም በጥንቃቄ በመምረጥ ጻፍ።

፪. **አዎንታዊነት፡** የምትጽፈው አዲስ ድንቅ ፓራዳይም አዎንታዊ ብቻ መሆን አለበት። አሉታዊ መልዕክት ያለውን ድንቅ ፓራዳይም፣ ለሃያ አንድ ቀናት ጽፈህ ካነበብከ፣ አሉታዊ ፓራዳይም በውስጥህ ይገነባል። ስለዚህ በሚቀጥለው ገጽ ላይ የምትጽፈው ፓራዳይም እና በፓራዳይምህ ሥር የሚሰፍሩ ዝርዝር ሀሳቦች በሙሉ አዎንታዊ መሆን አለባቸው።

፫. **አሁንነት፡** አዲስና ድንቅ ፓራዳይምህን ስትጽፍ፣ ወደ ፊት እንደምታሳካው አድርገህ ሳይሆን አሁን እንደተሳካ አድርገህ ነው መጻፍ ያለብህ። ለሃያ አንድ ቀናት የምትጽፈውን አዲስና ድንቅ ፓራዳይምህን፣ ወደ ፊት እንደሚሳካ ተስፋ አድርገህ የምትጽፈው ከሆነ፣ ሁሌም ቢሆን ተስፋ ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው። አዲስ ድንቅ ፓራዳይምህን እንደተሳካ አድርገህ ስትጽፈው ግን፣ ሕልምህን መኖር፣ ሕይወትህንም መቀየር ትችላለህ።

---

፮. ፓራዳይም

# አዲስ ድንቅ ፓራዳይም

# ቀን ፯

*******

# የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች

*"አሸናፊ ሰዎች ተሸናፊ ሰዎች ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር የማድረግ ልማድ አላቸው!"*

አሸናፊ ሰዎች ያሸንፋሉ፤ ተሸናፊ ሰዎች ደግሞ ይሸነፋሉ። ሕይወትን ልብ ብለህ ከተመለከትክ፣ አሸናፊዎች ለማሸነፍ በመሥራት ሁሌም ሲያሸንፉ፣ ተሸናፊዎች ደግሞ፣ ምንም እንኳ ለመሸነፍ ባይሠሩም፣ ላለመሸነፍ በመሥራት ሁሌም ይሸነፋሉ። አሸናፊዎች የሚያሸንፉት አሸናፊ ሆነው ስለተወለዱ ሳይሆን፣ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስላሏቸው ነው። በሕይወትህ ማሸነፍ ከፈለግክ፣ የአሸናፊነትን ልማዶች በአዕምሮህ በደንብ መገንባት አለብህ።

ከዚህ በፊት ያሉትን ሁለት ምዕራፎች በደንብ አጥንተህ በመረዳት፣ ትልቁን ሕልምህንና ድንቅ ፓራዳይምህን በአዕምሮህ እየገነባህ ስለሆነ እንኳን ደስ አለህ። ትልቅ ሕልምህ እና ድንቅ ፓራዳይምህ፣ ራስህን ሕልሙን ማሳካት ወደሚችል ሰውነት በመቀየር፣ ሕይወትህን እንድትቀይር ይረዱሃል። አሁን ደግሞ ሦስተኛውን ወደ ሕልምህ ለመሄድ የሚረዳህን ወሳኝ የሆነ የአዕምሮ ፕሮግራም ትገነባለህ። ይህ ድንቅ የአዕምሮ ፕሮግራም "ልማድ" ይባላል፤ የአሸናፊ ሰዎች ልማድ!

ፓራዳይም ከልጅነትህ ጀምሮ፣ በአዕምሮህ የተገነባ የልማዶች እና እምነቶች ድምር ነው። ፓራዳይምህን ሙሉ በሙሉ ወደ ድንቅነት ስትቀይረው፣ ድንቅ ሕይወት መኖር ትጀምራለህ። ፓራዳይምህን ወደ ድንቅ ፓራዳይምነት ቀይረህ፣ አንዳንድ ልማዶችህን ወደ ድንቅ ልማድነት ካልቀየርካቸው ግን፣ የዕድገት ፍጥነትህን ሊቀንሱና ወደ ኋላ ሊመልሱህ ይችላሉ። በዚህ ምዕራፍ፣ ትኩረታችንን የምናደርገው "ልማዶች" ላይ ነው። አሁን ያሉህ ልማዶች፣ ድንቅ እና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ናቸው ወይስ ተራ እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች? አሁን በአዕምሮህ ያሉ ልማዶች ተራ እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ከሆኑ፣ እንዴት አድርገህ ወደ ድንቅ ልማዶች እንደምትቀይራቸው ማሰብ ያስፈልግሃል።

ተሸናፊ ሰዎች ቀላል ነገሮችን እንጂ "ከበድ ይላሉ" ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች ማድረግ አይፈልጉም። ተሸናፊ ሰዎች፣ ከባድ እና መሥዋዕትነት የሚጠይቁ ነገሮችን ማድረግ አይመቻቸውም። ለምሳሌ ተሸናፊ ሰዎች በጥዋት መነሳት፣ ኀላፊነት መውሰድ፣ ስፖርት ማዘውተር፣ ማንበብ፣ ትላልቅ ዕቅዶችን ማቀድ፣ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ሥራዎች መሥራት ወዘተ... አይወዱም። ተሸናፊ ሰዎች በየትኛውም መንገድ ቀለል ያሉ ነገሮችን ማድረግ ብቻ ነው የሚመቻቸው። ተሸናፊ ሰዎች ከሚመቿቸው ቀላላል ነገሮች መካከል "አርፍዶ መነሳት፣ ኀላፊነት አለመውሰድ፣ ትናንሽ ሥራዎችን መሥራት፣ ሁሌም አቋራጭ መንገዶችን መጠቀም፣ ማማረር፣ ማሳበብ፣ ተዝናኖት ማብዛት፣ የሚረባውንና እንቶ ፈንቶውን ማውራት፣ እንዲሁም ሱስ እስኪመስል ድረስ ማኅበራዊ ድረ ገጾችን መጠቀምና ቴሌቪዥን ላይ ከልክ ያለፈ ጊዜ ማሳለፍ" የመሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

አሸናፊ ሰዎችም ልክ እንደ ተሸናፊ ሰዎች ሁሉ "ከባባድ" የሚባሉ ነገሮችን የማድረግ ልዩ ተፈጥሯዊ ፍላጎት የላቸውም። አሸናፊ ሰዎች እንደ ተሸናፊ ሰዎች ሁሉ አርፍዶ መነሳት፣ ቴሌቪዥን ላይ ቁጭ ብሎ ማምሸትና የመሳሰሉትን ቀለል ያሉ ነገሮች ማድረግ ይቀላቸዋል። ነገር ግን አሸናፊ ሰዎች እነዚህን ቀላላልና ምቾት ያላቸውን ነገሮች በማድረግ፣ እንደማያሸንፉ ጠንቅቀው ይረዳሉ። አሸናፊ ሰዎች ተሸናፊ ሰዎች ማድረግ የማይፈልጓቸውን ከባባድ ነገሮች በማድረግ፣ ሕይወትን ያሸንፋሉ፤ የሚፈልጉትን ውጤትም ያገኛሉ።

በቀዳሚው ገጽ ያነበብከው ጥቅስ ወይም የአሸናፊነት ቀመር ግን "አሸናፊ ሰዎች፣ ተሸናፊ ሰዎች ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር፣ ያደርጋሉ!" አይደለም የሚለው። የአሸናፊነት ቀመር የሚለው "አሸናፊ ሰዎች፣ ተሸናፊ ሰዎች ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር፣ የማድረግ ልማድ አላቸው!" ነው። ይህንን የአሸናፊነት ቀመር በልብህ መውቀር አለብህ። የአሸናፊ ሰዎች ልማድ በውስጥህ ስትገነባ፣ ሌሎች ሰዎች ማድረግ የማይፈልጓቸውን "ከባባድ" ነገሮች በማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የማድረግ ልማድ ጭምር በማዳበር፣ ሰዎች በቀላሉ የማያገኟቸውን ትላልቅ ውጤቶች መጨበጥ ትችላለህ።

አሁን ይህንን ተዓምራዊ የስኬት ቀመር በመጠቀም፣ ሕይወትህን እንዴት መቀየር እንደምትችል አስብ። ከዛሬ ጀምሮ በጥዋት በመነሳት፣ ቀንህን በጸሎት እና በምስጋና በመጀመር፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ፣ በጥዋቱ በማቀድ፣ ሥራ ቦታህ አስቀድመህ በመድረስ፣ ሥራዎችህን በትኩረት በመሥራት፣ ጊዜህን በአግባቡ በመጠቀም፣ ራስህን እና ቤተሰብህን ጤናማ መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊና ሥጋዊ ምግብ በመመገብ፣ በቂ ውሃ በመጠጣት፣ በቂ ዕረፍት በማድረግ እና ሌሎች ድንቅ ልማዶችን በማዳበር፣ ለሃያ አንድ ቀናት ብቻ ብትቀጥል፣ የት መድረስ እንደምትችል ማንም አይገምተውም። እነዚህን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስትጠቀምባቸው፣ ትልቁን ሕልምን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር በእጅጉ ይረዱሀል።

በአዕምሮህ አስቀድመው የተቀረጹ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ካሉ ግን፣ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልግሀል። ብዙውን ጊዜ የሰው ልጅ "ከነገ ጀምሮ በጥዋት መነሳት እጀምራለሁ፤ እንዲህና እንዲያ አደርጋለሁ" ብሎ ማታ ላይ ይወስናል። ጥዋት የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ ግን፣ በድብቁ አዕምሮው የተገነባው የመሸነፍ እና የማርፈድ ልማድ ቦታውን ይወስድና፣ ሰውዬው ተመልሶ እስኪረፍድበት ድረስ በመተኛት፣ ቀኑን በመሸነፍ እንዲጀምር ያደርገዋል። የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ ከአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ባልተናነሰ ሁኔታ ሕይወትህን የመቆጣጠር አቅም አላቸው። የተሸናፊነት ልማዶችህን አሁኑኑ ካላጠፋሀቸው፣ ሕልምህን እንዳታሳካ እና ሕይወትህን እንዳትቀይር እንቅፋት ሊሆኑብህ፣ በመጨረሻም ሊያጠፉህ ይችላሉ።

ስለዚህ አሁን ያሉህን የተሸናፊነት ልማዶች፣ በድንቅና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች መተካት እንድትችል፣ ልማድ ምንድን ነው? እንዴትስ ነው በአዕምሯችን የተገነባው? እንዴት አድርገንስ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶቻችንን በአሸናፊ ሰዎች ልማዶች እንቀይራቸዋለን? የሚለውን በጥንቃቄ እንመርምር።

# ልማድ ምንድን ነው?

ፈጣሪ በጥንቃቄና ድንቅ በሆነ መንገድ ስለፈጠረን ነው ልማድ የሚባል የአዕምሮ ፕሮግራም የሰጠን። ልማድ በድብቁ አዕምሯችን የሚገኝ የፓራዳይም ክፍል ሆኖ፣ በየቀኑ በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን ነገሮች የሚመዘግብ ፕሮግራም ነው። ልማድ ልክ እንደ ፓራዳይም ሁሉ፣ ለሃያ አራት ሰዓታት በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን ድርጊቶችና የምናከናውናቸውን ተግባራት በድብቁ አዕምሯችን ይመዘግባቸዋል። ከዚያም ነገሮቹን ደግመን ማድረግ ስንፈልግ፣ አስበን ሳይሆን፣ ምንም ሀሳብ ሳንሰጠው፣ ወዲያውኑ እንድናደርጋቸው ይረዳናል። ለምሳሌ ጥዋት ተነስተህ ገላህን ስትታጠብ፣ ልብስ ስትለብስ፣ ጫማ ስትጫማ፣ ቁርስ ስትበላ፣ መኪና ስትነዳና በአጠቃላይ በሕይወትህ በተደጋጋሚ የምታደርጋቸውን መሠረታዊ ነገሮች ስታደርግ፣ የምታደርጋቸው ሆነ ብለህና አስበህ ሳይሆን፣ በድብቁ አዕምሮህ ባሉ ልማዶችህ ተመርተህ ነው።

በሮግፐ እንዳንዴ በሕይወትህ መሠረታዊ የሆኑና በተደጋጋሚ የምታደርጋቸውን ነገሮች ሆነ ብለህ በተለየ መንገድ ማከናወን ትችላለህ። አብዛኛውን ጊዜ ግን፣ በሕይወትህ በመሠረታዊነት እና በተደጋጋሚ የምታደርጋቸውን ነገሮች፣ አስበህ ሳይሆን፣ ምንም ልብ ሳትለው በውስጥህ ያለው የልማድ ፕሮግራም ነው የሚያከናውንልህ። ስለዚህ በሕይወትህ የምታደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች የምታደርጋቸው አብዛኛውን ጊዜ ፈልገህ እና ሆነ ብለህ ሳይሆን፣ በውስጥህ በገነባሃቸው ልማዶችህ በመመራት ነው። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ካሉህ፣ የማሸነፍ ልማድ ስለምታዳብር፣ ሁሌም ታሸንፋለህ። የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ካሉህ ግን፣ ምናልባት አንዳንዴ ሆነ ብለህ ማሸነፍ ብትችል እንኳ፣ ወዲያውኑ ወደ ልማዶችህ በመመለስ፣ መሸነፍህ የማይቀር ይሆናል። አሁን እነዚህ ሕይወታችንን የሚቆጣጠሩ ልማዶች እንዴት አድርገው በአዕምሯችን እንደተገነቡ ቀጥለን እንመለከታለን።

# እንዴት ነው ልማዶች በአዕምሮህ የተገነቡት?

ልማዶች ልክ እንደ ፓራዳይም፣ ወደዚች ዓለም ስትመጣ፣ ካንተ ጋር አብረውህ የመጡ ሳይሆኑ፣ ከልጅነትህ ጀምሮ ከሰዎች እና ከአካባቢህ በመማር የለመድካቸው የአዕምሮህ ፕሮግራሞች ናቸው። ከጥዋት አንስቶ እስከ ማታ ሕይወትህን የሚቆጣጠሩት ልማዶች ሁሉንም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ፣ ሆነ ብለህ ራስህ የፈጠርካቸው ሳይሆኑ፣ ከአካባቢህ እና በሕይወትህ ተጽዕኖ ከፈጠሩ ሰዎች የወረስካቸው ናቸው። ትንሽ ጊዜ ወስደህ ጥሩ እና መጥፎ ልማዶችህን ብትፈትሻቸው፣ እነዚህን ሕይወትህን የሚቆጣጠሩ ልማዶች ከማን እንደተማርካቸው ወይም እንደወረስካቸው መገንዘብ ትችላለህ። አሁን በሕይወትህ ውስጥ መሠረታዊ የሆኑ ልማዶች እንዴት በአዕምሮህ ውስጥ እንደተገነቡ እና ሕይወትህን ምን ያክል እየተቆጣጠሩት እንደሆነ፣ ቀጣዮቹን ምሳሌዎች በመጠቀም እንመረምራለን።

### መልበስ

ዛሬ ጥዋት ልብስህን እንዴት እንደለበስክ፣ ጫማህንም እንዴት እንደተጫማህ አስብና ቀጥሎ የማቀርብልህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክር። ጥዋት ከቤት ለመውጣት ስትዘጋጅ፣ መጀመሪያ ያደረግከው የቀኝ እግር ጫማህን ነው ወይስ የግራ? ሱሪህንስ ስትለብስ ያስቀደምከው ቀኝህን ነው ወይስ ግራህን? ብዙ ሰዎችን እነዚህን ጥያቄዎች ስጠይቃቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ በግምት እንጂ፣ እርግጠኛ ሆነው አይመልሱልኝም። ብዙ ሰው የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ማስታወስ የሚከብደው፣ ጥዋት እነዚህን ነገሮች ሲያደርጋቸው ሆነ ብሎ እና አስቦ ሳይሆን፣ ምንም ሳያስብ፣ በልማዶቹ ስለሚያደርጋቸው ነው። በልማዶቹ ሳይሆን፣ አስቦና ሆነ ብሎ አድርጎት ቢሆን ኖሮ፣ ማንም ሰው የትኛውን ጫማ ቀድሞ እንዳደረገ ማስታወስ ይቀለው ነበር። "ልማድ ከሰይጣን ይበልጣል!" የሚባለውም ለዚህ ነው።

ጥዋት ከመኝታህ ተነስተህ፣ ምን እንደምትለብስ ቀድመህ አስበህ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ልብሱን እንዴት አድርገህ እንደምትለብስ እና ጫማውን እንዴት አድርገህ እንደምትጫማ፣ አንተ ምንም ሳታስብ ልማዶችህ ናቸው ሁሉንም ነገር ቀለል አድርገው የሚያደርጉልህ።

ወደ ልጅነት ጊዜህ ብንመለስ ግን፣ እነዚህን አሁን በልማዶችህ ቀለውህ የምታደርጋቸውን ነገሮች፣ በቀላሉ አታደርግም ነበር። ሕፃን ሆነህ ያለ ሰዎች እርዳታ በራስህ ለመልበስ ስትሞክር፣ ምን ያክል አድካሚ እንደነበረ ታስታውሳለህ? ብዙ ሕፃናት ልብሳቸውን አዙረው ይለብሳሉ፤ የቀኝና ግራ ጫማቸውንም ይቀያይራሉ። የጫማቸውን ክር ማሰር'ማ የማይታሰብ ነው። ከዚያ ግን ወላጆቻቸው በትዕግስት እንዴት እንደሚለብሱ ደግመው ደጋግመው በተግባር ያስተምሯቸዋል። ከብዙ መደጋገም በኋላ ልጆቹ ይከብዳቸው የነበረውን ነገር፣ ከምንም ሳይቆጥሩት ማድረግ ይጀምራሉ። ምክንያቱም "መልበስ" የሚባል አዲስ ልማድ በአዕምሯቸው ስለሚቀረጽ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ብዙ ልጆች ልብስ የመልበስ ልማድ በሦስት ዓመታቸው፣ የጫማ ክር የማሰር ልማድ ደግሞ በስድስት ዓመታቸው ነው የሚያዳብሩት።

በሕይወታችን ሙሉ ቀን በተደጋጋሚ የምናደርጋቸው ነገሮች፣ በአዕምሯችን እንደ ልማድ ሆነው መገንባት ይጀምራሉ። እነዚህ በአዕምሯችን የሚገነቡ ልማዶች፣ እንቅስቃሴዎቻችንን እና ድርጊቶቻችንን በመቆጣጠር፣ በየቀኑ እና በተደጋጋሚ የምናደርጋቸውን ነገሮች ቀለውንና ምንም ሳናስብባቸው እንድናደርጋቸው ይረዱናል።

## ቀኝና ግራኝ እጅ

ከሁለቱ የግራና የቀኝ እጆችህ፣ ሥራ ለመሥራት፣ የምትጠቀምበት እጅህ የትኛው ነው? ምግብ ለመብላት፣ ጽሑፍ ለመጻፍ እና የተለያዩ መሠረታዊ ነገሮችን ለማድረግ የምትጠቀምበት እጅህ የትኛው ነው? ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ከዓለማችን ሕዝቦች ዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ቀኝ እጃቸውን በብዛት የሚጠቀሙ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ግራቸውን በብዛት የሚጠቀሙ ናቸው። እኛ የሰው ልጆች ወደዚች ዓለም ስንመጣ፣ ቀኝ እጃችንን አብዝተን እንድንጠቀምም ሆነ ግራኝ እንድንሆን ተደርገን አልተፈጠርንም። ታዲያ "እንዴት አድርገን ነው አሁን ቀኝ ወይም ግራኝ የሆንነው?" ብለን ብንጠይቅ መልሱ "በልማዶቻችን ነው" የሚል ይሆናል።

ሕፃን ልጅ ሆነን፣ ነገሮችን በእጆቻችን መነካካት እና መሞካከር ስንጀምር፣ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ጣልቃ ካልገቡ፣ ደስ በሚለን እጃችን ነገሮችን ማድረግ እንጀምራለን፤ በዚያውም እንለምደዋለን። ነገር ግን በዚህ ዕድሜያችን በአካባቢያችን ካሉ ሰዎች መካከል አንዱ፣ ለምሳሌ በቀኝ እጃችን ብቻ ነገሮች እንድናደርግ ተጽዕኖ ከፈጠረብን፣ ቀኝ እጅ እንሆናለን። ማስተዋል ያለብን ነገር በሕፃንነታችን በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ተጽዕኖ ቢያደርጉብንም ባያደርጉብንም በተደጋጋሚ የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እንደ ልማድ ሆነው በአዕምሯችን የሚገነቡት በለመድነውና በተለማመድነው ልክ መሆኑን ነው። እነዚህ ልማዶች አንዴ በአዕምሯችን ከተገነቡ በኋላ፣ ሕይወታችንን መቆጣጠር ይጀምራሉ።

## እንጀራ

እንጀራን በእጃችን ጠቅልለን መብላት የተማርነው በልጅነታችን በለመድነው ልማድ ነው። አልበርት አይንስታይን ቆንጆ የባህላችን ምግብ የሆነውን እንጀራ በምርጥ ዶሮ ወጥ አዘጋጅተን ወደ ቤታችን ብንጠራው፣ እንደ ማንኛውም ሐበሻ እንጀራ በእጁ ጠቅልሎ መጉረስ ባይችል፣ ይሄ ሰውዬ "ሰነፍ መሆን አለበት" ተብሎ አይፈረድበትም። አንድ ነገር አላደረግከም ማለት፣ ልማዱ በውስጥህ አልተገነባም ማለት እንጂ የአንተ አቅም ውሱን ነው ማለት አይደለም።

አንተ ድንቅ የሰው ልጅ፣ የፈለግከውን ነገር ደጋግመህ በማድረግ፣ መልመድ ትችላለህ። አንድን አዲስ ነገር እንደ ልማድ በማዳበር፣ ምንም ሳታስበው ለማድረግ ከፈለግክ፣ ያንን ነገር በድብቁ አዕምሮህ፣ ልማድና ፓራዳይም ሆኖ እስኪቀረጽ ድረስ ደጋግመህ ማድረግ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ። ለምሳሌ እንጀራ ብቻ እየበላ ያደገ አንድ ሐበሻ፣ ፓስታ ብታቀርብለት፣ በሹካ ጠቅልሎ መብላት ሊከብደው ይችላል። ይህ ሰውዬ ፓስታውን በሹካ መጠቅለል የከበደው፣ ሰነፍ ስለሆነ ወይም ፓስታ የመብላት አቅም ስለሌለው ሳይሆን፣ በአዕምሮው ፓስታ የመብላት ልማድና ፓራዳይም ስላልተገነባ ብቻ ነው።

## ማንበብ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያነበብክ ያለኸውን የልማዶች ምስጢር እንዴት አገኘኸው? አንተ ጥሩ የአማርኛ አንባቢ ስለሆንክ ይህንን መጽሐፍ ስታነብ የምታተኩረው ከዚህ ጽሑፍ ምን እንደምትማር እንጂ፣ እንዴት አድርገህ አማርኛውን እንደምታነብ አይደለም። አማርኛ በደንብ በውስጥህ የገባ ቋንቋ ስለሆነ፣ ስለ ቋንቋው አስበህ ሳይሆን፣ ምንም ሀሳብ ሳትሰጠው በውስጥህ ያለው አማርኛ የማንበብ ልማድህ ነው መጽሐፉን የሚያነብልህ።

ይህ መጽሐፍ፣ በረንብ በማትረዳው ቋንቋ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ግን፣ የማንበብና የመረዳት ፍጥነትህ ምን ያክል ሊቀንስ እንደሚችል መገመት አያቅትህም። በአማርኛ የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ ለአንተ ቀላል የሆነው፣ አማርኛ ቀላል ቋንቋ ስለሆነ ሳይሆን፣ አማርኛ የማንበብ ልማድ በውስጥህ ስለተገነባ ነው። ይህ ሲባል ግን አማርኛን ስትወለድ ጀምሮ ነው የቻልከው ማለት አይደለም።

ወደዚች ዓለም ስትመጣ፣ ምንም ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ክህሎት አልነበረህም። ከዚያ ግን ከቤትና ትምህርት ቤት ቀስ በቀስ ማንበብና መጻፍ በመለማመድ፣ አማርኛ ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ልማድና ፓራዳይም በአዕምሮህ ቀረጽክ። ደስ የሚለው ነገር፣ አስቦ ለሚያምን "ሁሉም ነገር ይቻላል!" የተወሰነ ሰዓት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ደስ ስላለህ ወይም አስተማሪዎችህና ወላጆችህ እንደሚያስፈልግህ ስላሳመኑህ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ችለህ ይሆናል። እንግሊዝኛ ወይም ሌላ ቋንቋ መልመድ እየፈለግክ፣ እስከ አሁን ድረስ ሳትችል ቀርተህ ከሆነ ግን፣ አሁን እንዴት እንደሚቻል ግልጽ እየሆነልህ ነው ብዬ አምናለሁ።

ልማዶች ወደዚች ዓለም ስንመጣ ከኛ ጋር አብረው የመጡ ሳይሆኑ፣ ወደዚች ዓለም ከመጣን በኋላ በአካባቢያችን ካሉ ሰዎች የምንማራቸው፣ የምንወርሳቸውና የምንለምዳቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህ ከልጅነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በተደጋጋሚ የምናደርጋቸው ነገሮች በአዕምሯችን እንደ ልማድ ሆነው ይገነባሉ፣ እነዚህን ልማዶች በተደጋጋሚ ማድረጋችንን ስንቀጥል ደግሞ፣ በአዕምሯችን ልክ እንደ ፓራዳይም ሆነው ይገነባሉ። እነዚህ ልማዶች በአዕምሯችን በመገንባት ሁሉንም እንቅስቃሴዎቻችንንና ድርጊቶቻችንን መቆጣጠር ይጀምራሉ። እንቅስቃሴዎቻችንንና ድርጊቶቻችንን በመቆጣጠርም ሕይወታችንንና በሕይወታችን የምናገኛቸውን ውጤቶች መቆጣጠር ይጀምራሉ።

አሁን በሕይወትህ እያደረግክ ያለሀቸው ነገሮችና እያገኘህ ያለሀቸው ውጤቶች፣ የልማዶችህ ውጤቶች ናቸው። አሁን በምታገኛቸው ውጤቶች ደስተኛ ካልሆንክ፣ መቀየር ያለብህ በአዕምሮህ ያሉትን ልማዶች እና ፓራዳይሞች ነው። እነዚህ ልማዶች ካልተቀየሩ፣ ሕይወትህም ሆነ በሕይወትህ የምታገኛቸው ውጤቶች አይቀየሩም፣ የምታገኛቸው ውጤቶች ሊቀየሩ ቢችሉ እንኳ፣ ዘለቄታነት አይኖራቸውም።

ስለዚህ አሁን በአዕምሮህ ውስጥ ያሉትን ከሕፃንነትህ ጀምሮ የተገነቡ ልማዶችህን ፈትሻቸው። እነዚህ ልማዶች፣ እንቅስቃሴዎችህንና ድርጊቶችህን በመቆጣጠር፣ ድንቅ ውጤት እየሰጡህ ከሆነ፣ ይበልጥ ማጠናከር ያስፈልግሀል። ነገር ግን እየሰጡህ ያሉት ውጤቶች ተራ እና የማትፈልጋቸው ውጤቶች ከሆኑ፣ አሁኑኑ እነዚህን ልማዶች ከአዕምሮህ በማባረር፣ በሌሎች ድንቅ ውጤቶች ሊያስጡህ በሚችሉ ድንቅ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች መተካት አለብህ።

# የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች

ልማዶች የፓራዳይም ክፍል በመሆናቸው፣ ልክ እንደ ፓራዳይም በሕይወታችን ትልቅ ተጽዕኖ የመፍጠር ኀይል አላቸው። በአዕምሯችን የተገነቡት ልማዶች፣ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ከሆኑ፣ ሕልማችንን እንዳናሳካ እና ሕይወታችንን እንዳንቀይር ዕንቅፋት ይፈጥሩብናል። እነዚህን የማንፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በምንፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ካልቀየርናቸው፣ በሕይወታችን ማሸነፍ ይከብደናል።

በሕይወታችን ያሉንን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ ዘለቄታነት ባለው መንገድ ለመቀየር ግን፣ በአዕምሯችን የተገነቡት ልማዶች ያላቸውን ኀይል እና በሕይወታችን የሚፈጥሩትን ተጽዕኖ በጥንቃቄ መረዳት ያስፈልገናል። አሁን ይህንን እውነት በትክክል በመረዳት፣ በሕይወትህ ዘለቄታነት ያለው ለውጥ እንድታመጣ የሚረዱህን ሁለት ምሳሌዎች በመጠቀም፣ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችን እና በሕይወትህ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ እንመረምራለን።

## አርፍዶ መነሳት

አንድ ከጥዋቱ 11:00 ሰዓት ላይ መነሳት የሚፈልግ፣ ነገር ግን 2:00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድ ያለው ሰው አለ እንበል። ይህ ሰውዬ ማታ ከመተኛቱ በፊት፣ "ከነገ ጀምሮ 11:00 ሰዓት ላይ በመነሳት፣ ሕልሜን አሳካለሁ፤ ሕይወቴንም እቀይራለሁ" ብሎ የማንቂያ ደውሉን ሞልቶ፣ ይተኛል። ጥዋት የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ ግን፣ በአዕምሮው የተገነባው 2:00 ሰዓት የመነሳት ልማድ ቦታውን ይወስድና የተለያዩ ሰበቦችን በመደርደር፣ የማንቂያ ደውሉን አጥፍቶ ተመልሶ እስከ 2:00 ሰዓት ድረስ እንዲተኛ ያደርገዋል። ይህን የልማዶች ኀይል ያልተረዳው ሰውዬ በሚሆነው ነገር በመበሳጨት፣ በሚቀጥለው ቀን ሁለት የተለያዩ የማንቂያ ደውሎችን 11:00 ሰዓት ላይ እንዲቀሰቅሱት ሞልቶ ይተኛል። ጥዋት ሁለቱም የማንቂያ ደውሎች 11:00 ሰዓት ላይ ሲጮሁ ግን፣ የተለያዩ ሰበቦችን በመደርደር፣ ተመልሶ እስከ 2:00 ሰዓት ድረስ ይተኛል። አሁንም የልማዶችን ኀይል ያልተረዳው ሰውዬ፣ በሁኔታው በመበሳጨት፣ በሚቀጥለው ቀን አራት የማንቂያ ደውሎች 11:00 ሰዓት ላይ እንዲቀሰቅሱት ሞልቶ ይተኛል። ጥዋት አራቱ የማንቂያ ደውሎች ሲጮሁ ግን፣ እንደ ትናንትናዎቹ፣ አጥፍቷቸው ተመልሶ ይተኛል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም "11:00 ሰዓት ላይ መነሳት ከአቅሜ በላይ ነው" ብሎ በማሰብ በራሱ ላይ ተስፋ ይቆርጣል።

ልማዶች እንዴት እንደሚሠሩ ካልተረዳናቸው፣ የልማዶቻችን መጫወቻ ነው የምንሆነው። ይህ ሰውዬ የማንቂያ ደውሉን 11:00 ሰዓት ላይ እንደሞላው በሰዓቱ ያልተነሳው፣ 11:00 ሰዓት ላይ የመነሳት አቅም ስለሌለው አይደለም። ፈጣሪ አይደለም 11:00 ሰዓት ለመነሳት የሚያስችል አቅም፣ በሕይወት ዘመናችን ሙሉ ከምንጠቀምበት በላይ አቅም እና ችሎታ ሰጥቶናል። ይህንን ድንቅ አቅማችንን፣ እንድንጠቀምበት በሚረዱን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በመመራት ካልተጠቀምንበት ግን በሕይወታችን እንሸነፋለን። ይህ ሰውዬ 11:00 ሰዓት ያልተነሳው፣ 11:00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድ ስለሌለው ነው። ይህ ሰውዬ 11:00 ሰዓት መነሳት እየፈለገ 2:00 ሰዓት የተነሳው፣ 2:00 ሰዓት የመነሳት ልማድ ስላለው ነው። ይህ ሰውዬ ማታ አስር የማንቂያ ደውል ቢሞላም፣ "ከነገ ጀምሮ ልክ 11:00 ሰዓት ሲሞላ እነሳለሁ" ብሎ ቢፎክርም፣ 11:00 ሰዓቷ ስትመጣ ግን፣ ማታ ያሰበው ሀሳብ ሳይሆን፣ 2:00 ሰዓት የመነሳት ልማዱ ነው የሚያሸንፈው። ይህ ሰውዬ 11:00 ሰዓት ላይ መነሳት የሚፈልግ ከሆነ 2:00 ሰዓት የመነሳት የተሸናፊ ሰዎች ልማዱን፣ 11:00 ሰዓት ላይ በመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ መተካት አለበት።

"ታዲያ ይህ ሰውዬ እንዴት አድርጎ ነው የመሸነፍ ልማዱን በማሸነፍ ልማድ ሊተካው የሚችለው?" አሁን የልማዶችን ኀይል ለመረዳት የሚያስችልህን አንድ ምሳሌ እጨምርልሀለሁ። ከዚያ በኋላ እንዴት አድርገህ አሁን ያሉህን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአሸናፊ ሰዎች ልማዶች መተካት እንደምትችል አሳይሀለሁ።

## ሱስ

ሱስ ከባድ እና በሕይወታችን ትልቅ ችግር የሚፈጥር የተሸናፊ ሰዎች ልማድ ነው። ሱስም ልክ እንደ አብዛኞቹ አሉታዊ ልማዶቻችን፣ ሆነ ብለንና አስበን በአዕምሯችን የገነባነው ልማድ ሳይሆን፣ ከአካባቢያችን ካሉ ተሸናፊ ሰዎች ብዙም ሳናስብበት የምንወርሰው እና የምንለምደው የተሸናፊ ሰዎች ልማድ ነው። አሁን በሕይወታችን ያሉ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችን እና ሱሶችን፣ በአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስንቀይራቸው፣ ሕይወታችንን መቀየር እንችላለን።

በምሳሌ ለማስረዳት፣ አንድ የመጠጥ፣ ሲጋራ፣ ጫት ወይም አደንዛዥ ዕፆች የመጠቀም ሱስ ያለበትን ሰው እንመልከት። ይህ ሰውዬ በሱሱ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ስለቆየ፣ ከሱሱ ወጥቶ፣ የነጻነት ሕይወትን ማጣጣም ከአቅሙ በላይ ሊመስለው ይችላል። ሰውዬው ግን አሁን ያለውን የተሸናፊ ሰዎች ሱሱን በማቆም፣ ማሸነፍ እንደሚችል በራሱ ላይተማመን ይችላል። በተለይ ስለ ፓራዳይም እና ልማዶች ምስጢር ከመረዳቱ በፊት፣ ከሱሱ ነጻ ለመውጣት ብዙ ጊዜ ሞክሮ ያልተሳካለት ከሆነ፣ ተስፋ ሊቆርጥ ይችላል። እንደዚህ አይነት ሰው

የምታውቅ ከሆነ ወይም አንተም ከአንዳች አይነት ሱስ ነጻ ለመውጣት የምትፈልግ ከሆነ፣ ይህንን ምዕራፍ በጥንቃቄ በማጥናት እና በመጠቀም፣ ከማንኛውም ሱስ ነጻ መውጣት ትችላለህ።

በመጀመሪያ መረዳት ያለብን ነገር ማንም ሰው ሱሰኛ ሆኖ አልተወለደም፤ በልጅነት ዕድሜው ባለው አስተዳደግም አብዛኛውን ጊዜ ሱሰኛ ሆኖ አያድግም። የሰው ልጅ ብዙውን ጊዜ ወደ ሱስ ውስጥ የሚገባው፣ በወጣትነት ዕድሜው ነው። አንድ ሰው ሱሰኛ ከሆኑ ሰዎች ወይም ወደ ሱስ ከሚያስገቡት ሰዎች ጋር መተዋወቅና በተደጋጋሚ መገናኘት ሲጀምር፣ በልቡ የሱስ ልማዶች መገንባት ይጀምራሉ። በአንጻሩ ወላጆቹና በሕይወቱ መልካም ተጽዕኖ የፈጠሩ ሰዎች፣ ወደ ሱስ እንዳይገባ የሚጠብቁት ከሆነና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን በሕፃንነቱ ከቀረጹበት፣ እነዚህ ልማዶች ወደ ሱስ እንዳይገባ ይጠብቁታል። ነገር ግን እነዚህ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በአዕምሮው በደንብ ካልተገነቡ፣ እነዚህን መልካም ልማዶች ከማዳመጥ ይልቅ፣ የሱሰኛና ተሸናፊ ሰዎችን ልማዶች ማዳመጥ ከመረጠ፣ ራሱን በማይፈልገው የሱስ ልማዶች እስር ቤት ውስጥ ያገኛል።

በምንም ዐይነት አስቸጋሪ ሱስ ውስጥ ያለ ሰው፣ ሱሱን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀምሰው፣ ሱሱ ምንም አይመቸውም። ሱሰኛ የሆነ ሰው የአልኮል መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ጫት፣ ሺሻ፣ ሀሺሽ፣ ቢራ ወይም ቡና ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀምስ፣ ምንም ደስ አይለውም፤ እንዲያውም በጣም ነው የሚያስጠላው። ለመጀመሪያ ጊዜ ሱሱን ሲቀምስ፣ ሌሎች ሰዎች ይህን ሱስ እንዴት እንደወደዱትና እንዴት በማይጥምና በማይጣፍጥ ነገር ውስጥ እንደተጠመዱ ግራ ነው የሚገባው። ሁሉም ሱሶች እንደ ልማድ ሆነው በአዕምሮ ካልተገነቡ የሚጥም ነገር የላቸውም። ማንኛውም ሰው በዚህ ደረጃ ላይ ካለ፣ ወዲያውኑ ከሱሱ መሸሽ አለበት።

ከሱስ እና ከነዚህ ወደ ሱስ ከሚወስዱት ሰዎች በፍጥነት ካልሸሸ ግን፣ ይህንን ይጠላው የነበረውን ሱስ ቀስ በቀስ ከመጥላት ወዳለመጥላት ይሻገራል። ከሱሱና ሱሰኛ ጓደኞቹ ጋር መገናኘት ከቀጠለ ደግሞ፣ በድብቁ አዕምሮው በሱስ የሚሸነፉ ሰዎችን ልማድ መገንባት ይጀምራል። በድብቁ አዕምሮው ሱሱ መገንባት ሲጀምር ደግሞ፣ ሱሱን መውደድ፤ ከዚያም ቀጥሎ ማፍቀር ይጀምራል። ሱሱን መጠቀም ሲቀጥል ደግሞ፣ ሱሱና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶቹ፣ የአዕምሮው ዋና ልማዶች ሆነው በመገንባት ሕይወቱን መቆጣጠር ይጀምራሉ። ሕይወቱ በነዚህ የሱስና የተሸናፊ ሰዎች ልማድ ቁጥጥር ሥር ሲገባ ደግሞ ከዚህ እስር ቤት የማይወጣ ይመስለዋል። አሁን ለመላቀቅ አስቸጋሪ የሆነበት ማንኛውም አይነት ሱስ ውስጥ ያለ ሰው፣ ሱሱን ከመጥላት ወዳለመጥላት፣ ካለመጥላት ወደ መውደድ፣ ከመውደድ በፍቅር ወደ መውደቅ፣ በፍቅር ከመውደቅ በሱሱ ወደ መከተብ በማምራት ሂደት ነው አሁን ያለበት የማይፈልገው ደረጃ ላይ የሚደርሰው።

ማንኛውም በሱስ የታሰረ ሰው ከሱሱ ነጻ መውጣት ይችላል። ወደ ሱሱ ለመግባት በአዕምሮው መጥፎ እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች እንደገነባው ሁሉ፣ ከሱሱ ለመውጣትም በአዕምሮው ጤናማ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን መገንባት ነው የሚያስፈልገው። በርግጥ ሱሱን የቀመሰበት ቀን እንዳልተመቸው ሁሉ፣ ሱሱን የሚያቋርጥበት ቀንም ብዙ አይመቸውም። ሱሰኛ የሆነ ሰው ከሱሱ ነጻ መውጣት ይችላል፤ የመውጣት ሂደቱ ግን ጣፋጭ እና ቀላል አይደለም። በአዕምሮው ውስጥ ያሉት የሱስ እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ ከሱሱ ነጻ እንዳይወጣ ይታገሉታል። ነገር ግን እነዚህን የማይፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች አሸንፎ፣ በአዲስ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ሲተካቸው፣ የነጻነትን ሕይወት ማጣጣም ይችላል።

አንተም ሱስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች መጥፎ ልማዶችም ካሉብህ ችግሩ ተመሳሳይ ነው። በአዕምሮህ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ከተገነቡ፣ እነዚህ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ ከለመድካቸው ነገሮች እንድትላቀቅ አይፈልጉም። እነዚህን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዲስ እና ድንቅ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስትተካቸው ግን፣ ከነዚህ መጥፎ ነገሮች መላቀቅ ትችላለህ። እነዚህ አዲስ እና ድንቅ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዕምሮህ ሲገነቡ፣ ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር ሁሌም ይረዱሃል። ስለዚህ አሁን መጠየቅ ያለብህ ወሳኝ ጥያቄ "እንዴት አድርገህ ነው የማትፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዳዲሶቹ እና ድንቅ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች የምትተካቸው?" የሚለው ነው።

# የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች

ልማዶች የፓራዳይም ክፍል ስለሆኑ፣ ልማዶቻችንን ለመቀየር የምንጠቀምበት ዘዴ፣ ፓራዳይማችንን ለመቀየር ከምንጠቀምበት ዘዴ ጋር አንድ አይነት ነው። ትናንት ስለ ፓራዳይም ለውጥ ስናጠና፣ የማንፈልገውን ተራ ፓራዳይም በምንፈልገው ድንቅ ፓራዳይም ለመቀየር የምንጠቀምባቸው ሁለት ዘዴዎች እንዳሉ አጥንተን ነበር።

አሁን ያሉንን የማንፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በምንፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ለመተካት የምንጠቀመው ቀጥለው የቀረቡትን ሁለት ዘዴዎች ነው። ዘዴዎቹን በጥንቃቄ በማጥናት እንዳስፈላጊነቱ አንዱን ዘዴ፣ አልያም ሁለቱንም ዘዴዎች በጋራ መጠቀም በሚያስችሉህ ተጋልጠዎች ልማዶችህን መቀየር ትችላለህ።

፩. የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ
፪. የመደጋገም የልማዶች ለውጥ

## ፩. የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ

ልማዶቻችንን ለመቀየር መጠቀም የምንችለው የመጀመሪያ ዘዴ የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ ነው። የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ፣ ልክ እንደ "የመደጋገም የፓራዳይም ለውጥ"፣ አብዛኛውን ጊዜ አያጋጥምም፣ ካጋጠመ ደግሞ ብዙውን ጊዜ አሉታዊ ነው። ልማዶች በአዕምሯችን እንዴ ከተገነቡ፣ ሕይወታችንን እንደሚቆጣጠሩት እና ከነዚህ ልማዶች እንዳንወጣ እንደሚጠብቁን አስቀድመን ተመልክተን ነበር። ነገር ግን አንድ የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ ካጋጠመን፣ እነዚህን ልማዶች በፍጥነት እና በመደንገጥ መቀየር ግድ ይለን ይሆናል።

የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ፣ በሕይወታችን አንድ የሚያስደነግጠን ነገር በድንገት ሲከሰት፣ ወዲያውኑ በመደንገጥ፣ የምናደርገው የልማዶች ለውጥ ነው። በዚች ልዩ ክስተት፣ ከልጅነታችን ጀምሮ በአዕምሯችን የተገነቡ የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ወዲያውኑ በአዲስ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ይተካሉ።

የመደንገጥ የልማዶች ለውጥን በመጠቀም፣ ልማዶቻችንን በፍጥነት መቀየር እንችላለን። ነገር ግን የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ አብዛኛውን ጊዜ አያጋጥምም፤ ሲያጋጥም ደግሞ ብዙውን ጊዜ አሉታዊ እና በድንገት ሆኖ ነው። ስለዚህ በአዕምሯችን ውስጥ ያሉትን የማንፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በምንፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በዓላማ የምንቀይርበትን ዘዴ ማጥናት እንጀምር። መለወጥ የምትፈልጋቸውን ልማዶችህን በመደንገጥ የፓራዳይም የልማዶች ለውጥ ዘዴ በመጠቀም ለመለወጥ መታገል ወይም ምቹ ጊዜ መጠበቅ የለብህም። የመደንገጥ የልማዶች ለውጥ በቅጽበት የሚመጣ ስለሆነ፣ ራስህን ለመለወጥ ከልብ የመነጨ ፍላጎት ሲኖርህ የምትጠቀመው ዘዴ አይደለም። አሁን ራስህን ለመቀየር ሁነኛ የሆነውን የመደጋገም የልማዶች ለውጥ በመጠቀም፣ ልማዶችህን የምትቀይርበትን ዘዴ እንመልከት።

## ፪. የመደጋገም የልማዶች ለውጥ

አሁን ሕይወትህን እየተቆጣጠሩ ያሉት፣ የማትፈልጋቸው የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በአዕምሮህ፣ በድግግሞሽ እንደተገነቡት ሁሉ፣ የምትፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችም፣ እንዲሁ በአዕምሮህ በድግግሞሽ መገንባት ይችላሉ። አሁን የመደጋገም የልማዶች ለውጥን በመጠቀም የማትፈልጋቸውን ተራና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በምትፈልጋቸው ድንቅና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ለመተካት የምትጠቀምባቸውን ዘዴዎች መመርመር እንጀምራለን።

# የመደጋገም የልማዶች ለውጥ ልምምድ

በአዕምሮህ ውስጥ የተገነቡትን የማትፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በአዲስ እና በምትፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች የምትተካበትን ዘዴ አሁን እንመረምራለን። የመደጋገም የልማዶች ለውጥ ዘዴ ውስጥ ያሉትን አስር ርምጃዎች በጥንቃቄ ስትጠቀምባቸው፣ ልማዶችህን በመቀየር ሕይወትህን ትቀይራለህ።

፩. **ቅድመ ዝግጅት፡** ከትናንት ወዲያ፣ "ትልቅ ሕልም አለኝ!" በሚለው ምዕራፍ፣ ትልቅ ሕልምህን ለመወሰን፣ ራስህን ለማዘጋጀት በተጠቀምክባቸው አምስት ዘዴዎች በመጠቀም፣ ራስህን ለዚህ ድንቅ የመደጋገም የልማዶች ለውጥ ልምምድ አዘጋጅ። ይህን ልምምድ ለመሥራት የሚረዳህ ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታ እና በትኩረት ለማሰብ የሚያመች ጠረጴዛ እና ወንበር አስቀድመህ በጥንቃቄ በመምረጥ አዘጋጅ። ከሁሉም በላይ ግን ራስህን እና አዕምሮህን በትኩረት እና በጥንቃቄ ለመሥራት ለልምምዱ አዘጋጅ።

፪. **መሣሪያዎች፡** ይህንን ልምምድ ለመሥራት የሚረዱህን እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ እና አንድ ቀይ ወረቀት አስቀድመህ አዘጋጅ።

፫. **ልማዶችህን ጻፋቸው፡** ለዚህ ልምምድ ባዘጋጀኸው ማስታወሻ፣ አሁን ያሉህን ሁሉንም የአሸናፊ እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን ጻፋቸው። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ፣ የምትፈልገውን ነገር በማድረግ ድንቅ ውጤት ለማግኘት፣ ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር የሚረዱህ ልማዶችህ ናቸው። የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ደግሞ የምትፈልገውን ውጤት ለማግኘት፣ ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር ስትፈልግ ዕንቅፋት የሚሆኑብህና ወደ ሰበብ የሚጎትቱህ ናቸው። አሁን ያሉህ የአሸናፊ እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን መጻፍ፣ በየትኛው የስኬት ደረጃ ላይ እንዳለህ እንድትገነዘብ ይረዱሀል።

፬. **ቀይ ወረቀት፡** ለሕይወትህ አደጋ የሆኑ የማትፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ የአደጋ አመልካች በሆነው ቀይ ወረቀት ላይ ጻፋቸው። የምትፈልገውን ውጤት እንዳታገኝ፣ ሕልምህን እንዳታሳካ እና ሕይወትህን እንዳትቀይር እየከለከሉህ ያሉትን ሁሉንም የማትፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን ከነ ችግራቸው በቀዩ ወረቀት ላይ ዘርዝራቸው።

፭. **ማቃጠል፡** በቀይ ወረቀት ላይ የጻፍካቸውን፣ በሕይወትህ ለረጅም ጊዜ ያቃጠሉህን የማትፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በእሳት አቃጥላቸው። የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን የአደጋ ምልክት ባለው ቀይ ወረቀት ላይ ጽፈሕ በእሳት በማቃጠል፣ እነዚህን ልማዶች ከአዕምሮህ አባርራቸው። ከዚች ቅጽበት ጀምሮ፣ እነዚህን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በመጠቀም ሕይወትህን እንዲቆጣጠር እንደማትፈቅድለት ለአዕምሮህ ግልጽ መመሪያ ስጠው።

- እነዚህን "የመደጋገም የልማዶች ለውጥ" ልምምዶች በተግባር ካላደረግካቸው፣ ብዙ ዕውቀት እንጂ ለውጥ አታገኝም። ልማዶችህን በመቀየር ራስህን መቀየር የምትፈልግ ከሆነ፣ በመደጋገም የልማዶች ለውጥ ሥር ያሉትን ርምጃዎችና መመሪያዎች በመከተል በተግባር ሥራቸው።

፮. **የምትፈልጋቸውን ልማዶች ዘርዝራቸው፡** በአዕምሮህ መገንባት የምትፈልጋቸውን ሁሉንም ልማዶችህን አሁን በማስታወሻህ ላይ በዝርዝር ጻፋቸው። በማስታወሻህ ላይ የምትፈልገውን ከባድ ነገር ለማድረግ የሚረዱህንና ድንቅ ውጤት ለማግኘት የሚያጠነክሩህን፣ ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር የሚያበረታቱህን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ሁሉንም ዘርዝረህ ጻፋቸው። እነዚህ ልማዶች በቀዩ ወረቀት ላይ ከጻፍካቸው የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ተቃራኒ ሆነው፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት እንድትከፍል የሚረዱህ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ናቸው።

፫. **የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፡** በስድስተኛ ደረጃ ከዘረዘርካቸው የምትፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ዝርዝር ውስጥ፣ አሁን ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር በጣም የሚረዱህን ቀዳሚ መሆን ያለባቸውን ዋና ዋና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በገጽ 91 ላይ ጻፋቸው። "የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች" በሚለው ቦታ ላይ በመምረጥ የምትጽፋቸው ልማዶች፣ ከሌሎች የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በላይ በሕይወትህ ትልቅ ለውጥ መፍጠር የሚችሉ ድንቅ ልማዶች መሆን አለባቸው።

፬. **መደጋገም፡** ልማዶች ልክ እንደ ፓራዳይም በአዕምሯችን የሚገነቡት በመደጋገም ነው። አሁን እነዚህን የምትፈልጋቸውን በጥንቃቄ የመረጥካቸውን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በየቀኑ በተደጋጋሚ ጻፋቸው። እነዚህን አዲስ እና ድንቅ የሆኑ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በየቀኑ በተደጋጋሚ ስትጽፋቸው እና ጮክ ብለህ ስታነባቸው፣ በአዕምሮህ እንደ ዋና ልማዶች ሆነው መገንባት ይጀምራሉ። እነዚህን ድንቅ ልማዶች ለሃያ አንድ ቀናት በየቀኑ በተደጋጋሚ ስትጽፋቸው፣ ስታነባቸው እና ስታስታውሳቸው፣ በድብቁ አዕምሮህ ይቀረጻሉ። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዕምሮህ ሲቀረጹ ደግሞ፣ ሕይወትህን መቆጣጠር ይጀምራሉ።

- ዛሬ እያጠናን ካለነው ምዕራፍ ቀጥሎ አንድ "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መሥራት እንጀምራለን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በገጽ 95 ላይ ከተዘጋጀው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መስሪያ በተጨማሪም፣ አንተ በምታዘጋጃቸው አርባ ሁለት የመለማመጃ አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ፣ በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ፣ የድሮ ተራ ፓራዳይምህን በአዲስና ድንቅ ፓራዳይም የምትተካበትን የመጻፍ ልምምድ መሥራት እንጀምራለን።

፭. **ምናብ፡** አሁን ምናብህን በመጠቀም የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ ሕይወትህን ሲቀይሩት ተመልከታቸው። ዐይንህን በመጨፈን እና ረጋ ብለህ በመተንፈስ፣ እነዚህ በጥንቃቄ መርጠህ እየጻፍክ ያለህቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዕምሮህ ተቀርጸው ሕይወትህን ሲቀይሩ አልማቸው። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ ቀንህን ሲቀይሩት፣ ሕልምህን እንድታሳካ ሲረዱህ እና ሕይወትህን ለመቀየር መክፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ለመክፈል ሲያጠነክሩህ በዐይነ ህሊናህ ተመልከታቸው። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ ሕይወትህን ሲቀይሩት ስትመለከታቸው፣ ድንቅ ስሜት እና ደስታ ጨምረህ ተመልከታቸው። (ምናብ የአዕምሮ መሣሪያን እንዴት በትክክል መጠቀም እና ማጠንከር እንደምትችል ለመረዳት፣ በዚህ መጽሐፍ፣ በ፪ኛ ሳምንት ፲፪ኛ ቀን ያለውን የምናብ ምዕራፍ መመልከት ትችላለህ)

፮. **ድርጊት፡** ሥጋዊ አካላችን እና ድርጊቶቻችን ሁሌም በአዕምሯዊ አካላችን እና ልማዶቻችን ቁጥጥር ሥር ናቸው። ከአሁን ጀምሮ በድንቅ አዕምሯዊ አካልህ እና በአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ በመታገዝ፣ የአሸናፊ ሰዎች ድርጊቶችን ማድረግ ጀምር። በአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ በመታገዝ ለሃያ አንድ ቀናት ብቻ የአሸናፊ ሰዎች ድርጊቶችን ከወሰድክ፣ ሕይወትህ ሙሉ በሙሉ ይቀየራል። እነዚህን አስር ልምምዶች በመጠቀም የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን በአዕምሮህ ከገነባህ በኋላ፣ የድርጊት ርምጃ ስትጨምርበት፣ ልማዶችህን በመቀየር ሕይወትህን ትቀይራለህ።

## መመሪያዎች

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ በገጽ 91 "የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች" በሚል ርዕስ በተዘጋጀው ቦታ ላይ ከመጻፍህ በፊት፣ ቀጥለው የቀረቡትን ሦስት መመሪያዎች በጥንቃቄ በማንበብ ተከተላቸው።

፩. **አጋዥነት፡** የምትጽፋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ሕልምህን ለማሳካት እና ሕይወትህን ለመቀየር ከሌሎች ልማዶችህ በላይ የሚረዱህ መሆን አለባቸው።

፪. **አዎንታዊነት፡** የምትጽፋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች አዎንታዊ መሆን አለባቸው። ልማዶችህን ለመጻፍ የምትጠቀምባቸው ቃላት አዎንታዊ እንጂ፣ በምንም መንገድ አሉታዊ መሆን የለባቸውም።

፫. አሁንነት፡ የምትፈልጋቸውን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን ስትጽፋቸው፣ ወደ ፊት እንደምታዳብራቸው ልማዶች ሳይሆን፣ አሁን እንዳዳበርካቸው ልማዶች አድርገህ ጻፋቸው። ለሃያ አንድ ቀናት የምትጽፋቸውን ልማዶች፣ ወደ ፊት እንደምታዳብራቸው አድርገህ የምትጽፋቸው ከሆነ፣ ሁሌም ተስፋ ሆነው ነው የሚቀሩት። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን ስትጽፋቸው፣ ወደ ፊት እንደሚኖሩህ ልማዶች ሳይሆን፣ አሁን እንዳሉህ ልማዶች አድርገህ በተደጋጋሚ ለሃያ አንድ ቀናት ስትጽፋቸው፣ እነዚህ ልማዶች በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በአዕምሮህና በልብህ ውስጥም ይወቀራሉ።

## ተግባራዊ ምሳሌ

# የመደጋገም የልማዶች ለውጥ

**"ጥዋት የማንቂያ ደውል ከመጮሁ በፊት ቀድሜ ተነስቻለሁ!"**

የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ልምምድን መጻፍ ከመጀመርህ በፊት፣ አንድን የአሸናፊ ሰዎች ልማድ እንዴት አድርገህ ማዳበር እንደምትችል መጀመሪያ ሳሳይህ። የመረጥኩልህ ልምምድ፣ "ጥዋት የማንቂያ ደውል ከመጮሁ በፊት ቀድሜ ተነስቻለሁ!" የሚል ነው። በዚህ ልምምድ የምትማረው ምስጢር ማንኛውንም የማትፈልገውን ተራ የተሸናፊ ሰዎች ልማድ በምትፈልገው ድንቅ የአሸናፊ ሰዎች ልማድ መተካት እንደምትችል ነው።

በቀዳሚዎቹ ገጾች ከጥዋቱ 11:00 ሰዓት ላይ መነሳት ስለሚፈልግ፣ ነገር ግን ሁልጊዜ 2:00 ሰዓት ላይ ስለሚነሳ ሰው ጠቅሰን ነበር። ይህ ሰውዬ ማታ ከመተኛቱ በፊት የማንቂያ ደውሉን 11:00 ሰዓት እንዲቀሰቅሰው ሞልቶ ቢተኛም፣ ጥዋት የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ ግን ሰበበኛውን በማዳመጥ፣ የማንቂያ ደውሉን አጥፍቶ ተመልሶ ይተኛል። ይህ ሰውዬ በተደጋጋሚ 11:00 ሰዓት ላይ የማንቂያ ደውሉን አጥፍቶ ተመልሶ እስከ 2:00 ሰዓት ድረስ ከተኛ፣ "እኔ 11:00 ሰዓት ላይ የመነሳት አቅም የለኝም" ብሎ ሊያስብ ይችላል። "የኔ ተፈጥሮና አቅም 2:00 ሰዓት መነሳት ነው" ብሎ 11:00 ሰዓት ላይ ለመነሳት በመሞከሩ ተስፋ ሊቆርጥም ይችላል።

የሰው ልጆች አይደለም በምንፈልገው ሰዓት ለመነሳትና የምንፈልገውን ነገር ለማድረግ ቀርቶ፣ የማንፈልገውን ነገር እንኳ ለማድረግ የሚያስችል ድንቅ ተፈጥሮና አቅም አለን። ድንቅ አቅማችንን በተሸናፊ ሰዎች ልማዶች የምንጠቀምበት ከሆነ፣ የትም አንደርስም። ነገር ግን ድንቅ ተፈጥሯችንንና አቅማችንን በአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስንጠቀምበት ተዓምር መሥራት እንጀምራለን።

አንተም ከዛሬ በፊት ጥዋት የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ ለማዳበር ብዙ ሞክረህ ካልተሳካልህ፣ ዛሬ ትልቅ መፍትሄ ታገኛለህ። በዚህ ልምምድ የማትፈልገውን 2:00 ሰዓት የመነሳት የተሸናፊ ሰዎች ልማድ፣ እንዴት አድርገህ የመደጋገም የልማዶች ለውጥን በመጠቀም፣ በምትፈልገው 11:00 ሰዓት የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ መተካት እንደምትችል እንመለከታለን። (ለዚህ የመደጋገም የልማዶች ለውጥ ተግባራዊ ምሳሌ የተጠቀምኩት የሁለት ሰዓትና አስራ አንድ ሰዓት የመነሳት ልምምድ ነው። እባክህ እነዚህን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችና ሰዓቶች በራስህ ልማዶችና ሰዓቶች በመቀየር ራስህን ፈትሽ)

፩. ቅድመ ዝግጅት፡ ከትናንት ወዲያ፣ "ትልቅ ሕልም አለኝ!" በሚል ምዕራፍ፣ ትልቅ ሕልምህን ለመወሰን፣ ራስህን ለማዘጋጀት በተጠቀምክባቸው አምስት ዘዴዎች በመጠቀም፣ ራስህን ለዚህ ድንቅ የመደጋገም የልማዶች ለውጥ ልምምድ አዘጋጅ። ይህን ልምምድ ለመሥራት የሚረዳህን ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታ እና በትኩረት ለማሰብ የሚያመች ጠረጴዛ እና ወንበር አስቀድመህ በጥንቃቄ በመምረጥ አዘጋጅ። ከሁሉም በላይ ግን ራስህንና አዕምሮህን ለልምምዱ በትኩረት እና በጥንቃቄ አዘጋጅ።

፩. **መሣሪያዎች፡** ይህንን ልምምድ ለመሥራት የሚረዱህን እስክርቢቶ፣ ማስታወሻ እና አንድ ቀይ ወረቀት አስቀድመህ አዘጋጅ።

፪. **ልማዶችህን መጻፍ፡** ለልምምዱ ባዘጋጀኸው ማስታወሻ ላይ፣ አሁን ያለህን የማትፈልገውን 2፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት የተሸናፊ ሰዎች ልማድህን ጻፈው። በልምምዱ እንደዚህ ብለህ መጻፍ ትችላለህ። "በየቀኑ 'ማታ በአራት ሰዓት እተኛለሁ' ብዬ ባቅድ እንኳን፣ የተለያዩ ነገሮችን በማድረግ በጣም አምሽቼ፣ ከዚያም የማንቂያ ደውሉን ለ11፡00 ሰዓት ሞልቼ እተኛለሁ። ጥዋት 11፡00 ሰዓት የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ ግን፣ አምስት ደቂቃ ልተኛ ብዬ እስከ 2፡00 ሰዓት ድረስ እተኛለሁ። 2፡00 ሰዓት ስነሳ ግን በጣም ስለሚረፍድብኝ፣ ቀኔን በመቻኮልና በመረበሽ እጀምራለሁ። አርፍጄ በመነሳቴ ራሴን፣ ቤተሰቤን፣ ሥራዬን፣ ቀኔንና ሙሉ ሕይወቴን በአደጋ ውስጥ እየከተትኩ ነው"

፫. **ቀይ ወረቀት፡** አሁን ይህ ለሕይወትህ አደጋ የሆነው፣ ማታ አምሽቶ የመተኛትና ጥዋት እሳብቦ ተመልሶ እስከ 2፡00 ሰዓት ድረስ የማርፈድ የተሸናፊ ሰዎች ልማድህን፣ ቀድመህ ባዘጋጀኸው ቀይ ወረቀት ላይ ጻፈው። ይህ የማትፈልገው እና ለሕይወትህ አደጋ የሆነው የማርፈድ ልማድ እየሰጠህ ያለውን የማትፈልገውን ስሜት፣ ውጤትና ሕይወት፣ አደጋ አመልካች በሆነው ቀይ ወረቀት ላይ ጻፈው።

፬. **ማቃጠል፡** በቀዩ ወረቀት ላይ የጻፍከውን 2፡00 ሰዓት የመነሳት ልማድ፣ ከነችግሩና እየሰጠህ እስካለው የማትፈልገው ስሜት፣ ውጤትና ሕይወት በእሳት አቃጥለው። 2፡00 ሰዓት የመነሳት የተሸናፊ ሰዎች ልማድህን የጻፍክበትን አደጋ አመላካች ቀይ ወረቀት በእሳት በማቃጠል፣ አዕምሮህ ከዚች ቅጽበት ጀምሮ 11፡00 ሰዓት ላይ የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ፣ የማንቂያ ደውሉን አጥፍቶ ተመልሶ እስከ 2፡00 ሰዓት ድረስ መተኛት እንደማይፈቀድለት በግልጽ መመሪያ እየሰጠኸው ነው።

- ይህንን ልምምድ አንብበኸው ብቻ ካለፍከ፣ በሕይወትህ ዕውቀት ትጨምራለህ እንጂ ትልቅ ለውጥ አታገኝም። እነዚህን ልምምዶች እያንዳንዷን መመሪያ በመከተል ስታደርጋቸው፣ በምትፈልገው ሰዓት የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ በአዕምሮህ ትገነባለህ።

፭. **የምትፈልገውን ልማድ መጻፍ፡** በአዕምሮህ መገንባት የምትፈልገውን አዲሱን 11፡00 ሰዓት የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ አሁን በማስታወሻህ ላይ ጻፈው። ከዚህ በኋላ የመኝታ ሰዓትህንና ሕይወትህን እንዲመራና እንዲቀይር የምትፈልገውን 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድህን በግልጽ ጻፈው። አዲስ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድህን፣ እንዲሰጥህ ከምትፈልጋቸው ድንቅ ስሜቶችና ውጤቶች ጋር በዝርዝር ጻፈው።

፮. **የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፡** በገጽ 91 ላይ ያለው "የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች" ቦታ፣ የምትፈልጋቸውን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በመመሪያዎቹ መሠረት የምትጽፍበት መለማመጃ ነው። "11፡00 ሰዓት ላይ መነሳት" ማዳበር ከምትፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች መካከል አንዱ ከሆነ፣ ቀጥለው የተዘረዘሩትን መመሪያዎች በመከተል በጥንቃቄ ጻፈው።

፮.፩. **ግልጽ፡** በዚህ ገጽ የምትጽፈው 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች አዲስ ልማድ በግልጽ መጻፍ አለበት። ለምሳሌ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድህን "11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ፣ ወዲያውኑ ተነስቼ፣ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" በማለት መጻፍ ትችላለህ።

፮.፪. **አዎንታዊነት፡** አዲሱን እና ድንቁን ልማድህን ስትጽፈው፣ ለመጻፍ የምትጠቀምባቸው ቃላት አዎንታዊ ብቻ እንጂ አሉታዊ መሆን የለባቸውም። ለምሳሌ "11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ተመልሼ አልተኛም" ወይም "በጥዋት አላማርርም" ሳይሆን "11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ፣ ወዲያውኑ ተነስቼ፣ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" የሚል መሆን አለበት።

፫. አሁንነት፡ አዲሱ እና ድንቅ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድህን ስትጽፈው፣ ወደ ፊት እንደምታዳብረው ልማድ ሳይሆን አሁን እንዳለህ ልማድ አድርገህ ነው መጻፍ ያለብህ። ስለዚህ አዲሱን ልማድህን ስትጽፈው "ከአሁን በኋላ 11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ፣ ወዲያውኑ እነሳለሁ፤ ቀኔንም በምስጋና እጀምራለሁ" በሚል ሳይሆን "11፡00 ሰዓት ላይ የማንቂያ ደውሉ ልክ እንደጮኸ ተነስቼ፣ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" በሚል መሆን አለበት።

፬. መደጋገም፡ ልማድ ልክ እንደ ፓራዳይም በአዕምሯችን የሚገነባው በመደጋገም ነው። በየቀኑ የማንቂያ ደውሉን አጥፍተህ እስከ 2፡00 ሰዓት ድረስ የማርፈድ ልማድ በአዕምሮህ የሚገነባው በመደጋገም ነው። አዲሱ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድም በመደጋገም ነው የሚገነባው። 11፡00 ሰዓት ላይ የማንቂያ ደውል ሲጮህ፣ የማንቂያ ደውሉን አጥፍተህ እስከ 2፡00 ሰዓት ድረስ የምትተኛው፣ 11፡00 ሰዓት የመነሳት አቅም ስለሌለህ ሳይሆን፣ አዕምሮህን 2፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስለተቆጣጠረው ነው። የተሸናፊ ሰዎች ልማድ አዕምሮህን እስከተቆጣጠረው ድረስ፣ 11፡00 ሰዓት ላይ የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ፣ 2፡00 ሰዓት የመነሳት ልማድህ ከደውሉ የበለጠ በመጮህ፣ ተመልሰህ እንድትተኛ ይገፋፋሀል።

አሁን "የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ልምምድ" በሚለው ገጽ ላይ "11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ወዲያውኑ ተነስቼ፣ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" በማለት በተደጋጋሚ ስትጽፈው፣ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ በአዕምሮህ መገንባት ይጀምራል። አዲስ የአሸናፊ ሰዎች ልማድህን በተደጋጋሚ ለሃያ አንድ ቀናት ስትጽፈው ደግሞ፣ የድሮ የተሸናፊ ሰዎች ልማድህ ተሸንፎ ስለሚባረር፣ አዕምሮህን አዲሱ የአሸናፊ ሰዎች ልማድህ መቆጣጠር ይጀምራል።

- ከዚህ ምዕራፍ ቀጥሎ በተዘጋጀው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" የሃያ አንድ ቀናት የልማዶች ለውጥ ልምምድ መሥራት እንጀምራለን።

ይህንን ልምምድ ከመሥራትህ በፊት፣ አዕምሮህን ይቆጣጠረው የነበረው የተሸናፊ ሰዎች ልማድህ ብቻ ስለሆነ፣ የማንቂያ ደውሉ 11፡00 ሰዓት ላይ ሲጮህ፣ የማንቂያ ደውሉን አጥፍተህ ተመልሰህ እንድትተኛ ሲመክርህና ሲያስደርግህ ነበር። አሁን ግን በተደጋጋሚ ለሃያ አንድ ቀናት የአሸናፊ ሰዎች ልማድህን ስትጽፈው፣ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድ በአዕምሮህ መገንባት ይጀምራል። በመጀመሪያው ሳምንት ሁለቱም ልማዶችህ እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ፣ ትግሉ ቀላል አይሆንም። ነገር ግን በየቀኑ የአሸናፊ ሰዎች ልማድህን ለሃያ አንድ ቀናት መጻፍህን ስትቀጥል፣ የተሸናፊ ሰዎች ልማድህ ሙሉ በሙሉ መባረር ይጀምራል። ከሃያ አንድ ቀናት በኋላም 11፡00 ሰዓት ላይ የማንቂያ ደውሉ ሲጮህ በአዕምሮህ የሚጮኸው ድምጽ "11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ፣ ወዲያውኑ ተነስቼ፣ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" የሚል ብቻ ይሆናል። ደውሉን እና በአዕምሮህ የተገነባውን የአሸናፊ ሰዎች ልማድ በማዳመጥ፣ በየቀኑ ወዲያውኑ በመነሳት፣ ቀንህን በምስጋና ስትጀምር፣ 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድህ አንተነትህን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠረዋል።

፭. ምናብ፡ አሁን በምናብህ 11፡00 ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ወዲያውኑ በመነሳት ቀንህን በምስጋና ስትጀምረው ራስህን ተመልከት። (ምናብ የአዕምሮ መሣሪያን እንዴት በትክክል መጠቀም እና ማጠንከር እንደምትችል ለመረዳት በዚህ መጽሐፍ፣ በ፪ኛ ሳምንት ፲፪ኛ ቀን ያለውን "ምናብ የአዕምሮ መሣሪያ" የሚለውን ምዕራፍ ተመልከት)

ዐይንህን በመጨፈን እና ረጋ ብለህ በመተንፈስ በምናብህ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን በመከተል ወዲያውኑ በመነሳት ቀንህን በምስጋና ስትጀምር ራስህን ተመልከተው። የአሸናፊ ሰዎች ልማድህን በመከተል ጥዋትህ ብቻ ሳይሆን ቀንህና ሕይወትህ ሲቀየር በምናብህ ስሜትና እምነት ጨምረህ ተመልከተው። 11፡00 ሰዓት ላይ የመነሳት ልማድህ ሕይወትህን ሲቀይረው

በምናብህ ስትመለከት፣ አዲሱ የአሸናፊ ሰዎች ልማድህ በአዕምሮህ በመገንባት፣ ሕይወትህ መቀየር ይጀምራል።

፲. ድርጊት፡ አዕምሯዊ አካልህ ፲፩:oo ሰዓት ላይ የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድ ቁጥጥር ውስጥ ሲሆን፣ በአዕምሯዊ አካልህ ቁጥጥር ሥር ያሉት ሥጋዊ አካልህና ድርጊቶችህም በአሸናፊ ሰዎች ልማድህ ቁጥጥር ሥር ነው የሚሆኑት። ቀደም ሲል ከላይ የተቀመጡትን ልምምዶችና የሃያ አንድ ቀናት ልምምዶች በመከተል የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን በአዕምሮህ ስትገነባ፣ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ፣ የአሸናፊ ሰዎች ልማድህም "፲፩:oo ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ፣ ወዲያውኑ ተነስቼ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" ብሎ ነው የሚጮኸው። አሁን የማንቂያ ደውሉና የአሸናፊ ሰዎች ልማድህ የሚያጮሁትን ማንቂያ በማስማማት ድርጊት መውሰድ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ።

፲፩:oo ሰዓት ላይ የመነሳት የአሸናፊ ሰዎች ልማድህን በመከተል ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ወዲያውኑ በመነሳት ቀንህን በምስጋና ስትጀምር ድርጊትህም መቀየር ይጀምራል። ለተከታታይ ሃያ አንድ ቀናት በተዘጋጁት "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ገጾች፣ በየቀኑ "፲፩:oo ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ወዲያው ተነስቼ ቀኔን በምስጋና እየጀመርኩ ነው!" ብለህ በተደጋጋሚ በጽሑፍ ስትጽፈውና በድርጊት ስታደርገው፣ ፲፩:oo ሰዓት ላይ መነሳት በጣም ነው የሚቀልህ። የሃያ አንድ ቀናት የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በመከተል ፲፩:oo ሰዓት ላይ ስትነሳ፣ ሃያ ሁለተኛው ቀን ላይ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን አለመከተል ነው የሚከብድህ። ለሃያ አንድ ቀናት ፲፩:oo ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ስትነሳ፣ ሃያ ሁለተኛው ቀን ላይ የማንቂያ ደውሉን አጥፍቶ ተመልሶ እስከ 2:oo ሰዓት ድረስ መተኛት ነው የሚከብድህ። ለሃያ አንድ ቀናት ፲፩:oo ሰዓት ላይ ልክ የማንቂያ ደውሉ እንደጮኸ ከተነሳህ ሃያ ሁለተኛው ቀን ላይ፣ ደውሉ ሲጮህ አለመነሳት ነው የሚከብድህ።

የለመድካቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ማሸነፍና አዲሶቹን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በድርጊት ደረጃ መልመድ ቀላል አይደለም። የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በሀሳብና በጽሑፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን፣ በድርጊት ደረጃ በአዕምሮህ መገንባትና መልመድ ብዙ መሥዋዕትነት ያስከፍላል። ነገር ግን ለሃያ አንድ ቀናት ፲፩:oo ሰዓት የመነሳትና ለሁሉም የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ ለመታዘዝ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ከከፈልክ፣ ሃያ ሁለተኛው ቀን ላይ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን አለመከተል ነው የሚከብድህ። ለሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት በአዕምሮህ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን በሀሳብ፣ በጽሑፍና በድርጊት ለመገንባት፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ለመክፈል አሁኑኑ ወስን። አስተውል! የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዕምሮህ ሲገነቡ ሕይወትህ ሙሉ በሙሉ ይቀየራል።

ከዚህ በታች የተጻፉትን ድንቅ መፈክሮች በየቀኑ በተደጋጋሚ ጮክ ብለህ በማንበብ፣ አሁን ያሉህን የማትፈልጋቸውን የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በምትፈልጋቸው የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ተካቸው።

አሸናፊ ሰዎች ያሸንፋሉ፤ ተሸናፊ ሰዎች ደግሞ ይሸነፋሉ!

አሸናፊ ሰዎች የሚያሸንፉት፣ የአሸናፊ ሰዎች ልማድ ስላላቸው ነው!

ተሸናፊ ሰዎች የሚሸነፉት፣ የመሸነፍ ልማዶች ስላሏቸው ነው!

አዎ! አሸናፊ ሰዎች፣ ተሸናፊ ሰዎች ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር የማድረግ ልማድ አላቸው!

እኔ ድንቅ ነኝ! እኔ አሸናፊ ነኝ! ትልቅ ሕልም አለኝ!

ሕልሜን ለማሳካት፣ ተሸናፊ ሰዎች ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር የማድረግ ልማድ አለኝ!

የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስላሉኝ፣ ትልቁን ሕልሜን እያሳካሁ ነው!

አዎ! ራሴን እና ቤተሰቤን ብቻ ሳይሆን፣ አገሬን እና አህጉሬን እየቀየርኩ ነው!

# የአሽናፊ ሰዎች ልማዶች

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። አባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረኩኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

- 
- 
- 
- 
- 
- 
- 

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

- 
- 
- 
- 
- 

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋናና ደስታ ሞልቷል!

- 
- 
- 

**አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ ሌላ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሃል!**

*******

# “የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ”

“የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” በመሥራት ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህን ለመቀየር ዝግጁ ነህ? ዝግጁ ከሆንክ የሁለተኛውን ሳምንት ጥናት ከመጀመራችን በፊት፣ ዛሬ አንድ ድንቅ የሆነ “የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” መሥራት እንጀምራለን። ይህ ልምምድ ለሃያ አንድ ቀናት በተከታታይ እና ያለ ምንም ማቋረጥ የሚሠራ ልዩ ልምምድ ነው።

## ፩. “የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” ምንድን ነው?

“የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” ለሃያ አንድ ቀናት በተከታታይና ያለ ማቋረጥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተዘጋጁ ሃያ አንድ የመለማመጃ ገጾች የሚሠራ ልምምድ ነው። ይህ ልምምድ ከነገ ፫ኛ ቀን “የማሰብ ሂደት” ምዕራፍ ጀምሮ እስከ ፳፫ኛ ቀን “ራስን መገሰጽ” የሚለውን ምዕራፍ ድረስ የሚሠራ ልምምድ ነው።

የዚህ ልምምድ ዋና ዓላማ በአዕምሮህ ሕልምህን የሚያሳኩና ሕይወትህን የሚቀይሩ፣ ድንቅ ፓራዳይሞችና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን መገንባት ነው። ቀጥለው የቀረቡትን መመሪያዎች በመከተል ይህንን ልዩ ልምምድ ለሃያ አንድ ቀናት ያለ ምንም ማቋረጥ ስትሠራው፣ ሕልምህን የሚያሳኩና ሕይወትህን የሚቀይሩ ድንቅ ፓራዳይምና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዕምሮህ ትገነባለህ።

## ፪. “የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” ምስጢር ምንድን ነው?

“የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” ልዩ ምስጢር “መደጋገም” እና “መጻፍ” ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ቀጥሎ እንመለከታለን።

**መደጋገም፡** በአዕምሯችን ውስጥ የተወቀሩት ፓራዳይም እና ልማዶች በአዕምሯችን ውስጥ የተገነቡት በመደጋገም መሆኑን አስቀድመን ተመልክተናል። አሁን በአዕምሮህ ውስጥ ያሉት ፓራዳይም እና ልማዶች፣ በሕይወትህ የማትፈልገውን ውጤት የሚሰጥህ ተራ ፓራዳይም እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች ከሆኑ፣ በዚህ ልምምድ ሕልምህን በሚያሳኩና ሕይወትህን በሚቀይሩ ድንቅ ፓራዳይም እና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች መተካት ትችላለህ። በአዕምሮህ ውስጥ ያሉት የማትፈልጋቸው ተራ ፓራዳይም እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአዕምሮህ የተገነቡት በመደጋገም እንደሆነ ሁሉ፣ የምትፈልጋቸው ድንቅ ፓራዳይም እና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችም በአዕምሮህ የሚገነቡት በመደጋገም ነው። በዚህ ምዕራፍ ሥር የቀረቡትን አስር መመሪያዎች በመከተል ይህን ልዩ ልምምድ ለሃያ አንድ ቀናት ያለ ምንም ማቋረጥ ስትጽፈው፣ የማትፈልጋቸውን ተራ ፓራዳይሞች እና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ በምትፈልጋቸው ድንቅ ፓራዳይሞች እና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ትተካቸዋለህ።

**መጻፍ፡** የሰው ልጆች የተለያዩ የማሰብ ደረጃዎች አሉን። ለምሳሌ እኛ የሰው ልጆች ስናዳምጥ እናስባለን። ስናዳምጥ ከምናስበው በላይ ደግሞ ስናወራ የምናስበው ይበልጣል። ስናወራ ከምናስበው በላይ ደግሞ ስናነብ ይበልጥ እናስባለን። ከነዚህ ሦስት የማሰብ ደረጃዎች በላይ ግን ስንጽፍ የምናስበው የበለጠ የማሰብ ደረጃ ነው። “የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ” መሠረቱ “የመጻፍ የማሰብ ደረጃ” ነው። ትልቁን ሕልምህን በዚህ ከፍተኛ የማሰብ ደረጃ በመጠቀም በተደጋጋሚ ስትጽፈው፣ አዕምሮህን መቀየር ትችላለህ። ትልቁን ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በከፍተኛ የመጻፍ የማሰብ ደረጃ በመጠቀም፣ በተደጋጋሚ ስታስባቸውና ስትጽፋቸው፣ በአዕምሮህና በልብህ ይወቀራሉ።

## ፫. "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" በመጀመሪያ የት ነው የሚሠራው?

"የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" በመጀመሪያ የሚሠራው ገጽ 95 ላይ በተዘጋጀው የመለማመጃ ቦታ ላይ ነው። "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መመሪያዎችን በጥንቃቄ በማንበብ ከተረዳህ በኋላ፣ በሚቀጥለው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ገጽ 95 ላይ ልምምዶቹን መሥራት ትጀምራለህ።

## ፬. በ"፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ምንድን ነው የሚጻፈው?

በ"፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" የሚጻፉት ሦስት ነገሮች ናቸው። እነዚህ ሦስት ነገሮች ትልቅ ሕልም፣ ድንቅ ፓራዳይምና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ናቸው።

ቀጥሎ የቀረበው ሰንጠረዥ፣ በሚቀጥለው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መሥሪያ ቦታ ላይ ምን፣ የትና እንዴት እንደምትጽፍ በግልጽ ያሳያል።

| ምን | የት | እንዴት |
|---|---|---|
| ትልቅ ሕልም | በሚቀጥለው ገጽ ባለው **"ትልቅ ሕልም"** በተሰኘው ሳጥን ውስጥ | ▪ በዚህ መጽሐፍ በ፳፩ ቀን ትልቅ ሕልምህን በገጽ 56 ላይ በጥንቃቄ በመምረጥ ወስነሀል።<br>▪ ትልቁን ሕልምህን በሚቀጥለው **"ትልቅ ሕልም አለኝ!"** በተሰኘው ሳጥን ውስጥ በጥንቃቄና በትኩረት ጻፈው።<br>▪ ትልቁን ሕልምህን ስሜት እና እምነት ጨምረህ በተደጋጋሚ ስትጽፈው፣ በልብህ በማመንና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል፣ ሕልምህን በርግጠኝነት ታሳካዋለህ። |
| ድንቅ ፓራዳይም | በሚቀጥለው ገጽ ባለው **"ድንቅ ፓራዳይም"** በተሰኘው ሳጥን ውስጥ | ▪ በዚህ መጽሐፍ በ፳፩ ቀን አዲስ ድንቅ ፓራዳይምህን በገጽ 76 ላይ በጥንቃቄ በመምረጥ ወስነሀል።<br>▪ አዲስና ድንቅ ፓራዳይምህን በሚቀጥለው **"ድንቅ ፓራዳይም"** በተሰኘው ሳጥን ውስጥ በጥንቃቄ እና በትኩረት ጻፈው።<br>▪ ድንቅ ፓራዳይምህን ስሜት እና እምነት ጨምረህ በተደጋጋሚ ስትጽፈው፣ በልብህ በመወቀር፣ ሕልምህን እንድታሳካ እና ሕይወትህን እንድትቀይር ይረዳሃል። |
| የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች | በሚቀጥለው ገጽ ባለው **"የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች"** በተሰኘው ሳጥን ውስጥ | ▪ በዚህ መጽሐፍ በ፳፩ ቀን የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በገጽ 91 ላይ በጥንቃቄ በመምረጥ ወስነሀል።<br>▪ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በሚቀጥለው ገጽ **"የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች"** በተሰኘው ሳጥን ውስጥ በጥንቃቄ እና በትኩረት ጻፈው።<br>▪ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን ስሜትና እምነት ጨምረህ በተደጋጋሚ ስትጽፋቸው፣ ልማዶችህን በመቀየር፣ ሕልምህን እንድታሳካ እና ሕይወትህን እንድትቀይር ይረዱሃል። |

# "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ"

*** * ***

## ትልቅ ሕልም

ተመስገን! ዛሬ ____/____/________ እጅግ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!
ትልቁ ሕልሜ ስለተሳካ . . .

## ድንቅ ፓራዳይም

ተመስገን! ዛሬ ____/____/________ እጅግ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!
ትልቁን ሕልሜን የሚያሳካ እና ሕይወቴን የሚቀይር አዲስ ድንቅ ፓራዳይም ስላለኝ . . .

## የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች

ተመስገን! ዛሬ ____/____/________ እጅግ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!
ትልቁን ሕልሜን የሚያሳኩ እና ሕይወቴን የሚቀይሩ አዳዲስ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስላሉኝ . . .

# “የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ”

## *** ዳዊት ድሪምስ ***

## ትልቅ ሕልም

ተመስገን! ዛሬ 21 | 10 | 2012 እጅግ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!
ትልቁ ሕልሜ ስለተሳካ . . .

“እኔ ዳዊት ድሪምስ ነኝ!
ኢትዮጵያን እና አፍሪካን እየቀየርኩ ነው!
በወር 1,000,000.00 ብር እያገኘሁ ነው!”

## ድንቅ ፓራዳይም

ተመስገን! ዛሬ 11 | 11 | 2012 እጅግ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!
ትልቁን ሕልሜን የሚያሳካ እና ሕይወቴን የሚቀይር አዲስ ድንቅ ፓራዳይም ስላለኝ . . .

የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በጥልቀት በማጥናትና በመጠቀም እንዲሁም ምስጢሮቹን ድንቅ በሆነ መንገድ በማስተማር ራሴን፣ ቤተሰቤን፣ መሥሪያ ቤቴን፣ ኢትዮጵያን፣ አፍሪካን እና ዓለምን እየቀየርኩ ነው።

በመንፈሳዊ ሥነ-ምግባር የተቀደሰ፣ በአዕምሯዊ ጥበብ የበሰለ፣ ሥጋዊ ሚዛናዊነቱን የጠበቀ፣ በሰው ልጆች ፍቅር የሞቀ እንዲሁም በምስጋና፣ ጤንነት እና ስኬት የተባረከ ሕይወት እየኖርኩ ነው።

በወር አንድ ሚልየን ብር እያገኘሁ፣ የምወደውን መኪና እየነዳሁ፣ በምፈልገው ቤት እየኖርኩ፣ ዓለምን እየዞርኩ፣ በኢትዮጵያም የበጎ አድራጎት ሥራዎች በመሥራት ብዙ ሰዎችን እየረዳሁ ነው።

## የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች

ተመስገን! ዛሬ 11 | 11 | 2012 እጅግ በጣም ደስስስ... ብሎኛል!
ትልቁን ሕልሜን የሚያሳኩ እና ሕይወቴን የሚቀይሩ አዳዲስ የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች ስላሉኝ . . .

11:00 የማንቂያ ደውል ከመደወሉ በፊት አስቀድሜ በመነሳት ቀኔን በጸሎት እና በምስጋና እየጀመርኩ ነው።
11:00 በጥዋቱ ውጤታማ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ የምስጋና ሻወር እየወሰድኩ ነው።
12:00 ቀኔን በወረቀት ላይ በጥንቃቄ እያቀድኩ እና በምናቤ ረጋ ብዬ እየሳልኩ ነው።
01:00 ጤናማ ቁርስ በመመገብ እና ሙሉ ዝግጅት በማድረግ፣ የድሪምስ ቢሮ ቀድሜ እየደረስኩ ነው።
02:00 ከድሪምስ ቤተሰቦቼ ጋር ቀናችንን በአጭር የግምገማ፣ የስልጠና እና የዕቅድ ስብሰባ እየጀመርን ነው።
02:30 የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በማጥናት፣ በመጠቀም እና ድንቅ በሆነ መንገድ በማስተማር ራሴን፣ ቤተሰቤን፣ መሥሪያ ቤቴን፣ ኢትዮጵያን፣ አፍሪካን እና ዓለምን እየቀየርኩ ነው።
12:00 በተለያዩ ስልጠናዎች እና ሴሚናሮች ላይ የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን እያስተማርኩ ነው።
03:00 ከሦስት ሰዓት በፊት ቤቴ እየገባሁ፣ የምስጋና ሻወር እየወሰድኩ፣ ዕረፍት የሚሰጡኝን ሙዚቃዎች እና አነቃቂ ንግግሮች እያዳመጥኩ፣ ቀለል ያለ እራት እየተመገብኩ ነው።
04:00 ቀኔን በወረቀት ላይ በጥንቃቄ እየገመገምኩ እና ትልቁን ሕልሜን በምናቤ እያለምኩ ነው።
05:00 ፈጣሪዬን በማመስገን ከአምስት ሰዓት በፊት እየተኛሁ ነው።

## ፩. "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ለስንት ቀን ነው የሚሠራው?

"የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ለሃያ አንድ ቀናት የሚሠራ ነው። ይህ ልዩ ልምምድ ሕልምህን ለማሳካትና ሕይወትህ ለመቀየር የሚረዳህ ያለ ምንም ማቋረጥ፣ በየቀኑ የሚሠራ ልምምድ ነው።

## ፪. "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" በተደጋጋሚ የሚሠራው የት ነው?

በገጽ 95 የሠራኸው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ለአንድ ቀን ብቻ የሚሠራ ልምምድ ሳይሆን፣ በሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት በምታጠናቸው ምዕራፎች፣ ለሃያ አንድ ቀናት በተደጋጋሚ የሚሠራ ልምምድ ነው። ልምምዱ ከነገ ፳[ኛ] ቀን ከገጽ 115 ጀምሮ፣ እስከ ፳፰[ኛ] ቀን ገጽ 339 ድረስ ባሉት ሃያ አንድ ቀናት በተከታታይ የሚሠራ ነው።

- ከነገ ጀምሮ የምታጠናቸው ፳፩ ምዕራፎች፣ በመጨረሻ ገጾቻቸው ላይ፣ ይህንን "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ይዘዋል። ለሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት፣ በየምዕራፉ ውስጥ ያሉትን ምስጢራት አጥንተህ ከጨረስክ በኋላ፣ ይህንን "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" በየቀኑ በትኩረትና በጥንቃቄ መሥራት አለብህ። ይህንን ልምምድ በሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት ያለ ማቋረጥ በተደጋጋሚ ስትሠራ፣ ራስህን ሕልሙን ማሳካትና ሕይወቱን መቀየር ወደሚችል ድንቅ ሰውነት ትቀይራለህ።

በመጽሐፉ ውስጥ ከምታገኛቸው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ገጾች በተጨማሪ አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ማዘጋጀት ይጠበቅብሃል።

## ፫. በአርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ የሚጻፈው ምንድን ነው?

በመጀመሪያ አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች አዘጋጅ። በነዚህ አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ በሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት "ጥዋት እና ማታ" (በቀን ሁለት ጊዜ) በመጻፍ ራስህን ትቀይራለህ። በነዚህ አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ ለሃያ አንድ ቀናት ጥዋትና ማታ የምትጽፈው ምንድን ነው?

- በገጽ 95 "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ላይ ትልቅ ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በጥንቃቄ በመምረጥ ጽፈሀቸዋል።
- በመቀጠል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሚቀጥሉት ሃያ አንድ ምዕራፎች መጨረሻ በተዘጋጁት "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ቦታዎች ላይ፣ በገጽ 95 የጻፍካቸውን፣ ትልቅ ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በድጋሚ መጻፍ ትጀምራለህ።
- አሁን ደግሞ በነዚህ አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ፣ በገጽ 95 የጻፍካቸውን ትልቅ ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በየቀኑ ጥዋትና ማታ (በቀን ሁለት ጊዜ) ለሃያ አንድ ቀናት ትጽፋቸዋለህ።
- አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ያስፈለጉበት ምክንያት "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምዶቹን" በተከታታይ ለሃያ አንድ ቀናት ጥዋትና ማታ (2 × 21 = 42) ስለምትጽፍበት ነው።

በገጽ 95 ላይ የጻፍካቸውን ትልቅ ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተዘጋጁ "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" መጻፊያ ቦታዎች ላይ በቀን አንድ ጊዜ በመጻፍ እና በአረንጓዴ ወረቀቶቹ ደግሞ በቀን ሁለቴ (ጥዋት እና ማታ) በመጻፍ በልብህ ትወቅራቸዋለህ።

ትልቁን ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በቀን ሦስት ጊዜ (በልምምድ መጻፊያ ገጾችና በአረንጓዴ ወረቀቶች ላይ)፣ ለሃያ አንድ ቀናት በመደጋገም ስትጽፋቸው፣ የልብህ ውቅራት በመሆን፣ ሕይወትህን ይቀይሩታል።

- በቀዳሚዎቹ ሁለት ምዕራፎች የድሮ ተራ ፓራዳይምህንና የተሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን የአደጋ ምልክት ባለው ቀይ ወረቀት ላይ ጽፈህ እያጦጥለህል። አደጋ የሚፈጥሩትን የማትፈልጋቸውን ፓራዳይምና ልማዶች በቀይ ወረቀት ላይ ጽፈህ በማቃጠልም፣ ከሕይወትህ አባረሀቸዋል። የማትፈልጋቸውን ፓራዳይሞችና ልማዶች በቀይ ወረቀት ላይ ጽፈህ የምታቃጥላቸው ግን እንዴ ብቻ ነው።

  እነዚህን የማትፈልጋቸውን ፓራዳይም እና ልማዶች በየቀኑ በቀይ ወረቀት ላይ በተደጋጋሚ ከጻፍካቸው፣ በአዕምሮህ በባሰና በበለጠ መንገድ ጠንክረው ሊገነቡ ይችላሉ። የማትፈልጋቸውን ፓራዳይሞችና ልማዶች አንድ ጊዜ በቀይ ወረቀት ላይ ጽፈህ ስላቃጠልከ፣ ለአንዴና ለዘለዓለም ከሕይወትህ ተባረዋል።

- አሁን በአዕምሮህ መገንባት የምትፈልጋቸውን ድንቅ ፓራዳይሞችና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች በአረንጓዴ ወረቀቶች ላይ ለሃያ አንድ ቀናት ጥዋትና ማታ በተደጋጋሚ ትጽፋቸዋለህ። እነዚህን የምትፈልጋቸውን ድንቅ ፓራዳይሞችና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶች፣ ልማትን፣ ልምላሜንና እድገትን ብቻ ሳይሆን ሕይወትን ጭምር በሚያመለክተው አረንጓዴ ወረቀት ላይ በተደጋጋሚ ለሃያ አንድ ቀናት ስትጽፋቸው፣ በአዕምሮህ ውስጥ መገንባት ይጀምራሉ።

  ስለዚህ ከነገ ጀምሮ የቀረቡትን ምዕራፎች ካጠናህ በኋላ፣ በየምዕራፎቹ መጨረሻ ላይ ያለውን "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ትሠራለህ። በመቀጠል ደግሞ በነዚህ አርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶች ላይ "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ክፍል የሆኑትን ትልቅ ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን ለሃያ አንድ ቀናት ጥዋትና ማታ በመጻፍ በልብህ ትወቅራቸዋለህ።

## ፳. ሃያ አንድ ምዕራፎች

እነዚህን ልምምዶች ከነገ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት ስትሠራቸው፣ ከልምምዶቹ ጎን ለጎን ሃያ አንድ ምዕራፎችን ታጠናለህ። በሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት የምታጠናቸው ምዕራፎች በሦስት ክፍሎች (ሳምንታት) የተከፋፈሉ ሲሆኑ፣ የየራሳቸው የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች ያሏቸው ናቸው። በየሳምንቱ የቀረቡት በሰባት ቀናት የሚጠኑት ሰባት ምዕራፎችም የተለያዩ የሕይወት እና ስኬት ምስጢራትን የሚያስተምሩ ናቸው። በመጀመሪያ በነዚህ ሃያ አንድ ምዕራፎች ያሉ የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮችን በጥንቃቄ ማጥናት አለብህ። ከዚያ በመቀጠል ይህንን "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" በትኩረት መሥራት ትጀምራለህ።

የሚቀጥሉትን ሃያ አንድ ምዕራፎች ስታጠና እና ልምምዶቹን ስትሠራ ግን አዳዲስ ምስጢሮችን ትማራለህ። በነዚህ ምዕራፎች አማካኝነት በምትማራቸውና በምትረዳቸው አዳዲስ ምስጢሮች መሠረት፣ በ"፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድህ" ላይ የምትጽፋቸውን ነገሮች ማስተካከል፣ ማደስና መቀየር ትችላለህ።

በርግጥ "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ላይ የምትጽፋቸው ነገሮች በየቀኑ የሚቀያየሩ ሳይሆኑ፣ አንድ ዐይነት መሆን አለባቸው። ነገር ግን በየቀኑ በምትማራቸውና በምትረዳቸው ምስጢሮች እገዛ እየጻፍከ ያለኸው ነገር መቀየር እንዳለበት ከተረዳህ፣ በ"የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" እና በአርባ ሁለት አረንጓዴ ወረቀቶችህ ላይ የምትጽፋቸውን ሀሳቦች ማስተካከል፣ ማደስና መቀየር ትችላለህ።

በነገው ዕለት የምትጽፋቸው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ሀሳቦች ዛሬ ከጻፍካቸው "የ፳፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ሀሳቦች ጋር አንድ ዐይነት መሆን አለባቸው። ነገ በምታጠናው ምዕራፍ፣ የማሰብ ሂደት ምን እንደሆነና እንዴት አድርገህ በትክክል በማሰብ ሕልምህን ማሳካትና ሕይወትህን

መቀየር እንደምትችል ትማራለህ። ነገ የምትማራቸውን የማሰብ ሂደት ምስጢሮች መሠረት በማድረግ፣ ነገ የምትጽፈውን "የ፷፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ማገደስ፣ መቀየርና ማስተካከል ትችላለህ።

- እነዚህን ልምምዶች በተግባር ካላደረግካቸው፣ በሕይወትህ ብዙ ዕውቀት እንጂ ለውጥ አታገኝም። ሕልምህን ማሳካትና ሕይወትህን መቀየር የምትፈልግ ከሆነ፣ በዚህ ልምምድ የቀረቡትን ሁሉንም ርምጃዎችና መመሪያዎች በመከተል መሥራት አለብህ።

## ፱. ምናብ

ምናብ የአዕምሮ መሣሪያ ዛሬ ካለህ የሕይወት አውድ በመውጣት፣ ሕልምህ ወደተሳካበትና ሕይወትህ ወደተቀየረበት ቀን የምትሄድበት የአዕምሮ መሣሪያ ነው። (ምናብ የአዕምሮ መሣሪያን እንዴት በትክክል መጠቀም እና ማጠንከር እንደምትችል ለመረዳት በዚህ መጽሐፍ ፪ኛ ሳምንት ፲፪ኛ ቀን ያለውን ምዕራፍ መመልከት ትችላለህ)

በየቀኑ እነዚህን ልምምዶች ስትጽፋቸውና ጮክ ብለህ በተደጋጋሚ ስታነባቸው፣ ምናብህን በመጠቀም እነዚህ ልምምዶች ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ሲቀይሩት ተመልከታቸው። ትልቁን ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህንና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በየቀኑ በተደጋጋሚ ስትጽፋቸው፣ በሕይወትህ የሚፈጠረውን ትልቅ ለውጥ በምናብህ ተመልከተው። በዚህ ልምምድ በተደጋጋሚ የምትጽፋቸው ነገሮች በአዕምሮህ ተቀርጸው ሕይወትህን ሲቀይሩ፣ ዐይንህን በመጨፈን እና ረጋ ብለህ በመተንፈስ ተመልከታቸው። በዚህ ልምምድ የምትጽፋቸው፣ ትልቅ ሕልምህ፣ ድንቅ ፓራዳይምህና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህ፣ ሕይወትህን ሲቀይሩ በምናብህ ስትመለከታቸው፣ ድንቅ ስሜት እና ደስታ ጨምረህ ተመልከታቸው።

## ፲. ድርጊት

ድንቅ የመድረክ ንግግር 80 ከመቶው ቅድመ ዝግጅት፣ 20 ከመቶው ደግሞ የመናገር ክህሎትና አቀራረቡ ነው። ይህ የውጤታማ የመድረክ ንግግር ቀመር ነው። ውጤታማ የመድረክ ንግግር ለማቅረብ ከምንም በላይ ወሳኝ የሆነው ነገር "ቅድመ ዝግጅት" ነው፤ ልብ የሚነካ መልካም መልዕክት ለማስተላለፍ ድንቅ "የመናገር ክህሎትና አቀራረብ" አስፈላጊ መሆኑ ሳይዘነጋ ማለት ነው።

አንተም፣ በዚህ "የ፷፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" ባሉ የመጀመሪያ ዘጠኝ ርምጃዎች መሠረት ትልቁን ሕልምህን ለማሳካት አዕምሮህን እና ልብህን አዘጋጅተሃል። በነዚህ ዘጠኝ ርምጃዎች ትልቁን ሕልምህን፣ ድንቁን ፓራዳይምህን እና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን በዚህ መጽሐፍ እና በአረንጓዴ ወረቀቶች ላይ በተደጋጋሚ በመጻፍ፣ በአዕምሮህና በልብህ እየወቀርካቸው ነው። በነዚህ ርምጃዎች መሠረትም ትልቁን ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ለመቀየር አዕምሮህንና ልብህን በደንብ አዘጋጅተሃል።

አሁን የድርጊት ሰዓት ነው። ድንቅ የአገር መሪዎች እና የመድረክ ተናጋሪዎች፣ አስቀድመው በደንብ የተዘጋጁበትን ሀሳብ በሕዝብ ፊት ወጥተው በድንቅ አቀራረብ እንደሚያቀርቡት ሁሉ፣ አንተም ሕይወትህን በተግባር የምትቀይርበት ሰዓት ደርሷል። በዚህ "የ፷፩ ቀን ሥር ነቀል ለውጥ ልምምድ" 10ኛ ደረጃ ትልቁን ሕልምህን፣ ድንቅ ፓራዳይምህን እና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችህን እውን የሚያደርጉ ድንቅ ድርጊቶችን በተግባር ማሳየት ጀምር። እነዚህን ድርጊቶች፣ ደስ ቢልህም ባይልህም፣ ሲደክምህ ሳታርፍ፣ መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ያለ ምንም ድርድር በመክፈል በተግባር ማሳየትህን ቀጥል።

በሚቀጥሉት ሃያ አንድ ቀናት ትልቁን ሕልምህን የሚያሳኩ ድንቅ ፓራዳይምና የአሸናፊ ሰዎች ልማዶችን አስቀድመህ በተደጋጋሚ በማሰብ እና በመጻፍ በልብህ ውቀር። በመቀጠል ትልቁን ሕልምህን የሚያሳኩ ድርጊቶችን በማድረግና መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት በመክፈል ራስህን፣ ቤተሰብህንና መሥሪያ ቤትህን ብቻ ሳይሆን አገርህን፣ አህጉርህንና ዓለምን ቀይር።

*******

# ምስጋና

ይህ የምስጋና ገጽ ነው። ስለተሰጠን ጸጋ እና በረከት ፈጣሪን ስናመሰግን የተሻለ የምናመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልናል። አባክህ በዚህ የምስጋና ገጽ አሁን በሕይወትህ ውስጥ ስላሉ "በረከቶች እና መልካም ነገሮች"፣ ዛሬ ስለተማርካቸው "የሕይወት እና ስኬት ምስጢሮች" እንዲሁም ሕልምህን በማሳካት ሕይወትህን ስለሚቀይሩ "ድንቅ ውሳኔዎች" በሙሉ ልብህ አመስግን።

ተመስገን! ዛሬ በነዚህ 7 በረከቶች እና መልካም ነገሮች ስለተባረከኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 5 የሕይወትና ስኬት ምስጢሮች ስለተማርኩ፣ ልቤ በምስጋና እና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

*

*

ተመስገን! ዛሬ እነዚህን 3 ድንቅ ውሳኔዎች በማሳካት ሕይወቴን ስለምቀይር፣ ልቤ በምስጋናና ደስታ ሞልቷል!

*

*

*

**አሁን ስላለህ ጸጋ እና በረከት ስታመሰግን፣ የምታመሰግንበት ጸጋ እና በረከት ይጨመርልሀል!**